# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት።



ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

ለ/31

www.ethiopianorthodox.org

| | በውስጡ የሚይዘው | ገጽ |
|---|---|---|
| | 2. የነቢይነቱ ማዕርግ | 182-184 |
| | 3. የንጉሥነቱ ማዕርግ | 184-186 |
| ምዕራፍ ፭ | የክርስቶስ ሞት | 187-188 |
| ምዕራፍ ፮ | የክርስቶስ ትንሣኤ | 189-190 |
| ምዕራፍ ፯ | የክርስቶስ ዕርገት | 190-191 |
| ክፍል ፮ | እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ | 191-198 |
| ምዕራፍ ፩ | የመንፈስ ቅዱስ ህልውና | 191-198 |
| | 1. መንፈስ ቅዱስ ፫ኛ አካል መሆኑ | 191-194 |
| | 2. የመንፈስ ቅዱስ ብሂል | 194-195 |
| | 3. የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት | 195-197 |
| | 4. መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል መሆን | 197-198 |
| ምዕራፍ ፪ | የመንፈስ ቅዱስ ሥራ | 198-201 |
| | 1. መንፈስ ቅዱስ ከዓለሙ ጋር ያለው ግንኙነት | 198-199 |
| | 2. መንፈስ ቅዱስ ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት | 199-200 |
| | 3. የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ | 200-201 |
| ክፍል ፯ | ክብረ ቅዱሳን | 201-216 |
| ምዕራፍ ፩ | ቅዱሳን በጠቅላላው | 201-216 |
| | 1. የቅድስና ትርጉም | 201-206 |
| | 2. ቅዱስነት የሚገባው | 206-209 |
| | 3. ቅዱሳን በብሉይ ኪዳን | 209-208 |
| | 4. ቅዱሳን በሐዲስ ኪዳን | 209-212 |
| | 5. የቅዱሳን ዓይነት | 212-216 |
| ምዕራፍ ፪ | ቅድስት ማርያም | 216-225 |
| | 1. ቅድስናዋ | 216-218 |
| | 2. ክብረ ድንግል በነቢያት | 218-222 |
| | 3. ዘለዓለማዊ ድንግልናዋ÷ቅድስናዋ | 222-223 |
| | 4. ምስጋና እንዲገባት | 223-224 |
| | 5. ክብር እንዲገባት | 224-225 |
| ምዕራፍ ፫ | ቅዱሳን ሐዋርያት | 225-226 |
| ምዕራፍ ፬ | የቤተ ክርስቲያን አባቶች | 227-231 |
| | 1. የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዓይነት | 227-228 |
| | 2. ሰማዕታት | 228-230 |
| | 3. ጻድቃን | 230-231 |
| ምዕራፍ ፭ | ከቅዱሳን ጋር ያለን ግንኙነት | 231-234 |
| ምዕራፍ ፮ | ጸሎት | 234-237 |
| ምዕራፍ ፯ | ጸሎተ ፍትሐት | 237-240 |





| | በውስጡ የሚይዘው | ገጽ |
|---|---|---|
| ክፍል ፰ | ቤተ ክርስቲያን | 240-250 |
| ምዕራፍ ፩ | የቤተ ክርስቲያን ህልውና | 240-243 |
| ምዕራፍ ፪ | የቤተ ክርስቲያን መሠረት | 243-247 |
| ምዕራፍ ፫ | የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር | 247-250 |
| ክፍል ፱ | የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት በጠቅላላው | 251-297 |
| ምዕራፍ ፩ | የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት | 251-253 |
| ምዕራፍ ፪ | የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ቁጥራቸውና አገልግሎታቸው | 253-257 |
| | 1. የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ቁጥራቸው | 254 |
| | 2. የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተግባራቸው | 254-255 |
| | 3. የሚደገሙና የማይደገሙ ምሥጢራት | 255-256 |
| | 4. ለሰው ሁሉ የሚሰጡና ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚሆኑ | 256-257 |
| ምዕራፍ ፫ | ምሥጢረ ጥምቀት | 258-267 |
| | 1. የቃሉ ትርጉም | 258-259 |
| | 2. ጥምቀት አስቀድሞ በምሳሌ መነገሩ | 259-261 |
| | 3. የንስሐ ጥምቀት | 261 |
| | 4. እውነተኛው ጥምቀት መቼና በማን ተመሠረተ | 261-262 |
| | 5. ለጥምቀት የሚያስፈልጉ አንቀጾች | 262-263 |
| | 6. ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ | 263-265 |
| | 7. ጥምቀት ፩ ጊዜ ብቻ መሆን | 265-266 |
| | 8. ጥምቀት የሚታይ አገልግሎትና የማይታይ ጸጋ መኖሩ | 266 |
| | 9. ጥምቀት በደም | 266-267 |
| | 10. የጥምቀት ጥቅም | 267 |
| ምዕራፍ ፬ | ምሥጢረ ሜሮን | 267-270 |
| | 1. የቃሉ ትርጉም | 267-268 |
| | 2. የምሥጢረ ሜሮን አመሠራረት | 268-269 |
| | 3. የምሥጢረ ሜሮን አገልግሎት መቼና በማን ተመሠረተ | 269-270 |
| | 4. የምሥጢረ ሜሮን ጥቅም | 270 |
| ምዕራፍ ፭ | ምሥጢረ ቁርባን | 271-278 |
| | 1. የቃሉ ትርጉም | 271 |
| | 2. ስለ ምሥጢረ ቁርባን በብሉይ ኪዳን የተመሰሉ | 271-273 |
| | 3. የምሥጢረ ቁርባን አመሠራረት | 273-274 |
| | 4. ውላጤ ኅብስት ወወይን | 274-276 |
| | 5. ምሥጢረ ቁርባን መሥዋዕት መሆኑ | 276-277 |
| | 6. መቼና መቼ መቀረብ እንዲገባ | 277-278 |
| | 7. የምሥጢረ ቁርባን ጥቅም | 278 |




www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም ፤

የቤተ ክርስቲያናችንን እምነትና ትምህርት [illegible]ቀ የያዘውን ቀዋሚውንና ነዋሪውን ትምህርታችንን ሁሉ የያዘውን ይህን መጽሐፍ ፤ ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትና ትምህርት ሙሉ አስረጅነት ሊሰጥ በሚችለው ቃል «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት» ብዬ ሰይሜ አቅርቤዋለሁ ።

ይኸንን የመሰለውን እምነትና ትምህርት የያዘውን መጽሐፍ ብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት «ዶግማ» ብለው ይጠሩታል፤ ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ቃሉን እንዳለ ወስደው ይጠቀሙበታል ። የእኛንም እምነትና ትምህርት አጠቃልሎ የያዘውን ይህን መጽሐፍ በዚሁ ቃል ዶግማ ብለን ብንሰይመው ቀዋሚ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ ። ይኸም ዶግማ የሚለው ቃል ለምንና ምንን ለመሰለ አገልግሎት ሊውል እንደሚችል እንደሚከተለው እገልጣለሁ ።

ዶግማ የሚለው ቃል ግሪክኛ ነው፤ ትርጉሙም ትእዛዝ፣ አዋጅ፣ ውሳኔ ማለት ነው፤ ይኸውም የማይለወጥ ቃል፣ የማይታለፍ ትእዛዝ፣ የማይሻር አዋጅ፣ የማይለወጥ ውሳኔ ማለት ነው ። በዚህም መልክ ሃይማኖት ነክ የሆኑ የማይለወጡ የማይሻሻሉ ሕጋዊ መልክ ያላቸው ትምህርቶች በዚህ ስም ይጠራሉ ። ሌላም በዚህ መልክ የተነገሩላቸው ይኸንንም የመሰለ ትርጉም የያዙ ቃላት በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም በብዛት ይገኛሉ፤ እነዚህን ሁሉ በግሪክኛው «ዶግማ» ሲላቸው በእኛ ትርጉም ግን ትእዛዝ፣ ምሳሌ፣ አዋጅ ሲላቸው ይገኛል[1]።

ዶግማ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በሆነ አነጋገር የተለየ ትርጉምን የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ሆኖም በቤተ ክርስቲያን አነጋገር ዶግማ በሚልበት ጊዜ በሊቃውንት ተጠንቶ በሲኖዶስ የተወሰነው፣ በቅዱስ መጽሐፍና በቅዱስ ትውፊት ተደግፎ የታወጀው፣ የተደነገገው፣ መቼም ቢሆን ሊለወጥ የማይቻለው ትምህርትና ሃይማኖታዊ ውሳኔ ሆኖ ይገኛል፤ ይኸም ማለት ዘመን የማይሽረው፣ ባለሥልጣንም የማይለውጠው፣



www.ethiopianorthodox.org

በአስተያየትም የማይሻሻል እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርቱ ማለት ነው ::

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የሃይማኖት ቀኖና መሆኑን ስናምን ከቅዱስ መጽሐፍ የተውጣጣውን ቅዱስ መጽሐፍንም መስሎ እርሱንም ተደግፎ የወጣውን ቤተ ክርስቲያናችን የምታምነውንና የምታስተምረውን ይኸን የመሰለውን ቀጥተኛ ውንና እውነተኛውን ትምህርት ዶግማ ብንለው ተገቢውን ስያሜ አገኘ ማለት ነው ::

ቤተ ክርስቲያን እምነቷንና ትምህርቷን አንድ ጊዜ በዚህ መልክ ከወሰነችው በኋላ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ቢኖር፣ በችግርም ወይም በምቾት፣ ወይም በሌላ ልዩ ልዩ ምክንያትም ቢሆን ሊለወጥ፣ ሊሻሻልም የማይችል፣ ወይም ዕዝል ቅጥል ሊገባበት፣ ሊጨመርበት የማይገባው ነው:: የአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ረዘመ ብለው ሊያሳጥሩት፣ አጠረም ብለው ሊያስረዝሙት የማይቻል ውሳኔ እንደመሆኑ ዶግማውም ቤተ ክርስቲያን እንደያዘችው እንደምታስተም ረውም አድርጎ መቀበልና አጥብቆም መያዝ ለቤተ ክርስቲያን ዜጋ ሁሉ በግድ አስፈላጊ ነው :: እንግዲህ እምነታችንና ትምህርታችን በዚህ መልክ ከፍተኛ ውሳኔ በመሆኑ አማንያን ሁሉ አክብረው መያዝ እንዳለባቸው ያረጋግጣል፤ ስለዚህም «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት» ብለን ከፍተኛ ውሳኔነቱን አረጋግጠን ጽፈናል ::

የአንዳንድ ባለሥልጣን አዋጅ ወይም ትእዛዝ በልዩ ልዩ ችግር ወይም ምክንያት የሚለወጥ የሚሻሻል ቢሆንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ዶግማ ነውና አንድ ጊዜ በሲኖዶስ ከተወሰነ በኋላ ቀዋሚ ነው፤ ለዘለዓለም ነዋሪ ነው፤ ሰዎች ይለወጣሉ፣ የቤተ ክርስቲያንም መሪ ሊለወጥ ይችላል፤ ትምህርቱ ግን ምንም ጊዜ ቢሆን ከቶ አይለወጥም::

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሆነ እንደሆነ እንደጊዜው፣ እንደቦታውም፣ እንደ ልዩ ልዩ ሁናቴው ይለወጣል፣ ይሻሻላልም፤ ይኸም መሆን ያለበት ግዴታ ነው:: እምነቱና ትምህርቱ ግን ከቅዱስ መጽሐፍ የወጣ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ



የጸደቀ እውነት ስለሆነ፣ መቼም ቢሆን በምንም ምክንያት አይለወጥም አይሻሻልም ::

አንዲቷ ቤተ ክርስቲያንም ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር የምትለየው ወይም የምትገናኝ መሆኗ የሚገለጠው፣ አንድም የሚታወቀው በዚህ ሃይማኖታዊ ትምህርትን በሚሰጥ እምነትና ትምህርት መጽሐፍ ብቻ ነው :: አንዲት ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን፣ የምትቀበለውንም ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ወይም የምታወግዘውን፣ የማትቀበለውን አስተያየት ለይታ ያስታወቀች እንደሆነ ልዩነቱን አንድም ግንኙነቱን ሕዝቡ ሳይቀር ሊያውቀው ፣ በየጊዜውም ሊገነዘበው ይችላል፤ ቤተ ክርስቲያኗም በዚህ መልክ እምነቷንና ትምህርቷን ደህና አድርጋ ለተከታዮቿ ልትገልጥና ልታስታውቅበት ትችላለች::

ትምህርቱ የቤተ ክርስቲያን ዓምድ ምሰሦም ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የትምህርቱ መነገሪያና መታወጃ ቦታ ናት፤ ስለዚህ ይኸ የቀና ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን እንዲነገር፣ ሁሉም ያውቀውና ይረዳው ዘንድ አስፈላጊ ስለሆነ በተለየ ዝግጅት በዚህ መልክ ቀረበ ::

አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ

አሜሪካ፣ ካሊፎርኒያ በርክሊ

፲፱፻፺፬ 2002



www.ethiopianorthodox.org

ብሆን አልረሳትምና መጽሐፉን በዚህ መልክ አዘጋጅቼ አበረክታለሁ ።

በዚህ ጽሑፍ ያልተለመዱ ቃላት፣ ያልተሰሙም ምሥጢራት በብዛት ቢኖሩበትም መሠረተ እምነቱ ያው እንዳለ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰፋ ያለ አገላለጥ በመስጠቱ ለተመልካቹ ሰፋ ያለ አስተያየትን (ግንዛቤን) ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ። ሁል ጊዜ መጽሐፍን መመልከት ደግሞ በንጹሕ አእምሮና በቀና መንፈስ መሆን አለበት፤ ማለት ለመረዳት፣ ለምርመራም መሆን አለበት፤ ለዚህም ራስን ደህና አድርጎ አዘጋጅቶ መቅረብ ያስፈልጋል።

በዚህ መልክ በቅን ልቡና በትሁት ሰብእና መጽሐፍን የተመለከቱት እንደሆነ፣ የተጣመመ፣ የተዛባም አስተያየት ቢኖረውም እንኳን ተመልካች እያቃና ይመለከተዋል፣ በክፉት ለመሰለፍ ፈልጎ፤ አንባቢም መስሎ ቢቀርብ ግን ጣፋጩ መራራ፣ ነጩ ጥቁር ሊሆንበት ይችላል። ከዚህም ጋር አንባቢው በመንፈስ የበለጸገ የመረዳትም ኃይል ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል፣ ምክንያቱም መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይቶ መንፈስ በሚያስተምረን ቃል መሠረት መረዳት ይኖርብናልና፣ ተንኰለኞች ግን ለመንፈሳዊ ምሥጢር ባዕዶች ናቸው ፈጽሞ አይረዱትም፣ ይኸንንም «እኛ ግን የዓለምን መንፈስ አልወሰድንም፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን መንፈስ ነው፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ሥጦታ እናውቅ ዘንድ» ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ ይነግረናል[1]።

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስን አጋዥ ጠበቃም በማድረግ እያንዳንዱን ክፍል እንደሚከተለው ስንገልጥ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት እንዲረዳ እምነታችን ነው ።

አዘጋጁ ።





# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምሕርት

## ክ ፍ ል ፩

## ስለ እግዚአብሔር መኖር በጠቅላላው

### ም ዕ ራ ፍ ፩ የእግዚአብሔር ሕልውና፤

1. ሃይማኖት የሁሉ መሠረት :-

የክርስቲያን ሕልውና መሠረተ ትምህርቱም መነሻው የእግዚአብሔርን ሕልውና ማወቅና በእርሱም ማመን ነው፤ ማለት እግዚአብሔር እንዳለ ማመን፤ መግቦቱንና ሐልዎቱን ማወቅና ባንድ እግዚአብሔርም ማመን ነው። የዓለም ሁሉ ፈጣሪ እርሱ ነው፤ የሚታየውን የማይታየውንም ሁሉ የፈጠረ እርሱ ብቻ ነው[1]። በእግዚአብሔር ማመን ለሰው ልጅ ሁሉ የቀደመ፣ አንድም ዋናው አስፈላጊ ተግባሩ ነው። ምክንያቱም የሕይወቱ ዘመን ሁሉ እርሱን የተደገፈና ከርሱም ጋር የተያያዘ ነውና። የሰው ልጅ ከየት እንደመጣና ወዴት እንደሚሔድ፣ ለምንስ እንደመጣና እንዴትስ፣ እስከመቼስ ለመኖር እንደሚችል የሚመራው ይህ ዓይነት እምነት ብቻ ነው። ሁሉን ያስገኘ እግዚአብሔር ፍጹምና በዓለምም ምሉዕ ሲሆን፣ የማይመረመር ረቂቅ፣ የማይደረስበትም ምጡቅ ነው።

ከዚህም ጋር የሰው ልጅ እውቀት የተወሰነና የተለካ፣ ፍጹምነትም የሌለው ስለሆነ፣ እንደ እግዚአብሔርነቱ ዐውቆ ሊያመልከው እንጂ፣ በመራቀቅ፣ በመጠበብ፣ በፍልስፍና ባሕርዩን ሊመረምረውና መጠኑ ይህን ያክላል፣ መልኩም ይህን ይመስላል፣ ብሎ ልክና መልክ ሊያወጣለት፣ አንድም ግምት ሊሰጠው ከቶ አይችልም[2]። እንዲህም ስለሆነ እንደ እግዚአብሔርነቱ ዐውቀን ይኸን ይመስላል ይኸንንም ያክላል ብለን ካልገመትነው እንዴት ልናምነው ይገባል ሊሉት ከቶ አይቻልም። ስለዚህም አስረጂ ሐዋርያው ዮሐንስ ሲናገር «አልቦ ዘረከቦ፣ ወአልቦ ዘይረክቦከ፣ ወአልቦ ዘየአምረከ፣ ወአልቦ



www.ethiopianorthodox.org

ዘይክል ርእዩተከ፣ ለሊከ ተአምር ርእሰከ»[3] በማለት አስረድቷል:: ይህም ማለት ያገኘህ የለም፣ ሊያገኝህም የሚችል የለም፣ አንተ የማትመረመር ረቂቅ ነህ ማለቱ ነው:: አንዳንድ ሊቃውንት ስለ እግዚአብሔር መኖር ሲናገሩ ተራቀቅን፣ መረመርን ብለው እንደ ማቲማቲክስና እንደ ፊዚክስ (ሥነ ፍጥረት) እርግጠኛ ውጤቱን ክብደቱን ወይም ቁመቱን መልኩንና ጠቅላላ አቀዋሙን ሊረዱና ሌላውንም ሊያስረዱና ሊገልጡም ስላልቻሉ፣ እግዚአብሔር የለም ይላሉ:: በዚህም በተወሰነ ዕውቀታቸው እነርሱ ብቻ በድለው ሳይቀሩ ሌላው እንዲበድል ያደርጋሉ፤ በእርግጥም ልቦናቸው ቀረባ ቅርብ የሆኑትን ያስታሉ::

አሁን በእውነትና በቅንነት ብንመለከት እግዚአብሔር የሌለ ሁኖ አይደለም፤ ግን ፍጡር አስቦ ሊደርስበትና መርምሮም ሊረዳው ስለማይችል ብቻ ነው፥ ምክንያቱም ማንም ፍጡር ቢሆን እንኳን እግዚአብሔርን ማለት ባሕርዩ የረቀቀውን አምላክ ለመመርመርና መርምሮም ለመድረስ ቀርቶ እርሱ የፈጠራት ነፍስ ረቂቅ ስለሆነች የነፍስን ጠባይ መጠኗንና ዓይነቷንም ያወቀና የተረዳ ሊቅ እስካሁን ከቶ በዓለም ውስጥ አልተገኘም፤ ከእንግዲህም ወዲህ አይኖርም፤ ነገር ግን አወቅን የሚሉ ሁሉ ነፍስን መርምረው አልደረሱባትም፤ ምንም እንደሆነች አላወቋትም፤ እንግዲያውስ አላገኟትም፤ ስለርሷም ፍጹም ዕውቀት የላቸውም ቢባል የቀለለ ይሆናል:: እንደዚህ ሁሉ ገና ያልተመረመሩ ዓለማት (ፕላኔቶች) ይገኛሉ፤ እነርሱን እንኳን ያላወቀ፤ ከነርሱም ገና ያልደረሰ ፍጡር ስለእግዚአብሔር ሕልውና ሊያውቅና ሊረዳ ከቶ አይችልም::

እግዚአብሔር በዓለሙ ምሉዕ ሲሆን ሰው ሊመረምረውና መጠን፣ አንድም ግምት ወይም ልክና መልክ ሊሰጠው አይችልም፤ «ሥውር ውእቱ ዘኢይረከብዎ በሕሊና፣ ወምጡቅ ውእቱ ዘኢይጤይቅዎ በልቡና፣ ነዋህ ውእቱ ዘኢይበጽሕዎ አንሥርት፣ ቀላይ ውእቱ ዘኢይጸብትዎ ዓሣት» ሲል ኤጴፋንዮስ ያስረዳናል::[4] ይህም አገላለጥ ማንም መርምሮ አስቦ ሊደርስበት የማይችል ረቂቅ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: እንዲህም ስለሚሆን ቢቸገሩም እግዚአብሔር የለም አይባልም፤ እግዚአብሔር ፈጣሪ





ቢቸገሩም እግዚአብሔር የለም አይባልም፤ እግዚአብሔር ፈጣሪ ስለሆነ በርቀት፣ በምጸት፣ በፍልስፍና፣ በምርምር የሚገኝ አምላክ አይደለም፤ በዚህም ሊገኝ አለመቻሉን ማወቅና መረዳት ደግሞ ለሰው ልጅ ሁሉ ግልጥ ሊሆን ያሻል::

በእንደዚህ ያለ መንገድ እግዚአብሔር የሚደረስበት፣ የሚገኝም ቢሆን ኖሮ የሃይማኖት ትምህርት ሁሉ የፍልስፍና ትምህርት በሆነ ነበር፤ ሃይማኖትም ራሱ ፍልስፍና በሆነ ነበር፤ እግዚአብሔርም ፈጣሪ መሆኑ ቀርቶ አንድ ረቂቅ ፍጥረት ገና ያልታወቀ ያልተደረሰበትም፣ ፍጡር ወደፊት የሚደረስበት የሚጨበጥ በሆነ፤ እንደ ፍጥረትም ሁሉ በተገመተ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በሃይማኖት ብቻ ይታያል፤ በጸሎት ብቻ እናነጋግረዋለን፤ እርሱም መልስ ይሰጣል፤ እንደ አምላክነቱም ፍጥረቱን ሁሉ ይመግባል፣ ይጠብቃል፤ ስለዚህ ስለርሱ የሚነገረው ትምህርት ሁሉ የሃይማኖት ትምህርት ይባላል:: እንግዲያውስ እግዚአብሔር በልብ ብቻ ይረዳል፣ ይታመናል፣ ማለት በሃይማኖት ብቻ ይገኛል፤ ይታሰባል እንጂ በምጸት፣ በርቀት አይገኝም ሥውር ነው::

ይኸንንም ሐዋርያው ዮሐንስ «ክዱን ብከ ዕበይከ፣ ወሥውር ብከ ኃይልከ፣ ለሊከ ብከ አንጠላዕከ ወለሊከ ብከ ተከደንከ» ሲል አስረድቷል::[5] ይኸም ማለት አንተ ኃይልህ የተከደነ፣ ጌትነትህም የተሠወረ ነው፤ የምትጋርደው አንተ ነህ፤ አንተ ለራስህ የተሠወርክ ነህ፤ ማንም ሊያይህ ወይም ሊያገኝህ አይችልም ማለቱ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔርን ማወቅ አዋቂዎች ነን በሚሉና ከሥልጣኔ ወደኋላ በሆኑት ሕዝቦች መካከል ምንም ልዩነት የላቸውም፤ እነዚህ በእውቀታቸው ኃይል ብቻ እግዚአብሔርን ለማግኘት ይጥራሉ፤ ካላገኙትም የለም ይላሉ::

እነዚያ ደግሞ ለመኖሩም ላለመኖሩም ሐሳብ የላቸውም፤ አወቅን የሚሉት ግን ሙከራቸው ሁሉ በሳይንስ ብቻ የተደገፈ ሲሆን፣ ውጤት ካላገኙበት እምነታቸው ከዚያው ጋር የተጣበቀ በመሆኑና ስለእግዚአብሔር መኖር በሚያደርጉት ምርመራ መንገዱ ሁሉ የጠፋባቸው ስለሆኑ አናውቅም ማለትን ውርደት



www.ethiopianorthodox.org

ያደርጉታል፤ የለም ማለት ግን ለነርሱ ቀላል መስሎ ይታያቸዋል፤ ስለዚህ በድፍረት እግዚአብሔር የለም ይላሉ:: እግዚአብሔር እንዳለ ግን ሥነ ፍጥረቶች በግልጥ መመስከራቸው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ንጹሕ ሕሊና ያለው ሰው ሁሉ የሚረዳውና የሚያስረዳው በነርሱ አማካኝነት ነው[6]:: እንግዲያውስ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው፣ ይኽን ዓለም ያስገኘ አምላክ እንዳለ ማመን፣ በንጹሕ ሕሊናም መቀበል ለሰው ልጅ ሁሉ ግዴታ ይሆናል:: አየረ አየራትን፣ ዕመቀ ዕመቃትን የፈጠረ፣ ባሕርዩን በባሕርዩ ሰውሮ የሚኖረው፣ በዓለም ሙሉ የሆነው አምላክ ባላዋቂዎች ዘንድ እንደሌለ ቢገመትም፣ የእግዚአብሔር ሕልውና በብዙ መልክ የተገለጠ ስለሆነ እግዚአብሔር አምላክ አለ ብለን በሃይማኖት ጸንተን እንመሰክራለን::

## 2ኛ. የሰው አእምሮና የእግዚአብሔር ጠባይዕ :-

ሰው ከሌላው ፍጥረት ሁሉ ተለይቶ ከፍ ያለ ታላቅም ፍጥረት እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ተስማምተውበታል::[7] የሰው አእምሮ ከሌላው ፍጥረት ሁሉ የተሻለ የማሰብና የመመርመር ዕድል አለው፤ ግን ትልቅም ቢሆን ቢያስብም ቢመረምርም ዕውቀቱ የተወሰነ ነው፤ ያስባልም ቢባል ቅሉ ሊያስብ የሚችለውን ያህል የተወሰነውን ብቻ ያስባል፣ በዚያውም ይወስናል፣ አምላክ ግን ሁል ጊዜ ሥውር ነው ረቂቅም ነው፤ ስለዚህ የሰው አእምሮ ፈጽሞ አይደርስበትም:: ስለርሱ እንዲናገር በርሱም ብቻ እንዲያምን እንጂ ከዚያ የማለፍ ችሎታ የለውም:: ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በተደረገው ጥናትና ምርምር እግዚአብሔር ሊደረስበት አለመቻሉ በቂ ማስረጃ ይሆናል፤ ይኸውም ቅሉ ለሁሉም አይሰጠውም:: ስለእግዚአብሔር የሚደረገው ጥናት ሁሉ ማንኛውም ሰው ከአእምሮው ውሱንነት የተነሣ እንደመሰለው ያስባል፣ ይናገራልም እንጂ ከዚያ የወጣ ፍጹም ዕውቀት የለውም:: አምላክ ደግሞ እንደ አምላክነቱ እንጂ እንደሰው አሳብ አይደለም፤ ማለት ለሰው ልጅ ከቶ አይረዳም፣ አይመረመርም፤





እርሱ ግን ሌላውን ያያል ሌላውንም ያውቃል፣ ግን እርሱን የሚያይ እርሱንም የሚያውቅ ከቶ የለም::

አምላካችን ቸር ስለሆነ፣ ሌላውንም እንድንመረምር ሌላውን እንድንረዳ ምሥጢሩን ገልጦልናል፣ ክፍት በርም ሰጥቶናል:: «ሥሉስ ቅዱስ ዘያሌቡ ወኢይትሌቦ ዘያዐውቅ ወኢይትዐወቅ፣ ዘያኤምር፣ ወኢይትአመር ዘይእኅዝ ኵሎ ወኢይትአኀዝ» ሲል መጽሐፍ ይነግረናል::[8] ይኸም ማለት ሥሉስ ቅዱስ ያሳውቃል እንጂ አይታወቅም፣ ያስረዳል እንጂ አይረዳም፣ ሁሉን ይይዛል ሁሉንም ይገዛል እንጂ አይያዝም አይገዛም ማለት ነው::

በእርግጥም በዳሰሳና በጥርጥር እንጂ የዓለም ፈላስፎች የጥናታችን ውጤት ይኸ ነው በማለት ስለ እግዚአብሔር ሕልውና የሰጡት ማስረጃ ከቶ የለም፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ጠባዕይ የማይመረመር የሰው ዕውቀት ደግሞ ውሱን መሆኑን ያመለክታል:: እግዚአብሔር እንዳለ ግን በልዩ ልዩ አገላለጡ የታወቀ የተረዳም ነው፤ ማንም አሌ የሚል የለም:: የእግዚአብሔር ሕላዊ ብዙውን ጊዜ ከሰው ሕይወት ጋር የተገናኘ፣ አንድም ከሰው ሕይወት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ሲገለጥ ለምርመራም ክፍት በር ሲሰጥ ይገኛል::

የእግዚአብሔር ሕላዌ የተወሰነ አይደለም፣ በየጊዜው ከሰው ልጅ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት እንዲሁም በሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በሚያደርገው አገላለጥ ሕልውናው ሊታወቅ ይችላል:: ከሥነ ፍጥረት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት፤ በሚሠራውም ተአምራት፤ በመጽሐፍ ቅዱስም በአደረገልን አገላለጥ ስለርሱ በመጠኑም ቢሆን እንድናውቅ አድርጎናል:: ምንም እንደ እግዚአብሔርነቱ ለማወቅ ባንችልም እንኳን አእምሮአችን የቻለውን የተረዳውንም ያህል ለማወቅ ዕድል ሰጥቶናል:: ስለ እግዚአብሔር ሕልውና የሚጠራጠር የለም፤ የእግዚአብሔርንም መኖር ፈጽሞ ሊክድ የሚችል የለም፣ በቀጥታ ግን ይኸ ነው ብሎ ለመኖሩም ላለመኖሩም የሰጠው ማስረጃ የለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የለም ብሎ ፈጽሞ እንዳይክድ ለመኖሩ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፤ ከነዚህም ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ዋናው አስረጂ ራሱ ተፈጥሮው ነው፡፡ ሰው ከየት መጣ፣ ለምን መጣ፣ የትስ ነበር፣ ለሚለው ጥያቄ ሁሉ፣ መልስ የሚገኘው በሃይማኖት ብቻ ነው፤ ማለት በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ተፈጠርኩ፣ እግዚአብሔር ፈጠረኝ፣ የስሙ ቀዳሽ፣ የመንግሥቱም ወራሽ እንድሆን ፈጠረኝ ሲል ይመልሳል፡፡ ያለዚያ ግን ሁልጊዜ ጥያቄው ጥያቄን ሲያስከትል ይኖራል እንጂ ምንም መፍቻ የለውም፡፡ ይኸ ነው ብሎ ለመኖሩም ላለመኖሩም ፍጹም ማስረጃ ስለ እግዚአብሔር ሊሰጥ ያልቻለውና በየጊዜው የተለያየ ማስረጃ የሚቀርበው ደግሞ የሰውን ደካማነት የአእምሮውንም ውሱንነት የሚያመለክት ነው፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ልዩ ልዩ ሊቃውንት እየተነሡ ስለ እግዚአብሔር መኖርና አለመኖር ልዩ ልዩ አስተያየት ይስጡ እንጂ አለመኖሩን ቅሉ የሚያስረዱት በእግዚአብሔር ቃል፣ በእግዚአብሔርም ስም ነው፤ ይኸም እግዚአብሔር እንዳለ እነርሱ ራሳቸው ይመሰክራሉ ማለት ነው፡፡ የሆነው ሆኖ ግን ሁሉም የሚያውቁት ስለእግዚአብሔር ሊያውቁ አለመቻላቸውን ነው፡፡

እንግዲህ ጥንት የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ወደፊትም ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር እግዚአብሔር ለሰው ልጅ እንደ ሃይማኖቱ ስፋት፣ እንደምግባሩ ብዛት፣ ይገለጣል እንጂ እንደ ዕውቀቱ ብዛት፣ እንደአእምሮው ስፋት፣ እንደምርምሩ ውጤት ወይም እንደ ፍልስፍናው ርቀት አለመሆኑን፣ አሁንም እንገንዘብ፡፡ የሰው ልጅ ሐሳብ በየጊዜው የሚለያየው ቅሉ የሰውን የዕውቀት ደረጃ መለያየት ያመለክታል፣ ማለት እግዚአብሔር አንድ ሲሆን በተለያየም ጊዜ ቢሆን በዚያውም በአንድ ጊዜም ቢሆን፣ የሰው ልጅ አሳብ የመለያየቱን ያህል የተለያየ አስተያየትን ያቀርባል ፡፡ ያልተማረው ሕዝብ በአእምሮው ልክ እግዚአብሔርን ዝቅተኛ አድርጎ በእንጨት፣ በድንጋይ በሌላም ነገር መስሎ ያመልካል፤ ይኸም የአእምሮውን መጠን ያመለክታል፡፡ ዝቅተኛ ግምት የሰጠው ቅሉ ሰውየው በአሳብ ዝቅተኛ ስለሆነ ነው እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ዝቅተኛነት መግለጡ አይደለም ፡፡





አንዳንድ ደግሞ እግዚአብሔር ታላቅ ነው ፣ ግን አንድ አምላክ ብቻ አይደለም በማለት ብዙ አማላክት እንደሆኑ አስመስለው እንደ ተረዱትና እንደመሰላቸው አድርገው ያመልካሉ፡፡ ይኸም የዕውቀታቸውን መጠን ያመለክታል እንጂ አሁንም አምላክ ያው አንድ ብቻ ነው፣ በየጊዜው የሚለያይ አይደለም፣ ሁለተኛም ሦስተኛም አምላክ የለም ፡፡

እውነተኞች አማኞች ግን ቅዱስ መጽሐፍን ተከትለው በልዩ ልዩ ጊዜ ራሱ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያደረገውን አገላለጥ፣ ያደረገውንም ተአምራት በመከተል እውነትን ሲናገሩ፣ ሲሠሩ፣ በዚያውም አምነው ጸንተው እግዚአብሔር እንዳለ እርሱም አንድ እንደሆነ፣ ሁሉም በርሱ እንደተፈጠረ ማመን ብቻ ሳይሆን ይኸነኑ ሲያስተምሩ ሲያስረዱ ይገኛሉ ፡፡

## 3ኛ. <u>እምነት ወይም ዕውቀት ወደ እግዚአብሔር ይመራል</u> ?

የእግዚአብሔርን መኖር የሚክዱ ሁሉ፣ ፍጹም ዕውቀት ስለሌላቸው እንጂ ከቶ እንደ እግዚአብሔርነቱ ተረድተውት እግዚአብሔርን የሚክዱ ባልኖሩም ነበር፣ ስለዚህ ማንኛውንም ነገር ለመተውም ሆነ ለመቀበል ዕውቀት እንደሚቀድም ሁሉ ስለ እግዚአብሔር መኖርም በሰው ዘንድ አስቀድሞ ፍጹም ዕውቀት ያስፈልጋል፡፡ እንግዲህ የእግዚአብሔርን መኖር በሁለት ፍጹምነት ባላቸው አስረጂዎች ልናውቅ ይገባናል፣ እነዚህም አንደኛ አእምሮ የሚረዳውና ዐይን የሚያየው ሥነ ፍጥረታዊ አስረጂ ነው፣ በዚህም አስረጂ ቅዱስ ጳውሎስ ሲጠቀምበት እንዲህ ይላል «ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል» ሲል በሰፊው አስረድቶበታል፡፡[9]

ብዙዎች ሳይንቲስቶችም በንጹሕ ዕውቀታቸው ይኸን አስረጂ ተጠቅመውበት ስለ እግዚአብሔር ሐልዎት መስክረዋል፤ ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ነገር ሁሉ ያለ አንድ አንቀሳቃሽ ሊገኝና ሊንቀሳቀስ እንደማይችል ገልጠው አስረድተዋል፣ ማለት ለዓለም አንድ አስገኝ እንዲሁም አንቀሳቃሽ ባለቤት



www.ethiopianorthodox.org

አለው በማለት አስረድተዋል፣ ያለ አንድ አንቀሳቃሽ ኃይል ይኽ ዓለም የማይንቀሳቀስ ነው ሲሉ ያስረዳሉ። እርሱ ማን ነው ለሚለው ጥያቄ ግን አንዳንዶቹ «አንድ ኃይል» አለ በማለት ወደ ኃያሉ አምላክ መርተው ያደርሳሉ። አንዳንዶቹ ግን በንጹሕ አሳባቸው እንደተረዱት ሌላውን የሚያንቀሳቅስ እርሱ ግን የማይንቀሳቀስ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም፣ ያው ዓለምን የፈጠረ አምላክ ነው ሲሉ በግልጥ ይናገራሉ።

ሁለተኛው ከዚህ የበለጠ ልባዊ ዕውቀት የተባለው አስረጂ ነው፣ ማለት አንድ ሰው በፍጹም ልቡናው ጠልቆ በሕገ ልቡናው ዐውቆ የሚያምነው እምነት ነው። ከልቡናው አንቅቶ የሚያምን ሰው ሁሉ ልቡናው በመንፈስ ቅዱስ የበራለት ስለሆነና የጥርጥርም ነቅዐ የሌለበት ፍጹም እምነት ሊኖረው ስለሚችል ከሁሉ የበለጠ ስለ እግዚአብሔር መኖር ጠንቅቆ ዐውቆ እግዚአብሔርን ሲያምን፣ ሲያከብርና ሲፈራ አምልኮቱንም በሚገባ ሲፈጽም ይኖራል፣ ለምሳሌ አብርሃምን እንመልከት።[10] እንደነዚህ ያሉት ሰዎች በልቡናቸው መንፈስ ቅዱስ ስላደረባቸው ስለእግዚአብሔር መኖርና ስለ ቅዱስ ፈቃዱ እንዲሁም በጠቅላላ ስለ እግዚአብሔር የሚነገረውን ሁሉ በቶሎ ይረዱታል፣ ጠልቀውም ያውቁታል። ይኽንም የሚያስረዳ ትምህርት ቅዱስ ጳውሎስ ሲሰጥ «ለእኛ ግን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ገልጸልናል፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ረቂቅ ጥበብና ምሥጢር ሁሉ መርምሮ ያውቃልና» ሲል አስረድቷል።[11]

እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር መኖር የሚያውቁ በሥነ ፍጥረት የተራቀቁ፣ ግዙፋኑንና ረቂቃኑን ፍጥረታት እናውቃለን የሚሉ፣ የራቀውን አቅርበን የረቀቀውን አጉልተን እናያለን፣ አንድም እናሳያለን የሚሉ ፈላስፎች ብቻ አይደሉም፣ ግን ትሑት ሰብእና ቅን ልቡና ያላቸው መንፈሳውያን ሊቃውንትና ምዕመናን ሁሉ እንደሆኑ እንወቅ እንረዳ። ይኽንም እውነት ሠለስቱ ምእት በአንድ ድምፅ እንዲህ ሲሉ ያስረዳሉ፦ «ወኢመኑሂ ሐልዮ ወአዕሚቆ ኢይክል ረኪበ ሕላዊሁ ለእግዚአብሔር፣ እመሂ ተለዓለ እስከ ሰማያት ወኀለፈ እምአጋእዝት .... ።»[12]





ይኽም ማለት ማንም ቢሆን አስቦ፣ አውጥቶ አውርዶ ዐውቆ የእግዚአብሔርን ሕላዌ ሊያገኝ አይችልም፣ እስከ ሰማይ እንኳ ቢወጣ፣ አጋእዝት (መላእክት) ያሉበትን፣ እንኳን ቢያልፍ ሲሉ ያስረዳሉ። እንዲያውም ከዚህ ላይ የሰው ልጅ የመላእክትን ሐልዎት አልፎ ሊሔድ እንደሚችል ሲያስረዱ እግዚአብሔር ግን መቼም ቢሆን ሊደረስበት ሊገኝም እንደማይቻል ጥብቅ የሆነ መረጃን ሰጥተዋል።

በሥጋዊ ጥበብ የተራቀቁ ሥጋዊውን ዓለም ያወቁ ከቶ ስለ እግዚአብሔር ሊያውቁ ሊመረምሩም አይችሉም፣ እንዲህም ከሆነ እግዚአብሔር የለም ብለው በሐሰት ደፍረው ሊናገሩ አይችሉም አይገባቸውም፣ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና፣ ሊመረመርም አይቻልምና።[13]

እንዲህም ከሆነ ይኽን ከመሳሰሉት ሁሉ የሚጠበቅ ሃይማኖታዊ ቁም ነገር አንድም መንፈሳዊ ነገር ከቶ የለም፣ ወይም ለመንፈሳዊ ነገር አስረጅ የሚሆን እንደሌላቸው እንወቅ እንረዳ። እንዲህ ያለው ሰው እንኳን እርሱ መርምሮ ሊረዳ ሌሎችም የተረዱ ቢነግሩት ሊረዳ አይችልም፣ መንፈሳዊ ነገርም አያስደስተውም፣ ስንፍና ይመስለዋል፣ እንደተረትም ይቀበለዋልና።[14]

## ም ዕ ራ ፍ ፪

## ስለ እግዚአብሔር መኖር አስረጂዎች።

ባለፈው ምዕራፍ እንደተናገርነው ልቡናቸው ብሩህ ለሆኑ ለማይጠራጠሩም ሰዎች ስለ እግዚአብሔር መኖር ብዙ አስረጂ አያስፈልጋቸውም፣ ራሱን ሥነ ፍጥረትን መርምረው በሕግ ጠባይዕ ተራቅቀው ያውቃሉና። ነገር ግን ሰነፍ ሰው እንኳን አስቦ መርምሮ ሊደርስበት፣ ቢነግሩትም አይቀበልም፣ ምክንያቱም ከስንፍናው የተነሣ በልቡናው እግዚአብሔር የለም ይላልና።[1] አንዳንድ ሰነፍ ሰው ስለ እግዚአብሔር መኖር ሲጠራጠር፤ ሌላውንም ሲያጠራጥር ስለሚገኝ ቢነግሩትም ሊቀበል ስለማይችል፣ ሊቀበልም ቢፈቅድ ቅሉ ልዩ ልዩ አስረጂ ስለሚሻ



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱሳት መጻሕፍት የተስማሙባቸውን የዓለም ሊቃውንትም የተጠቀሙባቸውን፣ ስለ እግዚአብሔር መኖር በቂ የሆኑትን አስረጂዎች ከዚህ እንደሚከተለው እንዘረዝራለን::

### 1ኛ. የፍጥረተ ዓለም አስረጂ :-

ማንኛውም እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለአንድ ዓላማ የተፈጠረ እንደሆነ፣ በራሱም ፈጣሪነት የተፈጠረና በዕድሉ የተገኘ፣ ዓላማም የሌለው ምንም ፍጥረት እንደሌለ እንረዳለን:: ይህ የተከናወነ ዓለም በራሱ ፈቃድና ዕድል፣ አንድም በድንገት የተገኘ አይደለም፣ ነገር ግን ከጥበበኞች በሚበልጥ ጥበበኛ፣ አንድም ጥበብን ለሁሉ በመጠኑ በሚያድል ሁሉንም ለማድረግ በሚችል በእግዚአብሔር ፈቃድና ቃል የተፈጠረ ነው እንጂ:: የእግዚአብሔር የእጁና የቃሉ ፍጥረቶች ሁሉ የሰውን ልጅ እርሱን ወደ ማመን ይስቡታል፣ እምነቱንም ያረጋግጡለታል:: ይኸንም እውነት ነቢዩ ዳዊት ሲያስረዳ «ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር ወግብረ እደዊሁ ያየድዓ ሰማያት» ይላል::[2] ይህም ማለት ሰማዮች የአምላክን ምሥጋና ይናገራሉ፣ የሰማይም ጭፍሮች የእጆቹን ሥራ ያወራሉ በማለት ዓለም በጠቅላላው የአምላክ ፍጥረት መሆኑን ያስረዳሉ::

ይህን የመሰለ አስረጅ በመስጠት ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ሲል አስተምሮናል «እግዚአብሔርን ማየት ተገልጠላቸዋልና የማትታወቅ ባሕርዩ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድማ በፍጥረት ትታወቃለች ትገለጣለችም እርሷም የዘለዓለም ብርታቱ አምላክነቱም ያለ ምክንያት ይሆን ዘንድ::[3] ይኸን ሥነ ፍጥረታዊ አስረጂ በመመርኮዝ በእግዚአብሔር ለማመን ብዙ ሊቃውንት ተጠቅመውበታል፣ አንዳንድ ያልተማሩ ሕዝቦች እንኳን ሥነ ፍጥረትን ያለ አግባብ የሚያመልኩበት ዋናው ምክንያት እነርሱን የፈጠረውን አምላክ አገኘን እርሱንም አመለክን መስሏቸው፣ አንድም ብለው ነውና::

አሁንም ቢሆን ሁሉን የሠራ/የፈጠረ፣ የሁሉ መሪ፤ የሁሉም አሳዳሪ፤ ሁሉም በእርሱ የሆነ፣ በእርሱም ፈጣሪነት የተፈጠረ፣ ያለ እርሱም አንዳችም የሆነ የሌለ፣ ልዑል





እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል፤ ይኸም ማለት በፍጥረቱ ክንውን ይታወቃል::[4] ሥነ ፍጥረታዊ አስረጂን ተመርኩዞ ያመነ ሁሉ፣ ከውድቀት ከጥርጥርም ማዕበልነት ይድናል:: ሥነ ፍጥረታት ከወሰናቸው ሳያልፉ ሕገ ተፈጥሮን ሳያፋልሱ እየሠሩ እየተገኙ እግዚአብሔርን ማስመስገን ብቻ ሳይሆን ስለርሱም መኖር ያለማቋረጥ ይመሰክራሉ:: ስለዚህ እኛም በነዚህ ቀዋምያን አስረጂዎች ተመርተን አንድም ተረድተን የእግዚአብሔርን ሕልውና እንመን::

### 2ኛ. የፍጥረቱ ክንውን አስረጂ:-

እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ያማረና የሠመረ ነው፣ እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም መልካም ሆነ፣[5] የእያንዳንዱ ፍጥረት ወሰን ደንበር፣ ፀጥታና ዓላማ ሕግም አለው፣ ይህም ሁሉ ክንውን በአድናቆት ወደ ጥበበኛው ወደ ሠራተኛው አምላክ መርቶ ያደርሳል:: አንድ ጥሩ ነገር ተሠርቶ የትም ቢሆን ሲገኝ በመጀመሪያ የሚጠየቀው ማን እንደሠራው፣ የት እንደተሠራ ነው፣ ምክንያቱም ያለአንድ ሠራተኛ ተከናውኖ ተሠርቶ የሚገኝ ነገር የለምና፣ በግድ ባለቤት አንድም ሠራተኛ መኖር አለበት::

ነቢዩ ዳዊትም የሥነ ፍጥረቱን ሁሉ መከናወን ዐይቶ ሕሊናው በአድናቆት ተውጦ፣ «ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚአ፣ ወኩሎ በጥበብ ገበርከ» ሲል ይኸን ዓለም አምላክ ተጠብቦ ተራቆ እንደፈጠረው መስክሯል:: ይኸም ማለት አቤቱ ሥራህ እንደምን ድንቅ ነው፣ ሁሉንም በጥበብ አደረግህ፣ ምድርም በባለጠግነትህ መላች ሲል መዘመሩ ነው::[6]

የፍጥረቱም ክንውን አንድ ፍጡር ያንዱን መልክና ጠባይዕ ሳይወስድ ጥንቱን በሥነ ፍጥረት ጊዜ በተወሰነለትና በተመደበለት፣ በተሠራለትም ሥርዓት ጸንቶ ይኖራል፣ ይኸም ማለት ነፋሳት በመንፈስ፣ አፍላጋት በመፍሰስ፣ በጋና ክረምትም በመመላለስ፣ መዓልትና ሌሊትም በመፈራረቅ:: በዚህም መልክ ማንኛውም ፍጥረት ሁሉ በሥርዓቱ ጸንቶ መኖሩ አንድ ጥበበኛ ተጠብቦ ተራቆ ተግቶም የሠራው



www.ethiopianorthodox.org

እንደሆነ ያመለክታል። ይኸም ከጥበበኞች የሚበልጥ ጥበበኛ እግዚአብሔር እንደ ፈጠረው በሰፊው ያስረዳል ማለት ነው።

ይህ ዓለም በዕድል አንድም በድንገት እንዲሁ የተገኘ ቢሆን ኑሮ አንዱ ሲያልፍ፤ አንዱም ሲተርፍ፤ አንዱ የአንዱን ቦታ ሲይዝ፤ አንዱም ባሕርዩን ሲለውጥ በተገኘ ነበር፣ ነገር ግን ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ጊዜው ብዙ ሲሆን ፍጥረቱ ሁሉ ጠባዩን ይዞና ጠብቆ በሕጉ ይገኛል። ይኸም ሁናቴ ፍጹም ጥበበኛ በሆነ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ሁሉም መፈጠሩን የሚያጠይቅ ነው። ከዚህም ሌላ ካስገኘው አልፎ እንዲሁ በዕድሉ የተገኘ ነገር ከቶ በዚህ ዓለም እስከ አሁን አልተገኘም፣ እንዲሁም ወደፊት አይገኝም፣ ስለዚህ አንድ ነገር ሲገኝ ሠራተኛውን የግድ ያስታውሳል፣ በግድም ሠራተኛ ሊኖረው ያስፈልጋል። ይህ ዓለም ግን ከሥራው ክንውንና ጽንቶም ከመኖሩ ይልቅ ለአንድ ዓላማ የተፈጠረ ስለሆነ፣ ሁሉም በዓላማው ጸንቶ በመኖሩ በቀጥታ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ያስታውሳል፣ የእግዚአብሔርም ፍጥረት እንደሆነ ያጠይቃል።

አንዳንድ ሊቃውንት መረመርን ብለው ምንም ውጤታቸው በጣም አጥጋቢ ባይሆንም እንኳን፣ ይኸ ዓለም እንዲሁ ግብር እምግብር ተፈጠረ ብለው ቢያምኑና፣ ቢናገሩም ቃሉ፣ ከመጀመሪያ ግብር በግድ ያደርሳቸዋል፣ ስለዚህ የመጀመሪያው ግብር ግን ከምን ተገኘ ቢሏቸው ከአንድ ኃይል ከአንድ ሥልጣን ማለታቸው የታወቀና የተረዳ ነው። እንግዲህ ይኸ ኃይል የተባለው የመጀመሪያው፣ የፍጥረቱ ሁሉ መገኛ አንድም አስገኝ የሆነው ምንድን ነው ብለው ቢጠይቋቸው ስለ እርሱ በቂ መልስ ሊሰጡ አይችሉም፣ እንግዲያውስ ይኸ ኃይል የተባለው አንቀጽ ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ ችሎታና ኃይል ያለው እንደሆነ ማመንና መቀበል አለብን። ይኸም አስተያየት ከጥንት ፈላስፎች የወረደ ወይም የተጀመረ ነው፣ ብዙ ጥያቄ አዘል አስተያየቶች ለጊዜው አስቸጋሪ ሁነው ይቆዩ እንጂ ዘመኑ በደረሰ ቁጥር እየተፈቱ አስረጅነትም እያገኙ ብዙም ነገሮች እየተገለጡ ሲሔዱ ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ያለው አስተሳሰብ ግን ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ያለው ያው ሁኖ





ይገኛል፣ ምክንያቱም ፈጣሪ ስለሆነ አይሻሻልም አይለወጥም፣ እነርሱም ደግሞ ሊደርሱበት ሊመረምሩትም ሊያገኙትም አልቻሉምና። በእውነትም ታላቅ ኃይል ነው፣ ኃያልም አምላክ ነው፤ ስለዚህ አሁንም ወደፊትም ማንም ሊደርስበት አይችልም። ብቻ ለፍጥረቱ በሚያደርገው ቸርነት፣ ለፍጥረቱ በሚያደርገው አገላለጥ ብቻ ልንረዳና ልናምን እንደርሱነቱም ልናውቅ እንችላለን እንጂ።

## 3ኛ. የሕገ ልቡና አስረጂ:-

ሁላችን በተፈጥሯችን የተሰጠን በሕሊናችን ተጽፎ፤ አንድም ተቀርጾ ከደማችን ጋር ተዋሕዶ የሚኖር ሕገ ልቡና አለ፣ ይኸውም ሁል ጊዜ ደጉን፣ ተስማሚውን ነገር እንድንሠራ፣ መጥፎውን ክፋውን ግን እንድንተወው እንድንሸሸውም የሚያነሣሣን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድም የሚገልጥ፣ ተቃራኒውን ሁሉ እንድንጠላው እንድንሸሸውም የሚያስታውስ ነው። ኃጢአትን ሰውየው ደክሞ ሰንፎም ይሠራዋል እንጂ ይኸን ሁሉ ሳያውቅ ኃጢአት የሚሠራ ሰው ከቶ የለም። ይህን ጥብቅ የሆነ የተፈጥሮ ሕግ በልቡናችን የሳለና የቀረጸ፣ ለዓለም ባለቤት የሆነ አንድ ጥበበኛ ፈጣሪ እንዳለ ያስረዳናል፤ በእግዚአብሔርም እንድናምን ያስገድደናል። ይህ ሊሆን የቻለው ደግ ቢሠሩ ዋጋን፤ ክፉ ቢሠሩ ፍዳን የሚከፍል እውነተኛ ዳኛ ደግና የታመነ አምላክ መኖሩ በሰው ሁሉ ሕሊና አስቀድሞ ስለተቀረጸ ነው። በአእምሮ ጠባይዕ አውቀው እግዚአብሔርን ያመኑት ብዙዎች ናቸው፤ በዚህም የተመሠረተ እምነት ከቶ ጊዜ አይለውጠውም።

## 4ኛ. ታሪካዊ አስረጂ:-

የሰው ነገድ ሁሉ ከታወቀበት ከተመዘገበበትም ጊዜ ጀምሮ በፈጣሪ የማያምን ሰው እንዳልነበር አሁንም እንደሌለ ታሪክ ይነግረናል፣ እያንዳንዱም ነገድ ለአምላኩ እንደ ሕጉ ያልፈጸመ አልነበረም። ስለዚህ፣ ያለ መካሪ ያለ አስተማሪ ተራውና ያልሰለጠነው ሕዝብ ሁሉ፣ እንደችሎታው አምልኮቱን ሲፈጽም ይገኛል። የአምልኮቱና የሥርዓቱ አፈጻጸም ግን እንደ



www.ethiopianorthodox.org

ጠባዩና እንደ ኑሮው ደረጃ እንደ ዕውቀቱም መጠን ሰው ሁሉ የተለያየ ነው፣ ነገር ግን አምላክ ስለመኖሩ ስለርሱም ክብር ሁሉም አምኖ መሥራቱ ሃይማኖት የወል ሁኖ በሰው ልጅ ጠባይዕ የተመሠረተ መሆኑን ያስረዳል።

ይኸ ሁሉ ስለ እግዚአብሔር መኖር በሰፊው የሚያረጋግጥ ነው። እግዚአብሔር ባይኖር እንዴት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የነበረው ልዩ ልዩ ነገድ ለአምላኩ መሰዋዕት ያቀርብ ነበር? ዛሬም ያለው የሰለጠነውም ያልሰለጠነውም ሕዝብ በትክክል፣ ለእግዚአብሔር አምልኮት እንደኑሮው መጠን ያቀርባል፣ ከሥራው ሁሉ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ማመንን ታላቅ ቁም ነገር አድርጎ ይይዛል። እንዲህስ ከሆነ በእርግጥም እግዚአብሔር አለ፣ ሰውን ወደርሱ የሚስብ፣ ጸጋን የሚሰጥ፣ ክብርን የሚያወርስ፣ ቸርም። ይህን ዓለም አከናውኖ የፈጠረ፣ አሁንም የሚከባከብ፣ ለጋስ፣ በዚህም ምክንያት ትንሹም ትልቁም፣ የቀድሞውም፣ ያሁኑም ሕዝብ ሃይማኖት አለው፣ በእግዚአብሔር ያምናል። እምነት አንድም ማመን በሰው ልጅ ዘንድ የወል መሆኑ በእርግጥ እግዚአብሔር መኖሩን ያስረዳል።

ማንም ሰው ለጊዜው በሥጋ ቢመቸው የመንፈስ ጸጥታ ሲጎድልበት ማለት እምነቱ አምልኮቱ ሲጓደልበት ሊረጋጋ ዕረፍትንም አግኝቶ ሊኖር አይችልም። አንድ ሰው ለጊዜው ለሰው ይምሰል የተመቸውና የደላው፣ መንፈሳዊ ተግባርም የማያሻው መስሎ ቢታይም ሌሊት በስውር ሕሊናው ሲከሰው ሲወቅሰው ሲፈርድበትም ይገኛል። ይኸ ሁሉ ቀጥተኛ የእግዚአብሔርን መኖር የሚያስረዳና ሁሉም በእግዚአብሔር አምኖ መኖር እንዳለበት የሚያስገድድ አምልኮቱንም በሚገባ እንዲፈጽም የሚያስታውስ ነው። በዚህም ምክንያት በዓለም ላይ ያለ ሃይማኖት የሚኖሩት ሕዝቦች በጣም በቁጥር ያነሱ ናቸው፣ እነርሱም ጸጥታን ሳያገኙ፣ በዓለም ላይ በመኖራቸው እየተበሳጩ፣ ተስፋም ቆርጠው የሚገኙ ናቸው። እርግጥነው በውጭ ሲታይ ኃጢአተኛው ሰው ሁሉ አምላክ የሌለው መስሎ ያለ ኃፍረት የኃጢአትን ስልት ሲያጠና፤ ሲሠራ፤ ሲፈጽም ይገኛል፤ ሌላውም እርሱን በመከተል ሲሳብ ይገኛል። ነገር ግን





ሁሉም በሥውር ሕሊናው ሲወቅሰው፣ ሲፈርድበትም ሲያዝን ይገኛል።

ይህ ከዚህ በላይ የዘረዘርነው ሐተታ ሁሉ ክርስቶስን ለማይቀበሉና ከክርስትና ውጭ ለሆኑት ሕዝቦች ብቻ ነው እንጂ ለእኛ ለክርስቲያኖችስ መድኃኒታችን መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ፣ በዚህ ዓለም በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙ ማስረጃዎችን አስቀድሞ ስለሰጠን ስለ እግዚአብሔር ፍጹም ዕውቀት አለን፣ ምንም ጥርጥር የለብንም፣ እርሱም በትምህርቱ «አቡየ ፈነወኒ ወአነሂ ተፈኖኩ» «ዘርእየ ኪያየ ርዕዮ ለአቡየ» እያለ እግዚአብሔር እርሱም ከአምላክ የተገኘ አምላክ እንደሆነ በማስረዳት በሥራው ድውይ እየፈወሰ፣ ሙት እያስነሣ፣ ለምጽ እያነፃ፣ ልዩ ልዩ ተአምራትንም እያደረገ በእግዚአብሔር ሐልዎት ማመን እውነተኛ ሃይማኖት እንደሆነ፤ እግዚአብሔርም እንዳለና ፈጣሪም እርሱ ራሱ ብቻ እንደሆነ ነግሮናል፣ አስተምሮናል።[7]

ትምህርቱንም በእርግጥ አምነን ተቀብለነዋል። እኛ ክርስቲያኖች ማዕበልና ሞገድ የሚያማታውን ይኸን ዓለም ለመሻገር የምንችለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመን እንደሆንና፣ የርሱንም ትምህርት የተከተልን እንደሆነ ነው፣ በእርሱም እንድናምን እርሱንም እንድንሰማና እንድንከተል እግዚአብሔር አብ አዘናል «ከደመናውም ውስጥ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይኸ ነው፣ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ»።[8]

ስለዚህ እርሱ እውነተኛ መምህር፣ እርሱ እውነተኛ ድልድይና መሸጋገሪያ መሆኑን ማመንና ማረጋገጥ ግዴታችን ነው። እውነተኛ መንገድ፣ እውነተኛ ፈጣሪ፣ እውነተኛ አዳኝ እርሱ ብቻ እንደሆነ መመስከር አለብን፣ እርሱ «እኔ ትንሣኤም ሕይወትም ነኝ»[9] ብሎ የመሰከረውን ማመንና መቀበል አለብን።

አንዳንድ ከሃይማኖት የወጡ ከክርስቲያናዊ ምግባር የተናወጡ፣ ኃጢአታቸውን ያለ ሐፍረትና ያለ ፍርሃት ለመሥራት እንዲያመቻቸው ብቻ እግዚአብሔር የለም ይላሉ፣ ሌላውንም ለመምራት ይሞክራሉ፣ ነገር ግን «ተዋቸው ዕውሮች



www.ethiopianorthodox.org

ናቸው፣ እውሮችንም የሚመሩ፣ ዕውርም ዕውርን ቢመራው ተያይዘው ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ»[10] ብሎ ክርስቶስ የመሰለው ምሳሌ ይፈጸምባቸዋል::

ስለ እግዚአብሔር መኖር በሰፊው የተናገሩ ከሥጋዊያን ሊቃውንት እንኳን ብዙዎች ናቸው፣ አንዳንድ ግን ይህን በአፍራሽ መንገድ እንወስዳለን ቢሉ ቅሉ በቂ አስረጂ ሊሰጡ አይችሉም፣ ተመልሰውም የእግዚአብሔርን ስም ሲጠሩና በእግዚአብሔርም ሥነ ፍጥረት ሲያስረዱ ይገኛሉ::

ማነኛውም ለኃጢአቱ መሸፈኛ ለጥፋቱ መጠገኛ የሆነው መስሎት ከዚህ ከእውነተኛው መስመር ይወጣል እንጂ ተፈጥሮው እያስረዳው መንፈሱም እየወቀሰው ሁሉም በውስጣዊ ሕሊናው በእግዚአብሔር አምኖ ይገኛል:: እንግዲህ ይህን አስረጂ ገንዘብ ያደረገ ሁሉ ከዚህ በላይ በተሰጠው ማስረጃ መሠረት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲገለጥለት አእምሮው እንዲበራለት እግዚአብሔር መኖሩን ዐውቆ፣ ከኃጢአት ርቆ ንጽሕናውን ጠብቆ መኖር ይገባዋል ::

## ም ዕ ራ ፍ ፫

## የእግዚአብሔር አንድነት::

### 1. እግዚአብሔር አንድ ነው፣

እግዚአብሔር አንድ ነው፣ አከልም መሰልም የሆነውና የሚሆነው ሌላ አምላክ የለም፣ ይኸንንም እውነት ራሱ አምላክ ለሙሴ እንዲህ ሲል ገልጦለታል:: «ለአንተ ይኸ ሁሉ ተገለጠ እርሱ እግዚአብሔር አምላክ አንድ እንደ ሆነ ታወቅ ዘንድ ሌላም እንደሌለ»::[1] ከ፲ቱ ቃላት ውስጥ የመጀመሪያው አንቀጽ «እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ ከምስር ምድር ያወጣሁኽ ከባርነት ቤት ያወጣሁኽ:: ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ በፊቴ...» ሲል አውጇል::[2] ምንም በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ የሆነውን አምላክ በአካል፣ በስም፣ በግብር ፫ ብንልም ሦስት አማልክት ከቶ አንልም አንድ አምላክ ብቻ እንጂ:: ፫ቱም አካላት በባሕርይ በአምላክነት አንድ ናቸውና::





ይኸንም በአዋጅ መልክ «ስማ እሥራኤል ሆይ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ እግዚአብሔር ነው::» ሲል ነቢዩ ሙሴ ተናግሯል::[3]

ይኸም ቃል ለእግዚአብሔር ተቀናቃኝ ተወዳዳሪም የሚሆን ሌላ አምላክ አለመኖሩን አንድ አምላክ እርሱ ብቻ መሆኑን የሚገልጥ ቃል ነው:: ይኸንም የመሰለ አስረጅ እንደገና እንዲህ ሲል ይናገራል «... ይኸነን ከጥንቱ ማን አሰማ፤ በዚያስ ዘመን የተናገረ ማነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከኔ ሌላም አምላክ የለም:: ጻድቅ አምላክ የሚያድንም ከኔ ሌላ የለም»[4]:: ከክርስትና ውጭ የሆኑ ወገኖች በሦስት አማልክት እንደምናምን፤ ሦስት አማልክትም እንዳሉን አድርገው እኛን የሚገምቱ የሚናገሩም አሉ፣ ግን ስሕተተኞች ናቸው፣ ምክንያቱም እኛ ክርስቲያኖች የምናምነው አንዱን አምላክ ብቻ ነውና::

ይኸንንም የአንድነቱን አገላለጥ ማንነቱንም እግዚአብሔር ለሙሴ ብቻ የገለጠው የነገረውም አይደለም፣ በየጊዜው ለተነሡ ነቢያትም ገልጧል፣ አስረድቷልም እንጂ፣ ለምሳሌ ለነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈሱ ገልጦለት እንዲህ ሲል ተናግሯል:: «እንዲህ ይላል እግዚአብሔር የእሥራኤል ንጉሥ የሚያድነ ውም እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ:: እኔ በፊት ነኝ እኔም በኋላ ነኝ፣ ከእኔም ሌላ አምላክ የለም»::[5]

በሐዲስ ኪዳንም እንዲሁ ለቅ. ሐዋርያት ተገልጦላቸው የእግዚአብሔር አምላክን አንድነቱን ወይም አንድ መሆኑን አስፍተው አጉልተው ተናግረዋል፣ ከነርሱም ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ «... ሌላም አምላክ እንደሌለ ከአንዱ በቀር ማንም አምላክ ብሎ ቢጠራ በሰማይ በምድርም ያለው ብዙ አማልክት እንደሆኑ ብዙም ጌቶች፤ እኛ ግን አንድ አምላክ አለን እግዚአብሔርአብ ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለርሱ ...» ሲል የእግዚአብሔርን አንድነት በሰፊው ገልጧል::[6] እንዲሁም «እግዚአብሔር አንድ ነውና፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው አንድ ነውና እርሱም ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ» ሲል ይገልጥልናን::[7] እግዚአብሔር አብ አምላክ ነው፣ እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ወልድም አምላክ ነው፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው እንዲህም ስለሆነ ሦስት አማልክት አይባሉም፣ አንልምም፤ አንድ አምላክ እንጂ።

ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ሲናገር እንዲህ ይላል:- «ኢየሱስ ግን አለው፦ ለምን ቸር ትለኛለህ አንድም ቸር የለም ከአንዱ በቀር እርሱም እግዚአብሔር»።[8] ይኸ ሰው ከክርስቶስ ዘንድ ምስጋናን ሽቶ፣ አንተ ቸር ነህ ስለው አንተም እንጂ ይኸን ሁሉ ሥጦታ የሰጠህ ቸር ነህ እባላለሁ ብሎ ውዳሴ ከንቱ ሽቶ፣ ክብር ጠብቆ ነበር፣ ግን ክርስቶስ እንዴት ቸር ይለኛል ብለህ እኔን ቸር ትለኛለህ? ቸርማ እንዳልልህ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም አለው። እውነተኛው ቸር እግዚአብሔር መሆኑን ከርሱም በቀር ሌላ ቸር አለመኖሩን ገለጠለት። አንተ የሚገባህን ትእዛዝ ፈጽምክ እንጂ የቸርነት ባሕርይ የለኸም፣ በባሕርዩ ቸር የሆነ ቸርነትም ያለው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው ሲል በአንድ በኩል የእግዚአብሔርን አንድነት በ፪ኛው በኩል ቸርነት ለእግዚአብሔር የባሕርዩ መሆኑን ገልጦ ተናገረ። እንግዲህ ሦስቱ አካላት በባሕርይ አንድ እንደመሆናቸው በባሕርዩ ቸርነት ያለው አንድ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑ ነው። እግረ መንገዱንም ስለራሱ አምላክነትና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላለው አንድነት ገልጦ ተናገረ። ሃይማኖታቸው ያቀና ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንትም ስለ እግዚአብሔር አንድነት በዋናው የሃይማኖት አንቀጽ በጸሎተ ሃይማኖት «ነአምን በ፩ዱ አምላክ ....» ሲሉ ተናግረዋል።[9]

እንግዲህ የእግዚአብሔር አንድነት በሚል ርእስ ስንናገር አማልክት ብዙ ሁነው ኅብረት ፈጥረው፣ አንድነት ወይም ስምምነት ኑሯቸው አንድ ሆኑ በማለት መናገራችን አይደለም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በመሠረቱ አንድ አምላክ ነውና፣ ሁለተኛም ሦስተኛም የለውም፣ «ኢኮነ ፪ተ ወኢ ፫ተ አላ ፩ዱ ውእቱ» ይለዋልና።[10] እንዲሁም ባልና ሚስት ሁለት ሲሆኑ አንድ አካል ናቸው እንደሚለው አገላለጥ አይደለም።[11] እነርሱ በእግዚአብሔር ቃል አንድ ቢሆኑም በጾታም በአካልም ሁለት ናቸውና፣ እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ አንድ ነውና። እንዲሁም





የሕዝብን አንድነት ወይም ስምምነት ኅብረትን ለመግለጥ ሕዝቡ አንድ ሆነ፣ እንደሚለው አይደለም።[12] በጾታ በዕድሜ በማዕረግ የተለያየ በቁጥር የበዛ ሕዝብ ይገኛልና። እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ አንድ ነው ተጨማሪ የለውም፣ ከእርሱ አስቀድሞ ማንም አልነበረም፣ ከእርሱም በኋላ ምንም አልመጣም፣ ደግሞም አይመጣም፣ እርሱ ብቻ ነበር፣ አለ፣ ለዘለዓለም እርሱ ብቻ ጸንቶ ይኖራል። «አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር» በማለት እንድንጸልይ ጌታ ኢየሱስ ያስተማረን የእግዚአብሔርን አንድነቱን ለመግለጥ ነው።[13]

የእግዚአብሔር አንድነቱን በዚህ መልክ እናምናለን፣ በዚህም መልክ እናሳምናለን፣ ግን አንዱ እግዚአብሔር በአካል በስም በግብር ሦስትነት እንዳለው ደግሞ አንረሳም፣ እንዲያውም በብሉይ ኪዳን ሳይቀር አንዱን እግዚአብሔርን ብዛት ባለው ቁጥር ሲናገር የነበረው ይኸን የአንዱን እግዚአብሔርን የስምና የአካል የግብር ሦስትነት ለመግለጥ ነው። እርሱም እንዲህ ይላል:- «የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማሁ፣ እንዲህ ሲል 'ማንን እልካለሁ፣ ማንስ ይሄድልናል' አልሁም እነሆኝ እኔን ላከ»።[14]

ከዚህ ላይ ጥቅሱ የአንድነቱም የሦስትነቱም መግለጫ ሁኖ ቀርቧል ማለት ማንን እልካለሁ ሲል አንድነትን፣ ማንስ ይሄድልናል ሲል ደግሞ ሦስትነትን ያሳያልና። እንዲሁም በነቢዩ ዘካርያስ አገላለጥ አንዱ ላኪ ሌላው ደግሞ ተላኪ መሆኑን ያሳያል «አመስግኚ ደስም ይበልሽ አንቺ የጽዮን ልጅ እነሆ ወደ አንቺ መጥቻለሁና በመካከልሽም እኖራለሁ አለ እግዚአብሔር። በዚያም ቀን ብዙ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ይሆናሉ፣ ሕዝብም ይሆኑኛል፣ በመካከላቸውም እቀመጣለሁ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ወደ አንቺ እንደላከኝ ታውቂያለሽ»።[15]

እንግዲህ አንዱ ላኪ ሌላው ተላኪ መስሎ ሲገኝ ብዛትን ያመለክታል። ግን ላኪው እግዚአብሔር አብ፣ ተላኪው እግዚአብሔር ወልድ ሲሆን፣ ሁለቱም በባሕርይ አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ ይባላል እንጂ ሁለት አማልክት ከቶ አይባሉም።



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስ ወንጌላዊም ሲገለጥ «በመጀመሪያ ቃል ነበር» ይልና ለቃል ቀዳማዊነቱን ጥንታዊነቱን አስታውቆ ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት እኩልነት ሲገልጥ ደግሞ «ወቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ» ሲል ሁለትነት ያለው አገላለጥን ያሳያል:: ይኸም አገላለጥ የሥላሴን ሦስትነትና አንድነት ይገልጣል፣ ይሁን እንጅ በኢአማንያን ዘንድ ሁለት ፈጣሪ እንዳለ አስመስሎ ያሳያል፣ ቃል ራሱን የቻለ ሁኖ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር ብሏልና:: ነገር ግን እንዲህ ያለው ጥርጣሬ ጎልቶ እንዳይታይ ወንጌላዊው ወዲያውኑ የባሕርይ አንድነታቸውን ሲገልጥ «ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል» ቃልም ያልኋችሁ ሌላ ባዕድ ቃል ባዕድም ባሕርይ አይደለም፣ ያው በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ የሆነ እግዚአብሔር ነው ብሎ አስረድቷል::[16] የሥላሴን የአካልና የስም የግብርም ሦስትነታቸውን ግን ወንጌላዊያን በግልጥ አስረድተው ተናግረዋል::[17]

እንግዲህ እግዚአብሔር አምላክ በባሕርይ አንድ ሲሆን እንዴት ሦስት ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም ሦስት ሲሆን እንዴት አንድ ይባላል የሚል ስሜት ሊኖርበት የሚችል ብዙ ነው:: በመሠረቱ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በተረዳ በጎላ ልከኛውን አውጥቶ ከመሠረቱ ገብቶ በማቲማቲክስ ልከኛነት ሊያስረዳ የሚችል ከቶ የለም፣ ስለዚህም ምስጢረ ሥላሴ ተብሏል:: ሆኖም ቅዱሳት መጻሕፍት ያቀረቡልንን መግለጫ በመከተል ቅዱስ መንፈስም በገለጠልን መሠረት እንደሚከተለው እንገልጣለን:: የተለያዩ ሦስት አካላት እንዳሉ አድርጎ ዮሐንስ አቅርቦልናል «እኔ አብን እለምናለሁ ሌላ አጽናኝ እንዲልክላችሁ:: እርሱም ለዘለዓለሙ በእናንተ አድሮ ይኖራል»::[18]

ይኸም አስረጅ ግልጥ አድርጎ ሦስትነትን ያሳያል፣ በእርግጥም ሦስት ማለት ይገባል። እንዲሁም በጥምቀት ጊዜ የተገለጠው ምሥጢር የሥላሴን ሦስትነት፣ የሚገልጥ ነው:: ይኸውም ወንጌላዊው ማርቆስ እንደገለጠልን «በዚያን ጊዜም ከውሀው ወጣ ሰማዮች ሲቀደዱ አየ፣ መንፈስ ቅዱስም እንደ





ርግብ ሲወርድበት ድምፅም ከሰማይ ወጣ፣ እንዲህ ሲል አንተ ነህ ልጄ የምወድህ ደስታዬን የማይብህ::[19]

በነዚህ በሁለቱ ወንጌላዊያን አገላለጥ እንደምንረዳው ያለ መቀላቀል ፫ አካላት እንዳሉ ነው:: ግን የሥላሴ ስማቸው ያልተገለጠ በመሆኑ ሌላም አስተያየት የሚያስከትል በመሆኑ ቅዱስ ማቴዎስ በተሻለ መልክ ለሥላሴ ስመ ተፋልሶ እንደሌለባቸው አድርጎ እኩልነታቸውንም በመግለጥ ስማቸውን ጠርቶ እንዲህ ሲል ያስረዳናል:: «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ እስተምሩ አጥምቋቸውም፣ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም» ሲል እናገኛለን::[20] ይኸም ሁሉ ሲሆን ግን በባሕርይ አንድነታቸውንም ስለምናምን አንድ አምላክ ዘለዓለማዊ ብለን እናምናለን፣ እናመልካለን::

## 2. የእግዚአብሔር አካላዊነት::

እግዚአብሔር አምላክ የሁሉ ፈጣሪ የሁሉም አስገኝ እንደመሆኑ አካላዊነቱ የታወቀ ነው:: በዓለምም ሙሉ ሆኖ ሁሉን የሚያስተዳድር የሚቆጣጠር እርሱ ብቻ ነው:: ከቶ እርሱ የሌለበት እርሱም የማይመለከተው የማያስተዳድረው ፍጥረት የለም፣ እንዲያውም እርሱ ብቻ ዓለምን ይወስናል እንጂ እርሱን የሚወስን ከቶ የለም:: የእግዚአብሔር በዓለም ሙሉ መሆን ከጠባይዓቱ መግለጫዎች ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል፣ ከመሠረታዊ እምነታችንም አንዱ ክፍል ይኸው ነው፣ ምክንያቱም አምላክ ስንጠራው ይሰማናል፣ በጎ አድራጎታችን ሁሉ ይመለከትልናል፣ ለሠራነው ሁሉ ዋጋ ከፋይነቱን ለመረዳት ያስችላልና::

የእግዚአብሔርን አካላዊነት ከመመልከት ጋር ለአካሉ ቅርጽ መልክ እንዳለው አድርገው የሚገምቱ አሉ፣ መጻሕፍትም በንባብ ይኸኑ ያሰማሉ፣ ለምሳሌ «ንግበር ሰብእ በአርዓያነ ወበአምሳሊነ» የሚለው[21]:: እንዲሁም «እስመ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ኀበ ጻድቃኑ፣ ወእዝኑሂ ኀበ ስእለቶሙ»[22] የሚሉትን፣ ያመለክታሉ:: ይሁን እንጂ ቅርጽ መልክ መጠን ያለው ሁሉ ስፋቱን ጥበቱን ርዝመቱንም ክብደቱን በጠቅላላም መጠኑን ሁሉ በግድ ያመለክታል፣ ውሳኔውን ይገልጣልና::



www.ethiopianorthodox.org

እንዲህም ከሆነ ደግሞ አምላክ ውሱን ነው በማለት ብዙ ሊቃውንት የእግዚአብሔርን ሕልውና አካላዊነትም ተቀብለው ስለቅርጹ ስለመልኩ፣ የሚነገረውን በቸልታ ያልፉታል፣ ይኸንም አስተያየት በቀና መንፈስ ሲመለከቱት እውነት ነው ያሰኛል፣ ምክንያቱም «ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ፣ አላ ወልድ ዋሕድ ዘሀሉ ውስተ ሕጽነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ» የሚለው ወንጌላዊው ምስክርነት ትክክለኛ ቃል ነውና::[23] እንዲሁም «አልቦ ዘይሬኢ ገጽየ ወየሐዩ አሐተ ሰዓተ በዲበ ምድር» የሚለው አስረጂ የእግዚአብሔርን ቅርጽ መልክ ለማወቅ የማይቻል መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ይገኛል::[24]

እግዚአብሔርም መንፈስ ስለሆነ የሚያየው ከቶ የለም፣ ሊኖርም አይችልም:: እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ መልክ ቅርጽ የለውም፣ ሊኖረው አይችልም፣ ቢኖረውም ያየው የለምና ይኸን ይመስላል፣ ይኸንንም ያክላል የሚለው የለም::[25] የማይታየውን የማይመረመረውንም አምላክ ይኸን ይመስላል ይኸንም ያክላል ብሎ ቅርጽ ሰጥቶ፣ መልክ አውጥቶ ወሰን ለይቶ መናገር እንደ ድፍረት ይቆጠራል:: ከላይ ለተጠቀሱት አስረጂዎች ሁሉ ልዩ ትርጓሜን በመስጠት አስተያየታቸውን እንደሚከተለው ይገልጣሉ:: ለምሳሌ «ንግበር ሰብአ በአርያነ ወበአምሳሊነ» ያለው ትርጉም እግዚአብሔር በመልክ፣ በቅርጽ በመጠንም እኛን ሰዎችን ይመስላል ማለት ሳይሆን ሰው የእግዚአብሔር ምሳሌ የሚሆነው በዕውቀቱ፣ በገዥነቱ፣ በሕያውነቱ፣ ሌላም ይኸን በመሳሰለ እንደሆነ ያትታሉ የሚመስለውም አስተያየት ይኸ ነው:: እንዲሁም «እግዚአብሔር ዐይኑ ወደጻድቃኖቹ ጆሮው ወደልመናቸው ነው» ያለው እግዚአብሔር አምላክ ሁሉን ማወቁን ሲጠሩት መስማቱን፣ ፈጥኖ መርዳቱን በመመልከት እንደሆነ አስፋፍተው ይናገራሉ::

ይኸን ሁሉ አማናዊ ለማድረግ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ወገን ሁሉ በጸናች እጅ ከፍ ባለችም ክንድ ከግብፅ ባርነት ነፃ አወጣቸው ሲል ሲናገር እናገኛለን፤ ይኸም ማለት እግዚአብሔር በእጅ መሥራቱን ሸክም መሸከሙን አያመለክትም :: እንደ አምላክነቱ ሁሉን ለማድረግ መቻሉን ሥልጣኑን ችሎታውን ለመግለጥና ለማስረዳት የተናገረው ነው





እንጂ:: በእርግጥም እግዚአብሔር አምላክ ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉትን እሥራኤልን ከፍ ባለ ሥልጣኑ በሚያድንም ኃይሉ እንደ ተቤዣቸው ፣ ከባርነት ቀንበርም ነፃ እንዳወጣቸው የታወቀ ነውና::

## የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ የሚያምኑት የሚያስተምሩትም::

1. እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን መልኩ ቅርጹ መጠኑም ይኸን ይመስላል፣ ይኸነንም ያክላል የማይባል፣ የማይታይ፣ የማይታወቅ መሆኑን ነው::

2. ወንጌላዊው ዮሐንስም በጻፋቸው መጻሕፍት በወንጌሉም በመልዕክቱም መላልሶ እንደ መሰከረው እግዚአብሔርን ያየው የሌለና ወደፊትም ሊያየው የሚችል እንደሌለ ነው:: እግዚአብሔርንስ ያየ ከሌለ እንዴት ግምታዊ አነጋገር ተሰጥቶ መልኩ፣ ቅርጹ፣ ይኸን ይመስላል ሊባል ይቻላል?:: አሁንም ለእግዚአብሔር መጠን፣ ቅርጽ፣ መልክ፣ ሰጥቶ መናገሩ እግዚአብሔርን ውሱን ያደርገዋልና ያላዩትን የማያውቁትን ይኸን ይመስላል ይኸነንም ያክላል ብሎ መናገሩ ዝርዝር ሁኔታውንም መግለጡ በጣም ከባድ ነገር ነው::

የኛም ቤተ ክርስቲያን አባት የሆነው አባ ሕርያቆስም የእግዚአብሔርን ሐልዎት በተገቢው መንገድ ሲናገር መጥቶ ስለቅርጹ ስለ መልኩ ግን በአፍራሹ መንገድ እንዲህ ሲል ይናገራል «አኮ ዘቦቱ ለመለኮት እንግዳ ወፍጽም ወዘባን እንተ ድኅር ሀበ ዘይትርአይ ወበዘይትገመር:: አላ ግልቡበ ውእቱ በነደ እሳት ነደ እሳትሰ ለሊሁ ውእቱ» ይላል:: ይኸም ማለት ለመለኮታዊ አካል አንገት ደረት የለውም፣ የፊት የኋላ መልክ የለውም፣ በጉልህ ለመታየት ይቻል ዘንድ፣ ነገር ግን እርሱ በነበልባለ እሳት የተሸፈነ የተጋረደም ነው፣ ነበልባለ እሳትም ያልኩት እርሱ ራሱ ነው ሲል ሰፋ አድርጎ ገልጦ እናገኘዋለን::[26]



www.ethiopianorthodox.org

እኛም ይኽነኑ እውነተኛ አስተያየት እንከተላለን እናስተምራለን፣ ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያናችን አባት አስተያየት ነውና:: ለእሳት ነበልባል አካል አለው፣ ነገር ግን ረቂቅ ነው፣ ስለዚህም ቅርጽ የለውም ይኽን ይመስላል ይኽነን ያክላል አይባልም የኋላው የፊቱ ቅርጽና መልክ የትኛው እንደሆነ ሊታወቅ አይችልምና:: እንግዲያውስ መለኮታዊ አካልም <u>ይኽን ይመስላል ይኽነንም ያክላል</u> ተብሎ ግምታዊ አነጋገር ሊሰጥ አይቻልም::

የእግዚአብሔርን ህልውና ማመን፣ ፍጹም አካል ያለው መሆኑን ማመን አለብን፣ ግን እንደ እሳት ነበልባል ቅርጹን መልኩን ለመለየትና ለማወቅ የማይቻል መሆኑን ማወቁና ማመኑ ደግሞ ተገቢ ነው:: በ፲፰ኛው ምእት ዓመት በሀገራችን በዚህ ርእስ ክርክር መደረጉ ይታወቃል፣ ግን ውሳኔው ትክክል አይደለም የተሰጠውም አስረጅ በቂ አይደለም::

«ርቱዐ ሃይማኖት» የሚባለው መጽሐፍ «.... ከመ ቦቱ ጥዩቀ ዘሀሎ ኅዕለ ሰብእ መልክዕ፣ ርእሰኒ ወጸጉርኒ፣ ወአዕይንትኒ፣ ወአዕዛንኒ፣ አፍኒ ወእድኒ፣ ወእግርኒ፣ ወአጻብእኒ፣ ወዝኩሉ ይትረከብ በኅዕለ አምላክ ዘሀሎ በኅዕሌነ»[27] በማለት ለክርስቶስ ሰው ለሆነው አምላክ ያለውን ቅርጽና መልክ ግዘፍ ሁሉ ለመለኮታዊ አካል ሰጥቶ ገልጦ ተናግሮ እናገኘዋለን::

ለመለኮትም ይኸ ሁሉ ይኖረው ዘንድ ሥጋ የለውም ግዙፍም አይደለም መንፈስ ነው እንጂ እግዚአብሔር አብ በደመና ድምፅ አሰማ ይባላል እንጂ ከቶ ተገልጦ አልታየም::[28] ሙሴም የእግዚአብሔርን መልክ ለማየት ፈልጎ ፊትህን አሳየኝ ብሎ ለምኖ ነበር ነገር ግን ለማየት የማይቻል ሆኖ እንደቀረበት እናገኛለን::[29]

ነቢያትም እግዚአብሔርን ያዩት በብዙ ምሳሌና በራእይ እንጂ ፊት ለፊት በትክክለኛ መለኮታዊ መልኩን፣ መለኮታዊ ገጹን አይደለም፤ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ለማየት አይቻልምና፣ ለምሳሌ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በንጉሥ አምሳል በዙፋን ተቀምጦ ተወስኖ አይቶታል::[30] ነቢዩ ዳንኤልም





እንዲሁ በራእዩ እግዚአብሔርን በፍታ ተላብሶ በአፈር ወርቅ ዝናር ታጥቆ እንዳየው ገልጦልናል::[31] ሌሎች ነቢያትና ሐዋርያትም እንዲሁ በራእይ እንደተገለጠላቸው ውሱን መስሎ በክብር ዙፋን ተቀምጦ፣ የዘመኑን ንጉሥ መስሎ አይተውታል[32]:: እታዲያ ይኸ ሁሉ ምሳሌ እንጂ አማናዊ ሆኖ አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ ውሱን አይደለምና፣ በዓለሙ ሁሉ ሙሉ የሆነ ሁሉን የሚያይ ከሁሉ የሚደርስ፣ ሁሉን የሚይዝ መልኩ ቅርጹ መጠኑ የማይታወቅ ነውና::

አካል ያለው ግን ቅርጹ የማይታወቅ መጠኑ የማይታይ ከፍጥረቱ ውስጥ ብዙ ይገኛል እንዲህ ያለ ብዙ ነገር መኖሩ ሲታወቅ ፈጣሪ እግዚአብሔርማ ይኽን ያክላል ተብሎ ቁመቱን መጠኑን፣ ይኽነንም ይመስላል ብሎ መልኩን ቅርጹን ግምት ሊሰጥ የሚችል ማነው? ይኽን ካላልንማ እግዚአብሔርን ዝርው ያደርግብን የለም ለሚለው ፍራቻ እግዚአብሔር ዝርው አይደለም፣ ህልውና አለው፣ ስለዚህም አካል አለው ህልውና ያለው ሁሉ አካል አለውና ግን ቅርጹና መልኩ፣ መጠኑም የማይታወቅ ነው ::

እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ የሚዳሰስ አካል እንደኛም ያለ ቅርጽ አለው፣ ምክንያቱም ሰው ሆኗልና፣ ሥጋንም ለብሷልና:: እኔን ያየ ሁሉ አባቴን አየ፣ ሲል የተናገረው በመለኮት አንድ መሆኑን ከአባቱ ጋርም ያለውን አንድነቱን ለመግለጥ እንጂ እንደ እርሱ ያለ ግዙፍ አካልና ቅርጽ እንዳለው አድርጎ መናገሩ አይደለም:: ይኽነንም የመሰለ እኔና አብ አንድ ነን ሲል ተናግሯል፣ ይኸም ኀቡረ ህላዊ መሆኑን በመለኮት አንድ መሆኑን ለመግለጥ እንጂ አብ እንደኔ ሥጋን ለብሷል፣ እንደኔ ሰው ሆኗል፣ እንደኔም ግዙፍ አካል አለው ስለዚህ አንድ ነን ማለቱ አይደለም::

የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር በዐይነ ፍጡራን የሚታይ በልቡና ፍጡራን የሚገምት ይኽን ይመስላል፣ ይኽነንም ያክላል የማይሉት አምላክ ነውና::



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፩

## የእግዚአብሔር ባሕርይ መግለጫዎች::

የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዳለ እንናገራለን፣ በእግዚአብሔርም እናምናለን ስንል የእግዚአብሔር ባሕርይ እንዴት ይገለጣል? ህላዊውስ (አኗኗሩ) እንዴትና በምን ይታወቃል የሚል አስተያየት በልቡናችን ይወጣል ይወርዳልም፣ ግን መልሱ እንደሚከተለው ይሆናል::

እግዚአብሔር ባሕርዩ ረቂቅ ነው፣ ስለዚህ ይህን ያክላል፣ ይህንም ይመስላል፣ ከዚህ የለም፣ ከዚያ ይኖራል፣ በማለት ስለርሱ የሚሰጥ ሐተታ ሊኖር አይችልም፣ ይኸንንም በአለፉት ምዕራፎች ተናግረናል፣ ምክንያቱም ፍጡር የፈጣሪውን አኗኗርና ባሕርይ መርምሮ ሊያውቅና ሊደርስ አይችልምና:: ከጥንት ጀምሮ ፈላስፎች ጊዜያቸውን ያሳለፉት ይኸን ምሥጢር ለማወቅ በመመርመር ነበር፤ ግን ፩ኛውስ እንኳን ከዚህ ደረስኩኝ፣ ይኸነንም አስረጅ አገኘሁኝ ሲል ግልጥ የሆነ አስረጂ አልሰጠም:: ይኸም ከሆነ፣ አሁንም ስለእግዚአብሔር የሚሰጠው ሐተታ ሁሉ ያኑ የመሰለ መሆኑ ነው:: ይሁን እንጂ እንደ እውነተኞች ክርስቲያንነታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረን፣ ቅዱስ መንፈሱም በገለጠልን መሠረት በመጠኑ ስለርሱ እናውቃለን::

ባሁኑ ጊዜ ማለት በአፀደ ሥጋ ሳለን ስለእግዚአብሔር ያለን ዕውቀት የተወሰነና የተመጠነ ቢሆንም ቅሉ አምፃዌ ዓለማትነቱን፣ ፈጣሬ ፍጥረታትነቱን እናምናለን፣ እርሱንም እናውቃለን፣ በኋላ ግን እርሱ እንደሆነ እንደርሱነቱ በፍጹም ዕውቀት እናውቀዋለን፣ ማለት ዓይን በዓይን እናየዋለን «ዛሬ እኛ እናያለንና በምሳሌ በመስተዋት እንድናይ፣ የዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፣ ዛሬ ከእውቀቱ ክፍያ ዐውቃለሁ የዚያን ጊዜም አውቃለሁ እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ» ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ ይነግረናል::[1]





ቅዱስ መጽሐፍ ስለእግዚአብሔር ባሕርይ የማይመረመር ምሥጢር የማያስገባም በር መሆኑን ሲያስረዳ «እግዚአብሔር መንፈስ ነውና»[2] ብሎ ዘግቷል፣ ይኸም ማለት ረቂቅ፣ የማይታይ፣ የማይጨበጥ፣ የማይመረመር ነዋሪ ነው ማለት ነው:: እንግዲህ «እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ፣ ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ» ሲል ሊደረስበት ሊመረመር ግምትም ሊሰጠው የማይቻል መሆኑን ነቢዩ ኢሳይያስ ተናግሯል::[3]

ሆኖም እንደ እግዚአብሔርነቱ በሚገባ ለማወቅ ባንችልም እግዚአብሔር ቸር ከመሆኑ የተነሣ ዘወትር ከፍጥረቱ ጋር በሚያደርገው ግንኙነትና አገላለጥ እንደተረዳነው ቅዱሳን አባቶችም በልዩ ልዩ ድርሰታቸው እንዳስተማሩን ሁሉ፣ ቅዱስ መንፈሱም እንደ አእምሮአችን ስፋት መጠን እንዳበራልን ሁሉ፣ የምናውቀውን የምናምነውን ብቻ ከዚህ እንደሚከተለው በመጠኑ እንገልጣለን::

### 1ኛ. በዓለም ሙሉ ስለመሆኑ::

ልዑል እግዚአብሔር ታላቅና ገናና አምላክ ከመሆኑ የተነሣ በዓለም ምሉዕ ነው፣ ፍጥረቱም ሁሉ የርሱ ነው፣ እርሱም የሌለበት እርሱም የማይደርስበት ቦታ ከቶ የለምና:: በነቢዩ በኤርምያስ አድሮ «በውኑ እኔ የቅርብ አምላክ አይደለሁምን? የሩቅም አይደለሁም፣ ሰው በስውር ቢሸሸግ እኔ አላየውምን? ይላል እግዚአብሔር፣ በሰማይና በምድር የመላሁ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር» ሲል ሰፊ ማስረጃን በመስጠት ተናግሯል::[4] እግዚአብሔርን የሚወስነው ከቶ የለም፣ እርሱም በተወሰነ ቦታ የሚኖር ውሱንም አይደለም::

ልዑል እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ የታመነም የባሕርይ አምላክ ስለሆነ፣ በአንድ ቦታ የማይወሰን መሆኑን በልዩ ልዩ አስረጂ ገልጧል:: በዓለምም ምሉዕ ነው ስንል ደግሞ በሚታየውም በማይታየውም በራቀውም በቀረበውም ፍጥረት፣ በጠቅላላውም በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው ማለት ነው:: ነቢዩ ዳዊትም «ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ ዓለምኒ ወኩሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ» ሲል ተናግሯል::[5] ይኸም ማለት ምድር



www.ethiopianorthodox.org

ምላቷም ለእግዚአብሔር ናት፣ ዓለምም በርሷም ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ ማለቱ ነው:: ዓለም የእግዚአብሔር ገንዘቡ ናት እግዚአብሔርም በዓለም ሞልቶ ይኖራል:: ከቶ እርሱ የሌለበት ቦታ የለም:: ቅዱስ ጳውሎስ፣ ዓለም ሁሉ በርሱ ሕይወት አግኝቶ ይኖራል፣ ይንቀሳቀሳልም ብሏል::[6] ከቶ እግዚአብሔር የሌለበት ቦታ እግዚአብሔርም ያላደረበት ፍጥረት ሕይወትን አግኝቶ የሚኖር የለም::

እንደገና ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔርን በዓለም ምሉነት ሲገልጥ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ፣ ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ፣ ወደሰማይ ብወጣ አንተ ከዚያ ነህ፣ ምንጣፌንም በሲኦል ባነጥፍ ከዚያ እነሆ አንተ አለህ፣ የወገግታ ክንፎችን ብወስድ በባሕር ዳርም ብቀመጥ ከዚያም ደግሞ እጅህ ትመራኛለች፣ ቀኝህም ትይዘኛለች» ሲል ግልጥ አድርጎ ተናግሯል::[7] እግዚአብሔር በአንድ ቦታ የሚቀመጥ የሚወሰንም አይደለም፣ ዓለምን እርሱ ይወስናል እንጅ እርሱን ከቶ የሚወስነው የለም ውሱንም ከሆነ አምላክ ሊሆን ሊባልም አይቻልምና:: ይህንም አማናዊ አድርጎ ቅዱስ ሉቃስ ሲመሰክር «ዓለሙን የፈጠረ አምላክ በእርሷም ያለውን ሁሉ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና፣ ከቶ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም» ሲል ያስተምረናል::[8]

በዓለም ምሉዕ ነው ስንል ግን ዓለምን እርሱ ይወስናል እንጅ ዓለም እርሱን አይወስነውም፣ ከቶ እርሱን የሚወስነው ነገር የለም፣ የሚሠውረው፣ የሚጋረደው፣ የሚከለክለውም የለም፣ እንዲህ ሲሆን ግን እኛ እንደመሰለን ቦታ ለይተን እግዚአብሔርን በሰማይ ያለህ እንለዋለን፣ ክርስቶስም ሲያስተምር «አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር» ብሎ በዓለም ምሉዕ ሲሆን በሰማይ መኖሩን መስክሯል[9]:: ይኸም አገላለጥ ስለ ልዕልናው ስለ ክብሩ ስለ ከፍተኛነቱ ለማስረዳት ነው እንጂ በውስጥም እርሱ ነው፣ በአፍአም እርሱ ነው፣ በላይ እርሱ ነው፣ በታችም እርሱ ነው፣ ጠፈሩ እርሱ ነው፣ መሠረቱም እርሱ ነው፣ በዓለምም ምሉዕ ከመሆኑ የተነሣ ሁሉን በትክክል ያስተዳድራል:: ይመራል ይመግባል::





## 2ኛ. ስለ ከሃሊነቱ::

ኃያል እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው አምላክ ነው:: ይኸውም በሥነ ፍጥረት ይታወቃል፣ ማለት ይህን የተከናወነ ዓለም ብቻውን ያለረዳት በመፍጠሩ፣ ለዓለምም ልክ መልክ ወሰንና ድንበር በመለየቱና ሲፈጥርም ያቃተው ሳይኖር ሁሉን አስተካክሎ በመፍጠሩ የፈጠረውም ፍጥረት ብዙ ሲሆን ሁሉን አስተካክሎ በመጠበቁ፣ በመመገቡና በማስተዳደሩ ከሃሊነቱ ይታወቃል ::

መፍጠርን ያቆመው ደክሞት የማይችልም ሆኖ አይደለም፣ የፈቀደውን ያህል ፈጥሯልና: «ኩሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር» ሲል ነቢዩ ዳዊት ተናግሯልና::[10] ለመፍጠር ለመሥራት ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን የሚወስነው ፈቃዱ ብቻ ነው፣ ከፈቀደ ብዙ ይሠራል፣ ካልፈቀደ ግን ይተወዋል፣ ቅዱስ ፈቃዱ በሆነ ጊዜ በቃሉ ሲያዝዝ ብቻ ሆኖ ይገኛል፣ የሰዓት የቅጽበት ያህል አይቆይም:: ይኸን የተከናወነ ዓለም የፈጠረው ሁሉን ለማድረግ ስለቻለና ሁሉንም ለመፍጠር ስለፈቀደ ነው::

እግዚአብሔር የሁሉ ጌታ፣ የሁሉ ንጉሥ፣ የሁሉም ገዥ ነው፣ ሁሉን ለመሥራት የቻለ እርሱ ብቻ ነው፤ ስለዚህ ሁሉን ጀመረ ሁሉንም ፈጸመ፣ ከቶ አቅቶት የቀረ ነገር የለም:: «ሁሉን እርሱ አለ ሁነውም ተገኙ፣ አዘዘም ተፈጠሩ»[12] በዚህም መሠረት ሁሉን ፈጠረ አቅቶት የቀረ ነገረ የለም:: በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ሊደረግ ይቻላል፣ ስለዚህ ራሱ አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም እንዲህ አለው፣ «በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? ባልኩህ ዘመን ወደአንተ እመጣለሁ፣ የዛሬ ዓመት ሲሆን ሣራ ልጅ ይሆንላታል»[13] ለእግዚአብሔር ከቶ የሚሳነው ነገር እንደሌለ ይኸ ትልቅ ምስክር ነውና:: ኢዮብም «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንክ እኔ አውቃለሁ፣ አሳብህንም ይከላከል ዘንድ እንዳይቻል»[14] እያለ ስለከሃሊነቱ ወይም ስለችሎታው በሰፊው ተናግሯል::

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም «እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር» ብሏል፣ ይህም ማለት ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ከቶ የለም ማለት ነው::[15] እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ



www.ethiopianorthodox.org

ችሎታ እንዳለው ይኸን መስክሯል፣ ይኸንም ቃል የተናገረው መልአክ፣ የጻፈውም ወንጌላዊ ስለሆኑ ምስክርነታ ቸው ከፍ ያለ ነው፣ ስለዚህ እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ ችሎታ እንዳለው ማመን አለብን:: ከቶ እንደ እግዚአብሔር የሠራ ለመፈጸም የቻለ የለም፣ እርሱ ብቻ ጀማሪ እርሱ ብቻ ፈጻሚ ነው:: ስለዚህ እርሱ ብቻ ሁሉን ለማድረግ ቻለ:: ክርስቶስም ሲያስተምር በሰው ዘንድ የማይቻለው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚቻል መስክሯል::[16] ሁሉን ቻይ ለመሆኑ ነቢዩ ኤርምያስ የሰጠው ምስክርነት የሚከተለው ነው «አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ እነሆ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋችም ክንድህ ፈጥረሃል፣ ለአንተም የሚሳንህ ነገር የለም»[17] ሲል አስረድቷል::

የእግዚአብሔር ከሃሊነት በዘመን አይወሰን፣ በሚዛን አይለካ፣ በቁጥር አይመደብ፣ በሰው እጅ አይመጠን፣ በእውነት ፍጹም ከሃሊ ነው፣ ፍጹም ከሃሊም እርሱ ብቻ ነው ብለን እንወስናለን:: ሰው ከሃሊ ቢባል ብዙ ጉድለት ብዙም ድካም አለበት በሕማም፣ በሞት ይለወጣል፣ ደካማነት ይታይበታል፣ እግዚአብሔር ግን፣ ይኸ ቀረህ የማይባል ፍጹም ከሃሊ ነው፣ እንዲያውም ለሰው ልጅ ኃይልን የሚሰጥ የሚያድል እርሱ ብቻ ነው:: የሰው ኃይሉ ለተወሰነ ጊዜ በተወሰነም ሀገር ላይ ብቻ ነው፣ ምንም ቢሆን ዘመን ይሽረዋል፣ የበለጠ ኃያል ተነሥቶ ይጥለዋል፣ ያረጃል፣ ያፈጃል፣ በበለጠም ይሞታል፣ እግዚአብሔር ግን ዘመን አልፎ ዘመን ቢተካ ሁልጊዜ ኃያል ነው፣ በባሕርዩ ሞት በመንግሥቱ ሽረት የለበትም፣ ሁሉን ለማድረግ ሁሉን ለመሥራት ሁል ጊዜ ለመኖር ኃይል ገንዘቡ የሆነ እርሱ ብቻ ነውና::

እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለውና ሁሉንም ያደረገ አምላክ እርሱ ብቻ ነው፣ ይኸንም ነቢዩ ኢሳይያስ ሲመሰክር «እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አጭር አይደለችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፣ ነገር ግን ኃጢአታችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለየች፣ ከፊታችሁም ከእናንተ ፊቱን ሠወረች እንዳይሰማ» ይላል::[18]





## 3ኛ. ስለ ዘለዓለማዊነቱ:-

እግዚአብሔር ቀድሞ የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር ዘለዓለማዊ አምላክ ነው፣ ይኸም ማለት ዘመን አይወስነውም፣ ከዘመን በፊት ነበር፣ አሁንም አለ፣ ወደፊትም ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኖራል:: «ኢይበጽሖ ሕሊና ሰብእ ለቅድምናከ ወኢይረክቦ ሥምረተ መላእክት ለደኅሪተከ» ሲል ዮሐንስ አስረድቷል::[19] ይኸም ማለት በሰው ሐሳብ እግዚአብሔር ጥንት እንዲህ ነበር ብሎ ቀዳማዊነቱን ለመመርመር አይችልም፣ አእምሮው አይደርስምና፣ ፍጻሜህንም የመላእክት አሳብ እንኳን አይደርስበትም ማለቱ ነው::

ሁሉ ያልፋል፣ ይጠፋል፣ ያረጃል፣ የተሾመው ይሻራል፣ በጠቅላላም ለፍጡር ሁሉ ቀዋሚና ነዋሪ ህልውና የለውም፣ የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖርም እግዚአብሔር ብቻ ነው:: «ተራሮች ሳይፈጠሩ ምድርም ዓለሙም ሳይፈጠር ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አንተ ነህ» ሲል ነቢዩ ዳዊት ዘለዓለማዊነቱን አስረድቷል::[20] ኢዮብም በበኩሉ እነሆ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፣ እኛም አናውቅም የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም» ሲል ብሉየ መዋዕል አምላክ መሆኑን መስክሯል::[21] እንደገናም ነቢዩ ዳዊት የአምላክን ዘለዓለማዊነት አጉልቶ ሲገልጥ «ጌታ ሆይ አንተ ግን ለዘለዓለም ትኖራለህ መታሰቢያህም ለልጅ ልጅ ነው» ይላል::[22]

ከዘመን በፊት ነበር፣ በዘመን መካከል አለ÷ ከዘመን በኋላም ይኖራል፣ አያረጅም አያፈጅም ሁል ጊዜ እርሱ እንደሆነ ይኖራል:: መጀመሪያና መጨረሻ የለውም፣ መለወጥ ወይም መናወጥ ማለቅ መድቀቅ የለበትም፣ በመንግሥቱ ሽረት፣ በባሕርዩ ሞት የለበትም፣ ለመገኘቱም ምክንያት የለውም፣ ቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ነው፣ ዛሬም ያለ ነው፣ ደግሞም ዓለሙን አሳልፎ፣ ወደፊትም ለዘለዓለሙ ጸንቶ የሚኖር እርሱ ብቻ ነው:: ነቢዩ ኢሳይያስ ዘለዓለማዊነቱንም በዓለም ሙሉነቱንም በአንድ ጊዜ ሲገልጥ እንዲህ ይላል፣ «ያዕቆብ ሆይ የጠራሁህ እሥራኤል ሆይ ስማኝ እኔ ነኝ፣ እኔ የፊተኛው ነኝ፣ እኔም የኋለኛው ነኝ፤ እጄም ምድርን መሠረተች፣



www.ethiopianorthodox.org

በምላሴ የለችምና» ሲል መስክሯል::[32] እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ «እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዐይኖች ፊት ሁሉ፣ የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» ሲል ሁሉን የሚያውቅ ከማንም የማይጠይቅ መሆኑን ገልጦ ተናግሯል:: ልዑል አምላክ ማንም ሊነግረው አይሻም፣ ከማንም ጋር አይማከርም፣ ፍጹም ዐዋቂ ስለሆነ እንደ ዐዋቂነቱ እንደ ፍጹም ጥበቡ ይሠራል::[33]

በዓለም ምሉዕ እንደመሆኑ በዓለም ያለውን የሚሠራውን የሚታሰበውን ሁሉ፣ ያውቃል:: ከመደረጉ አስቀድሞ የሰውን ልቡና ይመረምራል:: እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ ከማንም የማይጠይቅ አምላክ ነው:: ኩላሊት ያጤሰውን፣ ልቡና ያመላለሰውን ያውቃል፣ ስለዚህ ሰውረንም ገልጠንም ብንሠራ በርሱ ዘንድ እንደተተከለ ትርሽማ እንደተሰጣ ሽማ ግልጥ ሆኖ ይታያል::

ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔርን አዋቂነት በአድናቆት ሲገልጥ እንዲህ ይላል «እግዚአብሔር ገናና ነው፣ ኃይሉም ከፍተኛ ነው:: ለእውቀቱም ወሰን የለውም»::[34] እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል፣ ግን ይታገሣል፣ ቻይ እንደመሆኑ ሁሉን ይችላል፣ ስለዚህም ሰሎሞን ሲናገር «የእግዚአብሔር ዐይኖች በሥፍራው ሁሉ ናቸው ጻድቃንንና ኃጥአንን ይመለከታሉ» ይላል::[35] ስለታጋሽነቱም ዝም ቢል፣ ስለመሐሪነቱም ቻል ቢል እነደማያውቅ ልንገምተው ከቶ አይገባንም፣ እውነተኛ አዋቂና ልባዊም አምላክ ነውና:: እርሱ ሳያውቅ የእርሱም ቅዱስ ፈቃድ ሳይሆን ከቶ የተሠራ ወደፊትም የሚሠራ የለም::[36] ሰው አዋቂ ቢባል በዕድሜ ይለወጣል በሞት ይጠፋል ወይም ፍጡር እንደመሆኑ ዕውቀቱ የተወሰነ ይሆናል፣ ያውም ቅሉ የሚገለጥለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፣ እግዚአብሔር ግን አምላክ ስለሆነ ዕውቀቱ የባሕርዩ ነው፣ ያውም ፍጹም ነው፣ መቼም መቼ አይለወጥም፣ ምንም ምን አይሠወረውም::

የእግዚአብሔር ዕውቀት የከዋክብትን ብዛት ያውቃል ስለዚህም በየስማቸው ይጠራቸዋል::[37] የእያንዳንዱን እርምጃ እርሱ ይቆጣጠራል፣ ሁሉን ያከናውናል::[38] እኛ ማንኛውንም





ነገር ከአምላክ ሰውረን የሠራን ይመስለናል እንጂ አምላክ ሥውሩንም ግልጡንም ያውቃል፣ ሥራችንንም እርምጃችንንም እርሱ ይቆጣጠራል፣ ይኸንንም ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ይገልጠዋል:: «አቤቱ አንተ መረመርከኝ አወቅኸኝም:: መቀመጤንም መነሣቴን አወቅህ፣ አንተ አሳቤን ከሩቅ አስተዋልከ፣ መንገዴንና እረፍቴንም አንተ በረበርከ፣ አንተ መንገዴን ፈጽመህ አወቅህ»::[39] አምላክ ሁሉን ስለሚያውቅ የተቸገረውን ይረዳል፣ ያዘነውንም ያጽናናል፣ የሚጮኸውን ይሰማል ይረዳል ::

## 5ኛ. ስለ ፍጹም ጥበቡ:-

የእግዚአብሔር ፍጹም ጥበብ በዚህ በተከናወነው ዓለም (ፍጥረቱ) ይታወቃል፣ ማለት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ጸንቶ በመኖሩ በጥንካሬው፣ ወሰኑን ደንበሩን ሳያጠፋ ጸንቶ በመኖሩ ዓላማውን ባለመለወጡ፣ ሠራተኛው ወይም ተጠባቢው ፍጹም ዐዋቂና ጥበበኛ መሆኑን ያስረዳል፣ ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር እንደሆነ ነው:: ስለ ፍጹም ዕውቀቱ ሐዋርያው ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ባለጠግነት ጥበቡና ዕውቀቱ እንዴት ትልቅ ነው?:: ፍርዱስ እንዴት የማይመረመር ነው፣ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም» ሲል በአድናቆት ገልጦት ይገኛል::[40] ሰዎች ተጠብበው የሠሩት በጊዜ ብዛት ሲያልቅ፤ አንድም ሲደቅ፤ መሥራቱን ሲያቋርጥ እናገኘዋለን፣ የእግዚአብሔር ፍጥረት ግን ሳያልቅ ሳይደቅ፣ ጊዜ ሳይለውጠው ባለበት ጸንቶ ሥራውን በመቀጠል እስካሁን ስለሚገኝና ወደፊትም ጸንቶ ስለሚኖር የሠራተኛውን ፍጹም ጥበብ ይመሰክራል:: ለዚህም አስረጂ «አቤቱ የእጅህ ሥራዎች ምንኛ ይበዙ፣ ሁሉንም በጥበብ ፈጠርከ» ሲል ነቢዩ ዳዊት ያመሰግናል::[40]

ዓለም በጠቅላላው የእግዚአብሔር የጥበብ ሥራ ነው፣ ስለዚህም ቅዱሳን ሁሉ በእግዚአብሔር ፍጹም ጥበብ በአድናቆት ተውጠው ሁልጊዜ ዕጹብ ድንቅ በማለት ላይ ይኖራሉ:: የምርምርም ማዕበል እያንገላታቸው ወደ ቀደመ አለዕውቀታቸው ሲመልሳቸው ይገኛሉ::[41] አሁንም ቢሆን እያንዳንዱን ሥነፍጥረት አተኩረው በተመለከቱት ልብም አድርገው በመረመሩት ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔርን ፍጹም ጥበብ ሊያስረዱ ይችላሉ። ዝንጉዎች ሰዎች ብቻ የእግዚአብሔርን መኖር ስለማያውቁ፣ ለማወቅም ስለማይጠይቁ፣ ፍጹም ጥበቡንና አስደናቂ ፍጥረቱን ሁሉ፣ የዓለምንም ክንውን ሊረዱና ሊገነዘቡ አይችሉም፣ ስለዚህ ይኽ የተከናወነ ዓለም እንዲሁ በዕድል የተገኘ ነው እያሉ፣ አንድም እንደተገኘ አድርገው የአእምሮአቸውንና የሕሊናቸውን ዓይን አሳውረው ይገኛሉ። የእግዚአብሔር ጥበቡ ረቂቅ ስለሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ግዙፉ ዓለም ሊረዳው አይቻለውም፣ ስለዚህም ከአድናቆት ውጭ ሆኖ ይገኛል። መንፈሳዊን ምሥጢር ለማወቅ በመንፈስ ባሕር መጥለቅ ያስፈልጋልና።

## 6ኛ. ስለ ቅዱስነቱ፡-

እግዚአብሔር አምላክ በባሕርዩ ፍጹም ቅዱስ ነው፣ ቅድስናም ገንዘቡ ነው ማለት ክፉት የሌለበት ኃጢአት የማይስማማው ቸርና ርኅሩኅ ነው። መላእክት፣ ሊቃነ መላእክት ሠራዊት፣ አጋእዝት ኃይላት ሥልጣናት መናብርት ኪሩቤልና ሱራፌል ሁሉ ሲያመሰግኑት ቅድስናውን በመግለጥ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ነውና። ይኽንንም ነቢዩ ኢሳይያስ «አንዱም ለአንዱ ይጮህ ነበር፣ እንዲህ ሲል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ፣ ምድር ሁሉ የቅድስናውን ምስጋና መላች» ሲል ገልጦ ተናግሯል[42]። ምድርም ሰማይም ቅድስና የሚያገኙት ፍጥረቱ ሁሉ የሚቀድሱት በእግዚአብሔር ነው።

ዮሐንስ ወንጌላዊም በራእዩ «... ዕረፍትም አልነበራቸውም ሌትና ቀን እንዲህ ሲሉ፣ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ ሁሉን የያዘ፣ የነበረና ያለ፣ የሚመጣም» እያሉ እንደሚያመሰግኑት ጽፎልናል።[43] ኢያሱም የአምላክን ቅድስና ሲያስረዳ «... እግዚአብሔርን ልታመልኩ አትችሉም፣ እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና» ይላል።[44] ነቢዩ ዳዊትም ስለ እግዚአብሔር ቅድስና ሲመሰክር «እግዚአብሔር አምላካችንን ከፍ አድርጉ፣ ቅዱስ ነውና፣ በታችም በእግሩ ስገዱ» ይላል።[45] ነቢዩ ዳዊት እንደገና «እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው በሥራውም ሁሉ ቅዱስ ነው»ሲል ቅድስናውን አጉልቶ





ተናግሯል።[46] የቅድስና መገኛው ሰውንም መላእክትንም፣ ሌላውንም ፍጥረት ሁሉ የሚቀድስ እግዚአብሔር ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን የእሥራኤል ቅዱስ እያለ ፴፱ ጊዜ ይጠራዋል፣ ፍጹም ቅዱስ እርሱ ብቻ ነውና። ለሰው ልጅ ሁሉ ቅድስናን የሚያድል የሚቀድስ እርሱ ብቻ ነውና። እርሱም ቅዱስ ንጹሕ ሆኖ ሰው ሁሉ ንጹሕ እንዲሆን እንዲህ ሲል ያዛል። እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ንጹሓን፣ ቅዱሳን ሁኑ።[47]

የእግዚአብሔር ንጽሕና ከሰው የተለየ ስለሆነ፣ ፍጹም ንጹሕ ፍጹም ቅዱስ ይባላል፣ ማለት ሰውን ንጹሕ ቅዱስ ቢሉት ጽድቅም ኃጢአትም ይስማማዋል፣ ስለዚህ ጽድቅን የሚሠራበት ጊዜ አለው፣ እንዲሁም የሰው ልጅ ተዋርዶ በኃጢአት የሚወድቅበት ጊዜ አለው፣ ይኽም ከሆነ፣ የሰው ልጅ እንደ ነጭ ልብስ ነው ማለት ይቻላል። ይኽ ነጭ ልብስ የሰጡትን የቀለም ዓይነት በትክክል ይቀበላል ይስማማዋል። ለእግዚአብሔር ባሕርይ ግን ጽድቅ እንጂ ኃጢአት አይስማማውም፣ ለውሀ ባሕርይ ቅዝቃዜ እንጂ ሙቀት፣ ለእሳት ባሕርይ ሙቀት እንጂ ቅዝቃዜ እንደማይስማማው። ስለዚህ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ቅዱስ ይባላል፣ ቅዱስም ስለሆነ፣ ሁልጊዜ በመላእክትም በሰውም ዘንድ ቅዱስ ቅዱስ ሲባል ይኖራል። «እስመ ንጹሓት ጠባይዓቲሁ ለእግዚአብሔር ዘእንበለ ነውር» ይለዋልና።[48] ብዙዎች ቅዱሳን በእግዚአብሔር ቸርነትና ጸጋ ስለተቀደሱ ቅዱሳን ይባላሉ፣ የእግዚአብሔር ግን ቅዱስነቱ የባሕርዩ ስለሆነ፣ ፍጹም ቅዱስ ነው። ቅዱስ ማለትም፡- 1ኛ ልዩ ማለት ነው ከኃጢአት የተለየ ነውና። እንዲሁም ከሁሉ የራቀ የተለየም ነውና። 2ኛ ንጹሕ ማለት ነው፣ እግዚአብሔርን በዚህ ጊዜ በደለ፣ ኃጢአትም ሠራ የሚለው የለምና[49]። ሌሎች ፍጥረቶች ግን ቅዱስ ቢባሉ ከርሱ አብነት ተነሥተው ነው፣ ለእግዚአብሔር ግን ንጽሕና የባሕርዩ ነውና። ይኽም ቅጽል በእርግጥ ሊሆን የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ግን በጸጋው እርሱ ለቀደሳቸው ቅዱሳንም እንዲሁ ይውላል። እንዲህም ከሆነ «ስምህ ይቀደስ» አምላካችን ሆይ አንተ ቅዱስ ነህ» እያልን ማመስገን ለፍጥረት ሁሉ፤ በተለይም ለሰው ልጅ



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ የግዴታ ተግባሩ ነው፡፡ እርሱንም ለመዋሐድ እርሱንም ለመምሰል ደግሞ ቅዱስ መሆን ለሰው ልጅ ሁሉ ግዴታው ነው፡፡

3ኛ ቅዱስ ማለት ክቡር ማለት ይሆናል፣ ክቡር ስንል ደግሞ ከሰው ክብር የተለየ ፍጹም ክብር ያለው ክብርም ገንዘቡ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፣ ምክንያቱም ሰውን ክቡር ስንል ከሰው በተሰጠውም ከእግዚአብሔርም ባገኘው ጸጋ ነው፣ እግዚአብሔር ግን ክብሩ የባሕርዩ ነውና፡፡ ክቡርም ስንል ኀፍረት ውርደት የማይስማማው ክብር የባሕርዩ የሆነ ክብርና ምስጋና ገንዘቡ የሆነ አምላክ ነው ማለት ነው፡፡

4ኛ ቅዱስ ማለት ጽኑዕ ማለት ይሆናል፣ ምክንያቱም ከቶ እግዚአብሔር ደክሞ ሰንፎ አያውቅም፡፡ ሰውን ጽኑዕ ስንል ድካም ይስማማዋል በሕመም በሞት ይጠፋል፣ ይለወጣል፣ ኃይሉ ይደቃል፣ እግዚአብሔር ግን ጽንዓቱ የባሕርዩ ነውና፣ ይኸውም ለዘለዓለም ነውና፤ ስለዚህ በመላእክትና በሰው ልጅ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እየተባለ ለዘለዓለም ሲመሰገን ይኖራል፡፡

## 7ኛ. ስለ መንፈስነቱ (ረቂቅነቱ):-

እግዚአብሔር ረቂቅ የማይመረመር ተመርምሮም የማይደረስበት መንፈስ ነው፡፡ እርሱ የፈጠራቸው ረቂቃን ፍጡራን እንኳን ማንም ሊያያቸው ሊይዛቸው የማይቻሉ ከፍጥረታቱ መካከል ይገኛሉ፣ እርሱ ግን ከዚህ በበለጠ ፍጹም መንፈስ ነው፡፡ ስለዚህም ወንጌላዊ ዮሐንስ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስ ይሰግዱለታል በእውነትም» ሲል እውነተኛ ቃልን አስተላልፏል፡፡[50]

መንፈስ ማለት ረቂቅ ቅርጽ የሌለው ወይም የማይታወቅ መልኩ የማይታይ አጥንትና ሥጋ ጅማትም፣ የሌለው በጠቅላላ የማይያዝ፣ የማይዳሰስ፣ አካል ማለት ነው፣ ስለዚህ፣ ክርስቶስ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል «....እጄንና እግሬን እዩ እኔ ነኝና ዳሱኝ እዩም ለመንፈስ ሥጋ አጥንት የለውምና፣ እኔ ግን እንዳለኝ እዩ"፡፡[51] እርሱ ከፈጠራቸው ከነፍሳት ከነፋሳትም፣ ከመላእክትም የበለጠ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ እግዚአብሔርን



www.ethiopianorthodox.org



አካል ባለው ግዘፍም ባለው ነገር እየመሰሉ የሚናገሩ አሉ፣ ስሕተት ነው፣ እግዚአብሔር ፍጹም መንፈስ ነውና፡፡

እንግዲህ እግዚአብሔር ፍጹም መንፈስ ነው፣ ማለት የማይታይ የማይዳሰስ ረቂቅ ነው፤ እንዲህም ሲሆን ሰውን በአርአያውና በምሳሌው ፈጠረው እንላለን ሰው ግዙፍ ነው ይታያል፣ ይዳሰሳል ምሳሌው እታዲያ የት ላይ ነው፣ ይኸ እንዴት ሊታረቅና ሊገናኝ ይችላል ብለን ስንመረምር መልሱ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስረዱት ሰው ከሌላው ፍጥረት ተለይቶ በእውቀቱ በገዥነቱ የፍጥረቱ ሁሉ ኃላፊ በመሆኑ የእግዚአብሔር ምሳሌ ሊሆን ችሏል፡፡ ይኸንም ቅዱስ ጳውሎስ «አዲሱንም ሰውነት ልበሱ፣ በእውቀት የሚታደስ በፈጣሪው ምሳሌ ያለውን» ሲል አስረድቷል፡፡[52] ከማንኛውም ፍጥረት ተለይቶ ሰው የከበረ፣ አዋቂ የሆነ፣ የስሙ ቀዳሽና የክብሩ ወራሽ የሆነ ነው፡፡ እነዚህም ሁሉ ባሕርያት ሰውን የእግዚአብሔር ምሳሌ ያስደርጉታል ወይም ያሰኙታል፡፡

ሰው ከፍጥረቱ ሁሉ በላይ ነው፣ ሁሉንም ይገዛል ያስተዳድራል፣ ለዚህም የሚያበቃው ከሥጋ ብቻ የተፈጠረ ሳይሆን ከመንፈስ የተፈጠረ በመሆኑ ነው፡፡ ይኸም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተሰጠው የእውቀት የሕይወት፣ መንፈስ ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም ሰው በንጽሕናውና በቅድስናው እግዚአብሔርን እንዲመስል ከሁሉ የነፃ አድርጎ አምላክ ፈጥሮት ነበርና፡፡ ይኸንም ቅዱስ ጳውሎስ በድጋሜ እንዲህ ሲል ያስረዳል «በሕሊናችሁም መንፈስ ትታደሱ ዘንድ አዲሱን ሰው ትለብሱ ዘንድ በእግዚአብሔር ምሳሌ በእውነተኛው ጽድቅና በቅድስና የተፈጠረውን»፡፡[53]

እንግዲህ እግዚአብሔርን መምሰል በቅርጽ በአካል በመልክ ሳይሆን፣ በእውቀት፣ በቅድስና በጽድቅ በነዚህ እንድንመስለውና እነዚህን ገንዘብ አድርገን እንድንኖር ፈጠረን፡፡ መንፈስ ግን እንዴት እንደሚገለጥ እርሱ ራሱ ሳይሆን በልዩ ልዩ ምሳሌ፣ ይታያል፣ ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ በርግብ፣ በእሳት፣ በነፋስ፣ አምሳል ታይቷል፡፡[54]

እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በራእይ በምሳሌ እንጂ ሊታይ ሊዳሰስ፣ ሊደረስበትም የማይቻል ነው:: እግዚአብሔርን ከቶ ያየው እንደሌለ ወንጌላዊው ዮሐንስ «እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም:: በአባቱ ጭን ያለ አንድ ልጁ እርሱ ነገረን እንጂ» ሲል አስረድቷል::[56] ልጁ ኢየሱስ ሰው ስለሆነ መለኮቱ ከሥጋ ጋር ስለተዋሐደ በሥጋዊ አካሉ አይተነዋል፣ ዳሰነዋልም እንጂ እንደ መለኮትነቱ እርሱን ሊያየው ሊዳስሰው የሚችል የለም፣ መንፈስ ነውና:: በጥንት ዘመን የእግዚአብሔር ባለመዋል የሆነ ሙሴ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል፣ ምን እንደሚያክልም ለማወቅ ፈልጎ እግዚአብሔር እንዲገለጥለት እንዲታየውም ለመነ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር አለው «እኔ ቸርነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ:: በፊትህም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ ይቅር የምለውንም ይቅር እላለሁ፣ የምምረውንም እምራለሁ:: አለም ፊቴን ማየት አይቻልህም ሰው አይቶኝ አይድንምና»::[57]

በዚህ አገላለጽ እንደምንረዳው ቸርነቱና ምሕረቱ ሲገለጥ ሲያልፍ ታየ እንጂ እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም:: ስለዚህ ይኸን ያክላል፣ ይኸንንም ይመስላል ብለው ግምት ዓይነት ቅርጽ መልክ ሊሰጡት ከቶ አይቻልም:: መላእክት አምሳክን እየመሰሉ የተገለጡበት የተናገሩበት፣ የሠሩበትም ጊዜ አለ፣ ስለዚህ በአንዳንድ ቦታ በብሉይ ኪዳን የነዚያን መገለጥ የእግዚአብሔር መገለጥ አድርጎ ጽፏል::[58]

እንዲሁም በራእይ በምሳሌ የተገለጠበትን የእግዚአብሔር መገለጥ እያደረገ የጻፈ አለ::[59] በአጠቃላይ ግን የምናስረዳው ሰው ከሆነው ከባሕርይ ልጁ ከኢየሱስ በቀር እግዚአብሔርን ያየው ከቶ የለም:: ለወዳጆቹ እንደነ አብርሃም ላሉ እግዚአብሔር ተገለጠላቸው ይባላል፣ ግን በሰው መልክ፣ በሰው አርአያ እንጂ በእግዚአብሔርነቱ በመለኮታዊ አርአያነቱ አይደለም፤[60] ምክንያቱም እግዚአብሔር በባሕርዩ መንፈስ ነውና፣ ባሕርዩን በባሕርዩ የሰወረ ነው፣ ለማንም ሊገለጥ ሊታይ ከቶ አይቻልምና::


www.ethiopianorthodox.org



## ፰ኛ. ስለ እውነተኛነቱ:-

እግዚአብሔር እውነተኛ ነው፤ እርሱ ራሱ እውነት ነው:: ነቢዩ ዳዊት ለዚህ ሲመሰክር «እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው፣ በሥራውም ሁሉ ቸር ነው» ብሏልና::[61] እግዚአብሔር ወልድም የአባቱን እውነተኛነት ሲገልጥ «ጻድቅ አባት ሆይ ዓለም አያውቅህም፣ እኔ ግን አውቅሃለሁ፣ እሊህም አወቁ እንደላከኝ» ሲል ተናግሯል::[62]

እግዚአብሔር በባሕርዩ ጻድቅ ስለሆነ፣ የሚሠራው ሁሉ ጽድቅ ነው፣ ከቶ ሐሰት የለበትም:: እንዲሁም ሰው ሁሉ ወደ ጽድቅ እንዲመራ ያዛል፣ ስለዚህም የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፣ ከእግዚአብሔርም የተወለደ ኃጢአትን አይሠራም፣ ሐሰት አይናገርም፣ ጽድቅን፣ እውነትን ያዘወትራል እንጂ:: ስለዚህም ክርስቶስ ሲያስተምር ያመኑበት አይሁድን አለ፣ «እናንተ በነገሬ ብትጸኑ በእውነት ደቀመዛሙርቶቼ ናችሁ:: እውነትንም ታውቃላችሁ፣ እውነትም አርነት ያወጣችኋል»::[63] ወንጌላዊው ዮሐንስ ደግሞ በራእዩ እንዲህ ሲል ይመሰክራል «የውሀወችም መልአክ ሲል ሰማሁ፣ አንተ ጻድቅ ነህ፣ አቤቱ የምትኖር፣ የነበርከም፣ የምትቀድስም በዚህ ፈርደሃልና:: የቅዱሳንና የነቢያትን ደም አፍስሰዋልና ደምንም ሰጠኻቸው ይጠጡ ዘንድ ይገባቸዋልና»::[64]

እግዚአብሔር በእውነት ፈራጅ በእውነትም ዋጋ ከፋይ መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር «እንግዲህም የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል:: እግዚአብሔር የሚሰጠኝ በዚያች ቀን ጻድቅ ፈራጅ ለኔም ብቻ አይደለም መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ» ሲል ይናገራል::[65]

## ፱ነኛ. ስለ መሐሪነቱ:-

እግዚአብሔር በባሕርዩ መሐሪና አዛኝ ይቅር ባይም ነው፣ ቁጣው እንደሰው አይደለም፣ በመጀመሪያ ይችላል፣ ይታገሣል፣ ከተመለሱለትም ቂም የለውም ይቅር ይላል:: ይኸንም በሰፊው የተረዳው ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔርን መሐሪነት፣ እንዲህ ሲል በመዝሙሩ ይገልጥልናል «እግዚአብሔር መሐሪና ጸጋ

ሰጭ ነው፣ ቁጣው የዘገየ፣ ምሕረቱም የበዛ ነው»[66] እግዚአብሔር እንደሰው አይደለም ማለት የሰው ፊት ዓይቶ አይቆጣም፣ በነገረ ሰሪም አይመራም፣ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ ነውና:: እንዲሁም ማንም ሰው ቢያጠፋ የሚድንበትን የሚመለስበትን መንገድ ያዘጋጀል፣ ዕድሜ፣ ጊዜ፣ ቦታ ለንስሐ ይሰጣል፣ እንዳልሰማና እንዳላወቀ ሆኖ ይችላል፣ ይታገሣልም::

ይኽን በማውሳት ነቢዩ ሙሴ የተናገረውን እንመልከት «እግዚአብሔር አምላክህ መሐሪ አምላክ ነውና፣ አይተውኽም ፈጽሞ አያጠፋህም የአባቶችን መሐላ አይረሳም እርሱ የማለላቸውን»[67] ይኽን ምሕረቱን ቸርነቱን ይቅር ባይነቱን እያጎሉ የተናገሩ ብዙዎች ናቸው::[68]

እግዚአብሔር ለሁሉም አዛኝ ርኅሩኅ ሲሆን በበለጠ የርሱን ምሕረት ደጅ ለሚጠኑና ስሙን ለሚጠሩ የበለጠ ያዝንላቸዋል፣ ይራራላቸዋል፣ ስለዚህም ይቅር ይላቸዋል:: ራሱ እግዚአብሔር ለሙሴ «የምምረውን እምረዋለሁ፣ ለምራራለትም እራራለታለሁ» ሲል ተናግሯል::[69] ቅድስት ማርያምም ስለእግዚአብሔር መሐሪነት «ወሣህሉኒ ለትውልድ ትውልድ ለእለ ይፈርህዎ» ብላ በጸሎቷ ጊዜ ገልጣ ተናግራለች::[70]

እግዚአብሔር ፍጹም መሐሪ ይቅር ባይም ነው፣ ይኽም በበለጠ ጎልቶ የሚታየው የርሱን ምሕረት ደጅ በሚጠኑ ወገኖች ነው፣ ይኽነንም ለማስረዳት ሊቀ ነቢያት ሙሴ «አንተም አወቅህ እግዚአብሔር አምላክህ እርሱ አምላክ እንደሆነ፣ የታመነ አምላክ ኪዳኑን የሚጠብቅ ምሕረቱን ለሚወዱት ትእዛዙንም ለሚጠብቁ እስከ ሽህ ትውልድ» ሲል አስረድቷል::[71] በበለጠ ነቢዩ ዳዊት ሲገልጥ «ሰማይ ከምድር ከፍ እንዲል እንዲሁ ቸርነቱ በሚፈሩት ላይ በዛች» በማለት ሰፋ አድርጎ ተናግሯል::[72]

ኃጢአቱን ለሚያምን ለሚናዘዝም፣ ለሚመለስም ቆርጦ ለተነሣ የእግዚአብሔር ምሕረቱ የበዛ ነው:: ለይቅርታውም ወሰን የለውም፣ ይኽንንም እንደገና ነቢዩ ዳዊት ሲገልጥ «አቤቱ አንተ ቸር ይቅርም ባይ ነህና፣ ቸርነትህም ወደ አንተ ለሚጠሩት ሁሉ ታላቅ ነውና» ሲል ገልጦ ተናግሯል::[73]





## 10ኛ. ስለ ታማኝነቱ:-

አምላካችን እግዚአብሔር እውነተኛ የታመነ የባሕርይ አምላክ ነው፣ ዘመን አይለውጠውም፣ በሥራውም አይጸጸትም ስለዚህ ቃል ኪዳኑን አያፈርስም፣ በጠቀላላው በተናገረው በሥራው ጸንቶ የሚኖር አምላክ እርሱ ብቻ ነው:: መንገዱም ሁሉ የቀና ነው:: እግዚአብሔር እውነተኛ ነው፣ ሐሰትም የለበትም:: እውነተኛ ጻድቅም እሱ ብቻ ነው[74] «ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር እንደሰው አይደለም፣ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም» ሲል ነቢዩ ሙሴ ተናግሯል::[75] እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ነው የርሱ የሆነውን ሁሉ የሚያውቅ ሁሉንም የሚጠብቅ ለማንም አሳልፎ የማይሰጥ የታመነ የባሕርይ አምላክ ነው:: ይኽነንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አጉልቶ ሲያስረዳ «ሌላ ፈተና አላገኛችሁም፣ እንደሰው ያለ ፈተና እንጂ፣ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ ነው፣ አይተዋችሁም፣ ትፈተኑ ዘንድ በማትችሉት:: ነገር ግን ከፈተናችሁ ጋር መውጫውን ያደርግላችኋል ትታገሱ ዘንድ እንድትችሉ» ሲል ማብራሪያ ሰጥቷል::[76]

እንደገናም ይኸው ሐዋርያ «እርሱ የጠራችሁ የታመነ ነው፣ እርሱም ይኽንን ያደርገዋል» ሲል የእግዚአብሔርን ታማኝነት ገልጦ ተናገረ::[77] ሁሉ ያልፋል ይለወጣል እግዚአብሔር ግን እርሱ ዘለዓለማዊ እንደመሆኑ ኃይሉም አይለወጥ «ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም» ብሎ ራሱ ክርስቶስ ተናግሯል::[78] እግዚአብሔር የታመነ ነው፣ የሚናገረው የሚሠራው በእውነት ነው፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ሐሰት የለም፣ ይኽነንም ነቢዩ ዳዊት ሲመሰክር «አቤቱ ቸርነትህ በሰማይ ነው፣ እውነትህም እስከ ደመና ድረስ ነው» ብሏል::[79]

እንደገና ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታማኝነትና እውነተኛነት፣ በሰፊው ሲገልጥ «... ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቃትም፣ እምነቴንም አላጎድልበትም፣ መሐላዬን አላረክስም፣ ከከንፈሬም የወጣውን አልለውጥም አንድ ጊዜ በቅድስናዬ የማልሁ፣ ለዳዊትም አልዋሽበትም» ሲል ገልጦ



www.ethiopianorthodox.org

ተናግሯል::[80] በቃል ኪዳኑ ለጸኑ ተስፋውን ደጅ ለጠኑ፣ ሕጉን ለሚጠብቁ ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋቸውን ለመክፈል የታመነ ነው፣ ቃሉን አይለውጥም ምሕረቱን አያጎድልም፣ መሐላውንም አያፈርስም:: አምላክ ከክፉ ነገር በመጠበቁ፤ በመመገቡ፣ በማስተዳደሩ፣ ሁሉ እውነተኛነቱን ታማኝነቱን ይገልጣል፣ ይኸንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጥ «እግዚአብሔር ግን እውነተኛ ነው፣ የሚያጸናችሁ ከክፉም የሚጠብቃችሁ» ሲል ገልጦ ጽፏል::[81] እንደገናም ይኸው ሐዋርያ ሲገልጥልን «እርሱ እስከፍጻሜ የሚያጸናችሁ ያለ ነውርም እንድትሆኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን እግዚአብሔር እውነተኛ ነው፣ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልጁ አንድነት የጠራችሁ»::[82]

እንግዲህ አምላክ በቃሉ የጸና የታመነ ነው፣ በኪዳኑ ብንጸና እርሱም የጸና ይሆናል፣ ብንክደው ግን ለእኛ ወዮልን እርሱ ግን ለዘለዓለሙ የታመነ የባሕርይ አምላክ ነውና::

## 11ኛ. ስለ ትክክል ፍርዱ:-

እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ፍጹም አምላክ ነው፣ እንዲሁም ጻድቅ የባሕርይ አምላክ ነው:: እንዲህም ስለሆነ፣ በማንም በማን ላይ በሐሰት በግብዝነት አይፈርድም፣ ለሁሉ በትክክል ይፈርዳል እንጂ፣ ስለዚህም ሕግ አፍራሹን ሳይፈራ ሳያፍር ይፈርድበታል፣ ሕግ ፈጻሚውንም የሰው ፊት ዐይቶ ሳያዳላ ይፈርድለታል:: ደኃውን አይንቅም፣ ባለጸጋውንም አይፈራም፣ ለሁሉም በእውነተኛ ፍርድ እንደየሥራው ይፈርድለታል፣ ወይም ይፈርድበታል፣ ለዚህም ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል መስክሯል «በእውነት አስተዋልኩ እግዚአብሔር በሰው ፊት እንዳያዳላ»[83]:: ክርስቶስም ራሱ ሲመሰክር የባሕርይ አባቱን «ጻድቅ አባት ሆይ» ሲል ጻድቅ በማለት እውነተኛነቱን መስክሯል::[84]

ቅዱስ ጳውሎስም «እንግዲህም የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል:: እግዚአብሔር የሚሰጠኝ በዚያች ቀን ያ ጻድቅ ፈራጅ» ሲል እግዚአብሔር እውነተኛ ትክክለኛም ፈራጅ መሆኑን ገልጦ ተናግሯል::[85] በዚህ ዓለም ላይ በመፍራት በማፈር የሰውን ፊት ዐይቶ መማለጃ በልቶ በማድላት በሐሰት





የሚፈርደው ብዙ ነው፣ እውነተኛ ደኛ ሊገኝ አልተቻለም፣ ወደፊትም ከሰው ወገን ሊገኝ እንደማይቻል ያለፉት ሰዎች ሥራ በሰፊው ያስረዳል፣ እግዚአብሔር ግን ቀድሞም ሆነ አሁን የማይለወጥ፣ ጉቦ የማይቀበል፣ መማለጃ የማይበላ፣ የሰው ፊት ዐይቶ የማያዳላ እውነተኛ ፈራጅ ዳኛ ነው::

## 12ኛ. ስለ ፍጹም ፍቅሩ:-

ልዑል እግዚአብሔር በባሕርዩ ፍጹም ፍቅር ነው፣ ሁሉን በትክክል የሚወድ አድልዎ የሌለበት እርሱ ብቻ ነው:: ፍጹም ፍቅሩም በፍጥረቱ ሁሉ ሞልቶ ሰፍቶ ይታያል፤ በተለየ ግን በሰው ነገድ ላይ ጎልቶ ይገኛል፣ ስለዚህም የእግዚአብሔር ስም መፍቀሬ ሰብእ ይባላል:: በፍጹም ፍቅር ሰውን ይወዳል ለዚህም ማስረጃ በመጀመሪያ በመልኩና በምሳሌው ሰውን ፈጠረው:: ከፍጥረቱም ሁሉ ለይቶ በነባቢት ነፍስ አከበረው፣ ስለዚህም መልካም ደስታን በጎ ዕድልን፣ ቅዱስ ቡራኬን ለሰው ልጅ ሁሉ፣ በተለይም ለሚፈሩትና ለሚያመልኩት ይሰጣል::[86] በኋላም ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ይህን ዓለም በተለይም የሰውን ልጅ ማዳኑ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣና የፍቅርም መግለጫ እንደሆነ፣ የታወቀ ነውና፣ ይኸንም ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረው እንዲህ እያሉ መስክረዋል «እግዚአብሔር እንዲሁ ዓለሙን ወዶታልና አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ በርሱ ያመነ ሁሉ እንዳይጠፋ፣ የዘለዓለም ሕይወት ትሆንለት ዘንድ እንጂ»::[87]

አባ ሕርያቆስም «ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት» ፍጹም ፍቅር ኃያል ወልድን ስቦ ወደ ሞት አደረሰው ሲል ጽፏል::[88] አምላክ እርሱ እኛን መውደድ ብቻ ሳይሆን እኛም እርስ በራሳችን እንድንዋደድ ያዝናል፣ «የማይዋደድም እግዚአብሔርን አላወቀውም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና"::[89] እንዲሁም ይኸው ወንጌላዊ በመቀጠል «....እግዚአብሔር ወደኛ ያለችውን ፍቅር እኛ አወቅን፣ አመንም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና:: በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፣ እግዚአብሔርም በእርሱ»::[90] እንዲህ አድርጎ አምላክ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ከበደለኛው ከሰው ጋር



www.ethiopianorthodox.org

አንድነቱን እንደሚያደርግ ገለጠልን:: ከ፮ቱ ቃላተ ወንጌል ውስጥ ፩ዱ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚል ነው::[91] እግዚአብሔር በባሕርዩ ዘለዓለማዊ እንደመሆኑ ፍቅሩም ጊዜያዊና ቅጽበታዊ ተለዋዋጭም አይደለም፣ ዘለዓለማዊ ነው እንጂ::

እግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር ስለሆነ፣ አድልዎም ስለሌለበት ዓለምን በትክክል ይወዳል፣ ስለዚህ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ፩ያ ልጁን ለዓለም ቤዛ ይሆን ዘንድ ሰጠው::[92] ይኸንንም ቅዱስ ጳውሎስ አጉልቶ ሲናገር .«በዚህም በእግዚአብሔር በእኛ ፍቅሩን አስታወቀው ገና ኃጢአተኞች ሳንሆን ክርስቶስ ስለኛ ሞተልን» ይላል::[93]

ምንም አንዲት እናት በማሕጸን ተሸክማው የነበረውን ሕፃን ከመመገብ ቸል ብትል እግዚአብሔር አምላክ የፈጠረውን ፍጥረት ከመጠበቅ ከመመገብ ቸል አይልም:: እግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር በመሆኑ የመጨረሻውን የፍቅር ደረጃ እንደርሱ የያዘ የለም፣ ለአስረጅም ያህል ሥጋዬን ብሉ፣ ደሜንም ጠጡ ብሎ የሰጠውን እንመልከት፣ ከርሱ በቀር ሌላ ይኸን ያደረገ የለምና:: የሰውን ልጅ ሁሉ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ያዳነው ብቻ ሳይበቃው ከዚያም ወዲህ የሚሠራውን ኃጢአት ሁሉ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ይቅር ይላል:: እግዚአብሔር ለሁሉ ቸር ነው፣ ስለዚህ ሁሉን ይጠብቃል፣ ያለርሱ ፈቃድ እርሱም ሳያውቀው ከማንኛውም ፍጥረት አንድስ እንኳን የሚጠፋ የለም፣ ከጠጉር አንዱ እንኳን ሊወድቅ እንደማይችል በእውነተኛ ትምህርቱ ገልጦታል::[94] ልዑል እግዚአብሔር ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ኃጢአተኛውን በቶሎ አይቀስፍም፣ ንስሐ የሚገባበትን ወራት አብዝቶ ዘመን አስፍቶ ይሰጣል እንጂ::[95]

ልዑል እግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር ስለሆነ ማንም እርሱን አምኖ የተጎዳ የለም፣ እንዲያውም ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያሻውን ሳይለምነው አስቀድሞ ይሰጠዋል::





# ክ ፍ ል ፪

# ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት በጠቅላላው፣

## ም ዕ ራ ፍ ፩

## ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ እግዚአብሔር ስለመጻፋቸው::

### 1. ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ እግዚአብሔር መጻፋቸው :-

ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፉ፣ አንድም እስትንፋስ እግዚአብሔር የሆኑ ናቸው:: ቅዱሳት መጻሕፍትን በሌላ ቃል መጻፍት አምላካውያት ይላቸዋል::[1] አምላክ ያጻፋቸው፣ በአምላክ ፈቃድ የተጻፉ፣ የአምላክን ነገር የሚናገሩ ለማለት ነው:: ይህንም ሁሉ አስረጂ ስላገኘን ቅዱሳት መጻሕፍት ወይም ቅዱስ መጽሐፍ እያልን ከሌሎች መጻሕፍት ለይተን ለዚህ ብቻ ክብርን ሰጥተን እንቀበላለን:: በዚህም ስም ማንኛውም መጽሐፍ ሊጠራበት አይቻልም ደግሞም አይገባም:: ቅዱስ የሚለው ቅጥል እስትንፋስ እግዚአብሔር ለሆነው ለቅዱስ መጽሐፍ ብቻ የተሰጠ ነውና:: ቅዱሳት መጻሕፍት እስተንፋስ እግዚአብሔር ለመሆናቸው አንድም በመንፈስ እግዚአብሔር ለመጻፋቸው ቀጥተኛ ምስክር የሚሆነው በዚሁ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላቶች ናቸው፣ ከዚያም ውስጥ እንዲህ ሲል ይጀምራል፣ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማጥናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ያስረዳናል::[2] ይህ መጽሐፍ ሁሉ የሚለው ቃል በመላ ቅዱስ መጽሐፍ እስትንፋስ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚያስገነዝብ የታመነም ምስክር ነው:: በዚህም አስተያየት ቅዱሳን አባቶች የቤተ ክርስቲያንም ሊቃውንት ሁሉ ይስማሙበታል::



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ እግዚአብሔር ተጻፉ ስንል የጸሐፊዎች መብት ከየት እስከ የት እንደነበር ማወቅ ያስፈልጋል፣ ምናልባት ሰዎች ሳያውቁት ስሜትም ሳይኖራቸው የእግዚአብሔር መንፈስ በጆሯቸው እያሾከሾከ፣ አንድም አፋቸውን ከፍቶ ፊታቸውን ጸፍቶ አናገራቸው አጻፋቸውም ወይም እነርሱ የመንፈስ ማኅደር እንደመሆናቸው ለዚህ በቅተው ራሳቸው ተናገሩት የሚል ነው:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምትሰጠው አስተያየት ግን ቅዱስ ጴጥሮስ የተናገረውን እውነተኛ የምስክር ቃልን በመደገፍ ነው፣ ማለት «ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፣ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩ እንጂ» የሚል ነው::[3] ይህም ማለት ነቢያት ሀብተ ትንቢትን ከራሳቸው አንቅተው ያወጡት አንድም ያገኙት አይደለም፣ ይህም ከሆነ የተናገሩት ሁሉ በእግዚአብሔር ገላጭነት እንደሆነ፣ ግልጥ ነው፣ ማለት በእግዚአብሔር መሪነት እየተመሩ እግዚአብሔር እየገለጠላቸው ተናግረዋል እንጂ:: እንግዲያውስ እያንዳንዱ ነቢይ ወይም ሐዋርያ በጻፈው ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር እንደመሆኑ እንዲህ ብለህ ጻፍ እንዲህ አድርገህ ሥራ የሚል የመንፈስ አጋዥነት እየተሰጣቸው ወይም በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት እየተነሳሱ እንደጻፉ ልናምን ይገባናል:: እያንዳንዱ ነቢይ በእግዚአብሔር ገላጭነት ከእግዚአብሔር ታዞ የጻፈው ለመሆኑ የሚያስረዳው «ወመጽአ ቃለ እግዚአብሔር ላዕለ...» እያለ ይጽፉልና::

ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፈ ስለሆነ፣ ፍጹም እውነት አለው፣ ሊለወጥም የማይቻል ቃል ነው:: ከዚህም በላይ በግልጥ እግዚአብሔር እየታየ አንድም ድምፁን እያሰማ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ እንዲህም ብለህ ተናገር እያለ ድምጹን ያሰማበት፤ በልቡናውም የቀረጸበት ጊዜ አለ::[4]

ለምሳሌ ልዑል እግዚአብሔር ለሙሴ ፲ ቀን በደብረ ሲና በሕሊናው ቀርጸለታል፣ በ5ቱ ብሔረ ኦሪት ውስጥ የሚገኘው ፭፻፸ ወነበቦን ያጠይቃል:: ለዚህም አስረጂ የሚሆን ጥቂት





ምሳሌዎችን እንጠቅሳለን፣ «እግዚአብሔርም ሙሴን በነዚህ ቃሎች መጠን ከእናንተ ከእሥራኤል ጋር ቃል ኪዳን አደርጋለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው»::[5] እንዲሁም በሌላ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፣ «አሁንም ይህችን መዝሙር ለእናንተ ጻፉ ለእሥራኤልም ልጆች አስተምሯቸው፣ ይህችም መዝሙር በእሥራኤል ላይ ምስክር ትሆንልኝ ዘንድ በአፋቸው» ይላል::[6]

ከመጻሕፍት ነቢያትም ውስጥ እንዲሁ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህን የዕውነት ቃል የሚደግፍና ምስክር እንደሆነ ያጸድቃል፣ እርሱም እንዲህ ይላል፣ «እግዚአብሔርም ታላቅ ሰሌዳ ወስደህ ምርኮ ፈጠነ ብዝብዛም ቸኰለ ብለህ በሰው ፊደል ጻፍበት»::[7] ይህም አስረጂ ነቢያት በመላ በቃል ከእግዚአብሔር ጋር እንደተነጋገሩ በእርሱ ተመርተው እርሱ ገልጾላቸው እንደጻፉት ያመለክታል:: በዚህም መሠረት በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ተጻፈ:: ቅዱስ መጽሐፍም መሆኑ ያመኑ ሕዝቦች ወዲያውኑ ለቅዱስ መጽሐፍ የተለየ ክብር ሰጥተው ልዩ ጥንቃቄም አድርገው እንዲይዙትና ሌሎችም እንዲከተሉት እንዳስተማሩ እናገኛለን::[8] ዳዊት ደግሞ በመዓልትም በሌሊትም ሕጉን የሚጠብቁት ቅዱሳን መጻሕፍትንም የሚያነቡት ብፁዓን ናቸው ሲል አመስግኗቸዋል::[9] ዳዊት ታላቅ ንጉሥ ሲሆን የተጻፈውን የሚያነቡ የተባረኩ እንደሆኑ ሰፋ አድርጎ ገልጿል፣ የዳዊትም መዝሙር የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በመንፈስ እግዚአብሔርም ለመጻፉ ክርስቶስ ሲመሰክርለት «እኔ አማልክት ናችሁ አልኩ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን፣ መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና .....» ሲል መስክሯል::[10] ይህ ሁሉ ስለ መጻሕፍተ ሕግጋትና መጽሐፍተ ነቢያት አገላለጥ ሲሆን፣ ስለ መጻሕፍተ ሐዲሳት ደግሞ ከዚህ ያላነሰ፣ ይኸንም የመሰለ ብዙ አስረጂ አለን::

ቅዱሳን ሐዋርያት የሚናገሩት የሚሠሩት በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው እንደሆነ፣ ለማጠየቅ «የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁም፣ የአባቴ መንፈስ እንድትናገሩ ያደርጋችኋል እንጂ» ሲል ራሱ ክርስቶስ መስክሯል::[11] በእርግጥም ሐዋርያት በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኙ ጽፈዋል ተናግረዋል ሠርተዋል:: ስለ ቅዱስ መንፈስም እነርሱ መስክረው



www.ethiopianorthodox.org

በቁጥርም በተራም ትንሽ ለየት ያለ አስተያየት ይገኝበታል፣ ሆኖም ደንበኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን አሁን እርሱ ስለሆነ በእርሱም መሠረት ዛሬ እንደገና ታትሞ ለሕዝብ ተዳርሶ ይገኛል፣ እንግዲህ ከዚህ ውጭ ሌላ መጽሐፍ ስለሌለ አለ ብሎ መናገሩም መጻፉም ትርፍ ነው ማለት ነው።

የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ቁጥር:-

፩ኛ ቀኖና መጻሕፍት የሚባሉት፣

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ
7. " መሳፍንት
8. " ሩት
9. " ሳሙኤል ቀዳማዊ
10. " " ካልዕ
11. " ነገሥት ቀዳማዊ
12. " " ካልዕ
13. " ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. " ዜና መዋዕል ካልዕ
15. " ዕዝራ
16. " ነህምያ
17. " አስቴር





18. መጽሐፈ ኢዮብ
19. መዝሙረ ዳዊት
20. መጽሐፈ ምሳሌ
21. " ተግሣጽ
22. " መክብብ
23. መኃልየ መሐልይ ዘሰሎሞን
24. ትንቢተ ኢሳይያስ
25. " ኤርምያስ
26. ሰቆቃወ ኤርምያስ
27. ትንቢተ ሕዝቅኤል
28. " ዳንኤል
29. " ሆሴዕ
30. " አሞጽ
31. " ሚክያስ
32. " ኢዩኤል
33. " አብድዩ
34. " ዮናስ
35. " ናሆም
36. " ዕንባቆም
37. " ሶፎንያስ
38. " ሐጌ
39. " ዘካርያስ
40. መጽሐፈ ሚልክያስ



www.ethiopianorthodox.org

$Ex_2$ Given

$W = 20M$

$S_1 = 1$ in $1$ for Cutting

$S_2 = 1$ in $2$ for filling

$n = 1$ in $5$

$h = 0.4M$

$b_1 = \frac{b}{2} + n.h$

$= \frac{20}{2} + 5 \times 0.4$

$= 12$

$h_1 = h + \frac{W_1}{n_1}$

$= 0.4 + \frac{20}{5}$

$= 4.4$

$A_F = \frac{1}{2} b_1 . h_1$

$= \frac{1}{2} \times 12 \times 4.4$

$= 26.4 \; M^2$

$A_C = \frac{1}{2}\left[\frac{(\frac{b}{2} - n.h)^2}{n-s}\right]$

$= \frac{1}{2}\left[\frac{(\frac{20}{2} - 5 \times 0.4)^2}{5-1}\right]$

$= \frac{1}{2}\left(\frac{10-2}{4}\right)^2$

$= 2 \; M^2$

www.ethiopianorthodox.org

በ፪ኛ ደረጃ የብሉይ ኪዳን ቀኖና የሚባሉት፣

1. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል
2. " " ካልዕ
3. " ጦቢት
4. " ዮዲት
5. " አስቴር
6. " መቃብያን ቀዳማዊ
7. " " ካልዕ
8. " " ሣልስ
9. " " ሲራክ
10. ጸሎተ ምናሴ
11. ተረፈ ኤርምያስ
12. ሶስና
13. መጽሐፈ ባሮክ
14. " ጥበብ
15. መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ
16. ተረፈ ዳንኤል
17. መጽሐፈ ኩፋሌ
18. " ሄኖክ

በዚህ መልክ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፶፬ ይሆናሉ፣ ከነዚህ የሚወጣ ሌላም የሚገባበት የሌለ ቀኖና ቅዱስ መጽሐፍ ተብለው የሚጠሩ። ከነዚህም ሌላ ፳፯ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አሉ፣ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:-





የሐዲስ ኪዳን ቀኖና መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ "
4. የዮሐንስ "
5. የሐዋርያት ሥራ
6. የጳውሎስ መልእክት ፲፬ቱ
   - ሀ. ወደሮሜ
   - ለ. ወደ ቆሮንቶስ ፩ኛ
   - ሐ. " " ፪ኛ
   - መ. ወደ ገላትያ
   - ሠ. ወደ ኤፌሶን
   - ረ. ወደ ፊልጵስዩስ
   - ሰ. ቆላስይስ
   - ሸ. ወደ ተሰሎንቄ ፩ኛ
   - ቀ. " " ፪ኛ
   - በ. ወደ ጢሞቴዎስ ፩ኛ
   - ተ. " " ፪ኛ
   - ቸ. ወደ ቲቶ
   - ኀ. ፊልሞና
   - ነ. ወደ ዕብራዊያን

20. የጴጥሮስ መልእክት ፩ኛ
21. " " ፪ኛ



www.ethiopianorthodox.org

22. የዮሐንስ መልእክት ፩ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት ፪ኛ
24. " " ፫ኛ
25. የያዕቆብ መልእክት
26. የይሁዳ መልዕክት
27. የዮሐንስ ራእይ

እነዚህ ፳፯ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከ፵፮ቱ መጻሕፍተ ብሉያት ጋር ሲደመሩ ፹፩ (ሰማንያ አምስት) ይሆናሉ:: ከነዚህ መጻሕፍት የሚያንስ የሚበልጥ፣ የሚቀነስ የሚጨመር ሳይኖር በቀኖናነታቸው ታውቀው ቢነገሩ የተሻለ ነው፣ ግዴታም ነው፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያናችን በአስተማረችው ቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግበው የሚገኙ እነዚሁ መጻሕፍት ብቻ ናቸውና::

3. <u>የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናነት</u>፣

ቅዱስ መጽሐፍ የእምነታችን ምንጭ የሕይወታችን መደገፊያ የሥራችን መመሪያ ሆኖ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትልቅ መጽሐፍ ነው:: ይኸም መጽሐፍ ከዘመን ወደ ዘመን ስሙ ሳይለወጥ፣ የመጻሕፍቱም ቅደም ተከተላቸው ሳይፋለስ፣ ቁጥራቸው ሳይቀነስ ወይም ሌላ ሳይጨመርበት በንጽሕና በጥራትም ቤተ ክርስቲያን ስትጠብቀው የቆየች ነው:: የቤተ ክርስቲያንም ተቀዳሚ ሥራዋ ቅዱስ መጽሐፍን በአለበት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የእርሱ ተርጓሚም፣ አስተማሪም ሁና መገኘት ነው::

ይኸንም የሃይማኖት መነሻ የሚሆነውን ቅዱስ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን በሕጋዊነት ጠብቃ ለምስክርነት የያዘቻቸው በትውፊታዊ አነጋገር ፹፩ መጻሕፍት እንዳሉን ነው፣ ግን ይኸን ቁጥር የሚናገረው የሕግ መጽሐፍ በዝርዝር በገለጠው ጊዜ ቁጥሩ እንዳልሞላ ተገንዝበናል:: እንዲሁም የተሻለ ቁጥር ይዞ የመጣው በኢትዮጵያ ሊቃውንት ተዘጋጅቶ ሉንዶን በአፊሴት ቀ.ኃ.ሥ. ያሳተሙት መጽሐፍ ስለሆነ፣ እርሱን





የመጨረሻ አስረጅ አድርገን አቅርበነዋል:: እንደርሱም አቆጣጠር ፵፮ ብሉይ ኪዳን እንዲሁም ፳፯ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በድምሩ ፸፫ መጻሕፍት ናቸው::

እነዚህ መጻሕፍት በሊቃውንት ዓለም የሚነበቡ፣ የሚተረጎሙ ሲሆኑ በቤተ ክርስቲያንም የቀኖና መጻሕፍት የሚሆኑ፣ ወይም የሚባሉ እነዚህ ናቸው:: በአፊሴት የታተሙ መጽሐፍ በብሉይ ኪዳን ብቻ ሦስት ክፍል ሲኖረው በመጨረሻው ክፍል ከሚገኙት መጻሕፍት ውስጥ ተራቸው ተፋልሶ ቦታቸውንም ለቀው ይገኛሉ::

ምናልባት በሌሎች ቤተ ክርስቲያን አፓክሪፋ የሚባሉትን ሰብስበው በአንድ ጥራዝ ለይተው ቦታቸውን ሳይጠብቁ በዚህ እንዲገኙ ያደረጉት ዜፍቴሮካኖን (ሁለተኛ ቀኖና) ይሆናል በማለት እንደሆነ ይገመታል:: የሆነው ሆኖ ቀኖና መጽሐፍ ቅዱስ ማለት እውነተኛ ሕጋዊ ለማለት ነው፣ ስለዚህም ስሙ መጠበቅ፣ ቁጥሩም ልከኛ መሆን፣ ተራውም ሳይዘባረቅ መደበኛ ቦታውን ይዞ መገኘት አለበት:: ቀኖና የሚያሰኘውም ዘይቤ ልከኛነቱ፣ ዕርግጠኛነቱ ነው::

የሆነው ሆኖ ፹፩ የሚለውን ቁጥር ሳይጠበቅ ፸፫ቱ መጻሕፍት የኢትዮጵያ ቀኖናዊያን መጻሕፍቶች ተብለው ቢመዘገቡና ቀኖናነታቸው ቢረጋገጥ መልካም ነው:: ሁሉም በየበኩሉ የሚያወጣውና የሚያገባው መጽሐፍ ሳይኖር በሊቃውንት ጸድቆ በማኅተም ታትሞ የቀረበው ቀኖና ቅዱስ መጽሐፉችን ለእምነታችን ለሥነ ሥርዓታችን ምንጭና መነሻ ነው::

4. <u>ቅዱስ መጽሐፍ የሃይማኖት ምንጭ መሆኑ</u> ፣

ለክርስቲያናዊ እምነታችን መነሻውና መድረሻው ቅዱስ መጽሐፍ ነው:: ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈስ እግዚአብሔር እንደመጻፉ እምነታችንና ትምህርታችን በእርሱ ላይ የተመሠረተ ነው::

የእግዚአብሔርን ማንነት፣ የፈቃዱን ምንነት፣ የባሕርዩንም ፍጹምነት የምንረዳው በዚህ ቅዱስ መጽሐፍ አማካይነት ነው::



www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔርን ፈጣሪ ፍጥረታትነቱን፣ አምጻዔ ዓላማትነቱን፣ ታላቅነቱን፣ ከእርሱ በላይ ማንም የሌለና የሁሉም አስገኝ እርሱ ብቻ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፣ እኛም እንዲሁ እናምናለን፤ በዚህም መሠረት በፍጹም እምነት እናመልከ ዋለንና::

ፈጣሪ ከሰው የሚፈልገው ምን እንደሆነ ማንም ሊያውቀው አይችልም፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ የምናውቀው፣ እኛ እንደ ቅዱስ ፈቃዱ ለመሥራትና ለመኖር የምንችለው ቅዱስ መጽሐፍ በሰጠን አስረጅነት ብቻ ነው:: በዚህም መልክ በቅዱስ መጽሐፍ የተመሠረተው እምነት እርሱ ብቻ እውነት ነው:: እንዲህም ያለው እምነት ሰው ሠራሽና በመሰልም የሚሔድ አይሆንም፣ ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ የሃይማኖት ምንጭ ነው፣ እንዲሁም ቅዱስ መጽሐፍ የሃይማኖት ቀኖና ይባላል:: በእውነትም የሃይማኖት ቀኖና እርሱ ብቻ ነው:: ቅዱስ መጽሐፍ የሃይማኖት ቀኖና ለመሆኑ በሚከተሉት ቀዋሚ ምስክሮች ልንረዳ እንችላለን::

1. ቅዱስ መጽሐፍ ሁል ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ሕልውና ይናገራል፣ ለእርሱም ብቻ እንድንታዘዝና በእርሱም እንድናምን ይነገረናል::[22]

2. ክርስቶስም ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትም የተጻፈውን ሕግ እንድናከብርና እንድንቀበል ከእርሱም ሌላ የሃይማኖት ቀኖና እንደሌለ ነግረውናል::[23]

3. ፈሪሳውያን ቅዱስ መጽሐፍን እንደሐሳባቸው በመተርጎ ማቸው ክርስቶስ እነርሱን ሲዘልፍ ለሃይማኖታዊ መመሪያቸውም እርሱ መሆኑን በመመስከር የተናገረበትን እናገኛለን[24]::

እግዚአብሔር ቅዱስ መጽሐፍን እንዲሁ በከንቱ በመንፈሱ አላጻፈውም፣ ስለእርሱነቱ እንድናውቅ በርሱም እንድናምን እርሱን ብቻ እንድናመልክ የእምነቱን ትምህርት፣ የአምልኮውን ሥርዓት ሁሉንም አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በዚሁ ላይ ገልጦ ጽፎ ሰጥቶናል:: ቅዱስ መጽሐፍ በመጀመሪያ ስለ እግዚአብሔር





ሕልውና ይሰብካል፣ ያስተምረናል፣ መርቶም ወደርሱ ያደርሳል፣ ወዲያው ለርሱ የሚሆነውን የሚገባውን የሰው ልጅ እንዲያደርግ በሚገባም እንዲፈጽም ያዛል:: ምንም ሙሉ በሙሉ ለማስረዳት ቅዱስ መጽሐፍ ለሰው ሁሉ ግልጥ ባይሆንና ኀሡውርም ነገር ቢኖርበት ለእምነታችን መነሻና መድረሻ ፍጹም የሃይማኖት ቀኖና እርሱ ብቻ ነው፣ ሌላ የለምና::[25]

እንግዲህ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ሐሳቦች ያልተገለጡም ምስጢሮች ያሉ መስሎ ቢታይ፣ ለሃይማኖትም መስተቃርን የሆኑ ቃላት ያሉ መስሎ ቢታይም ለሥጋውያን በመንፈስ እግዚአብሔር ሳልታነጹ እየመሰላቸው እንጂ የእግዚአብሔር ቃልና ሥራ ፍጹም ነው፣ ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ የርሱ ቃል ስለሆነ ሙሉ ነው፣ ፍጹምም ነው፣ ሁሉን ለማስረዳት ሁሉንም ለመምራት በቂ የሃይማኖት ቀኖና ነው::

የቅዱስ መጽሐፍ ሐሳብ ትርጉሙም ለሰው አስቸጋሪ መሆኑ እንኳን ለሚያነበው ለጻፈው ሰው ሳይቀር ምሥጢር እንደሆነበት ዳንኤል እንዲህ ሲል ያስረዳናል:: «አዳመጥኩኝ ነገር ግን አልገባኝም፣ ጌታ ሆይ ከዚያ በኋላስ ምን ይሆናል ብየ ጠየቅሁኝ፣ ዳንኤል ሂድ እነዚህ ቃላት እስከ መጨረሻው ጊዜ የታተሙ ምሥጢራት ሆነው ይቆያሉ አለኝ»::[26]

እንዲሁም ነቢዩ ዘካርያስ በእግዚአብሔር የተገለጡት ምሥጢሮች ሁሉ ሥውር መሆናቸውን እንዲህ ሲል ይገልጣል፤ «ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ መልሼ ጌታዬ ሆይ እነዚህ ምንድን ናቸው አልኩት፣ ከኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ መልሶ. እነዚህ ምን እንደሆኑ አታውቅምን? እኔም ጌታዬ ሆይ አላውቅም አልኩት»::[27] እንዲሁም ቅዱስ መጽሐፍ ከጊዜያዊ ሕይወታችን ጋር በተለይም ከዘመኑ ሳይንስ ጋር የተለያየ መስሎ ቢታይም ከሁሉ በፊት ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ሥጋዊ ዓለማችን መመሪያና አስረጅነት የተጻፈ አለመሆኑን መገንዘብ አለብን፣ ስለዚህ ከሥጋዊ ዓለም ጋር በማነፃፀር የተመለከትነው እንደሆን የምንፈልገውን ነጥብ ልናገኝበት አንችልም፣ ይኸም ማለት ቅዱስ መጽሐፍ ጉድለት ኑሮበት የሳይንሱ ውጤት ግን ፍጹም አስረጅነት ያለው ሆኖ መገኘቱ



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም፣ መገንዘብ ያለብን ቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈው ስለመንፈሳዊ ዓለማችን መሆኑንና በመንፈሳዊውም ዓላማ ተመርኩዘን መንፈሳዊውን ሕይወት መንፈሳዊውንም ዓለም ብቻ እንድናውቅበት በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፈ መሆኑን መረዳት አለብን።

## ም ዕ ራ ፍ ፪

## ቅዱስ ትውፊት፣

ትውፊት ማለት ተወፈየ ካለው ከግእዙ የወጣ ቃል ነው፣ በዚህም መሠረት ትውፊት ማለት አባት ለልጅ፣ መምህር ደግሞ ለደቀመዝሙር፣ ሌላም እንዲሁ ለተከታዩ የሚያስተላልፈው ቅርስ፤ የሚያወርሰውም ውርስ ነው። እንግዲህ ትውፊት ስንል ከአበው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እስከ እኛም የደረሰው፣ እኛም በክብር ተቀብለን እንድንይዘውና እንድንጠብቀው፣ ለተተኪውም ትውልድ በተገቢው መንገድ ልናስተላልፈው የሚገባን ውርስ ነው።

ይኸን ትውፊት የመሰለ ትርጉም ያለው ቃል በጽርእ ፓራዶሲስ፣ በላቲን ደግሞ ትሬደሺን የሚባል አለ፣ ቀጥተኛ ሐሳቡና ትርጉሙ ከኛ ትውፊት ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው፣ እንዲሁ ከአበው ወደ ውሉድ የሚተላለፍ ውርስ የሚጠበቅም አደራ ማለት ነውና። ትውፊት ባልን ጊዜ በጽሑፍ የዋለውን ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በቃል የተላለፈውንና አሁንም የሚተላለፈውን ሁሉ የሚይዝ ነው። ከተጻፈው ትውፊት ይልቅ በቃል የሚተላለፈው ወይም ያልተጻፈው የበለጠ ተቀባይነት አለው፣ ምክንያቱም ከክርስቶስ ጀምሮ ሐዋርያትም ይሁኑ ወይም የነርሱ ተከታዮች ከጽሑፍ ይልቅ ትምህርቱን ሁሉ ያስተላለፉት በቃል ነውና። ይኸም የቃል ውርስ ለክርስቲያናዊ እምነትና ትምህርት ሁሉ መነሻና መድረሻ ምንጭም ሆኗልና። ጌታችን ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የእውነት መንፈስን እንደሚልክላቸው እርሱም በመጣ ጊዜ ወደ እውነት እንደሚመራቸው በቃል የነገራቸውንና ያስተማራቸውን ሁሉ እንደሚያስረዳቸው በግልጥ ነግሯቸው



www.ethiopianorthodox.org



ነበር።[1] ያ ቅዱስ መንፈስ በመጣ ጊዜ በቃል የተላለፈውን ሁሉ አሳሰባቸው ቅዱሳን ሐዋርያትም፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በቃል አስተማሩ፤ እነርሱም የቃሉን ትውፊት እንዲጠብቁ አስጠነቀቁ። ከዚህም ሁሉ የተነሣ ከተጻፈው ትውፊት ይልቅ ያልተጻፈው ወይም የቃሉ ትውፊት የበለጠ አስተማማኝነት ነበረው፣ ስለዚህም ወንጌላዊው ሉቃስ እንዲህ ሲል በሰፊው ገልጦልናል። «በአይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑ እንዳስተላለፉልን .....»።[2] ይኸ ወንጌላዊና ሐዋርያ በሰጠው ምስክርነት ሁሉም የተላለፈው በቃል እንደሆነ እየዋለ እያደረ ግን በጽሑፍ እንደዋለና የቃሉም የጽሑፉም ትውፊት ለቤተ ክርስቲያን በጣም ጠቃሚ እንደሆነ የሚገልጥ ምስክርነቱን ሰጥቶናል።

የመጀመሪያው ክርስቲያናዊ እምነትና ትምህርት የተመሠረተው ቅዱስ መጽሐፍም የተተረጎመው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የተከፈተችው በዚሁ ባልተጻፈው ትውፊት ነው። ቅዱሳን ሐዋርያት በቃል በተሰጠው ትውፊት መጽናት፣ ያነኑም እያንዳንዳቸው መጠበቅ እንዳለባቸው ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እንዲህ እያሉ ያስጠነቅቁ ነበር።

«በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እምነትና ፍቅር አድርገህ ከኔ የሰማኸው ጤናማ ቃል ምሳሌን ያዝ። መልካሙንም አደራ በኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ»።[3] ይኸንም የመሰለ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆረንቶስ ሰዎች የቃሉን ትውፊት በመጠበቃቸው ምሥጋና እንዳቀረበላቸው እንዲህ ሲል እናገኛለን «ወንድሞቼ ሆይ በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ ወገን ፈጽማችሁ ስለያዛችሁ አመሰግናችሁ አለሁ» በማለት ተናግሯል።[4]

ወንጌላዊ ዮሐንስ ከተጻፈው ይልቅ ያልተጻፈው ትውፊት ብዙ መሆኑን ይኸም በመጠኑ የተጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስ እነደሆነ እንድናምን፣ አምነንም ድኅነትን እንድናገኝ እንደተጻፈ እንዲህ ሲል ያስረዳናል «ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይኸ ተጽፏል»።[5]

የቃል ትውፊት የመጀመሪያ የክርስቲያናዊ ትምህርት መነሻ እንደሆነ የተገለጠ ለዚያን ጊዜ ብቻ ሳይሆን አሁንም ሊተላለፍ ሊወርድ ይገባዋል፤ ምክንያቱም ከተጻፈው ይልቅ ያልተጻፈው አሁንም የሚተላለፈው ትውፊት በቤተ ክርስቲያን የተጠበቀው፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚነገረው ብዙ ነውና ወንጌላዊው ዮሐንስ ጌታ የተናገረው የሠራው ብዙ ሲሆን የተጻፈው በመጠኑ እንደሆነ፤ ያልተጻፈው ግን በጣም የበዛ እንደሆነ እንዲህ ሲል ያስረዳናል «ኢየሱስ ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፣ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል»::[6]

ወንጌላዊ ዮሐንስ በወንጌሉ ይህን ይመስክር እንጂ ምስክርነቱን በማጽናት በመልእክቱም ሰፋ አድርጎ ስለተጻፈው ትውፊት ገልጦ ጽፎ እናገኘዋለን::[7] የቤተ ክርስቲያን አባቶችም የሐዋርያትን ፍለጋ በመከተል በቃል አስተምረዋል፣ ይሁን እንጂ በጽሑፍም ብዙ አስፍረዋል:: በዚህም ሁሉ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ትውፊት በቃልና በጽሑፍ በማለት በ፪ ይከፈላል::

፩. <u>የቅዱስ ትውፊት መነሻ</u>:- ቅዱስ ትውፊትን ቤተ ክርስቲያናችን አክብራ ትቀበላለች ስንል ልትቀበልበት የሚገባ ከፍተኛ ማስረጃ አላት::

ሀ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው በቃል ብቻ ነው፣ ምንም ነገር ጽፎ አልሰጠም:: ወንጌላዊያንም ሲጽፉ እኛ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነ እንድናምን ብቻ በመጠኑ ጻፉ እንጂ እርሱ ያስተማረውንና የተናገረውን ሁሉ አልጻፉም:: እርሱ ያስተማረው የተናገረውም ብዙ ነበር፤ ያ እርሱ ለጊዜው ያልጻፈው ሲወርድ ሲዋረድ በቃል ሊተላለፍ ችሏል ይኸም ትውፊት ይባላል::

ለ. በቃልም በጽሑፍ በተሰጠን ትምህርት ጸንተን እንድንኖር ያልተጻፈ ትውፊትን እንድንጠብቅ ግዴታ እንዳለብን ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይመክረናል «እንግዲያውስ ወንድሞቼ ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ»::[8]





እንዲሁም በዚሁ መልእክቱ እንደገና እንዲህ ይላል «ወንድሞቼ ሆይ ከኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄደው ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን»::[9] እንግዲህ ይህ ሁሉ ማስረጃ የሚያመለክተው በጽሑፍ የተቀበልነው ቅዱስ መጽሐፍ ሲሆን ወይም ቅዱስ መጽሐፍ ሲባል አክብረን እንደተቀበልን ሁሉ በቅዱስ ትውፊት በተጻፈው በቃል በተላለፈውና ሲወርድ ሲዋረድ በመጣውም ጸንተን መኖር እንዳለብን ነው::

ሐ. ጥንታዊያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ ስለ ቅዱስ ትውፊት ክብር እየሰጡና አክብረው እንደተቀበሉት እኛም ልንጠብቀውም እንደሚገባን ያስረዳል::

መ. ለቅዱስ መጽሐፍ ትርጉም የአባቶች ትውፊት አስፈላጊ መሆኑ የታወቀ ነው፣ ስለዚህ ፍላጎቱ ራሱ ለቅዱስ ትውፊት መነሻ ሆነ:: እብራዊያንም እንኳን የብሉይ ኪዳን ትውፊት ጥንት ጀምሮ አላቸው፣ እርሱም ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር እኩል የሆነ ክብርም ያለው ነው::

፪. <u>እውነተኛ ትውፊት</u>:- በስመ ትውፊት ማንኛውንም መቀበል የለብንም፣ በእውነተኛውና በቅዱሱ ትውፊት መካከል ለዶክትሪናችን፣ ለቅዱስም መጽሐፋችን ተቃራኒ የሚሆኑ ትውፊቶች ሳይሆኑ ትውፊቶች መስለው የገቡ ሊገኙ ይችላሉና:: ቤተ ክርስቲያን ግን ቅዱስ መጽሐፍን ከሐሰተኛ መጽሐፍ ሁሉ ለይታ አጣርታ እንደተቀበለች ጠብቃ አክብራ እንደያዘችው ሁሉ አሁንም እውነተኛውን ትውፊት ለይታ አክብራ መያዝ አለባት:: ሐሰተኛ የሆነውን፤ ሰው ሠራሺ የሆነውን ሥርዓት እንደትውፊት አድርገውም ቢይዙት ከእግዚአብሔር ሕግ ውጭ ያደርጋል፣ ለቅዱስ መጽሐፍም ተቃራኒ ይሆናል:: እንደዚህ ያለውን ሰው ሠራሽ ሥርዓት ፈሪሳዊያን እንደትውፊት አድርገው ቢይዙት ጌታ እንደተቃወመ እናገኛለ::

እርሱም የሚከተለው ነው:- «እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ እናንተስ ስለወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምን



www.ethiopianorthodox.org

ትተላለፋላችሁ? ......»::[10] እንዲሁም በዚሁ ምእራፍ በ፭ኛው ቁጥር ላይ «..... ትላላችሁ ስለወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ .....»::[11]

በዚህም መሠረት ለቅዱስ መጽሐፍ ለእምነታችንና ለትምህርታችንም ተቃራኒ የሚሆን ትውፊት ሊሆን ሊባልም አይችልም፣ እንደዚህም ያለውን ቤተ ክርስቲያን ልትቀበለው ልትይዘውም ከቶ አይገባትም::

፫. <u>የቅዱስ የትውፊት ዘመን</u>:- ትውፊት በዓይነቱ እንጂ በዓረፍተ ዘመን አይገመትም፣ በጽሑፍ የዋለው ትውፊት ቤተ ክርስቲያናችን አክብራ ተቀብላ ስትሠራበት የቆየችው እንደተጠበቀ ሆኖ ከክርስቶስ ጀምሮ እስከ አሁን የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተናገሩት የሚሠሩት፣ በቅዱስ ሲኖዶስ አማካይነት የሚወስኑት ሁሉ በቅዱስ መንፈስ መሪነት የሚወሰን እንደሆነ ስለሚታመንበት እርሱም ትውፊት በመሆኑ ሊቀበሉትና ሊጠብቁት የሚገባ ነው::

ይኸን ቅዱሱን ትውፊት መስሎ ሳይጣራ የሚቀርብ፣ የሚጻፍ ወይም የሚነገር ቢኖር ግን በቤተ ክርስቲያን መጣራት መመዘንም አለበት:: ያለ ቅዱስ ትውፊት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ልትከፈት፣ ቅዱስ መጽሐፍም ሊተረጎም የማይችል ስለሆነ የቅዱስ ትውፊት ተቀባይነት ግድና አስፈላጊም ነው::

# ክ ፍ ል ፫

## ምሥጢረ ሥላሴ በጠቅላላው::

## ም ዕ ራ ፍ ፩

### እግዚአብሔር በሥላሴነቱ፣

የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ቤተ ክርስቲያን እንደ ተመሠረተች ወዲያውኑ በይፋ ታወቀ ተረዳ:: ዋናው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርትም በባሕርይ፣ በህልውና በአገዛዝ አንድ አምላክ ነው ያልነውን በአካል፣ በስም፣ በግብር ፫ ብሎ ማመንና ማስተማር እውነተኛ ትምህርት እንደሆነ ተወስነ::





እግዚአብሔር አምላክ በባሕርይና በህልውና አንድ የሆነው፣ በአካልና በስም በግብር ፫ ነው:: እግዚአብሔርን በ፩ነቱ ውዳሴ ክብር እናቀርብለታለን፣ በአካልም ፫ነቱን ገልጠን እንመሰክራለን፤ በይፋም እንናገራለን::

በጸሎተ ቅዳሴያችን ፫ነትን በ፩ነት እየገለጥን እንናገራለን፣ «አ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ባርከ ዲበ ሕዝብከ ....» በማለት ፫ነት ያለበትን አንድነት እንገልጣለን:: ይኸም በሥላሴ ላይ ያለንን እምነትና ትምህርት በተለያዩ የእምነት ውሳኔዎችና መግለጫዎች በይፋ ይሰጡ ጀመር (ጸሎተ ሃይማኖትና እርሱን የመሰሉ ምዕላዶች) :: ምሥጢረ ሥላሴ በዚህ መልክ ጎልቶ ቢነገርም በሰው አእምሮ የማይረዳ ሥውር ምሥጢር፤ የማያስገባም በር ሁኖ ይገኛል፣ እንዲሁ ግን እንናገራለን፤ እንዲሁም እናምናለን:: ምንም በሥላሴ ትምህርት ብናምን የእግዚአብሔርን አንድነቱን እናምናለን፣ አንድ አምላክን ብቻ እናመልካለን::

የእግዚአብሔርን መኖር የሚያውቁና በአንድ አምላክ የሚያምኑ ወገኖች ብዙ ናቸው፣ ከነርሱም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ:-

1ኛ. ክርስቲያን፣

2ኛ. ዕብራውያን፣

3ኛ. እስላሞች ናቸው:: ክርስቲያን ግን ከነዚህ ተለይቶ የሚታወቅበት በበለጠም እውነትን ይዞ የሚያምነው በባሕርይ በህልውና በአምላክነት አንድ እግዚአብሔር ያለውን በአካል፣ በግብር፣ በስም ሦስት ብሎ በመቀበል ነው፣ እነዚህም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው::

በሥላሴም ማመን የተለየ እውነተኛነቱ የተመሠከረለት ሃይማኖት ነው፣ ስለዚህ ክርስቲያኖች ከሌላው እምነት ተከታይ ተለይተው እውነተኞች ሆነው ይገኛሉ:: የክርስትናም ሃይማኖት በሥላሴ ማመን እውነትነት እንዳለው የተረዳ ነው፣ ምክንያቱም ይኸን እውነትነት ያለውን እምነት የተናገረ ባለቤቱ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው:: «ከሰማይም ድምፅ መጣ እንዲህ ሲል ይኸ ነው የምወደው ልጄ በእርሱ ደስታዬን የማይበት::[1]»



www.ethiopianorthodox.org

መጀመሪያውኑ እግዚአብሔር አምላክ ይህን ዓለም ሲፈጥር አንድ እንደሆነ፣ ሲታወቅ፣ በአካል በስም በግብር ሦስትነት እንዳለው ለማጠየቅ ሲል «ንግበር ሰብእ በአርአያነ ወበአምሳሊነ» ሰውን እንፍጠር በመልካችን እንደምሳሌያችን በማለት ሦስትነትን በማስረዳት ተናግሯል::[2]

ይኸም አባባል የክብር ምልክት የነገሥታትም አነጋገር መስሎ ቢታይም ማለት እግዚአብሔር በፍጥረቱ ተገብቶ እኛ በማለት ተናገረ ቢባልም ከዚህ የተሻለ አገላለጥ ያለውን አስረጅ እንዲህ ሲል ያቀርብልናል፣ «አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ» አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፣ ሲል ከአንድ የወጣ ቁጥር እንዳለው በማመልከት ተናግሯል::[3] ይኸም ከ፩ በላይ ቁጥርን ያመለክታል ማለት ነው:: ደግሞም በሰናዖር ምድር ከለዳውያን የጡብ ግንብ በሠሩ ጊዜ «ንዑ ንረድ ወንከአው ነገሮሙ ለከለዳውያን»፤ ኑ እንውረድ ቋንቋቸውን እንደባልቀው፣ ከርሳቸው አንድ የባልንጀራውን ቋንቋ እንዳይሰማ በማለት ፩ዱ ሌላውን ሲጋብዝ እናገኘዋለን፣ ይኸም ማለት ሦስትነት ተገልጦ ተነግሯል ማለት ነው::[4] ይኽን የመሰለ ብዙ አስረጂ በቅዱስ መጽሐፍ ይገኛል:: ሆኖም ግን ከዚህ በላይ ያተትነው ሐተታ የሰጠነውም አስረጂ ሁሉ የሦስትነት ማስረጃ ነው እንላለን እንጂ፣ በግልጥ ሦስትነትን ለይቶ አያመለክትም:: እስከ ዘመነ ሥጋዊ ድረስ ከአንድ ቁጥር የበለጠ መሆኑን ብቻ ይገልጣል እንጂ የሁለትነትና የሦስትነት አንድም ከዚያ የበለጠ የቁጥር ምልክትን የሚያስረዳ ሁኖ በመገኘቱ ዕብራውያንም ይኽን ለመመርመር ከባድ ሆኖባቸው እነማን ለማን እንደተናገሩት ሊያውቁት ባለመቻላቸው እንቆቅልሽ ሆኖባቸው ይኖር ነበር::

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል መስክሯል «ነገር ግን እስከ ዛሬ የሙሴ መጽሐፍ እየተነበበ መጋረጃው በልባቸው አለ:: ወደጌታ ግን በተመለሱ ጊዜ መጋረጃው ፈቀቅ ይላል»::[5] የተነገረው ትንቢት፣ የተቆጠረው ሱባኤ ሁሉ በክርስትና መንፈስ ካልተተረጎመ እስካሁን ድረስ ለነርሱ ዝግ መሆኑን ገልጦ ተናገረ::

ከዚህ በተሻለ አገላለጥ ግን ሦስትነትን ከአንድነት ጋር በማያያዝ እግዚአብሔር አምላክ ለአገልጋዩ ለሙሴ ሐመልማልን





ከነበልባል፣ ነበልባልን ከሐመልማል ጋር አዋሕዶ «አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ» እያለ በእሳቱ መካከል አንድነቱን ሦስትነቱን በመግለጥ ተናግሯል::[6] አምላክ አምላክ በማለት ሦስት ጊዜ መናገሩ የሦስትነት ምሳሌ ነው፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ብሎ የተናገረውም ቃሉ ያለመለወጡ አንድነትን የሚገልጥ ነው:: እንደገናም ሙሴ የሕዝቡ መባረኪያ ቃል አድርጎ ሦስትነትንም አንድነትንም በሚገልጥ መልክ እንዲህ ሲል ይናገር ነበር፣ «እግዚአብሔር ይባርክህ፤ ይጠብቅህም:: እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፣ ይቅርም ይበልህ:: እግዚአብሔር ፊቱን ወደአንተ ያንሣ ሰላምም ይስጥህ::[7]» እንዲህ እያለ ሦስት ጊዜ መላልሶ መናገሩ የሦስትነት፣ በአንድ አንቀጽ (ቁጥር) መናገሩ ደግሞ የአንድነት ምሳሌ ነውና::

ነቢዩ ዳዊትም በመዝሙሩ «ዐቢይ እግዚአብሔር ወዐቢይ ኃይሉ ወአልቦ ኍልቁ ለጥበቢሁ» እያለ አንድነትንም ሦስትነትንም ገልጦ ተናግሯል::[8] ማለት ዐቢይ እግዚአብሔር ያለው እግዚአብሔር አብን ነው፣ ወዐቢይ ኃይሉ ያለው ደግሞ ኃያሉን እግዚአብሔር ወልድን ነው፣ ወአልቦ ኍልቁ ለጥበቢሁ ያለው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ነውና:: በድጋሜም «ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልዐ ምድረ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዓ ሰማያት ወእምስትንፋሰ አፉሁ ኲሉ ኃይሎሙ»:: በማለት አንድነትንም ሦስትነትንም ገልጧል::[9] ሣህሉ ለእግዚአብሔር ያለው እግዚአብሔር አብን ነው፣ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዓ ሰማያት ያለው ቃለ እግዚአብሔር ወልድን ነው፣ ወእምስትንፋሰ አፉሁ ያለው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ነውና::

ነቢዩ ኢሳይያስም መላእክት በሰማይ ሆነው «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ» እያሉ ሲያመሰግኑ ሰምቷል::[10] ይኸም የሥላሴን ሦስትነት የሚያመለክት ምሳሌ ነው፣ ማለት ሦስት ጊዜ ቅዱስ ያለው የሦስትነት፣ እግዚአብሔር ያለው ደግሞ የአንድነት አስረጂ ነው:: ከዚህም ሌላ ልዑል እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለወዳጁ ምሥጢርን መግለጥ ልማዱ ስለሆነ፣ በቃል



www.ethiopianorthodox.org

ብቻ ሳይሆን በሥራም ለወዳጁ ለአብርሃም ሦስትነቱ ከአንድነቱ፤ አንድነቱንም ከሦስትነቱ ጋር በማያያዝ እንዲህ አድርጎ ገልጦለታል:: «ዓይኑን አነሳና አየ፣ እነሆም ሦስት ሰዎች ወደርሱ ቀረቡ፣ ባያቸውም ጊዜ ከድንኳኑ ደጅ ሊቀበላቸው ሮጠ፣ ወደምድርም ሰገደ፣» ይህ የሦስትነቱ ምልክት ነው:: የአንድነት ምልክት ደግሞ ከዚያ ደርሶ በነጠላ ቁጥር «አቤቱ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ እለምንሃለሁ፣ ባርያህን አትለፈኝ» አለ::[11] ይኸም ሥላሴ ሦስት ሲሆኑ አንድ፤ አንድ ሲሆኑ ደግሞ ሦስት መሆናቸውን የሚያጠይቅ ከፍተኛ ምሥጢር ነው:: ይህም ቅሉ ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌው የጎላ መስሎ ይታይ እንጂ ለዚያን ጊዜ ለእሥራኤላውያን ረቂቅ ምሳሌ ሆኖባቸው ሲኖሩ ነበር፣ ሆኖም እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሲያስተምር «ኩሉ ተውህበኒ እምኀበ አቡየ» ሁሉ ተሰጠኝ ከአባቴ ዘንድ ማንም ወልድን አያውቀውም ያለ አብ፣ አብንም ማንም አያውቀውም ያለ ወልድ፣ ወልድም ሊገለጥለት ከወደደው ሰው በቀር ሲል የራቀውን አቅርቦ፣ የረቀቀውንም ምሥጢር አጉልቶ፣ አካለ አብን፣ አካለ ወልድን፣ አካለ መንፈስ ቅዱስን በመለየት አስተማራቸው ገለጠላቸውም::[12] እንዲሁም በጥምቀት ጊዜ ወልድ ሲጠመቅ «ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ሠመርኩ» የምወደው ልጄ ይኸ ነው ብሎ አብ ሲያውጅ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል ወርዶ ረብቦ ታይቷል፣ በዚህን ጊዜ እውነተኛው የክርስቲያን ትምህርት ምሥጢረ ሥላሴ ተመሠረተ::[13]

እንዲሁም ደግሞ ይኸን የመሰለ አስረጂ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን በገለጠ፣ እውነተኛ አምላክነቱንም በአስረዳ ጊዜ አብ «የምወደው ልጄ ይኸ ነውና ስሙት» ሲል በደመና ሆኖ መስክሯል::[14] ይኸንም የመሰለ የሦስትነትን አስረጂ አካልን ስምን በመለየት ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ሰጥቷል «የተመረጡት እንደ እግዚአብሔር አብ ዕውቀት በመንፈስ ቅዱስም ለመታዘዝ በኢየሱስ ክርስቶስም በደሙ መረጨት»::[15] ሐዋርያትን ወደዚህ ዓለም ለስብከት ክርስቶስ ሲያሰማራቸው «ሂዱ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፣ <u>እነርሱንም አጥምቋቸው፣ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም</u>» ብሎ





ጥብቅ አደራን ሰጥቶ ምሥጢረ ሥላሴን አጉልቶ ሥላሴን በስም በግብር በአካል ፫ትነታቸውን አጉልቶ በመግለጥ አስረድቶ ልኳቸዋል::[16]

ሐዋርያትም ይኸን ይዘው በመልዕክታቸው በትምህርታቸው ምሥጢረ ሥላሴን አጉልተው ጽፈዋል፣ ለምሳሌ ዮሐንስ ወንጌላዊው በመልዕክቱ ሲጽፍ «በሰማይ ምስክር የሚሆኑ ሦስት ናቸው፣ አብ፣ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስም፣ እነዚህ ሦስቱ አንድ ናቸው» ብሎ ሦስት ሲሆኑ አንድ፣ አንድ ሲሆኑ ሦስት መሆናቸውን መስክሯል::[17] ቅዱስ ጳውሎስም «የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስም ምሕረት ለእናንተ ይሁን» ብሎ በቀና መንገድ ሦስትነትን አስረድቷል::[18] ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ብቻ ሳይወሰን በመልዕክቶቹ ሁሉ መጀመሪያና መፈጸሚያ ይኸንኑ በማጉላት መስክሮ ጽፏል፣ ይህን የመሰለ ፍጹምና እውነተኛ አስረጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ይገኛል::

የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በተመሳሳይ መልክ ምሥጢረ ሥላሴን ገልጠው ጽፈዋል፣ መጽሐፈ ባሕርይ የተባለው መጽሐፍ «ሥላሴ ቅድስት ህልዋን እንበለ ጥንት፣ ወዕሩያን፣ በአሐቲ ባሕርየ መለኮት» ሲል አስረድቷል::[19]

እንዲሁም የጥንት አባቶች የጸሎት መጀመሪያ የደስታም የመገረምም መግለጫ የሥላሴን ስም በመጥራት አንድነትን ሦስትነትን በመመስከር «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ» እያሉ ሲመሰክሩ ሲናገሩም ይገኛሉ:: የሥራም መጀመሪያ ሁሉ፣ ይህኑ አድርገው ወስነዋል:: ሦስትነታቸውን ትክክልነታቸውን በጎላ ለማስረዳት የሚከተለውን ምሳሌያዊ አስረጅ እንጠቀምበታለን፣ እርሱም አብን በልብ፣ ወልድን በቃል መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ እንመስላቸዋለን:: ይኸም ማለት ልብ፣ ቃል እስትንፋስ በአንድነት እንዲገኙ እንደማይለያዩም በሥላሴም መካከል መቅደም መቀዳደም፣ መብለጥ መበላለጥ እንደሌለባቸው ገልጠን እናስረዳለን:: እንደዚሁም የአካል ሦስትነታቸውን ለማስረዳት ያህል ሦስት ስንል በመለኮት በባሕርይ አንድ መሆኑን እንመሰክራለን፣



www.ethiopianorthodox.org

ይሜለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት ይለናልና::[20] ግብራቸውም አብ ይወልዳል፣ ያሠርጻል እንጂ አይወለድም አይሠርፅም፣ ወልድም ይወለዳል እንጂ አይወልድም አይሠርፅም አያሠርፅም፣ መንፈስ ቅዱስም ይሠርጻል እንጂ አይወልድም አይወለድም:: እግዚአብሔር በአካሉ ሦስት በመለኮቱ ግን አንድ ነው፣ ስለዚህ እግዚአብሔር በአንድነቱና በሦስትነቱ ነበር፣ አለ፣ ይኖራልም:: እግዚአብሔር በአንድነቱና በሦስትነቱ ጸንቶ ዓለምን ፈጠረ፣ ዓለምን ያስተዳድራል፣ በኋላም ዓለምን ያሳልፋል::

የሥላሴን የስም የግብር የአካል ሦስትነትን በትክክል በመግለጥ፣ እንዲሁም ቀዳሚነትም ተከታይነትም አለመኖሩን ኅቡረ ህላዌ መሆናቸውን «ተውልደ እምአብ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ዘእንበለ እም በከመ ይትወለድ ብርሃን እም ብርሃን:: ወበ ከመ አቡሁ አምላክ ዘበአማን ውእቱሂ አምላክ ዘበአማን፣ እስመ አብ ወለዶ ወኢፈጠሮ ወኢገብሮ:: ወበከመ አብ ብርሃን ውእቱ ወልድኒ ከማሁ ብርሃን እስመ አብ ወለዶ እምባሕርዩ፣ ወኩሉ ዘተወልደ እምባሕርይ ይነሥእ ባሕርዮ» ሲሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳሉ::[21]

ለእግዚአብሔር መጀመሪያና ዳርቻ አልነበረውም፣ ወደፊትም መጨረሻ ወሰን አይኖረውም፣ እንደ እግዚአብሔርነቱ በ፩ነቱ በሦስትነቱ ጸንቶ ነበር፣ አለ፣ ይኖራልም::

፩. <u>ምሥጢረ ሥላሴ</u>፣

ስለ ሥላሴ የምንማረውና የምናስተምረው ትምህርት ምሥጢር ተብሏል፣ ምሥጢርም ይባላል፣ ምክንያቱም በዓይን የማይታይ በእጅ የማይጨበጥ በሕሊና ብቻ የሚታሰብ፣ በፍጹም ሕሊና አምነው የሚቀበሉት እንጅ በምርምር የማይደረስበት ነውና:: በባሕርይ በሕልውና አንድ አምላክ የምንለውን በስም በግብር በአካል ደግሞ ሦስት ብሎ ማመን ታላቅ ምሥጢር ነው:: ሥላሴም አንድነታቸው ሦስትነታቸውን ሳይጠቀልለው፣ ሦስትነታቸውም አንድነታቸውን ሳይለያየው በአንድነት በሦስትነት ሲመስገኑ ነበሩ፣ አሁንም ይገኛሉ፣ ወደፊትም እንዲሁ ይኖራሉ፣ ይኸ እንዴት ሊሆን ይችላል





ሊባል አይቻልም ምሥጢር ነውና:: በየጊዜው የተነሱ ሊቃውንት ሰፋ ያለ ማስረጃ እንደሚከተለው ሰጥተዋል «አልቦሙ ጥንት፣ ወኢተፍጻሜት ለሥላሴ እንዘ አሐዱ ሠለስቱ፣ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ» ሲል ቅዱስ ባስልዮስ ጽፏል፤ ይኸም ማለት ለሥላሴ ጥንትነት ወይም ፍጻሜ የላቸውም፣ አንድ ሲሆኑ ሦስት፣ ሦስትም ሲሆኑ አንድ ነው ማለት ነው::[22]

«ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ተጋብአ በተከፍሎ ወተከፍሎ በተጋብኦ» ሲል ሱንትዮስ የተባለ ሊቅ ጽፏል:: ይኸም ማለት ፫ነት በአንድነት፤ አንድነትም በ፫ነት ያለ-መከፈል፣ ያለ-መለያየትም አንድ የሆኑ ማለት ነው::[23] «ሊሉያን እንበለ ትድምርት፣ ወኅቡራን እንበለ ተሌልዮ» እያሉ ሠለስቱ ምዕትም አስረጅ ሰጥተዋል::[24] ይኸም ማለት ሥላሴ የማይገናኙ የተለያዩ፣ ያልተለያዩም አንድነት ያላቸው ማለት ነው፣ ጠቅላላ ምሥጢሩ ግን አንድነት በሦስትነት አይከፈልም፣ ሦስትነትም በአንድነት አይለይም ማለት ነው፤ ምሥጢርም የሚያሰኘው ይኸ ሁሉ ሲደመር ነው:: እግዚአብሔር አብ ፈጣሪ ነው፣[25] እግዚአብሔር ወልድም ፈጣሪ ነው፣[26] እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ፈጣሪ ነው፣[27] ነገር ግን ሦስቱም በአምላክነት አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ አንድ ፈጣሪ ይባላል እንጂ ሦስት አማልክት ሦስት ፈጣሪዎች አንልም አይባልም:: እግዚአብሔር አብ አምላክ ነው፣ እግዚአብሔር ወልድም አምላክ ነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው::[28] እንዲሁም ስለሆነ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት ከቶ አንልም አይባልም፣ እንግዲህ ሦስት ሲሆን አንድ፣ አንድም ሲሆኑ ሦስት እንዴት እንደሚሆኑ እንመልከት::

2ኛ. <u>ሦስትነት በአንድነት</u>፣

ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስት የሚሆኑበት በስም በግብር በአካል ነው::

ሀ. <u>የስም ሦስትነት</u>

ለሥላሴ የስም ሦስትነት አላቸው፣ ይኸውም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ መባል ነው:: ምንም ስምን ለይተን



www.ethiopianorthodox.org

ሦስት ብንልም ከቶ ሦስት አማልክት አንልም አንድ አምላክ እንጂ። ይህም ስማቸው ከቶ አይፋለስም፣ አይለወጥም፣ በየስማቸው ሲመሰገኑ ጸንተው ይኖራሉ እንጂ፣ ማለት አብ አብ ይባላል እንጅ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም፣ ወልድም ወልድ ቢባል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም፣ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ ቢባል እንጂ አብ ወልድ አይባልም «አብሂ አብ ውእቱወ ኢኮነ ወልደ፣ ወኢኮነ መንፈስ ቅዱስ፣ ወልድሂ ወልድ ውእቱ ወኢኮነ አበወ ኢመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስሂ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ ወኢኮነ አበ ወኢወልደ፣ ኢይፈልስ ስመ አብ ለከዊነ ስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወስመ ወልድሂ ለከዊነ ስመ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወስመ መንፈስ ቅዱስሂ ለከዊነ ስመ አብ ወወልድ» ሲል አግናጥዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ አስረድቷል።[29]

በስም ክርስቲያን ነን እያሉ የክርስትናውን ስምና መልክ የሚያጠፉ መናፍቃን «ኢየሱስ ብቻ» እያሉ አብ የሚለውንም ወልድ የሚለውንም፣ መንፈስ ቅዱስ የሚለውንም ለኢየሱስ ብቻ እየሰጡ ስመ ተፋልሶ ያመጣሉ፣ ልዩ ኑፋቄን ይፈጥራሉ። በምንም መልክ አብ አብ ይባላል እንጂ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይሆንም አይባልም። እንዲሁም ወልድ ወልድ ቢባል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም። መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ቢባል እንጂ አብ ወልድ አይባልም። ሥላሴ በትክክል በስም ሦስት ናቸው፣ በአምላክነት ግን አንድ ነው፣ ይኸነንም «ሠለስቱ ስም አሐዱ እግዚአብሔር» ሲል ቄርሎስ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ያስረዳል፣[30]

ጌታችን ኢየሱስም «ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ በስም ሦስትነታቸውን ጠርቶ ተናግሯል።[31] ፫፻፲፰ ሊቃውንትም «ንባርኮ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ሲሉ ተናግረዋል።[32] ንባርኮ ብለው አንድነቱን፣ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለው የስም ሦስትነታቸውን ተናገሩ። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ብለን የሥላሴን ስም ከተናገርን ዘንድ የስማቸውንም ትርጉም እንደሚከተለው እንናገራለን፣ አብ ማለት አባት ማለት ነው፣ ምክንያቱም ወልድን ይወልዳል፣ መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻልና።





ወልድም ማለት ልጅ ማለት ነው፣ ምክንያቱም ወልድ አብን አክሎ አብን መስሎ ባሕርይ ዘእምባሕርይ ከአብ ተወልዷልና። መንፈስ ቅዱስ ማለትም ሠራፂ ማለት ነው፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ አብን አክሎና መስሎ ከአብ ብቻ ስለሠረፀ ነው። አብ ከባሕርዩ ወልድን ወለደ፣ መንፈስ ቅዱስን አሠረፀ፣ ስለዚህ አብ የባሕርይ አባት ይባላል፣ ወልድም የባሕርይ ልጅ ይባላል፣ መንፈስ ቅዱስም የባሕርይ ሕይወት ይባላል። እንዲህ ባለው አኳኋን በስማቸው ተፋልሶ ከቶ የለባቸውም፣ የሥላሴ የስማቸው ትርጓሜ የስማቸውም ሦስትነት ይህን የመሰለ ነው፣ አንድም እንዲህ ነው።

ለ. <u>የግብር ሦስትነት</u>፣

የሥላሴ የግብር ሦስትነት የሚታወቀው አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ በመሆን ነው። የግብር ትርጉም የአብ ግብር መውለድ ማሥረፅ ነው፤ ምክንያቱም አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርፅ እንጂ እንደ ወልድ አይወለድም እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅምና። ወልድም ከአብ ቢወለድ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም፣ እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ቢሠርፅ እንጂ እንደ አብ አይወልድም እንደ ወልድም አይወለድም። «አብሰ ኢተወለደ አላ ውእቱ ወላዴ ወልድ እምቅድመ ኩሉ ዓለም» ሲል አትናቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ያስረዳል።[33]

እንዲህ ባለ ግብር አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራፄ ሆነው ነበሩ፣ ሆነው አሉ፣ ለዘለዓለም ይኖራሉ፣ የሥላሴ የግብር ሦስትነታቸው ትርጉም ይህ ነው።

ሐ. <u>የአካል ሦስትነት</u>፣

የሥላሴ የአካል ሦስትነት አብ በወላዲነቱ ፍጹም አካል አለው፤ ፍጹም ህልውናም አለው፣ ወልድም በተለይ አካሉ በተወላዲነቱ ፍጹም አካል አለው፣ ፍጹም ህልውናም አለው፣ መንፈስ ቅዱስም በሠራፂነቱ ፍጹም አካል አለው፣ ፍጹም ህልውና አለው። ሥላሴ እንዲህ ባለ ርቀት እንዲሁም ባለ



www.ethiopianorthodox.org

ምልዓት በሰማይ በምድር በአፍዓ በውስጥ ምሉዓን ናቸው:: ዓለም በጠቅላላው በሥላሴ ፈጣሪነት እንደተፈጠረ ዘለዓለም ሥላሴ ምሉዓን ሆነው ይኖራሉ:: «በውስተ ዓለምኒ ሀሎ ወዓለምኒ ቦቱ ኮነ» ሲል ዮሐንስ ወንጌላዊ ተናግሯል::[34]

እንዲህ ባለ ስም እንዲህ ባለ ግብር እንዲህ ባለ አካል ሳይቀዳደሙ ቃል እስትንፋስ ከልብ እንዲገኙ ስማቸው ከአካላቸው አካላቸው ከስማቸው ሳይቀድም ሥላሴ ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉ:: ወአከ ሎሙ፡ሂ ለሥሉስ ቅዱስ ወአስማቲሆሙ፤ አልቦ እምውስቴቶሙ ዘይደኃር እሉ እሙንቱ ብሉያነ መዋዕል እምቀዲሙ ዘእንበለ ጥንት ወዘመን» ሲል ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ተናግሯል::[35] የልብነትን የቃልነትን የእስትንፋስነትን ምሥጢር ለማወቅ ሲፈለግ ቃል የሚያገናኛቸው ቢመስልም ምሥጢር አያገናኛቸውም፣ የወልድ መገኘት ልደት የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ሥርፀት ይባላል፣ ይህም በዕፁብ ይወሰናል እንጂ ሊመረመር አይቻልም:: «ልደተ ወልድ ወፀአተ መንፈስ ቅዱስ ይትነከር ወኢይትነገር» ሲል ዲዮናስዮስ ዘአርዮስ ፋጎስ አስረድቷል::[36]

3ኛ. <u>አንድነት በሦስትነት</u>፣

የሥላሴ አንድነታቸው በምንና በምን ነው? ብለን የመረመርን እንደሆነ በባሕርይ በመለኮት በመንግሥት በእግዚአብሔርነት በአምላክነት ነው፣ ሥላሴ በመንግሥት በባሕርይ በመለኮት አንድ ነውና:: አንዱ መንግሥት ደግሞ በአካል ሦስት ናቸው፣ ወላዲ ንጉሥ፣ ተወላዲ ንጉሥ፣ ሠራፂ ንጉሥ፣ አሐዱ ንጉሥ «ንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ» ሲል ሔሬኔዎስ ኤጲስ ቆጶስ ዘሀገረ ኤዶም ተናግሯል::[37]

ስለዚህ ሥላሴ በእግዚአብሔርነት በባሕርይ፣ በመለኮት አንድ ነው፣ እግዚአብሔር በአካል ሦስት ነው፣ «ወላዲ እግዚአብሔር፣ ተወላዲ እግዚአብሔር፣ ሠራፂ እግዚአብሔር» ይላልና::[38] ወንጌላዊ ዮሐንስም ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል ሲል ጽፏል::[39]





ወላዲ አምላክ፣ ተወላዲ አምላክ፣ ሠራፂ አምላክ፣ አሐዱ አምላክ «አምላክ ውእቱ አብ፣ አምላክ ውእቱ ወልድ፣ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ወኢይትበሃሉ ፫ተ አማልክተ» ሲል አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ተናግሯል::[40] አስቀድሞ ሊቀ ነቢያት ሙሴ «ሰማዕ እሥራኤል ከመ አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ» ሲል መስክሯል::[41] ፫፻፲፰ ሊቃውንትም በአንድ ድምፅ ውሳኔያቸው «ነአምን በአሐዱ አምላክ» ብለው የአምላክን ፍጹም አንድነቱን መስክረዋል:: ሦስት የሚያደርጋቸው አካል ከሆነ፣ አንድ የሚያደርጋቸው ደግሞ ባሕርይና ፈቃድ ነው:: ሦስትነት ያለበት አንድነት፣ መለያየትም የሌለበት ሦስትነት አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፣ እነርሱም አንድ አምላክ ይባላሉና፣ ደግሞ ናቸው:: በአካል ሦስት ከሆኑ በፈቃድ በባሕርይ አንድ መሆን እንደምን ነው? ያልን እንደሆነ አካል በአካል ህልው ሆኖ በአንድ ልቡናነት በአንድ ቃልነት በአንድ እስትንፋስነት ስለሚኖር ነው:: አብ በፍጹም አካሉ ልብ ነው፣ ሌላ ልብ የለውም «ህየንተ ልብ ዘዝዬ ነአምሮ ለአብ» ሲል ቴዎዶጦስ አዘንቆራ ተናግሯል::[42] ወልድም በፍጹም አካሉ ቃል ነው፣ ሌላ ቃል የለውም «ኢታምስልዎ ለዝቃል ከመ ቃላት እለዘከርናሆሙ ዘእንበለ ህላዌ ወአካል፣ አላ ፍጹም መልክእ ወአካል ከመ ገጸ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ» ሲል ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ተናግሯል::[43]

መንፈስ ቅዱስም በፍጹም አካሉ እስትንፋስ ነው፣ ለሥላሴ ሌላ እስትንፋስ የላቸውም «ወአኮ ውእቱ ዘከመ ነፍስ ዘሀሎ ውስቴትነ ዘንስሕቦ ኃቤነ እምነፋስ ለቁመተ ሥጋነ፣ አላ ውእቱ መንፈስ እግዚአብሔር ሲል ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ ተናግሯል::[44]

አብ በልብነቱ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው፣ ወልድም በቃልነቱ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው፣ መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋስነቱ በአብ በወልድ ህልው ነው:: «አብኒ ህልው ውእቱ በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ፣ ወወልድኒ ህልው ውእቱ በአብ ወበመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ህልው በአብ ወበወልድ» ሲል ፊላታዎስ ዘእስክንድርያ ተናግሯል[45]:: ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አብ ልባቸው ነው:: ለመንፈስ ቅዱስና ለአብም ወልድ ቃላቸው ነው:: ለወልድና ለአብ ደግሞ



www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሳቸው ነው፣ ማለት በአብ ልቡናነት ሦስቱም ያስባሉ፣ በውልድ ቃልነት ሦስቱም ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነትም ሦስቱ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ፣ በጠቅላላም ይገነዛዘባሉ ብለን እናምናለን።

ሥላሴ በአብ ለባውያን፣ በወልድ ነባብያን፣ በመንፈስ ቅዱስም ሕያዋን ይባላሉ። እስትንፋስ የሕያውነት መግለጫ ነውና «አብሂ ልቡናሆሙ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ፤ ወወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ፤ ወመንፈስ ቅዱስኒ እስትንፋሶሙ ለአብ ወለወልድ» ሲል አቡሊዲስ ዘሮሜ ተናግሯል»።[46] እንዲህ ባለ መገነዛዘብ ቃል እስትንፋስ ከልብ መቋረጥ እንደሌለባቸው ወልድም መንፈስ ቅዱስም ከአብ መለየት የለባቸውም።

በፈቃድ አንድ እንደመሆናቸው ለመዓትም ለምሕረትም በአንድነት ይሠራሉ፣ ይፈጽማሉ «ወአኮ አብ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር፣ ወወልድሂ በርእሱ ባሕቲቱ አኮ ዘይገብር፣ መንፈስ ቅዱስሂ አኮ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር፣ አላ ዘፈቀደ አብ ይፈጽምዎ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወምግባሮሙኒ አሐዱ ውእቱ» ሲል ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ተናግሯል።[47] አባ ሕርያቆስም አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይሄልዩ፣ ይትናገሩ፣ ይሠምሩ እያለ የሥላሴን የፈቃድ አንድነታቸውን አስፋፍቶ ጽፏል።[48]

እንዲህም ስለሆነ፣ ዓይነ ፍጡራን አያየውም፣ በአንድ በኩል ደግሞ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲል ከመላዕክት ከጻድቃን ጋር ይነጋገራል፣ ድምፁን ያሰማል፣ ይህም በዕፁብ ይወሰናል እንጂ አይመረመርም፣ ተገልጠውም የሚታዩ ቢሆን ይህ አብ ነው፣ ይህ ግን ወልድ ነው፣ ይህም መንፈስ ቅዱስ ነው ብሎ ለይቶ ማወቅ ለፍጡር አይቻለውም። አንዱን ለይቶ ያምናል እንጂ፣ «ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ» ሲል ወንጌላዊ ዮሐንስ ጽፏልና[49]። «ወኢይክል መኑሂ እምፍጡራን ይለቡ ፍልጠተ አካላት ወመለኮት በዘዚኢሆሙ ዘእንበለ ዳዕሙ የአምር ዘከሠተ በአምሳል፣ ወአርአያ» ሲል ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ተናግሯል።[50]

ደግሞም ሦስቱ ሁሉ ሕይወት ይባላሉ ግን አንድ ሕይወት ብቻ ነው፣ አብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ የልብነት ሕይወት፣





የልብነት ኃይል፣ የልብነት ጥበብ ነው፣ ወልድም ለመንፈስ ቅዱስና ለአብ የቃልነት ጥበብ፣ የቃልነት ሕይወት፣ የቃልነት ኃይል ነው። መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ የእስትንፋስነት ጥበብ፣ የእስትንፋስነት ሕይወት፣ የእስትንፋስነት ኃይል ነው። «አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አቡሁ ለቃል ጥበቡ ወኃይሉ ህልው ምስሌሁ» ሲሉ ሠለስቱ ምዕት ተናግረዋል።[51] ነቢዩ ዳዊትም ወአልቦ ኍልቈ ለጥበቢሁ ሲል አስረድቷል፣ ህብቱ ወይም ሥጦታው ብዙ የሆነ የመንፈስ ቅዱስን ነገር ተናገረ።[52] ሦስቱ እሳት ይባላሉ፣ ነገር ግን አንድ እሳት ነው፣ አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት አሐዱ ውእቱ እሳተ ሕይወት ዘእምአርያም» ሲል አባ ሕርያቆስ ያስረዳልና።[53]

እንዲህ ባለ ምልዓት ስፋት ርቀት፤ እንዲህም ባለ አንድነት ሦስትነት ሥላሴ ሳይወሳሰኑ አንዱ ካንዱ መቅደም መቀዳደም ሳይኖርባቸው አንዱ ለአንዱ መገዛት ሳይኖር በአካል በስም በግብር ሦስትነትን በፈቃድ በህልውና በአምላክነት አንድነትን ገንዘብ አድርገው ሥላሴ ቅድመ ዓለም ነበሩ፣ ዓለምን ፈጥረው አሉ፣ ዓለምን አሳልፈው ይኖራሉ። «አልቦ በውስተ ቅድስት ሥላሴ ግብርናት ወተጋንዮ ወኢይትሌዓል አሐዱ እምካልዑ በመዓርገ መለኮት ወኢይትኤዘዝ አሐዱ ለካልዑ ዘከመ ተለአኪ በሥልጣኑ አላ እሙንቱ ዕሩያን በአሐዱ ክብር ዘመለኮት»ሲል ሳዊሮስ ተናግሯል።[54]

በሥላሴ ዘንድ አንድነት ካለ ብሎ ሦስትነትን፣ ሦስትነትም ካለ ብሎ አንድነትን ሊያፈርስ፣ ወይም ሊቀንስ የሚችል ከቶ የለም። የክርስቲያን እምነትና ትምህርት ይኸን የተደገፈ በዚህም የጸና ነው። ምንም ስለ ሥላሴ የሚሰጠው ትምህርት ከባድ ቢሆንም ረቀቀብኝ ብሎ በባሕርይ በሕልውና፣ በመለኮት አንድ የሆነውን በስም፣ በአካል ሦስት ነው፣ የማይል ክርስቲያናዊ ትምህርት ሊባል አይቻልም፣ ሰውየውም ክርስቲያን ሊባል አይቻልም፣ አይገባውም።

ሥላሴ በመለኮት አንድ እንደመሆናቸው ይህን ዓለም ፈጠሩ አከናወኑ የፍጥረቱንም መፈጸሚያ ጉልላት ሰውን አደረጉ።



www.ethiopianorthodox.org

# ክ ፍ ል ፬

# ፍጥረተ ዓለም በጠቅላላው፣

## ም ዕ ራ ፍ ፩

## እግዚአብሔር በፍጥረቱ፣

ኃያሉ አምላክ ከፍጹም ኃይሉ እና ጥበቡ የተነሣ ይህን ዓለም አከናውኖ ፈጠረ፣ ሊቀ ነቢያት ሙሴ የሥነ ፍጥረትን ጉዞ በሚናገርበት ጊዜ የተጠቀመበት ቃል «ገብረ» የሚለው ነው፣ ይህንም «በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ» ሲል ተናግሯል::[1]

ገብረ የሚለው ቃል ባራዕ ከሚለው ከዕብራይስጡ ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው:: ይኸውም አደረገ፣ ሠራ፣ አከናወነ፣ መልክ ሰጠ፣ አበጀ ማለት ነው:: አንዳንዶቹ ይኸንኑ የቃል ትርጉም ይዘው አበጀ ማለት ፈጠረ ማለት አይደለም የነበረውን አበጀ አሳመረ ማለት ነው የሚል አስተያየትን ያቀርባሉ:: አበጀ ማለትም ቀድሞ የነበረውን አከናወነ፣ መልክ ሰጠ ማለት ነው፣ ፈጠረ ማለት ግን ያልነበረውን አስገኘ ካለመኖር ወደመኖር አመጣው ማለት ነው::

ይሁን እንጅ እግዚአብሔር አምላክ ፈጣሪ እንጅ ፍጡር ስለአይደለ የሆነውን የተፈጠረውንም ሁሉ ካልነበረበት አምጥቶ እርሱው ፈጠረው እንጂ የነበረውን የሆነውን አበጀ ማለት አይደለም፣ ከዚያ በፊት ሁኖ የተገኘ ነገር የለምና:: ስለዚህ ይኸን ዓለም እመ-ነበ አልቦ ኀበ ቦ፣ ማለት ካለመኖር ወደመኖር ካለመታየት ወደ መታየት አምጥቶ ፈጠረው:: በዚህ መልክ ገብረ የሚለውን ቃል ፈጠረ፣ አስገኘ፣ አወጣ ብለን እንተረጉማለን፣ ይህም እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ. አምጥቶ እግዚአብሔር መፍጠሩን ያስረዳል፣ ያረጋግጣልም:: ይኸንም የዓለም መፈጠር ትምህርትን ማመንና መናገር ከቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ውስጥ ከፍተኛውን ምዕራፍ ይዞ ይገኛል፣ ምክንያቱም የሁሉ መነሻ መሠረቱ የእግዚአብሔር





ፈጣሪነትን የዓለሙንም መፈጠር ማመን ነውና:: ከዚያ በኋላ ግን እርሱ የፈጠረው ዓለም ምንም ቢበድለው ለመታረቅና ይቅርም ለማለት ልጁን ኢየሱስን ወደዓለም እንደላከው፣ የዓለምም ድህነት ከልጁ መስዋዕትነት የተነሣ እንደሆነ እና ከዚያ በኋላ የተፈጸመውን የቸርነቱን ሥራ ሁሉ በዚሁ መሠረትነት ልንከታተል እንችላለን::

ዓለም በራሱ በፈቃዱም የሆነ እና የተገኘም አይደለም፣ እንዲሁም ዓለም አሁን እንዳለ ጸንቶ የሚኖር አይደለም:: ከእግዚአብሔር ፍጹም ጥበብ የተነሣ ዓለም የተፈጠረ፣ የተገኘ፣ የሆነም ነው እንጅ፤ ማለት ከእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድና ኃይል የተነሣ የተፈጠረ ነው:: ስለዚህ አሁንም በእርሱ ጠ ባቂነት፣ መጋቢነት ይመራል፣ ይንቀሳቀሳልም::

እግዚአብሔር በሦስትነቱ ነበር፣ ስለዚህም ባለመለያየት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአንድነት ዓለምን ፈጠሩ:: በመለኮት በፈጣሪነት አንድ ስለሆኑ አምላክ በአንድነቱ ዓለምን ፈጠረ፣ አከናወነ:: ይህንም ሐዋርያው ጳውሎስ «ሁሉ ከእርሱ ነው፣ በእርሱም ነውና፣ ወደርሱም ነው፣ ለእርሱም ምስጋና ይገባዋል፣ ለዘለዓለም አሜን» ሲል ይገልጥልናል::[2]

ዓለም በእግዚአብሔር ፈጣሪነት እንደተፈጠረ ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረው እንደሚከተለው ይገልጣሉ፣ ነቢዩ ዳዊት «ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ» ሲል ሰማይንና ምድርን የፈጠረ እርሱ እንደሆነ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ፈጣሪነት ገልጦ መስክሯል::[3] ነቢዩ ኢሳይያስ «ሰማያትን የፈጠረ ምድርንና በውስጧ ያለውን ያጸና፣ በእርሷም ላይ ለሚኖር ሕዝብ እስትንፋስን፣ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር ነው» ሲል እውነተኛ ምስክርነቱን ሰጥቷል::[4] እንደገናም ነቢዩ ዳዊት «ሰማያትን በጥበቡ የሠራ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና:: ብቻውን ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ ምሕረቱ ለዘለዓለምነውና» ሲል ይናገራል::[5]

እንደገናም ይኸው ነቢይ «ተስፋው በአምላኩ በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው፣ እርሱም ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእርሱ ውስጥ ያለውንም ሁሉ የፈጠረ» ሲል



www.ethiopianorthodox.org

ግልጥ አድርጎ የሁሉ ፈጣሪ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈጣሪነቱን ተናገረ::[6]

ሐዋርያትም ያወቁትንና የተረዱትን ምሥጢር በመግለጥ በጸሎታቸው እንዲህ ሲሉ መስክረዋል፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእርሱ የሚኖረውንም ሁሉ ፈጠርከ»::[7] ዮሐንስም የመላእክን ምስክርነት የሰማውን ቃል እንደሚከተለው ይገልጥልናል «ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃል፣ በአንተ ፈቃድም ሁኗልና ተፈጥሯልምና፣ ስለዚህ ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል»::[8]

ዓለም ከእግዚአብሔር ፍጹም ጥበብ እና ፈጣሪነት የተነሣ እንደተገኘ፣ በእግዚአብሔርም ፈጣሪነት እንደተፈጠረ በክርስቲያናዊ ማኅበር ውስጥ መናገር መደጋገም ይሆናል፣ ምክንያቱም ክርስቲያኑ ሕዝብ ይህንኑ አምኖ የተቀበለ አጽንቶም የያዘና የጠበቀ ነውና:: ዘመናዊ አስተሳሰብን ተከትሎ ቁሳዊ አካል ያለ ፈጣሪ የተገኘ፣ ከዘመንም በኋላ መልክን የያዘ፣ ሕይወትንም ያገኘ ነው በማለት ከሚናገሩት ባለቤትነት ከሌለው አስተያየት ቤተ ክርስቲያን ትለያለች፣ ምክንያቱም ያለ እግዚአብሔር ፈጣሪነት የሆነ፣ የሚሆንም፣ የተገኘም ነገር ከቶ የለምና:: ቁስአካልም ቢሆን ለመገኘት ፈጣሪ ያሻዋል፣ ለእርሱም መገኛ ምክንያት ያሻዋልና::

ጥንታዊ (ፕላቶናዊ) አስተሳሰብ ለዓለም ሁለት መነሻዎች በየዘመናቱ መካከል እንደነበሩ ያመለክታል፣ ይኸውም አንደኛ እግዚአብሔር ሲሆን ሁለተኛው ቁስ አካል የሚባለው ነው:: በዚህም አስተያየት እግዚአብሔር የነበረውን ቁስ አካል መልክ ሰጥቶ ቅርጽ አውጥቶ አቀረበው እንጂ እም'ነበ አልቦ መፍጠሩን አልፎታል:: የክርስትናው ትምህርት ግን ይህን አስተሳሰብ ፈጽሞ ውድቅ አድርጎ፣ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ተቀብሎ ከዚህ በሚከተለው በአራት የፍጥረት ደረጃ ይመድበዋል::

ይህም አንደኛ ከእግዚአብሔር እም'ነበ አልቦ 'ነበ ቦ ፍጥረት ሁሉ መፈጠሩን፣ ሁለተኛ ዓለም በዘመን መፈጠሯን፣ ሦስተኛም ዓለም ለአንድ ለሆነ ዓላማ በሆነም ምክንያት መፈጠ



www.ethiopianorthodox.org



ሯን፣ አራተኛም የፍጥረትን ክንውን ዘርዝሮ በማስረዳት ነው:: አሁን እኛ በእነዚህ አርዕስት ጠቅላላ ሥነ ፍጥረትን እንደሚከተለው እንመረምራለን::

## ፩. ፍጥረት እም'ነበ አልቦ 'ነበ ቦ፣

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከአለመኖር ወደ መኖር፣ ከአለመሆን ወደ መሆን አምጥቶ ፈጠረው፣ ይኸም ማለት ጥንት ከነበረው ቁስ እንደሚባለው ሳይሆን አምላክ በፍጹም ኃይሉና ጥበቡ ከአለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ፈጠረው::[9] ለዚህም ፍጥረት ቅርጽ ሰጠው፣ መልክም አወጣለት፣ ይህም ማለት ጥንት ያልነበረውን ወይም ጥንትነት የሌለውን ግብር አምጥቶ ፈጠረ ማለት ነው:: ከዚህ በኋላ ግን መልክ ቅርጽ ሰጠው፣ ወሰን ደንበር አበጀለት፣ ከዚህ በኋላ ሁሉን ግብር እምግብር ፈጠረው:: የፍጥረቱም ጉዞ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛ፣ ከትንሹ ወደ ፍጹም በማምራት ነው:: ለሁሉም ገዥና አስተዳዳሪ አድርጎ እስከፈጠረውና እስከሾመው እስከ ሰው ልጅ ፍጥረት ድረስ ዓለምን በ፮ ቀን ፈጸመው፣ የፍጥረቱም ሁሉ ራስ (ጉልላት) ሰውን አደረገ::[10]

ሁሉን ለማድረግ በሚቻለው ባሕርዩ የፍጥረት ሁሉ መነሻ የሆነውን ግብር ቁስ አካል) ከአለመሆን ወደመሆን፣ ከአለ-መኖር ወደ-መኖር አምጥቶ ፈጠረው፣ ይኸውም አምላክ የሁሉ ፈጣሪ እንደመሆኑ እንደጥበቡ ፈጠረው እንጅ ከነበረውና ከሆነው ግብር አለመሥራቱን ያመለክታል:: ከርሱ በፊት ከቶ የሆነ ፣ የነበረ የለም ነበርና፣ ስለዚህም «ምድርን በመሠረትኩኝ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርከ እውቀት ታውቅ እንደሆነ ንገረኝ» ሲል ያስረዳናል::[11] አምላክ እም'ነበ አልቦ አምጥቶ ምድርን መሥርቷል ስለዚህ፣ ምድርን በመሠረትኩኝ ጊዜ አንተ የት ነበርከ ሲል ባለቤትነቱን፣ ፈጣሪነቱን ገልጦ ልዑል እግዚአብሔር ተናግሯል:: እንዲሁም አምላክ ከነፃ ሠራተኝነቱ፣ ፈጣሪነቱ የተነሣ መጨነቅ መድከም ሳይኖርበት ሁሉንም በቃሉ «ለይኩን» ብሎ በተናገረ ጊዜ ማነኛውም ፍጥረት ሁሉ ሆኖ ተሠርቶ ተፈጥሮ መገኘቱን ሐዋርያው ጳውሎስ «በሃይማኖት እናውቃለን ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ከማይታየውም ነገር የሚታየው

እንደሆነ» ሲል እግዚአብሔር ዓለምን እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ አምጥቶ እንደፈጠረ ያስረዳል::[12] እንዲሁም ያልነበረውን ወደመኖር ያልሆነውን ወደመሆን አምጥቶ መፍጠሩን ይኸው ሐዋርያ እንደገና ሲያወሳ «በአመንበት በእግዚአብሔር ፊት ሙታንን የሚያስነሣ፣ ያልነበረውን እንደነበር የሚጠራ» ሲል ያስረዳል::[13]

በመጀመሪያ ዓለም ሲፈጠር በጠቅላላ መልክና ቅርፅ ያልነበረውን መሆኑን ባዶም እንደነበረ፣ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሰፊው ይነግረናል::[14] አምላክ ከጥበበኞች በሚበልጥ ጥበቡ ሁሉንም ከአለመኖር ወደ መኖር አመጣው፣ የአምላክነቱም ኃይል ይህንን ሊያደርግ ቻለ፣ ምክንያቱም አንድ ነገር ፈጣሪና ባለቤት ከሌለው ምንም ሊገኝ ባልቻለም ነበርና:: ለፍጥረት ሁሉ ምክንያት የሚሆነውን ግብር ግን እግዚአብሔር በመጀመሪያ አመጣው፤ ይህም ሊቀበሉት የሚገባ እውነት ነው:: ያም ግብር ለሌሎች ፍጥረታት መነሻ ሆኗል፣ ማለት ግብር እምግብር ለሚፈጠሩት ሁሉ ምክንያት ሆነዋል:: የመጀመሪያውን ግብር አምላክ በጥበቡ አስገኘው እንጂ በዕድሉ እንዲሁ የተገኘ አይደለም፣ ከምንም ምን ሊገኝ አይችልምና:: ለዓለም መገኘት፣ ለዓለም ፍጥረት ምክንያት ወይም መገኛው እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ሌላ መነሻ ምክንያት የለውም፣ ምክንያቱም እርሱ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነውና:: ስለዚህም ከፍጹም ጥበቡ ከፍጹም ኃይሉ የተገኘ ይህን ዓለም ከአለመኖር ወደመኖር አመጣው፣ የፈቀደውንም ያህል በፈቀደውም ዓይነትና መልክ ፈጠረ::

፪. <u>ፍጥረት በዘመን፣</u>

የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት የቅዱሳት መጻሕፍትም አስረጅነት እንደሚነግረን ዓለም የተፈጠረው በዘመን ነው:: እግዚአብሔር ብቻ ፈጣሪ እንደመሆኑ፣ ከዘመናት በፊት ወይም ውጭ ነበር፣ ግን ሁሉን የፈጠረ በዘመን ነው:: ዓለም በዘመን እንደ መፈጠሩ ዘመንም ከዓለም ጋር የተገኘ የተቆጠረ ነው:: ዘመኑ በዓለም ታወቀ፣ ዓለሙም በዘመን ተለካ፣ ተቆጠረም:: የዓለም ፍጥረትም የእግዚአብሔር





ውሳኔ ነው ማለት ቀድሞ አምላክ ያቀደውን ሲሠራ ዘመን ተቆጠረ እርሱ ግን ቀዳማዊ አምላክ ነው:: ይህንንም ነቢዩ ዳዊት «ተራሮች ሳይወለዱ ምድርና ዓለም ሳይፈጠሩ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ አንተ አምላክ ነህ» ሲል ያስረዳል::[15] መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱ ሲያስተምር አምላክ ከዘመናት በፊት እንደነበረና ዓለም በዘመን እንዲለካ እንዲቆጠርም «አሁንም አመስግነኝ፣ አንተ አባት ሆይ በአንተ ዘንድ ከጥንት ወደ አንተ ዘንድ በነበረች ምስጋና ዓለም ሳይፈጠር» በማለት አስረድቷል::[16] ሊቀነቢያት ሙሴም የዓለምን ተፈጥሮ ሲጀምር በቁጥር በስፍር በዘመን እንደሆነ እንዲህ ሲል ይነግረናል «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»::[17] ይህም የዘመን መቁጠሪያ መጀመሪያ መሆኑን ያመለክታል፣ ምን አልባት የራቀውን ያህል ቢርቅ በስፍርም በቁጥርም ጠቢባን ሁሉ እያንዳንዳቸው ቢለያዩም ዓለም በዘመን መፈጠርዋን ማንም አልካደም::

ስለዚህ፣ ዓለም ከዘመናት በፊት በነበረው አምላክ በዘመን መፈጠሩን፣ ዓለምም ራሷ የእርሱ የጥበቡ ውጤት መሆኗን ይመሰክራሉ:: የዓለም መፈጠር የዓለም ወደመኖር መጠራት ነው፣ ይኸውም አምላክ ምንም ግዴታ ሳይኖርበት፣ ድካምም ሳይሰማው ከፍጹም ኃይሉና ከፍጹም ጥበቡ የተነሣ መፍጠሩን ይኸን የተከናወነ ዓለም በትክክል መመልከት ነው::

ዓለም በዘመን እንደተፈጠረ፤ በመጨረሻም ጊዜ ዓለም ከዘመኑ ጋር ያልፋል፣ ከዚያ በኋላ ዓለም እንዲሁም ዘመን ፈጽመው አይገኙም:: ዓለም ከዘለዓለማዊው አምላክ ጥበብ የተነሣ ተገኘች እንጂ እርሷ ዘለዓለማዊት አይደለችም፣ ፈጣሪዋ እግዚአብሔር ግን ከዘመናት በፊት ነበር፣ በዘመናትም መካከል አሁን አለ፣ በኋላም ዘመናትንና ዓለምን አሳልፎ ለሁል ጊዜ ይኖራል:: ከዘመናት በፊት አምላክ እንደመኖሩ ቅዱስ ሐሳቡና ምክሩ ዓለምን ለመፍጠር መወሰኑ ጥንታዊ ቀዳማዊ ሊሆን ይችላል፣ ግን ዓለም የዚህ ቅዱስ ሐሳብ የዚህም ጥንታዊ ጥበብ ውጤት እንጂ ቀዳማዊ አለመሆኑን ነቢዩ ዳዊት «ወኩሎ በጥበብ ገበርከ» ሲል አስረድቷል::[18]



www.ethiopianorthodox.org

## ፫. የዓለም መፈጠር ምክንያትና ግቡ፣

ዓለም በእግዚአብሔር ፍጹም ጥበብ የተፈጠረ እንጅ እንዲሁ በዕድሉ የተገኘ፣ ወይም በአንድ ሌላ ጌታ የሆነ አይደለም፣ ስለዚህ ለአንድ የተቀደሰ ዓላማ የተፈጠረ ስለሆነ መነሻው ምክንያትና መድረሻው ግቡ አንድ ሊሆን ይችላል:: ዓለምን አምላክ ስለ ፫ ነገር ፈጥሮታል፤

1ኛ. ከሃሊነቱን ለመግለጥ፣ ማለት ሁሉን ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ መፍጠር ከፍተኛ ችሎታ ነው፤ ይኸንም ከእርሱ በቀር የቻለ የለምና:: ይኸነንም መጻሕፍት ተባብረው ደግፈውት እናገኛለን::[20]

2ኛ. ቸርነቱን ለመግለጥ፣ ማለት የፈጠረውን ሁሉ በትክክል መመገብ፣ ማስተዳደር፤ ሁሉን በትክክል መመልከት ቸርነት ነውና::[20] በእግዚአብሔር ዘንድ ትንሽ ትልቅ የለም፤ ሁሉም በርሱ ዘንድ አንድ ነውና፣ ትክክልም ነውና ተረስቶትም የሚቀር ከቶ የለምና::

3ኛ. ባለጸጋነቱን ለመግለጥ፣ ሁሉ የርሱ፤ ሁሉም ለርሱ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: የሁሉ ገዥ የሁሉም ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ ነውና:: በዚህ ዓላማ ለዚህም ግብ ሲል ዓለምን አከናውኖ አምላክ ፈጥሯል:: አምላክ ምንም ዓይነት ግዴታ የሌለበት ሲሆን በፍጹም ጥበቡና ነፃነቱ የሠራው ዓለም ይኸ የተከናወነው ነው::

እግዚአብሔር ዓለምን ለመፍጠር የተገደደበት ወይም የጎደለው ነገር ኑሮ ያንን ለመሙላት ሲል ከችግሩ የተነሣ የፈጠረው አይደለም፤ ከምሕረቱ ከቸርነቱ የተነሣ ፍጥረቱ ሁሉ ይገኝ ዘንድ ወደደ፣ ስለዚህም የተፈጠረው ሁሉ የክብሩ መግለጫ የስሙም ቀዳሽ ይሆን ዘንድ አደለው፤ ምክንያቱም ለፍጥረቱ ሁሉ ዓላማ ይኖረው ዘንድ ፈቀደ፣ ከዚህም ዓላማ የተነሣ የእግዚአብሔር ፍጥረት ግዕዛኑን፣ መጠኑን ዓይነቱን ጠብቆ እንዲኖር፣ እንደየ ግዕዛኑም ለእርሱ ምሥጋና እንዲያቀርብ አድርጎ ፈጠረው::





ሁሉም ለተቀደሰ ዓላማ እንደተፈጠረ፣ ማለት ለምሥጋና ለክብሩ መታወቂያ እንደተፈጠረ ቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው እንዲህ ሲል ይመሰክራል «ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር ወግብረ እደዊሁ ያየድዓ ሰማያት» ሲል ነቢዩ ዳዊት እውነተኛ ምስክርነቱን ሰጥቷል::[21]

ነቢዩ ዳንኤልም «ይባርክዎ ኩሎ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር» ሲል ተናግሯል::[22] መላእክትም ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ለሕፃኑ ክርስቶስ እጅ መንሻ አድርገው ያቀረቡት ምሥጋና ነው፣ እንዲህ ሲሉ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት፣ ወሰላም በምድር፣ ሥምረቱ ለሰብእ»::[23] በዚህም መግለጫ መሠረት የመላእክት ሥራቸው የተፈጠሩበትም ዓላማ ምስጋና መሆኑን ያመለክታል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በርሱ ፈጣሪነት፣ ለርሱም አገልግሎትና ክብር፣ ለተቀደሰም ዓላማ እንደተፈጠረ፣ ሁሉም ለርሱ ምሥጋና ሊያቀርብ እንደሚገባው ሲገልጥ «ሁሉም ከርሱ ነውና ወደርሱም ነው:: ለርሱም ምሥጋና ይገባዋል ለዘለዓለም አሜን» ሲል በሰፊው ያስረዳናል::[24]

ከዚህ ሁሉ ፍጥረት ሰው ተለይቶ የነባቢነት፣ የለባዊነት፣ የሕያውነት ባሕርይ ስላለው የስሙ ቀዳሽ የክብሩም ወራሽ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በዓርአያውና በምሳሌው ፈጠረው፤ እንዲሁም ሌላውን ፍጥረት ሁሉ ለሰው አገልግሎት፣ ለሰውም ጥቅም ሲል እንደፈጠረው እንረዳለን::[25] ሰውን ግን ለርሱ ስም ቀዳሽ ለርስቱና ለክብሩ ወራሽ እንዲሆን ዘለዓለማዊም እንዲሆን አድርጎ ፈጥሮታል:: እያንዳንዱም የሰው ልጅ በተፈጥሮ ነፃ እንደመሆኑ ለዚህ ለተፈጠረበት ዓላማ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ግዴታው ይሆናል::

ለሰውም ይኸነን የማወቅ ዕድል ወይም ኃይል ከመሠረቱ ተሰጥቶታል፣ ስለዚህ ይኸን ያውቃል፣ ይኸነንም ሁሉ ማወቁን ሐዋርያው ጳውሎስ «እግዚአብሔርን ማወቅ ተገልጦላቸዋልና፣ እግዚአብሔር እርሱ ገልጦላቸዋልና» ሲል ያስረዳናል::[26] በዚሁ ዓላማ በዚሁም መነሻነት እግዚአብሔር ይህን ዓለም ፈጠረ፣ አንድ ጊዜም ወስኖ አከናውኖም የፈጠረው ዓለም በተፈጠረበት ዓላማ ጸንቶ ይገኛል::



www.ethiopianorthodox.org

አምላክም የፈቀደውን ያህል ፈጠረ እንጂ እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ የጠየቀውና ያስገደደው የለም፣ ወይም ሳይፈጥረው ቀርቶ የጎደለበት ነገር የለም:: ለመፍጠር የፈቀደውን ያህል ፈጠረ፣ ፈቃዱ ወሰነው «ኲሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር» ሲል ነቢዩ ዳዊት ያስረዳናል::[27]

፬. <u>የፍጥረቱ ክንውን፣</u>

እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አገላለጥ መሠረት ዓለም የስድስት ቀናት ፍጥረት ናት:: ይኽነንም ቤተ ክርስቲያን አጉልታ አጽድቃም ታስተምራለች፣ ይህም ማለት አምላክ በቸርነቱ ይኽን ዓለም ካለመኖር ወደመኖር የመጀመሪያውን ግብር ካወጣ በኋላ እያንዳንዱን ፍጥረት ለይኩን እያለ እርሱ በወደደው መሠረት ግብር እምግብር እንዲፈጠር አድርጎታል:: ይኸም የፍጥረት ጉዞ ከታች ወደላይ፣ እንዲሁም ቅርጽ መልክ ካለመኖሩ ወደፍጹምነት፣ ከትንሽ ወደትልቅ በመሄድ እግዚአብሔር ሁሉንም በስድስት ቀን ፈጥሮ አስተካክሎ አቀረበ:: በመጀመሪያው የፍጥረት ሁሉ ምክንያት የሚሆነውን ግብር ፈጠረ ከዚህ በኋላ ሁሉም የቃሉ ፍጥረት ነው:: ለይኩን ባለጊዜ እየሆነ እየተፈጠረም እየተሠራም ተገኝቷል:: በዘፍጥረት እንደምንረዳው «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ካለ በኋላ እስከ ሰው ተፈጥሮ ያለውን ተራ በተራ የፍጥረቱን ዝርዝር ይናገራል:: ከዚያ በኋላ፣ ከፈጠረው ግብር አገናኝቶ ሰውን በእጁ ቀረጸው መልክም አወጣለት፣ ስለዚህም ሰው የእጁ ሥራ ይባላል «እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ፈጠረው፣ መሬት ከምድር፣ ባፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፣ ሰውም ሕይወት ያለበት ነፍስ ሆነ»::[28] ነፍሱን ግን ካለመኖር ፈጥሮ አምጥቶ አሳድሮበታል፣ ስለዚህ ሰው የተለያዩ ጠባያት ያለበት ልዩ ፍጥረት ሁኖ ይገኛል::

ይህን ዓለም ቅርጽ መልክ ሰጥቶ ካለመኖር ወደመኖር ወደፍጹምነት፣ ወደ መታየት ያመጣው መጀመሪያ መነሻ አድርጎ ከፈጠረው ግብር ከምድር እንጂ ጥንት ከነበረው ግብር ላይ ያሻሻለው ያነንም የለወጠው መልክ የሰጠው አይደለም፣ ለዓለም ጥንትነት የለውምና::





ዓለም መጀመሪያ መገኘቱ፤ ቀጥሎም መሻሻሉ፣ ለውጥ ማግኘቱም፣ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ሠራተኛነትም በነዚህ በስድስት ቀናት በተፈጸመው ሁኔታ እንጂ ከመቆየቱ ከመኖሩም የተነሣ ግብሩ በራሱ ለውጥ ያደረገ አይደለም፣ በዚህ መልክ እንደተፈጸመ አድርጎ ዳርዊን የተባለው ሰው እንደተናገረው አይደለም፣ አስተያየቱን ቤተ ክርስቲያን ፈጽማ አትቀበለውምና::

የመጀመሪያውን ግብር ለፍጥረት ሁሉ ምክንያት የሆነውን ያስገኘ፣ የፈጠረውም እግዚአብሔር ነው፣ ያንንም ያሳመረና፣ መልክ የሰጠ፣ እንደየ ግዕዛኑና እንደየ መጠኑ እንዲገኝ፣ ይሆንም ዘንድ በየዕለቱ እየሠራ፣ መልካም እንደሆነ፤ እያየ በመልካም ሥራውም እየተደሰተ የፈጸመው እርሱው ጥበበኛው እግዚአብሔር ነው::[29]

ልሁል አምላክ የፍጥረቱን ሥራ ከፈጸመ በኋላ ዕረፍት አደረገ ሲል ሙሴ የሚናገረው፣

1. እግዚአብሔር ደክሞት ኑሮ አርፎ ቆይቶ እንደገና ፈጠረ ለማለት አይደለም::
2. ለማሰቢያና ለውጥም ለማድረጊያ፣ ለማሻሻያ ዕረፍት ዐድርጎ ወይም ሥራውን አቋርጦ ቆይቶ በኋላ ቀጠለ ለማለትም አይደለም:: ሥራውን በዕርግጥ በ6 ቀናት ውስጥ አከናውኗል፣ ፈጽሟል፣ በሰባተኛው ቀን ግን የመፍጠር ሥራውን አቁሟል:: ዐረፈ የሚለው ቃል ለሥራ መቀጠያ ሳይሆን የአምላክ ግንኙነት የማያቋርጥ ከፍጥረቱ ሁሉ የማይለይ መሆኑን ለመግለጥ ነው:: በእርግጥም እግዚአብሔር ይኽን የተከናወነ ዓለም ፈጥሮ አልጣለውም፣ አልተለየውም፣ ይመግበዋል፣ ይጠብቀዋልም ፣ግንኙነቱንም ይቀጥላል እንጂ::

፯ተኛው ቀን ዕረፍት የሚባለው በሌላ በኩል እንደ አምላክነቱ ያለአስገዳጅ ያደረገው ነው እንጂ ግዴታ ኑሮበት ያን ለመፈጸም ወይም ከላይ እንደተገለጠው ደክሞት የማረፍ



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም፣ በፈቃዱ እንደፈጠረ እንደ እርሱውም ፈቃድ ያደረገው ስለሆነ፣ ሀረፈ እንጂ ሰዎች ሠርተው በተለያዩ ምክንያቶች ሥራን እንደሚያቆሙ፣ መልሰውም እንደሚቀጥሉ አይደለም:: ደግሞ እግዚአብሔር ከፈጠረው ከ፮ ቀናት ፍጥረት ሌላ የተፈጠረ ምንም ነገር የለም፣ ስለዚህ ሊቀ ነቢያት ሙሴ «ሰማይና ምድርም ተፈጸሙ ሠራዊታቸውም ሁሉ» ሲል ከዚያ በኋላ ሌላ ፍጥረት አለመኖሩን አረጋግጦ ዘግቷል::[30]

## <u>ም ዕ ራ ፍ ፪</u>

### <u>ዓለም በጠቅላላው</u>፣

ዓለም በጠቅላላው በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ብቻ ተፈጥሯል፣ ልዑል እግዚአብሔርም ኃያል እንደመሆኑ ከማንም ርዳታ ሳይሻ፣ አዋቂም እንደመሆኑ ከማንም ምክር ሳይጠይቅ ይኸን ዓለም አከናውኖ ፈጠረ:: ለዚህም አስረጂ «በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ» ሲል ሊቀ ነቢያት ሙሴ መሰከረል፤ የፍጥረት መጀመሪያም የሆኑትን ገለጠ::[1] ይኸንም ለማስረዳት ከቤቱ ይልቅ የባለቤቱ ክብር እንደሚገለጥ «ቤትን ሁሉ አንድ ሰው ይሠራዋል፣ ሁሉን የሠራ እግዚአብሔር ነው» ሲል እውነተኛ ምስክርነቱን ሐዋርያው ጳውሎስ ሰጥቷል::[2]

እንዲሁም በሃይማኖታችን ጸሎት በመጀመሪያው አንቀጽ «ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን» ሲሉ ሃይማኖታቸው የቀና አባቶች መስክረዋል::[3] ሊቀ ነቢያት ሙሴም ዓለም በእግዚአብሔር ፈጣሪነት እንደተፈጠረ የእግዚአብሔርም ፍጥረት ሁሉ ያማረና የተወደደ እንደሆነ፣ ፈጥሮም ሲፈጽም እያንዳንዱን ወገን እግዚአብሔር እንደባረከው በሰፊው የቃል ሰንሰለቱን በማያያዝ አስረድቶናል::[4]

እግዚአብሔር ሲፈጥር ለፍጥረቱ ሁሉ ምክንያት ሳይኖረው በቃሉ ብቻ ፈጥሯል፣ «ለይኩን» ባለ ጊዜም ሁሉ ሁኗል፣ ሁሉም ተፈጥሯል:: በኋላም ዓለም ሊያልፍ የሚችለው እንደዚሁ በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው:: ዓለም ተብሎ ከተፈጠረው ከሰው ፍጥረት በኋላ ግብር እምግብር ይገኝ እንጂ





የመጀመሪያውን ግብር ያስገኘ እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ለፍጥረቱም ረዳት አንድም አስገኝ ምክንያት አልነበረም:: እስከ ዛሬ የተመረመረውና የተደረሰበት፤ ገናም ያልተመረመረና ያልታወቀ ያልታየም ሥውር ዓለም ሁሉ፤ ልዩ ልዩ ፕላኔቶች ሁሉ ቢሆኑ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ተፈጥረዋል እንጂ እንዲሁ አልተገኙም፤ ሌላ ፈጣሪም የላቸውም:: የሚታየውም፣ የማይታየውም፣ የቀረበውም፣ የራቀውም በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ተፈጥሯል::

እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ፈጥሮ ሲፈጽም ታላቁን ፍጥረት ሰውን በመጨረሻ ፈጠረው፣ አንድ ሰው ቤትን ሠርቶ የሚፈጽመው በጉልላቱ ነው፣ እንደዚሁም የፍጥረቱ ሁሉ ገዢ የፍጥረቱም ሁሉ የበላይ ጉልላት ሰው ስለሆነ፣ የፍጥረት ሁሉ ጌጥ አድርጎ ልዑል እግዚአብሔር በመጨረሻ ፈጠረው::

### ፩. <u>ሁለቱ ዓለማት</u>፣

እግዚአብሔር አምላክ በ፮ ቀናት የፈጠረው ፍጥረት በዓይነት፣ በቁጥርም ብዙ ሲሆን ሁሉንም አጠቃለን ለመቁጠር ባለመቻላችን በመኖሪያቸው ወይም በዓለማቸው በ፪ ታላላቅ ክፍል ከፍለን እንናገራለን ይኸውም በሰማይና በምድር የሚገኙ ፍጥረታት በሚል ጠቅላላ አነጋገርነው::

እግዚአብሔር አምላክ በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ሲል የተናገረው ጥንቱንም ቢሆን በዚህ ዓይነት የሁለቱን ዓለማት አኗኗር ለማስረዳት ነው፤ ማለት ሰማይ የሚለው ራሱን ሰማይንና በሰማይ የሚኖሩትን ሰማያዊያን ነገዶችን፤ ሰማያዊያን ፍጥረቶችንም የሚመለከት እንደሆነ ነው:: እንዲሁም ምድርን ሲያነሣ፤ ራሷን ምድርንና በምድር የሚገኙትን ምድራውያን ወይም ግዙፋን ፍጥረትን ሁሉ እንደሚያመለክት ያጠይቃል:: ሊቀ ነቢያት ሙሴ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ብሎ ሰማይ የሚባለው የቱ እንደሆነ፣ በሰማይም ያሉ ፍጥረቶች፣ ስንት፣ ምንና ምን እንደሆኑ ሳይናገር እንዲሁ ያልፍና ምድራዊያንን ፍጥረታት ብቻ ያነሣል፣ የነርሱንም የፍጥረት ጉዞ ይናገራል::



www.ethiopianorthodox.org

እኛም ከዚህ ላይ በ፪ አርእስት እንደመከፈላችን ስለሁለቱም ዓለማት በመጠኑ ማወቅና መናገር እንዳለብን እንገነዘባለን:: ይኸን የሥነ ፍጥረት ትምህርት በ፪ ዓይነት መክፈል ሙሴ ይጀምረው እንጂ የሃይማኖት አባቶቻችን ፫፻፲፰ ሊቃውንትም ይኸኑ ተከታትለው «ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር፣ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ» ብለው በ፪ ከፍለው ወስነው ተናግረዋል::[5] በዚህ ውሳኔ ላይ አባቶች አሁንም ለሰማይም ለምድርም ፍጥረት ምንም ዝርዝር ማስረጃ አልሰጡም፣ «ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ» ብለው አለፉት እንጂ:: ግን ሰማይንም ሲያነሱ እግረ መንገዳቸውን በውስጡ የሚገኙትን ረቂቃንና መንፈሳውያን የሆኑ ወገኖችን ሁሉ ያመለክታል፣ ማለት ከጠፈር ጀምሮ እስከ ፯ኛው ሰማይ ያለውን የፍጥረት ወገን ሁሉ ይመለከታል::

ምድርንም ባነሱ ጊዜ ምድራዊ የሆነውን ሁሉ፤ የሚታየውን ግዙፍ ሕይወትም ያለውን፤ ሕይወትም የሌለውን፤ እንስሳውንም፤ የሰው ልጅንም፤ አዝርእትን አትክልትን ዕፀዋትንም፤ በጠቅላላም ሁሉን የሚመለከት ነው፣ ማለት እነዚህ ሁሉ በምድር ውስጥ ስለ ሚገኙ ይህን ሁሉ እንደሚመለከት የታመነ ነው::

ምንም ስለ ሰማይ ነቢዩ ዳዊት «ሰማየ ሰማያት ለእግዚአብሔር» ብሎ ሰማያዊው ዓለም እግዚአብሔርን ብቻ የሚመለከት፣ እግዚአብሔርም ብቻ የሚያውቀው እንደሆነ ቢናገርም ቅዱሳት መጻሕፍትን አጋዥ በማድረግ ስለሰማይና ስለሰማያውያን ነገድ በመጠኑም ቢሆን እንነጋገራለን:: በምድር ስላሉ ፍጥረታት ግን ሙሴ ዘርዝሮ እንደ ተናገረላቸው በየዘመኑ የተነሱ ሊቃውንትም ያኑ እየተከተሉ አሟልተው አስፋፍተው ተናግረዋል፣ ጽፈዋልም::

እኛም አሁን እርሱን በመከተል በአጠቃላይ መንገድ ስንናገር ዓላማችን እግዚአብሔር ድንቅ በሆነ ሥራው እንዲመሰገን ሁሉም በትክክል እንዲረዳው ለመግለጥና ለማሳወቅ ነው::





፪. <u>የሰማይ ተፈጥሮ፣</u>

«በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ» አመላክ አስቀድሞ ሰማየ ሰማያትን ፈጠረ:: ሰማይ የእግዚአብሔር መንበር ነው፣ ስለዚህ እርሱን አስቀድሞ ፈጠረ፣ አዘጋጀ::[6] ምንም ለሰማይ የተለየ ክፍል ምዕራፍ ቢኖረውም ሰማያዊ አካልን ሰማያዊ ነገድን ሁሉ የሚይዝ ስለሆነ፣ ለምድራዊ አካል ለሰው ልጅ መመርመር ስላልተቻለ ለሰማይ ምንም ዝርዝር መግለጫ በቅዱስ መጽሐፍ የለውም::

ነቢዩ ዳዊትም «ሰማየ ሰማያት ለእግዚአብሔር፣ ምድረሰ ወሀበ ለእጓለ እመ ሕያው» ብሎ ሰማያት ለእግዚአብሔርና ለሰማያውያን ነገድ ብቻ የተሰጠ መሆኑን፤ ምድር ብቻ ለሰው ልጅ የተሰጠች መሆኗን ገልጦ ተናግሯል:: በዚሁ መሠረት ከጥንት ጀምሮ ስለ ሰማይ በተረት መልክ የሚነገር ብዙ አስተያየት፤ እንደ እምነትም ሁኖ የሚያዝ አንዳንድ ነገር ነበር፣ ይኸውም ሰማይና መሬት እንደሞሰብና እንደሞሰብ እፊያ፣ እንደወጭትና እንደ ወስከንቢያ የተያያዙ፣ የተገጣጠሙ መስሏቸው ሰማይን ከምድራዊ ድንጊያ ጋር እንደተጋጠመ አድርገው «ወአስተጣበቅዎ ዲበ ኮክሕ» እያሉ የሚያስተምሩ ነበሩ:: እንዲሁም ምድርን እንደ ግድግዳ ሰማይን እንደጣራ አድርገው ተያይዞ ተዋቅሮ እንደሚገኝ አድርገው ይናገሩ ያስተምሩ ነበር:: ግን ሰማይ ከመሬት በስንት ሺህ ማይል ርቀት እንዳለ ለመግለጥ ባለመቻላቸው ይኸንን አስተያየት ሲያቀርቡ ኑረዋል::

ከአየሩ በላይ ተንጣሎ ተዘርግቶ የሚታይ ለስፋቱ ወሰን የሌለው ማንም ሊደርስበት የማይቻል ምጡቅ፣ ሊታይም የማይቻል ሩቅ የሆነ የእግዚአብሔርን የታላቁ ፈጣሪ ኃይልና ጥበብ የሚያስረዳ ከምድራዊ ዓለም የተለየ ሰማይ የሚባል ራሱን የቻለ ዓለም አለ:: ለሰማያዊ አካል፣ ለሰማይም ሠራዊት ጠቅላላ መግለጫ የሚሆን ትምህርት በቅዱስ መጽሐፍ ጎልቶ የተሰጠ ባለመኖሩ በሊቃውንት ዘንድ የተለያየና የበዛ አስተያየት ይገኛል፣ እንዲሁም የመንፈሳዊያንና የሥጋዊያን አስተሳሰብ በጣም ተለያይቶ በጊዜያችን ይገኛል::



www.ethiopianorthodox.org

በመሠረቱ ሰማይ በነጠላ ቁጥር ብቻ ሳይሆን በብዙ ቁጥር ሰማያት ተብለው የሚነገርላቸው ናቸው:: በአንዳንድ አነጋገር ሰማይ ብንል እንኳን ሁሉን አጠቃለን በማኀበር ስም መጥራታችን እንጅ ሰማያት ብዙ ስለሆኑ በአንድ ስም ብቻ መጥራት አይቻልም:: በዕብራይስጥ ሁልጊዜ «ሸማይም» ብሎ በብዙ ቁጥር እንጅ በአንድ ቁጥር የሚናገር ቃል የለም:: በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ የሚለውን በዕብራይስጥ አሁንም በብዙ ቁጥር ሸማይም ሲል ነው የምናገኘው:: ለምን ወደ ነጠላ ቁጥር ፩ ሊቃናት እንደተረጎሙት አይታወቅም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግን በየቋንቋው በነጠላ ቁጥር ሰማይ ብሎ ይገኛል::

ይሁን እንጂ ብሉይ ኪዳንም ሐዲስ ኪዳንም ሰማይን ብዙ ጊዜ በብዙ ቁጥር ሲያቀርብልን ነው የምናገኘው፣ ለምሳሌ «ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ወግብረ እደዊሁ ያየድዓ ሰማያት»[7]:: «ሰማየ ሰማያት ለእግዚአብሔር ምድርሰ ወሀበ ለእጓለ እምሕያው::[8] ይሴብሕዎ ሰማየ ሰማያት ለእግዚአብሔር፤ ማይኒ ዘመልዕልተ ሰማያት::[9]» እያለና ይኸንም የመሰለ በመጻሕፍተ ነቢያት ሁሉ እናገኛለን::

በሐዲስ ኪዳን ውስጥም ራሱ ክርስቶስ «አቡነ ዘበሰማያት» ብሎ የሰማያት ሁሉ ባለቤትነቱን፣ ሰማያትን ሁሉ አልፎ ለሰው ልጅ አባትነቱን ገልጦ አስተምሮናል::[10] እንዲሁም «አኮ ኩሉ ዘይብለኒ እግዚአ እግዚአ ዘይበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ዘእንበለ ዘይገብር ፈቃዶ ለአቡየ ዘበሰማያት» እያለ ተናግሯል::[11] «ነስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት» ሲል እናገኘዋለን::[12] በዚህም መልክ ሌላም ብዙ ይገኛል፣ በነጠላ ቁጥር ሰማይ ከሚል ይልቅ ሰማያት የሚለው የበለጠ ቦታን ይዞ ይገኛል::

ኦርቶዶክሳዊያን አባቶችም በሃይማኖት ጸሎት ሰማይን በብዙ ቁጥር ወስነው ሰጥተውናል፣ እንዲህ ሲሉ «ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሎ ገባሬ ሰማያት ወምድር::[13]» እንግዲህ ከዕብራውያን እምነትና ትምህርት ጀምሮ ሰማይን በብዙ ቁጥር ከመጥራት በላይ ለብዛቱ ወሰን አድርገው ቁጥር ሰጥተው እናገኛለን:: እንደ ዕብራውያን





እምነትና ትምህርት ሰማያት ሰባት እነደሆኑ ይናገራሉ፣ እነርሱም ዊሎን፣ ረቂዕ፣ ሸጣቅ፣ ዝቡል፣ ሞዓ'ነ፣ ማክን፣ ዓርቦት ናቸው::[14]

በኛም የሃይማኖት ምዕላዶች ውስጥ በዚህ ዓይነት ሰባት ሰማያት እንዳሉ ይነገራል ስማቸው እንደሚከተለው ነው::

1. ኤረር፤ ብሩህ ሰማይ ነው:: እርሱም ከጠፈር በላይ የመጀመሪያው ሰማይ ነው::
2. ራማ፤ 2ኛ ሰማይ ነው::
3. ኢዮር፤ መካከለኛ ሰማይ ነው:: እነዚህ ሦስቱ የመጀመሪያዎቹ ሰማያት ዓለመ መላእክት ተብለው ይጠራሉ፣ ዓለመ መላእክትም እንደሆኑ ይታመናሉ:: እነዚህም በአንድ ላይ የተያያዙ የተገናኙ ሳይሆን አንዱ ከሌላው ከፍተኛ ርቀት ያለው ነው፣ ለምሳሌ በዘመናዊ ተሽከርካሪ ከአንደኛው ወደ ሌላው ለመሔድ ቢቻል አንድ ሽህ ዓመት እንደሚፈጅ ይነገራል:: ኢዮር የሚለው በአንዳንድ ሊቃውንት አገላለጥ ከጠፈር ጀምሮ እስከ መጨረሻ ሰማይ ያለውን ሁሉ የሚገልጥ ቃል ነው::

«ዘኢዮር መንበሩ፤ ዘዲበ ኢዮር» ሲል ይገኛልና::

4. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፤ አራተኛ ሰማይ ናት::
5. ሰማይ ውዱድ፤ አምስተኛ ሰማይ ሲሆን እንደ አንዳንዶቹ አገላለጥ የመጨረሻ ሰማይ ነው ይሉታል::
6. መንበረ መንግሥት፤ ስድስተኛዋ ሰማይ ናት:: (መንበረ ስብሐት)
7. ጽርሐ ዓርያም፤ የመጨረሻዋ ሰማይ ይኸች ናት፣ ሰባት የተባሉት እነዚህ ናቸው::[15]

እንግዲህ ይኸን ስም፣ ይኸንም ቁጥር ይኸንንም አከፋፈል አባቶች ከቀደሙት አባቶች አግኝተው እንደወሰኑት የታወቀ ነው:: ሰማይ በስሙ ብቻ ብዛት ያለው ሳይሆን ሰባት ይባል



www.ethiopianorthodox.org

እንጂ ከአንድ ቁጥር በላይ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስም እስከ ፫ተኛ ሰማይ እንደተነጠቀ፣ ገሊ.፲ ጽፎ እናገኛለን::[16] የሚያሳዝነው ግን ጳውሎስን ያህል ጸሐፊ በራእይም ቢሆን በሥጋም ቢሆን እስከ 3ተኛው ሰማይ ድረስ ሲሔድ የሰማይን ሁኔታ፣ ምንና ምን እንደሆነ ምንና ምን እንዳለበት፣ እንዲሁ ስለቁጥሩ፣ ስለስሙ ሳይገልጥልን እንዲሁ አልፎት መሔዱ ነው:: ስለሰማይ ብዙ ክፍል ልዩ ልዩ ምዕራፎች እንዳሉት ራሱ ክርስቶስ «ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ቦቱ» ሲል ተናግሯል::[17]

ይኸንም የመሰለ አገላለጥ በሌላ ቦታ እናገኛለን፣ ማለት ሰማያት የተለየ አቀማመጥ የተለየም ደረጃ ወይም ማዕረግ ኑሯቸው ለቅዱሳን ሁሉ ተዘጋጅተው እንዳሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል «ንዑ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት ዘአስተዳለወ ለክሙ እምፍጥረተ ዓለም::[18]» ሲል ሰማያት ብዙዎች መሆናቸውንና እነርሱም ለቅዱሳን መዘጋጀታቸውን በሰፊው ይገልጣል:: እንዲህም ከፍጥረታት በፊት ሰማያት መፈጠራቸውን መዘጋጀታቸውን ሙሴ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ካለው ጋር ይኸ አምላካዊ ቃል ይተባበራል::

ስለሰማያት ከዚህ የበለጠ አገላለጥ ሊሰጥ አልተቻለም፣ ምክንያቱም ሰማያዊ ዓለም ረቂቅ አንድም መንፈሳዊ ዓለም ስለሆነ ሥጋዊና ደማዊ ሰው ሊያውቅ ስለ አልቻለ ነው:: እንዲሁም መንበረ እግዚአብሔርም ስለሆነ ማንም ሊያውቅ ስለርሱም ሊራቀቅ የቻለ የለምና:: እንዲሁም ነቢዩ ዳዊት «ሰማየ ሰማያት ለእግዚአብሔር» ብሎ ስለሰማይ ማንም ሊያውቅ አለመቻሉን ገልጦ በመናገር ዘግቶታል፤ ስለዚሁ እኛም በዚሁ እንወስናለን ግን ከሰማይ ጋር የተያያዙ ወይም የተገናኙ መስለው ስለሚታዩ ሰማያውያን አካላት በመጠኑ ልንናገር እንወዳለን::

ሀ. <u>ፀሐይ</u>፣

መዓልቱንና ሌሊቱን የሚለይ ለምድርና ለጨረቃ ብርሃንን የሚሰጥ ትልቁን የብርሃን ምንጭ ፀሐይን የፈጠረ





እግዚአብሔር ነው፣ እርሱም በመዓልት ይሰለጥን ዘንድ አዘዘው::[19]

ፀሐይ የኛ ፕላኔቶች ሁሉ ራስ ወይም ማዕከል ነው፣ ማለት ከእርሷ የተነሣ ሁሉም ዑደት ያደርጋሉና:: ፀሐይ በኛ አካባቢ ከሚኖሩት አካላት (ፕላኔቶች) በጣም ከፍተኛው ነው፣ ምድርን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ጊዜ የሚበልጥ እንደሆነ ይገመታል:: ፀሐይ ከመሬት በጣም የራቀ ስለሆነ በማኸል እጅ የሚያዝ አንድ እንክብል ነገር መስሎ ይታያል፣ ግን ፀሐይ ከኛ ዓለም ከምድር በጣም የራቀ ሁኖ ሳለ ብርሃኑ አንጸባርቆ፣ ደምቆ፣ ሙቀቱም አቃጥሎ ይገኛል:: ፀሐይ ከምን እንደተሠራ በውስጡም ምንና ምን እንዳለ ለማወቅ እስካሁን አልተቻለም፣ ምክንያቱም የሚያቃጥል ከመሆኑ የተነሣ፤ ጨረሩም ኃይለኛ ስለሆነ፣ ለምርምር ዕድል አልሰጠም፣ ሆኖም የዘመኑ ሊቃውንት በዘመናዊ መሣሪያ እየመረመሩ የተለያየ አስተያየትን መስጠት ጀምረዋል::

አምላክ የፈጠረው ፀሐይ ይኸን ያህል የሚያንፀባርቅ የሚያቃጥልም ሆኖ ለምርምር ዕድል ያልሰጠ ከሆነ፣ የእሱ ፈጣሪ የሆነውን ብዙ ሚሊዮን ጊዜ የሚያንፀባርቀውን የሚያቃጥለውን አምላክ ማን ሊያውቀው ማንስ ሊመረምረውና ሊደርስበትስ ይችላል?፣ አምላክም በምርምር ካልተገኘና ካልተደረሰበት ተብሎ ደግሞ የለም ሊሉት አይገባም:: ይኸን ሁሉ የራቀም የረቀቀም ዓለምን የፈጠረ አምላክን በሃይማኖት ብቻ ማየት በጸሎትም ብቻ ማነጋገር በቂ ነው::

ፀሐይ በኛ ዓለም ለሚገኙት ፕላኔቶች ሁሉ ማዕከል ነው ብለናል፣ ስለዚህ እርሱ ዑደት ባደረገ ጊዜ ሁሉም አቅጣጫውን እንደጠበቁ መስመራቸውንም እንደያዙ ሰማያዊያን አካላት ሁሉ ያጅቧታል:: ሁሉም ከርሷ ሙቀትን፣ ብርሃንንም ያገኛሉ፣ ከነዚህም ፕላኔቶች ውስጥ አንደኛዋ የኛ ዓለም የሆነችው ምድር ናት:: ከፀሐይ ሙቀት የተነሣ የውቅያኖስ ባሕር እንፋሎት ያወጣል፣ እርሱም ወደ አየር ተኖ ወጥቶ ከቀዘቀዘ በኋላ ዝናብ ይሆናል:: ከፀሐይ ሙቀትና ብርሃን የተነሣ አዝርእት አትክልት በጠቅላላውም እፀዋት ሁሉ ሕይወትን ያገኛሉ::



www.ethiopianorthodox.org

ሌላው ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ፍጥረት ሁሉ ምግብን ሕይወትን ከፀሐይ ብርሃን እንዲያገኝ ልዑል እግዚአብሔር አደለው:: አምላክ ከጥበቡ ብዛት የተነሣ ከፍተኛውን ብርሃን ሰጭ አካል ፀሐይን ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ነው የፈጠረው፣ ማለት ለዚህ ለኛ ዓለም እንዲደምቅ እንዲሞቅ፣ ብርሃንንም ሕይወትንም እንዲሰጥ ነው:: ከዚህ ሁሉ ጥቅሟ የተነሣ ፀሐይን የጥንት ሕዝቦች አምላክ ነው ብለው ያመልኳት ነበር፣ እልፍ ብሎ ግን እርሷን የፈጠረ እውነተኛውን አምላክ ያገኙ ነበር:: ፀሐይ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ተግባሩን ያለማቋረጥ ይፈጽማል፣ ምንም በሙቀታቸው በብርሃንነታቸው የፀሐይን ያህል ባያሞቁ ባያደምቁም፣ የፀሐይ ሠራዊት በመሆን እርሷን ተከትለው መሥመራቸውን ይዘው ዑደት የሚያደርጉ ሰማያዊያን አካላት ብዙዎች ናቸው፣ ከነርሱም ውስጥ ፀሐይን መስሎ ፀሐይን ተከትሎ የሚሠራ ጨረቃ ነው፣ ስለርሱም እንደሚከተለው እንመልከት፣

፪. <u>ወ ር ኀ</u>፣

በሕዝብ ዘንድ ጨረቃ እየተባለች የምትጠራው ፕላኔት በቤተ ክርስቲያን ልሳን ግን ወርኅ ተብላ ትጠራለች፣ እርሷም አምላክ ለብርሃን መገኛ ትሆን ዘንድ የፈጠራት ናት:: ይኸችም ሰማያዊት አካል በጥንት ዘመን ወር የሚቆጠረው፣ በዐላቱና አጽዋማቱ የሚወጣው በዚህችው በጨረቃ አቆጣጠር ስለነበር በወርኅ ስም ልትጠራ ትችላለች::

ጨረቃ ከ፯ቱ ዐበይት ከዋክብት አንደኛዋ እንደሆነች ቤተ ክርስቲያናችን ትናገራለች በዘመኑ አስተሳሰብ ደግሞ ከዚህ አስተያየት ብዙ ያልራቀ ከዘጠኙ ፕላኔቶች ውስጥ አንደኛዋ እንደሆነች ይነገርላታል:: ጨረቃ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አገላለጥ ከታላላቆች ብርሃናት ውስጥ ሁለተኛውን ቦታ የያዘችና በሌሊት እንድትሠለጥን አድርጎ እግዚአብሔር እንደፈጠራት ይነግረናል::[20] ጨረቃ ራሷን ችላ የብርሃን መገኛ ሁና እንደተፈጠረች ቅዱስ መጽሐፍ ቢነግረነም እንደሊቃውንቱ አስተሳሰብ ከፀሐይ ብርሃን ከ፯ አንድ እጅ እንደምትወስድ ይነገራል፣ በዘመናዊው አስተሳሰብም ጨረቃ ብርሃኗን ከፀሐይ እንደምታገኝ ታምኗል::





ጨረቃ ሁል ጊዜ ካለመታየቷ የተነሣ ለሥራ የወጣ ፕሮግራም የለም እንጅ በወጣች ጊዜ ብዙ ለማሠራት የሚችል የተለየ ብርሃን አላት:: ጨረቃ ጠፍ የምትሆንበት ጊዜ ግን በሁለት ወር ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው፣ ይኸም ማለት በአንድ ዓመት ውስጥ ስድስት ጊዜ ብቻ ሕፀፅ አላት ማለት ነው:: ይኸም የጨረቃ ሕፀፅና ጠፍ መሆን ከዑደቷ የተነሣ በመሬት ስትጋረድ ብቻ እንጅ እርሷ ጠፍ የምትሆንበት ጊዜ የምትጠፋበትም ምክንያት ከቶ የላትም:: የሆነው ሆኖ በሐሳበ ወርኀ ትምህርት ጨረቃ ተወለደች ወይም ወጣች የምትባልበት ጊዜ አለ፣ እርሱም ለመጀመሪያ ዕለት ፀሐይ ለመግባት ፬ ኪክሮስ ሲቀራት ጨረቃ ትወጣለች እርሷም በዚያ አራት አራት ኪክሮስ ብቻ አብርታ ትገባለች በማግስቱ ደግሞ ፬ ኪክሮስ ትጨምራለች እንዲህ እያለች በየዕለቱ ፬ ኪክሮስ እየጨመረች በ፲፭ኛው ዕለት ሙሉ ጨረቃ ትሆናለች ማለት ፷ ኪክሮስ ይሆናል፣ ሙሉ መዓልትና ሙሉ ሌሊት ትገኛለች ማለት ነው:: ጨረቃ ሕፀፅ ስትሆን ፳፰ ዕለት ወይም ፳፱ ዕለት ከሠራች በኋላ ነው፣ ማለት ፳፰ ዕለት አብርታ በ፳፱ነኛው ዕለት ጠፍ ስትሆን ኅፀፅ ይባላል፣ ፳፱ ዕለት አብርታ በ፴ኛው ዕለት ሕፀፅ ከሆነች ሙሉ ይባላል::

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት የብርሃናት ሹሞች አንድም መገብተ ብርሃናት የሚባሉ መላእክት አሉ፣ እነርሱም ፀሐይንም ጨረቃንም ይመግባሉ (ይጠብቃሉ) ተብሎ ይነገርላቸዋል፣ እነርሱ ፀሐይንም ጨረቃንም ይዘው እንደሚጓዙ እንደሚጠብቁ ይነገራል፣ ይሁን እንጂ በጥበበ እግዚአብሔር በኃይለ እግዚአብሔር ተጠብቀው እንደሚኖሩ ከብርሃናቸው ጋር ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ::[21] በዚህም መሠረት በዓመት ፫፻፶፬ ጊዜ ጨረቃ ዑደት ታደርጋለች:: ጨረቃ ተወለደች በሚባልበት ጊዜ ልዩ ልዩ ምልክቶች በሰውና በዓየሩ ላይ እንደሚታይ ብዙዎች ይናገራሉ፤ ማለት:-

1. ብዙዎች ሰዎች በሽታ ይቀሰቀስባቸዋል፣ ቁስል ይሰፋባቸዋል፣
2. ጊዜው ቀዝቃዛ ይሆናል ሌላም ይኸን የመሰለ ችግር እንዳለ ይነገራል::



www.ethiopianorthodox.org

በሽታ የጨረቃን መወለድ እያየ በሰዎች ላይ ችግርን ይፈጥር እንደነበር ጌታ ኢየሱስ ተናግሮታል።[22] ከዚህም የተነሣ ጨረቃን የሚያመልኩ፣ ጨረቃን የሚፈሩ አሉ፣ እንደ ፀሐይ አቆጣጠር አድርገው ዕለቱን ዓመቱን በጨረቃ የሚቆጥሩ ጾማቸውን የሚገድፉ በዐላቸውን የሚያከብሩ ይገኛሉ።

ጨረቃ በብርሃን ሰጭነት አካል ተመዝግባ ያለማቋረጥ ሥራዋን ስታካሄድ ትገኛለች፣ ይኸውም የታላቁን አምላክ ፍጹም ጥበብና ጥበቃ ያመለክታል። በዚህ በያዝነው ምዕት ዓመት ግን አምላክ በፈቀደውና ለሰው ልጅ በሰጠው ዕውቀት የሰውም ልጅ ባደረገው ታላቅ ጥረት ወደ ጨረቃ ለመሄድ ከዚያም አርፎ ስለርሷ ሁናቴ ለማጥናት ይችል ዘንድ የጠፈር መንኮራኩሩን ሠራ፣ ከአሰበውም ደረሰ ስለጨረቃም ማንነት ማጥናት ጀመረ። በአሁኑ ምርምር እንደተደረሰበት ጨረቃ ከአንድ ቋጥኝ መስል ደንጊያ እንደተሠራች ይነገራል፣ በውስጧም ሕይወት ያለው ፍጥረት የማይገኝባት አካል ናት። የፍጥረቷን ዕድሜ ለማወቅ የሚደረገው ጥናት ግን እንደቀጠለ ነው፤ ይሁን እንጅ ብዙ ዘመን እንደቆየች ዕድሜዋም ረጅም እንደሆነ የሚናገሩና ማስረጃ የሚሰጡ አሉ።

ለመሬት ቀረብ ብለው ከሚገኙት አካላት ጨረቃ አንደኛዋ ናት፣ ስለዚህም ነው በቀላሉ ወደርሷ የሰው ልጅ ለመድረስ የቻለው። ጨረቃ ለመሬት በጣም ቅርብ ናት፣ ደግሞም አነስተኛዋ አካል እርሷ ናት፤ ከእርስዋ በጣም የራቁ ፕላኔቶች ታናናሽ መስለው የሚታዩት ብዙ ጊዜ እርሷን የሚበልጡ ናቸው።

## ሐ. ከ ዋ ክ ብ ት፣

ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው አምላክ ማንም ቆጥሮ ሊደርስባቸው የማይቻሉትን ብዛት ያላቸውን ከዋክብት ፈጠረ። ብዙዎች ፕላኔቶችን ከዋክብት ናቸው የሚሉ ከዋክብትም ብለው የሚጠሩ አሉ፣ ይሁን እንጅ ከዋክብት ተብለው የሚጠሩ የተለዩ አካላት እንዳሉ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል።[23]

እንደ ፀሐይና እንደ ጨረቃ ብዙ አይድመቁ እንጂ እነርሱም የተፈጠሩበት ዓላማ መገብተ ብርሃናት እንደሆኑ፣





በሌሊት ይሰለጥኑ ዘንድ እግዚአብሔር ፈጠራቸው። ምንም ሌሎችም ፕላኔቶች ሁሉ ጥንድነት ያላቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቁጥር እንዳላቸው ብንገምትም ከዋክብት ግን ከሥሩ ከመሠረቱ ከዋክብት ተብለው በብዙ ቁጥር እንዲጠሩ በቅዱስ መጽሐፍም ተገልጦ እናገኛለን።[24] ይኸም የሚያመለክተው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አምላክ በብዛት እንደፈጠራቸው ነው። ስለ ከዋክብት ብዙ ጊዜ ስንነጋገር በብዙ ቁጥር በመጥራት ነው፣ የታወቀውንና ልዩ የሆነውን ኮከብ በስሙ ካልጠራነው በቀር፤ ይኸውም ከልማዳችን በዓይንም ከመመልከታችን የተነሣ ብዛታቸውን በመረዳት ነው።

ከዋክብት በብዙ ቁጥር መጠራታቸው ብቻ ሳይሆን ከቁጥርም በላይ የሆኑ ሊቆጠሩም የማይቻሉ እንደሆኑ አምላክ ለአብርሃም ቃል ኪዳን በገባበት ጊዜ የተናገረውን እናስታውሳለን እንዲህ ሲል «ወደ ሜዳም አወጣው አለውም ወደ ሰማይ አሻቅበህ እይ ከዋክብትንም ቁጥር ትቆጥራቸው ዘንድ ትችል እንደሆነ፣ አለውም እንዲሁ ዘርኽ ይሆናል።»[25] በእርግጥ ሰማይ በጠራ ጊዜ ሲታይ ከዋክብት ሰማዩን መልተውት ይታያሉ፣ በተለይም የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ በሚያሳይ ዘመናዊ መሣሪያ ሰማዩን የተመለከቱት እንደሆነ፣ ሁሉ ኮከብ ሁኖ ወይም ሁሉ በኮከብ ተሞልቶ ይገኛል። አምላክ ግን ሁሉንም የፈጠረ እርሱ ስለሆነ፣ ሁሉንም ያውቃቸዋል፣ በየስማቸውም ይጠራቸዋል፣ ያስተዳድራቸዋልም፣ ከርሱ የሚሠወርና እርሱም የማያውቀው ከቶ የለምና። ይኽንንም ነቢዩ ዳዊት «ዘይኌልቆሙ ለከዋክብት በምልአሙ ወይጼውዖሙ በበአስማቲሆሙ»[26] ሲል ብዛታቸውን ስምም እንዳላቸው ገልጦ ተናገረ። በተወሰነላቸው ቦታ ሁነው ስም ወጥቶላቸው ታውቀው ከሚገኙት ከዋክብት ሌላ በሰማዩ መካከል መቀነት መስሎ እንደ መሥመር ተጋድሞ ነጭ ሁኖ የሚታይ ነገር ይገኛል፣ ይኸውም ሌላ ነገር ሳይሆን የከዋክብት ክምችት ሁኖ ይገኛል፣ ይኸም አንዳንድ ጊዜ ወተት የተረጨ፣ ወይም ወተት የፈሰሰበት መስሎ ሰማዩ ይታያል፣ ስለዚህም በግሪክኛ ጋላክሲ ይሉታል፣ የወተት መንገድ ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ በሕዝብ አነጋገር የዮርዳኖስ ወንዝ ይሉታል፤



www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ንጣቱን በመመልከት ነው:: በአንዳንድ ተረቶች ግን የነፍሳት መንገድ ተብሎ ይጠራ እንደነበር ይገመታል:: በአጠቃላይ ግን ይኸ ሁሉ የሚያመለክተው ከዋክብት ከቁጥር በላይ መኖራቸውን ሰማዩን ሞልተውት እንደሚገኙ የሚያስረዳ ምልክት ነው::

የከዋክብት መገኘት ዋናው ዓላማ፣

1ኛ በሌሊት ብርሃን ይሰጡ ዘንድ ነው፣

2ኛ ዘመንን ለማስገኘት ለዓመታትም ለውጥ ምልክት ይሆኑ ዘንድ ነው:: «እግዚአብሔርም አለ ብርሃናት ይሁኑ በሰማይ ጠፈር በቀንና በሌሊት መካከል ይለዩ ዘንድ፣ ለምልክትም ይሁን፣ ለዘመንም ለዓመታትም»[27] ከዋክብት ዓላማ ቢስ በመሆን በዘፈቀደ የሚገኙ አካላት አይደሉም ሥርዓት ያላቸው መሥመራቸውን ጠብቀው ቦታቸውን ይዘው እንደሌላው ሰማያዊ አካል ሁሉ ዑደት የሚያደርጉ፣ ምግብናቸውንም የሚፈጽሙ ናቸው:: ከዚህ ጋር ለሰማዩ ዕንቁ ፈርጥ ጌጥ በመሆን እንደሚታዩ አድርገው ስለ ድንቅ ሥራው እግዚአብሔርን የሚያስመሰግኑ ፍጥረቶች ናቸው:: ስለዚህም «አሠርገወ ሰማየ በከዋክብት፤ ወምድረኒ በሥነ ጽጌያት...» ሲል ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ያሬድ አመስግኖበታል::[28]

በምሕዋረ ከዋክብት አማካይነት ዘመንን የሚቆጥሩ ጊዜያትን የሚለዩ ሁሉ፣ እንዲሁም በከዋክብት አቆጣጠርና አጠራር ብዙ ጥበባትን የሚያመነጩ አሉ:: ስለ ዘመን አቆጣጠርና መግቦት ግን በቤተ ክርስቲያናችን ዘንድ ከዋክብት ከፍ ያለውን ምዕራፍ ይዘው ይገኛሉ፣ ይኸውም እያንዳንዱ ወርኅ የራሱ የሆነ መጋቢ ኮከብ እንዳለው አድርጎ በመገመት ነው፣ በዚህም መልክ ለዓመቱ ፲፪ መግብተ አውራኅ ከዋክብት አሉት ማለት ለየወሩ አንዳንድ ኮከብ አለው ማለት ነው፣ ስማቸውም:-

1. ደለው
2. ሑት.
3. ሐመል
4. ተውር
5. ጀውዝ
6. ሺማን
7. አሰድ
8. ሰንቡላ
9. ዐቅራብ
10. ሚዛን
11. ቀውስ
12. ሺሺያ የተባሉት ናቸው::



www.ethiopianorthodox.org

ዓለም በጠቅላላው

ለነዚህ ደግሞ አርእስት የሚሆኑ ዓመቱን ከ፬ ተካፍለው የሚመግቡ ፬ ዓበይት ከዋክብት አሉ፣ እነርሱም ህልመልሜሌክ፣ ብርከኤል፣ ምልኤል፣ ናርኤል የሚባሉ ናቸው:: እነዚህ ከዋክብት ዓመቱን ለአራት ሲከፍሉት ለያንዳንዳቸው ዘጠና አንድ ዕለት ከአሥራ አምስት ኬክሮስ ይደርሳቸዋል:: ይኸም በአራት ሲባዛ ፫፻፷፭ ወይም ፫፻፷፮ ቀን ሊሆን ይችላል:: እነዚህም አራቱ ዐበይት ከዋክብት የዓመቱን መግበት ፲፪ቱን ከዋክብት ሲካፈሏቸው ለያንዳንዳቸው ፫ ይደርሳቸዋል፣ ስለዚህ ዓመቱን በዚህ መልክ ተካፍለው ሲመግቡ ይኖራሉ:: ሁሉም መሥመራቸውን በመጠበቅ ፀሐይን ተከትለው ዑደት ያደርጋሉ፣ በዚህን ጊዜ ለዘመናት ለዓመታት መለወጥ ምልክት ይሆናሉ::

ታላቁ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሰማይን ሠራዊት በቁጥር በዓይነት የበዙና የተለያዩ አድርጎ መፍጠሩን እናምናለን፣ ግን ሁሉንም ልንደርስበት፣ ሁሉንም ልናውቀው አለመቻላችን የተረጋገጠ ነው:: ሁሉ ግን በእርሱ እንደተፈጠረ በእርሱ ዘንድ ደግሞ እንደተቆጠረ የታወቀ ነው:: እኛ ግን ከዋክብትን እንኳን የሚታዩትን ለመቁጠር የማይቻለን መሆኑን ከላይ በተናገርነው ልንረዳ እንችላለን፣ ስለዚህ ይኸንኑ አምነን በዚህ እንገታለን:: እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ብዙ ነው፣ እያንዳንዱን ለመቁጠር ለሁሉም ስም ለመስጠት መርምሮ ለመድረስ አይቻልም፣ ግን ለእምነታችን መደገፊያ ለአእምሮአችን መመዘኛ የሚሆኑ እነዚህን ብቻ ጠቅሰን እንመለሳለን:: ሁሉም ለእግዚአብሔር ምሥጋና መፈጠሩን ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ሲል ያስረዳናል «ይሴብሕዎ ኩሉ ኃይሉ፣ ይሴብሕዎ ፀሐይ ወወርኅ፣ ይሴብሕዎ ከዋክብት ወብርሃን፣ ይሴብሕዎ ሰማየ ሰማያት፣ ማይኒ ዘመልዕልተ ሰማያት ይሴብሑ ለስመ እግዚአብሔር እስመ ውእቱ ይቤወኮኑ፣ ወውእቱ አዘዘ

ወተፈጥሩ» ይላል::[29] አሁንም እኛ ሥነ ፍጥረትን ተከትለን ለዕበዩ ክብርን ለስሙ ቅዳሴን ልንሰጥ ይገባናል::

መ. <u>ሰማያዊያን ሠራዊት</u>፣

ሰማያውያን ሠራዊት ብዙዎች ናቸው ስማቸው ዓይነታቸው ተጠርቶ ተቆጥሮም አያልቅም፣ እነዚህም አኗኗራቸውም ምጡቅ ነው፣ ግን ማን አመጣቸው፣ እንዴህስ አድርጎ ማን አስቀመጣቸው፣ እንዴትስ ይኸን ያህል ዘመን ሊቆዩ ቻሉ?፣ ይኸ ዓይነት ጥያቄ አእምሮ ላለው ለሰው ልጅ ሁሉ በእእምሮው የሚቀርብ ጥያቄ ነው፣ መልሱም በዚያው በየራሱ አእምሮ የሚመለስ ነው፣ በምንም መልክ ይኸን የመሰለ የተፈጥሮን ሕግ ጠብቀው አቀማመጣቸውን ዑደታቸውን አስተካክለው ደግሞም መሥመራቸውን ሳያዛቡ ፀሐይን በመከተል ሥርዓት ባለው መንገድ መሔዳቸው ሁላችንም መርተው ወደ ታላቁ ፈጣሪ ወደ እግዚአብሔር ያደርሱናል:: ነቢዩ ዳዊትም «ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ወግብረ እደዊሁ ያየድዓ ሰማያት» ሲል የተናገረው ስለዚህ ነው::[30]

ሰማያት አፍ አውጥተው ቋንቋ ለይተው ይናገራሉ ማለቱ አይደለም፣ ንባብ አእምሮ ያለው የሰው ልጅ ሁሉ ሰማያዊያን ሠራዊትን በመመልከት ከራሱ ጀምሮ እስከ ላይ በመውጣት ያለውን ሕግና ሥርዓት በመመልከት ለዓለሙ ሠሪ፣ መጋቢ አስቀድሞ እንዳለው ይረዳል፣ ፍጥረታትም ሁሉ ስለ አምላክ ሕልውና ያስተምራሉ፣ ያመለክታሉ ማለቱ ነው::[31] እነዚህን አካላት ሁሉ ማን ሠራቸው፣ በአየርስ ላይ ማን አንጠለጠላቸው አሁንስ ምን ያዛቸው ማንስ ይጠብቃቸዋል? ይኸን የመሰለ ጥያቄ ሲመጣ ራሳቸው በራሳቸው በሁኔታቸውም ሁሉን ያደረገ እግዚአብሔር እነርሱንም ሠራ ፈጠረ በማለት ይመሠክራሉ ማለት ነው፣ መርተውም ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ:: እግዚአብሔር ፈጣሪያቸው እንደሆነ ማስረዳት ብቻ ሳይሆን ይኸን ሁሉ ማድረጉን ፍጹም ጥበቡን ፍጹም ኃይሉን ያስረዳሉ፣ እንዲሁም ሁሉን የማይረሳ፣ ሁሉን የሚመግብ፣ ሁሉንም የሚያስተዳድር መሆኑ ቸርነቱንና በዓለም ሙሉነቱን ይመሰክራሉ::





የእግዚአብሔርን ታላቅነት የፍጥረትንም ክንውን በመመልከት በአድናቆት ተውጠው ለእግዚአብሔር ምሥጋና ያቀረቡ ብዙዎች ናቸው፣ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተለውን እንጠቅሳለን፣ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ይላል «ለእግዚአብሔር ምሥጋና ዘምሩ፣ ለአምላካችንም በመሰንቆ ዝማሬ አቅርቡ፣ ሰማዩን በደመናት የሚሸፍን ለምድርም ዝናምን የሚያዘጋጅ ሣርንም በተራሮች የሚያበቅል ...» ይላል::[32]

፫. <u>የምድር ፍጥረታት</u>፣

ልዑል አምላክ ምስጋና ይግባውና ከእሁድ አንሥቶ እስከ ዓርብ የፈጠረው ፍጥረት ዓይነቱና ስሙ ብዙ ነው፣ እንዲሁም ስም ያልተሰጣቸው፣ ገናም ያልታወቁና ያልተደረሰባቸው፣ ፍጥረታት ብዙ ናቸው:: ይሁን እንጂ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አገላለጥ፣ እንደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ትምህርት በ፮ቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታት በየነገዳቸው በየወገናቸው የተጠሩና የታወቁም ናቸው:: የየዕለቱን ፍጥረት ብቻ በመመልከትና ስማቸው የተጠሩትን ወገኖች ብቻ በመቁጠር ማለት ሊቀ ነቢያት ሙሴ የጠራቸውንና በዘፍጥረት 1 የተገለጡትን ፍጥረታት በመመልከት እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ፳፪ ፍጥረታት አድርገው የሚቆጥሩ አሉ:: ይሁን እንጂ መላእክትንና እነርሱን የመሰሉትን የታወቁትን ፍጥረታት ሁሉ መቼ እንዴት እንደተፈጠሩ በቅዱስ መጽሐፍ ያልተገለጡ ሲሆን ፍጥረት ይኸ የተገለጠው ብቻ ነው ብሎ ለመገመት ቁጥርም ለመስጠት ከቶ አይቻልም::

ልዑል አምላክ አንዳንዱን በእጁ ሌላውን ደግሞ በቃሉ ፈጥሯል፣ የበለጠውን ግን ግብር እምግብር እንዲገኝ አድርጓል፣ የምናምነውም ሁሉ በእግዚአብሔር መፈጠሩንና የሚታይ የማይታይም፣ የሚታወቅ የማይታወቅም ፍጥረት እንዳለ ነው:: «ምድር ራሷና በከርሠ ምድር ያለው ገና ምን እንደሆነ ያልታወቀ ያልተደረሰበትም ነው፣ ስለዚህ በኛ ዓለም እንኳን ያለውን ገና የሰው ልጅ ያላወቀው ሲሆን፣ ሌላውንማ የራቀውን የረቀቀውን ከሰው አእምሮም ውጭ የሆነውን ስንት ፍጥረት እንዳለ ማን ሊያውቅ ይችላል::



www.ethiopianorthodox.org

እያንዳንዱን ፍጥረት ለመመርመር ስለርሱም ለመናገር በፍጹም አይቻልም፤ ብቻ ሰውንና መላእክትን አምላክ ስሙን ለመቀደስ፣ ክብሩን ለመውረስ እንዲችሉ በዚህ ዓላማ ፈጥሯቸዋል። ሌላውን ፍጥረት ደግሞ ለአንክሮ ለተዘክሮ ለሰው ልጅ አገግሎትና ልዩ ልዩ ጥቅም ፈጥሮታል።

ሰማየ ሰማያት ለእግዚአብሔር ሲሆን ምድር ደግሞ ለአዳምና ለልጆቹ እንደተሰጠች ቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው ያስረዳል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን የሰው ልጅ የተራባውን ያህል ምድርን ገና ሳይመላ የምድርንም ሀብት በመላ ገና ሳይጠቀምበት ይገኛል። መሬት በጣም ሰፊ የሆነች አካል ናት፣ ትልቅነቷም ከዘጠኙ አካላት (ፕላኔቶች) ውስጥ ሦስተኛውን ደረጃ ይዛ ትገኛለች እርሷም ከሰው በቀር የአዝርእት የአትክልት የዕፅዋት የእንስሳት የአራዊት ዓለም ሁና ትገኛለች፣ ከክፍሏም ይበልጠው ባሕር ለበሶ ይገኛል። ምድር በመጀመሪያ ለፍጥረት ሁሉ ምክንያት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ ጋር ፈጠ ራት፣ ከእግዚአብሔር በታች የፍጥረቱም ሁሉ ገዢ የሚሆነው ሰው ሳይቀር የተፈጠረ ከርሷው ነው፣ ምድራዊ አካል የሚባለው ሁሉ በምድር የሚኖረውም ሁሉ የተፈጠረው ከእርሷው ነው።

መሬት የተፈጠረችበትን ዘመን ብዙ ሊቃውንት ሰፋ ራቅም አድርገው ማለት ዘመኑን አስረዝመው ይናገራሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ መካከለኛ ግምት ሰጥተው ይናገራሉ። እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አገላለጥ ግን በጣም ቅርብ ጊዜ እንደሆነ ይናገራል። ግን ሁሉንም የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን አምነን ምድራዊያን ፍጥረቶችን በመጠኑ እንደሚከተለው እንገልጣለን።

ሀ. <u>አዝርእት-አትክልት</u>፣

ልዑል አምላክ በዚህ በዓለማችን የሚገኙ ልዩ ልዩ ዓይነት የሆኑትን በመልካቸውም በመዓዛቸው በጣዕማቸው የተወደዱትን ወይም በልዩ ልዩ አገልግሎታቸው ለሰው ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡትን ዕፅዋት ዐዝርእት አትክልት ፈጠረ፣ ከነዚህም ውስጥ በምግብነታቸው ጣፋጭነት ያላቸውን፤ በመድኃኒትነታቸ ውም ፈዋሽነት ያላቸውን፣ በመልካቸው ደግሞ የሚያሸበርቁትን ለሌላም ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን እንደ አየሩ ልዩነት





እንደቦታውም አቀማመጥ የሚገኙትን ዕፅዋት ሁሉ እግዚአብሔር ፈጠረ፣ «እግዚአብሔርም አለ ምድር ሣርና ቡቃያ ታብቅል፣ ዘር የሚሰጥ የሚያፈራም ዛፍ እንደዘመዱ ዘርን የሚሰጥ።»[33] እነዚህ ዕፅዋት በየመልካቸው፣ በየጠባያቸው፣ እንደወገናቸው ይኖራሉ፣ እነዚህም ፈጣሪያቸውን ሲያስታውሱ፣ ስለርሱም አስገኝነት ሲመሰክሩ ይኖራሉ።

እነዚህ ዕፅዋት በፍሬያቸው፣ በቅርንጫፋቸው አማካይነት የሰው ልጅ ያባዛቸው እንጂ በመጀመሪያ እንዴት ተገኙ ማንስ አስገኛቸው እንደዚህ ያለውን ውበትና መወደድስ እንዴት ሊያስገኙ ቻሉ? መልሱም ሌላ ሳይሆን ይኸ ሁሉ ከፈጣሪያቸው ፍጹም ጥበብና ሁሉን ለማድረግ ከመቻሉ የተነሣ እንደሆነ በትክክል ያስረዳል።

ለ. <u>እንስሳትና አራዊት</u>፣

እንስሳት የቤት፣ የምድረ በዳ አራዊት ይሁኑ እንጂ በመላ እንስሳት የሚባሉ ንባብ አእምሮ ሕያውነት የሌላቸው በደመ ነፍስ ብቻ ጸንተው የሚኖሩ፣ ተንቀሳቃሽነት ያላቸው በብዙ መልክ ለሰው አገልግሎት የሚውሉ ማለት ብዙዎች ለሰው ምግብ የሚሆኑ፣ ሌሎችም ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው፤ እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ተፈጥረዋል። ከነዚህም እንስሳት ውስጥ በቁመታቸው በግዙፍነታቸው የሚያስደንቁም የሚያስፈሩም ይገኛሉ። ሌሎች ደግሞ ለመታየት የሚያምሩ ውበትና መወደድ ያላቸው፣ ስለዚህም በተለይ ቦታ እንዲረቡ የሚያደርጉ ይገኙባቸዋል። ሁሉም ለሰው ጥቅም ለሰው አገልግሎት የተፈጠሩ ስለሆኑ በጣም ችግር ካልገጠማቸው በቀር ሰውን ፈርተው ከሰው ሸሽተው የሚኖሩ ናቸው፣ እንዲያውም ጥቂቶች ለሰው ልጅ ታማኝ አገልጋዮች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ቤዛ እስከመሆን የሚያገለግሉ አሉ።

የምድረ በዳውን ክፍል እንስሳው ዝሆኑ ሌላም ግሩማን አራዊት ይዘውት ይገኛሉ። በለምለሙ መሬት አዝመራው አዝርእቱ አትክልቱ ዛፉ ተንሰራፍቶበት ይገኛል። በባሕሩም አሣው ጉማሬው አሣነባሪው ሌላም የማይቆጠሩ ተንቀሳቃሽ



www.ethiopianorthodox.org

አራዊት ይገኛሉ:: በአየሩ ወፉ አሞራው በጠቅላላው በየብስና በባሕር ተከፍሎ ምድርን አልብሶ የሚኖረው እንስሳ ዓይነቱ፣ ቁጥሩ፣ ስሙ፣ የበዛና የተለያየ ነው:: ይኸ ዓይነት ፍጥረት ሁሉ የሚገኘው በዚህ በኛው ዓለም ነው:: ሁሉም የተፈጠረው ደግሞ ለሰው አገልግሎት ነው፣ ይሁን እንጂ ሁሉም የፈጣሪውን ታላቅነት ሲገልጥ በሌላ በኩል ደግሞ ለሰው አገልግሎት እንዲውል፣ የሰው ወገን የሆነው ሁሉ እንዲጠቀምባቸው አምላክ ለሰው ሲሰጥ በእርሱና በሰው መካከል ያለውን ፍቅር አንድም ግንኙነት ምን ያህል የጠበቀ እንደነበር ያስረዳል:: አምላክ ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ ሰውን ለምድራዊ ነገድ ሁሉ ባለቤት አድርጎ ከአፈር ጀምሮ እስከ ተንቀሳቃሽ እንስሳ ድረስ ያለውን ፍጥረት ሁሉ ለሰው ንብረት አድርጎ ሰጠ:: የሰው ልጅ ግን የእግዚአብሔርን ውለታ የሥጦታውንም ዋጋ ባለማወቅ በሥጦታው የሚጠቀም በጣም ጥቂት ነው፣ ስለዚህ ግማሹ ጥቅማቸውን አውቆ የሚንከባከባቸው አለ፣ እንዲሁም ያለጥቅም ሁሉንም የሚያጠፋ አለ::

ይኸም ሁሉ ሁኖ ምድር ገና ብዙ ጥቅምን የምትሰጥ ተበልታም ያላለቀች ናት፣ በሰውም በሌላም ፍጥረት አሁንም ገና አልሞላችም ገናም በሙላ ከጥቅም ላይ አልዋለችም:: ምድር ከሰማያውያን አካላት ጋር በመገናዘብ ያለማቋረጥ ለሰው ልጅ ልዩ ልዩ አገልግሎትን ትሰጣለች፣ ማለት ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብት ጋር በመገናዘብ ዕለታትን አውራኀን ዓመታትን ታስገኛለች::

እንዲሁም ክፍለ ዘመናትን በመለወጥ፣ ሙቀትን ዝናምን ትሰጣለች፣ ነፋሳትንና ብርሃናትን ሌሎችንም ሕይወት የሚሰጡትን ምክንያቶች ሁሉ ትቀበላለች:: ይህም ሁሉ ሊሆን የቻለው ሰማያውያን አካላትና ምድራውያን ሠራዊት አምላክ የሰጣቸውን የተፈጥሮ ሕግ ጠብቀው ከመገኘታቸው የተነሣ ነው::

ምድራዊው ፍጥረት የታወቀ ከዕለት ኑሯችንም ጋር የተያያዘ ስለሆነ፣ ብዙ ጊዜ በአድናቆት እንመለከተው እንጂ ከራሳችን ከኛ ጀምሮ ተንቀሳቃሹም የማይንቀሳቀሰውም ፍጥረት ሁሉ፣ በአድናቆት ወደ ፈጣሪው ስቦና ጎትቶ የሚያደርስ ድንቅ የሆነ መምህር ነው::





ሰማዩና የሰማዩ ነገድ ሩቅ ስለሆነ ስለርሱ ብቻ ሲነገር እንደነቃለን እንዲሁም ሁል ጊዜ ስለርሱ እንዲነግሩን እንወዳለን:: ይኸም በበኩሉ የሚደገፍ ሌላ ድንቅ ነገር ነው፣ በእውነት ከሆነ ግን በዓይናችን ከምናየው ቅርብ ከሆነው ከዚህ ዓለም ጀምረን የራቀውን፣ የረቀቀውንም በዓይነ ሥጋም በዓይነ ነፍስም ብንመለከተው ለረቀቁና መልስ ለማይገኝላቸው ጥያቄዎች ሁሉ ቀጥተኛ መልስ ልናገኝላቸው በቻልን ነበር:: የሥነ ፍጥረት መገኘት ዋናው ዓላማ ለአምላክ ህልዎትና ፈጣሪነት ምስክር ለመሆን ነው፣ ስለዚህ ይኸንን ሁሉ ጥያቄ ከፍጥረታት እንዳገኘነው ሁሉ መልሱንም በዚያው በነርሱ ልናገኘው እንችላለን::

ከዚህ በላይ በመጠኑ እንደተገለጠው ፍጥረት ሁሉ ለእግዚአብሔር ህልዎት ገላጭ፣ ምስጋናም ሰጭ ሆኖ ተፈጥሯል፣ ይኸንም «ይባርክዎ ኩሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር» ሲሉ አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል ተናግረዋል::[34] በነዚህ ፍጥረታት አማካኝነት የሰው ኑሮው ይሳካል እርምጃውም ይታመናል፣ ስለአምላኩ ብዙ ትምህርት ያገኛል፣ ፍጥረታት ሁሉ ለሆነ ለተቀደሰም ዓላማ ተፈጥረዋልና:: ሥነፍጥረት ከኦርቶዶክሳዊ ትምህርታችን አንደኛውን ክፍል ሊይዝ የቻለው ከሌላው ትምህርት ይልቅ የነርሱ ህልውና፣ የነርሱ የተፈጥሮ ሕግን መጠበቅ፣ የነርሱም ሥነ ሥርዓትን መያዝ፣ ስለ ታላቁና ጥበበኛው ፈጣሪ በቀላሉ ሊያስረዱ ይችላሉና ነው:: እውነቱን ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ ይኸ ዓይነት አስረጅና ሌላም ይኸን የመሰለ ብዙ ምክንያት ወደ እውነተኛው ፈጣሪ መርቶ የሚያደርስ ነው::

ይኸንም ማር ይስሐቅ «ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘንተ ብከ ካልዕ መምህር እምአፍአ ዘይመርሐከ ኀበ አእምሮ ዝንተ ምሥጢር» ሲል ተናግሯል::[35] አምላክ ሥነ ፍጥረትን በዚህ ዓለማ ፈጠረ፣ በዚህም ዓላማነት መሠረተ፣ ጸንቶ እንዲኖርም ይጠብቃል ይመግባል፣ ያስተዳድራል::



www.ethiopianorthodox.org

# ም ዕ ራ ፍ ፲

## የእግዚአብሔር መግቦት፣

ዓለም ከእግዚአብሔር ቸርነትና ርኅራኄ ከፍጹም ጥበቡም የተነሣ የተፈጠረ የተገኘም እንደመሆኑ፣ የእግዚአብሔር መግቦትና አስተዳደር አመለካከትም ከቶ አይለየውም:: ከሃሌ ኩሉ እንደመሆኑም መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ወደ ተፈጠረበት ዓላማና ግብ ይደርስ ዘንድ ይመራዋል:: ልዑል እግዚአብሔር ይኸን የተከናወነ ዓለም በዕድሉ እንዳልተገኘ ሁሉ በዕድሉ ይኖር ዘንድ እንደማይተወው እንደማይለየውም ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች:: ይኸም እግዚአብሔር ዓለምን መጠበቅና ማስተዳደር በአንድ ቃል «መግቦት» ተብሎ ይጠራል:: አምላክ በጥበቡ የፈጠረውን ዓለም በየነገዱ በየወገኑም ጸንቶ ይኖር ዘንድ ያስብለታል፣ ይሠራለታል፣ ያስተዳድረዋልም::

ለዓለም ልክ መልክ ወሰንና ደንበር ያለውን ያህል በዓለማውም ጸንቶ እንዲኖር ወደ ተሻለም ግብ እንዲደርስ ከፍተኛም ውጤት እንዲኖረው እግዚአብሔር ይመራዋል:: ይኸም ማለት እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ከቶ አይለይም አይርቅም ማለት ነው፣ ባለቤቱ እርሱ ነውና:: እግዚአብሔር ዓለምን ይጠብቃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል ስንል የሰውን ነፃነት ወስዶ እርሱ ወደፈለገው ያዞረዋል፣ የፈለገውን ያሠራዋል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ሰው በተፈጠረበት ዓላማ ጸንቶ ከክብር ወደ ክብር የሚሄደውን እግዚአብሔር ያቃናለታል፣ ያሰበው ሁሉ ይሆንለታል፣ ይፈቅድለታልም ማለት ነው እንጂ:: ሰውን እግዚአብሔር ወደ ወደደው እንደፈለገው ያዞረዋል፣ እርሱም እንደፈቀደው ይከተለዋል ማለት አይደለም፣ ይኸስ ቢሆን ኑሮ ሰው እንደማንኛውም ሞተር ሁኖ ማንም ይዘውረዋል፣ ወደ ወደደውም ይወስደዋል ያሰኝ ነበር፣ የተፈጥሮም ነፃነት የሚባለው ሊኖረው አይችልም ነበር፣ ግን እንዲህ አይደለም::





## የእግዚአብሔር መግቦት በሁለት ዓይነት ይገለጣል፣

1. መጠበቅ፣

ዓለም በዕድሉ ያልተገኘ በራሱ ፈቃድም ያልተፈጠረ ስለሆነ፣ ያው ባለቤቱ ፈጣሪው እግዚአብሔር በፈጠረበት ዓላማ ጸንቶ ይኖር ዘንድ ይጠብቀዋል፣ ይኸስ ባይሆን ኑሮ ማንኛውም ነገር ፍጡር እንደመሆኑ ያልቅ፣ ይደቅ ይጠፉም ነበር:: ይኸ የተከናወነ ዓለም በተፈጠረበት መልክና ጠባይ፣ በተፈጠረበትም ዓላማ ጸንቶ ሊኖር የቻለው በመጀመሪያ አምላክ ከፍጹም ጥበቡ የተነሣ፣ ፍጹም አድርጎ በመፍጠሩ ሲሆን፣ አምላክም ከዓለሙ ያልተለየ ሁኖ ስለሚጠብቀው መሆኑ የታመነ ነው::

ዓለም በራሱ ያልሆነ ያልተገኘም እንደመሆኑ አሁንም በራሱ ፈቃድ ሊጸና ሊኖርም አይችልም፣ በግድ የፈጣሪው ጥበቃና መከባከብ ያስፈልገዋል:: ይኸም የአምላክ ጥበቃ የሚባለው ከፈጣሪነቱና ከፍጥረቱ ጊዜ ጀምሮ ተያይዞ ያለ እንጂ አዲስ ነገር አይደለም:: ጥበበኛው ሰሎሞን ስለ ዓለም ጥበቃ ሲናገር «የሆነውን ሁሉ ትወዳለህ ከፈጠርከው ውስጥ ከቶ የምትጠላው የለኽም፣ ጠልተኽ የፈጠርከው የለምና:: ከፈጠርከው ፍጥረትም ምንም የምትንቀው የለም:: አንተ ከጠላኸውማ በፊትህ እንዴት በጸና ነበር፣ ከጠላኸውና ካልወደድከውም ባልፈጠርከው ነበር:: አንተም ወደህ ያልፈጠርከው ካልሆነ እንዴት በተጠበቀ ነበር:: ለፍጥረቱ ሁሉ ትራራለህ ይቅርም ትላለህ» ሲል ትክክለኛውን እምነትና ትምህርት ገልጦ ተናገረ::[1] ልዑል አምላክ ይኸን ዓለም ፈጥሮ እንዳልጣለው እንደሚንከባከበውም እንደሚጠብቀውም ነቢዩ ዳዊትም በተጨማሪ ሰፋ ያለ ማስረጃ ሰጥቶ እናገኛለን፣ እርሱም እንዲህ ይላል «...... አንተ በሰጠኻቸው ጊዜ ይለቅሙታል፣ እጅህን ትከፍታለህ በበጎ ነገርም ይጠግባሉ:: ፊትሕን ግን በሰወርክ ጊዜ ይደነግጣሉ፣ ትንፋሻቸውንም ታወጣለህ ያልቃሉም፣ ወደ መሬታቸውም ይመለሳሉ፣ እስትንፋስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም የምድርንም ፊት ታድሳለህ::»[2]

እግዚአብሔር የፍጥረቱ ሁሉ መገኛ ነው ለተንቀሳቃሹ ሁሉ ኃይሉ አንቀሳቃሹም እርሱ ነው፣ ቅዱስ ቃሉ ስለዚህ



www.ethiopianorthodox.org

አስረጅ ሲሰጥ «በእርሱ እንኖራለን እንመላለሳለንም እንሆናለንም» ይላል::[3] የሚታየውንም የማይታየውንም ዓለም እግዚአብሔር ፈጠረ፣ አሁንም እግዚአብሔር ሁሉንም ይመግበዋል፣ ይጠብቀዋል ባለቤቱ እርሱ ብቻ ነውና::

፪. <u>በማስተዳደር ይመግበዋል፣</u>

ይኸ ዓለም ልክ ወሰን ያለው፣ ሕግና ሥርዓትም ያለው ስለሆነ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊ ጠባዩ እንደተፈጠረበት ጠባይና ሁኔታ እንዲገኝ በዚያውም ዓላማ ጸንቶ እንዲኖር እግዚአብሔር ፈጠረው፣ ሠራው በዚያውም ዓላማ ያስተዳድረዋል፣ ይመግበዋልም:: ቅዱስ መጽሐፍ በብዙ አቅጣጫ የእግዚአብሔርን አስተዳዳሪነት አስፍቶ ይገልጣል፣ እነሆ ከዚህም እንደሚከተለው ይገልጣል፣ «እነሆ የእግዚአብሔር ዓይን ወደ ሚፈሩት ናት ምሕረቱም ደጅ ለሚጸኑት ነው:: ነፍሳቸውን ከሞት ያድን ዘንድ በራብም ጊዜ በሕይወት ይጠብቃቸው ዘንድ::»[4]

የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በየጊዜው ስለ እግዚአብሔር መግቦት ስለ ዓለም አስተዳዳሪነት ጽፈዋል ተናግረዋል፣ ሁል ጊዜም የምንጸልየው አምላክ ይሰማናል፣ የምንሠራውን አምላክ ያይልናል፣ በጠቅላላውም ሕይወታችንን ይቆጣጠራል፣ በማለት ስለሆነ መግቦቱን አስተዳዳሪነቱን እናምናለን፣ ይኸን ከካድን ግን ሥራችን ሁሉ ከንቱ ይሆናል፣ ቀጥሎም ወደ አምላክ ቢስነት አስተያየት ያደርሰናል፣ ስለዚህ በእግዚአብሔር አስተዳዳሪነት መሪነት መኖራችን ማመኑ የቤተ ክርስቲያናችን እውነተኛው ትምህርትና እምነት ነው:: አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድም ቦታ አደጋ ሲፈጠር በመገኘቱ ለምሳሌ እንደ ማዕበል፣ እንደመሬት መናወጥ፣ እንደፕላኔቶች መጋጨትና መውደቅ፣ ሌላም ይኸን የመሳሰሉ ሲገጥሙ ለዓለም ጠባቂ ታዛቢም እንደሌለው የሚቆጥሩ አሉ:: ነገር ግን ይኸ ሁሉ በእግዚአብሔር ዕቅድ የሚደረግና የሚፈጸም እንጂ ያለእርሱ ፈቃድ የሚሆን ነገር ከቶ እንደሌለ ልናምን ይገባናል:: እርሱ በፈቀደው ጊዜ የሚደረግ እንጂ ሳያውቀው፣ እርሱ ሳይፈቅድ የሚደረግ ነገር ከቶ የለም፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለቅጣት





አንዳንድ ጊዜም ተአምራቱን ለማሳየት እግዚአብሔር ብዙ ምልክቶችን ያደርጋል፣ ይኸ ሁሉ የርሱ ሥራ እንጂ ከርሱ ፈቃድና ቁጥጥር ውጭ የሚደረግ ነገር እንደሌለ የታመነ ነው፣ ለምሳሌ ግብጻውያንን ለመቅጣት የውሀውን መልክና ጣዕምን እንደለወጠ፣ ልዩ ልዩ ተሐዋስያንም ያስቸግሩ እንደ ነበር፣ የበኩር ልጅ ሁሉ መሞት፣ ሌላም ይኸን የመሰለው የሥነ ፍጥረት ለውጥ ሁሉ የተፈጸመው ከእግዚአብሔር ተአምራት የተነሣ የተደረገ ነው:: እንዲህም አድርጎ የተቤዠውን ሕዝብ፣ ከግብጽ ባርነት ነፃ ያወጣውን እንደገና በሕግ አፍራሽነቱ ደግሞ እንደተጣላው ፳ው እልፍ አጋር በምድረ በዳ ወድቆ እንደ ቀረ እናውቃለን፣ ምክንያቱም አምላክ ታግሦ ቆይቶ ካልተመለሱለት ይቆጣል፤ ይቀጣልም ይኸን ተአምራትና ቅጣት ቅዱስ መጽሐፍ ለምሳሌ ያህል እንዲህ ሲል ይገልጥልናል፣ «በምስርም ተአምራቱን፣ ድንቁንም በጣኔዎስ ገዳም ባደረገ ጊዜ፣ ወንዛቸውን ፈሳሻቸውን እንዳይጠጧቸው ደም አደረገ:: ብዙ ተባይ ሰደደባቸው፣ ሰብላቸውንም ኳኑንቸር አጠፋባቸው፣ ፍሬያቸውንም ለክብኩባ ሰጠ፣ የለፉበትንም ለአንበጣ፣ ወይናቸውንም በበረዶ አጠፋ፣ በለሳቸውን በውርጭ፣ እንስሳቸውንም ለበረድ ከብታቸውንም ለመብረቅ አሳልፎ ሰጠ:: የቁጣውንም ትኩሳት ሰደደባቸው፣ ለቁጣውም መንገድ ጠረገ፣ ነፍሳቸውንም ለሞት አልራራለትም፣ ሕይወታቸውንም ለቸነፈር አሳልፎ ሰጠ:: የምስርንም በኩር ሁሉ ገደለ በካምም ድንኳኖች የጉልበታቸውን መጀመሪያ ሕዝቡን ግን እንደበግ አወጣቸው እንደ መንጋም በምድረ በዳ መራቸው»::[5]

## <u>ም ዕ ራ ፍ ፬</u>

### <u>የመላእክት ሕልውና፣</u>

ከጥንት ጀምሮ መላእክት እንዳሉ ህልውናቸውም የታመነ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ:: ብሉይ ኪዳን መላእክት መቼ እንዴት እንደተፈጠሩ አይነግረን እንጂ ከዘፍጥረት ጀምሮ የመላእክትን ህልውናቸውንና አገልግሎታቸ ውን እየገለጠ ያቀርብልናል፣ ለምሳሌ አዳም እንደበደለ ከገነት



www.ethiopianorthodox.org

ሲወጣ የቦታው ጠባቂ ሆኖ የተሾመ ኪሩቤል የተባለ የመልአክ ነገድ ነው።[1]

ያዕቆብም ከላባን ተለይቶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ የተገናኙት የእግዚአብሔር መላእክት ናቸው «ያዕቆብም መንገዱን ሄደ የእግዚአብሔርም መንገደኞች ተገናኙት። ያዕቆብም ባያቸው ጊዜ አለ እኚህ የእግዚአብሔር ጭፍሮች ናቸው። የዚያንም ሥፍራ ስም መኻናይም ብሎ ጠራው ሁለት ሠራዊት ማለት ነው።»[2] ይህን የመሰለ የተለያዩ መላእክት ስም በመጥራት፣ በአጠቃላይም መላእክት በማለት በብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታዎች ላይ እናገኛለን።[3] በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታ ከመወለዱ ጊዜ ጀምሮ መላእክት እንዳሉ፣ ህልውናቸው የታወቀ እንደሆነ ቅዱስ ሉቃስ መስክሮ ጽፎልናል።[4] ጌታም ፈተናውን በፈጸመ ጊዜ ወደ እርሱ መጥተው ያገለገሉት መላእክት እንደሆኑ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነግሮናል።[5] በጌቴ ሰማኒ ጌታ በሚጸልይበት ጊዜ መልአክ መጥቶ እንዳጽናናው እናገኛለን።[6] በተለይም በመጨረሻው የፍርድ ቀን ክርስቶስን አጅበው መላእክት እንደሚመጡ ወንጌላዊው ማቴዎስ ገልጦልናል።[7] ይኽን የመሰለ አገላለጥ ከመስጠት ጋር የተወሰኑ መላእክትን ስም ለይቶ በመጥራት፣ በአጠቃላይ ግን የመላእክትን አገልግሎት በሚመለከት ነገር ብዙ መግለጫ እናገኛለን።[8] ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በዚህ ነገር ልዩ ጥናት አድርገው መግለጫ በሰፊው የሰጡ አሉ፣ ለምሳሌ ዲዮናስዮስ ዘአርዮስ ፋጎስ፣ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ሌሎችም እንዲሁ።[9]

ቤተ ክርስቲያናችንም ብዙ ነገደ መላእክት እንዳሉ እነርሱም የእግዚአብሔር ፍጥረቶች እንደመሆናቸው እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ፣ እግዚአብሔርን፣ የሚያመሰግኑ እንደሆኑ በሰፊው ታስተምራለች። በጠቅላላውም ስለመላእክት ሁናቴ እንደሚከተለው እንመልከት።

## ፩. የመላእክት ተፈጥሮ ፤

የመላእክት የተፈጥሮ ጉዞ እንዴት እንደሆነ ግልጥ አይደለም፣ የፍጥረትን ሁሉ ዕለቱን፣ ምክንያቱንም ሙሴ ሲናገር የነርሱን ሁኔታ እንዲሁ አልፎት እንደሄደ እናገኛለን።





ሌላ በቅዱስ መጽሐፍ ስለዚህ የሚገልጽ ክፍል ባለመኖሩ ለሊቃውንት ጥናት ችግር ፈጥሮ ይገኛል፣ ማለት ቀረብ ያለ ማስረጃ ይዘው አንዳንዶች ይህ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ የተሻለ አስረጅ እነርሱ የያዙ እየመሰላቸው በተለያየ መልክ አቅርበውት ይገኛሉ። አንዳንዶች መላእክት የመጀመሪያ ፍጥረቶች እንደሆኑ ይናገራሉ፣ ይኸም ማለት የዕለተ እሁድ ፍጥረቶች እንደሆኑ በመግለጥ ነው። ይኽንም ለማለት የደፈሩት የመላእክት ተፈጥሮ ግብር እምግብር ነው፣ የሚለውን አስተያየት ተከትለው ነው፣ ማለት መላእክት የተፈጠሩት ከብርሃን፣ ከእሳት፣ ከነፋስ ነው በማለት ነው፣ እነዚህ ግብሮች የተፈጠሩ በዕለት እሁድ ነውና።

ከነዚህ ግብሮች ተፈጠሩ እስከ ማለት የደረሱበትም «ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ፣ ወለእለ ይትላእክዎ ነደ እሳት» የሚለውን ቃል በመተርጎም ነው።[10] ሌሎች ደግሞ መላእክት የተፈጠሩ እምኀበ አልቦ ነው፣ ስለዚህም መናፍስት ረቂቃን ናቸው፣ ግብር እምግብር የተፈጠረው ሁሉ ግዙፍ ነውና፤ ከግዙፍ የተገኘውም ሁሉ ግዙፍ ነውና በማለት ነው። መላእክት ስለተፈጠሩበት ዕለት ግን አሁንም ዕለተ እሁድ መሆኑን የሚያረጋግጡ አሉ። ሁኖም የዕለቱን የሰዓቱን ነገር ባንከተለውም እግዚአብሔር አምላክ ከፍጹም ጥበቡ የተነሣ እርሱ ባወቀ ለምስጋናና ለአገልግሎትም ፈጥሯቸዋል።

መላእክት በእግዚአብሔር ፈጣሪነት መፈጠራቸውን ሐዋርያዊው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስረዳናል «ነገር ሁሉ በርሱ ተፈጥሯልና፣ በሰማያት ያለ ሁሉ፣ በምድርም ያለ የሚታይም የማይታይም፣ መናብርትም፣ አጋዕዝትም፣ ሊቃናትም፣ ሥልጣናትም፣ ሁሉም በርሱ ተፈጠሩ።»[11] መላእክት በኃይል በችሎታም የሚያክላቸውም የለም፣ ፅኑአን ናቸው። አምላክ የርሱን ፈቃድ ይፈጽሙ ዘንድ ስለፈቀደ የሚያቅታቸው እንዳይኖር ጽኑአን አድርጎ ፈጥሯቸዋል።[12] መላእክት እንደ ሥራቸው ከባድነት እንደ አገልግሎታቸውም ብዛት አምላክ እርሱ ባወቀ ሁሉን የሚችሉበት ኃይልና ጽንዓት ሰጥቶ ፈጥሯቸዋል፣ ስለዚህ በዚህ ዓለም ለእነርሱ ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል የለም። ይኸነንም በትክክል ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ይገልጥልናል «መላእክትም ከርሳቸው በኃይል በችሎታ የሚበልጡ



www.ethiopianorthodox.org

የስድቡን ፍርድ እያመጣባቸው በእግዚአብሔር ፊት» ሲል ያስረዳናል::[13] መላእክት ይፈጠራሉ እንጅ አያገቡም፣ አይጋቡም፣ አይባዙም አይበዙም::[14]

፱. ባሕርያቸው፣

የመላእክት ተፈጥሯቸው ወይም ወገንነታቸው ከሰማያዊው፣ ወይም ከረቂቁ ዓለም ስለሆነ፣ ስለነርሱ ባሕርያት ብዙ አይታወቅም፣ ይሁን እንጅ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጠው የማይዳሰስ፣ ረቂቅ የሆነ አካል አላቸው፣ ስለዚህም መናፍስት ይባላሉ:: ይኸም ሁኔታ እምኀበ አልቦ የተፈጠሩ መሆናቸውን ይገልጣል፣ ግብር እምግብር ተፈጥረው ቢሆን ኑሮ ግዙፋን በሆኑ ነበርና::

በሌላ መልክ ግን እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ግብርን አስገኘ፣ ፍጥረቱም ሁሉ ከዚህ ግብር እምግብር ተፈጠረ፣ መላእክት ግን እንደ መጀመሪያው ግብር አምላክ እምኀበ አልቦ አምጥቶ ፈጠራቸው፣ ስለዚህም ከማንኛውም ግብር የተለዩ ረቂቃ ናቸው::

ስለሆነ ግን ርቀታቸው እንደፈጣሪያቸው አይደሉም፣ እርሱ ፍጹም መንፈስ ነውና፣ እነርሱ ግን ፍጡራን እንደመሆናቸው የማይዳሰሱ ይሁኑ እንጂ አካል አላቸው:: ለአገልግሎት ከፈጣሪያቸው በተላኩ ጊዜ ግዛፍ ያላቸው መስለው ግዛፍ እንዳላቸው ሁነው፣ የተላኩበትን ሀገር ሰው መስለው፣ የሀገሩን ልብስ ለብሰው፣ በሀገሩ ቋንቋ እየተናገሩ ተገኝተዋል፣ ይኸ ሁሉ ሁናቴ ግዙፋን ያሰኛቸዋል:: መላእክት ግን ቅርጽ የለሽ መንፈሳውያን አካል ናቸው፣ መንፈስም ማለት አጥንት፣ ሥጋ፣ ጅማት የሌለው የማይዳሰስ አካል መሆኑን ሉቃስ ደህና አድርጎ ነግሮናል::[15] በዚህም መሠረት መላእክት መናፍስት ሲባሉ ሥጋ አጥንት፣ አካል የሌላቸው መሆኑን ያመለክታል:: «ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈስ» የሚለው ከነፋስ መፈጠራቸውን ሳይሆን ረቂቃን መሆናቸውን ከረቂቁ ዓለም መፈጠራቸውን ያመለክታል:: «ወለእለ ይትለእክዎ ነደ እሳት» ረቂቅነታቸውን ሲያመለክት ደግሞ ነበልባል አላቸው:: ለነበልባል አካል የሚጨበጥ የለውም ቅርጽም የለውም እንደዚህም ሁሉ መላእክት





ህልውና አላቸው እንላለን እንጂ ስለቅርጻቸው የሚያስረዳ ስለሌለ መናፍስትነታቸውን ብቻ እንቀበላለን:: «ዘይሬስዮሙ ለመላእኪቲሁ መንፈስ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት» የሚለውን ሊቃውንት ሲተረጉሙ መላእክት ለመጀመሪያ ጊዜ ግብር እምግብር ለመፈጠራቸው ማለት ከነፋስና ከእሳት ለመፈጠ ራቸው አስረጅ ያደርጉታል:: እንደገናም ፈጣንነታቸውን በመመልከት ነፋስ፣ ፈጻምያን ፈቃድ መሆናቸውን በመመልከት ነደ እሳት ይላቸዋል፤ ይሁን እንጂ ተፈጥሯቸው እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ ነው ብለው ያጸድቃሉ::

መላእክት ሁል ጊዜ በወንድ ምሳሌ ይታያሉ::[16] እንዲሁም በሰው ቋንቋ ሲናገሩ የሰውም ልብስ ሲለብሱ ይታያሉ::[17] ከዚህም ሁሉ ጋር ክንፍ እንዳላቸው ይነገራል፣ በክንፍም ታይተዋል::[18] እንግዲህ አካል ከሌላቸው ክንፍም ሊኖራቸው አይችልም፣ ክንፈ-ጸጋ ካልሆነ በቀር፣ ይሁን እንጂ እንደ ልብሱ፣ እንደ አካላቸውም ያለው ለሰው ይመስላል፣ ለርእይ ብቻ በዚህ መልክ መታየታቸውን ለመግለጥ ነው:: ወደ ተላኩበት አገር ፈጥነው የሚደርሱ ናቸው፣ እስኪሠሩና እስኪራመዱ ጊዜ የሚፈጁ አይደሉም:: መላእክት የወንድና የሴት ጾታ የሌላቸው የማይበዙ የማይባዙ የማያገቡ የማይጋቡም ናቸው::[19] መላእክት የማይሞቱ የማይለወጡ ናቸው፣ ነገር ግን እንደሚባዙ የገለጡም አሉ:: እንዲያውም ዝሙት ሠርተው ወደ ምድረ ፋይድ ወረዱ ይላሉ፣ ይኸንን የሚናገረው በዘፍጥረት ምዕራፍ 6:2 የሚገለጠው አንቀጽ ስለ ደቂቀ ሴት እንጂ ስለመላእክት አለመሆኑን የትርጓሜ ሊቃውንት ይናገራሉ:: የመላእክት መኖሪያቸው በዚህ ነው ወይም በዚያም ነው ብሎ ቅዱስ መጽሐፍ የገለጠው ወስኖም የሰጠው ነገር ከቶ የለም::

በየትኛውም ቦታ በየትኛውም አቅጣጫ ሁነው ሲለምኗቸው ግን ፈጥነው ይደርሳሉ፣ ይኸ ከሆነ ብሎ ግን እንደ እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ ናቸው ማለት አይገባም:: መላእክት ሰማያውያን ነገድ ሰማያውያን ፍጥረታት እንደሆኑ በሚደረግልን አገላለጥ ልንረዳ ይገባናል፣ ይኸውም መላእክት ከሰማይ ወረዱ፣ የሰማይ ሠራዊት ሲላቸው፣ መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ ሰማዮች ተከፍተው ታያላችሁ መላእክት ከሰማይ ተላኩ ሲልና



www.ethiopianorthodox.org

ሌላም ይኸን የመሳሰለ አገላለፅ ሲሰጥ ሰማያውያን መሆናቸውን ያመለክታል፣ ግን መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ የሚለው ቃል:

1ኛ ሲወጡ የሚለውን ቃል እያስቀደመ በመገኘቱ፣

2ኛ መውጣት መውረድ ካለ ዘንድ ወደ ምድራዊነታቸው የበለጠ ያተኮረ ይመስላል፣ ወይም የተወሰነ ቦታ የሌላቸው መሆኑን በበለጠ ያመለከተ ይመስላል:: መላእክት የተፈጥሮ ጠባያቸውን ያላሳደፉ በንጽሕና የሚገኙ ናቸው:: ይኸም በነፃ ምርጫቸው ያደረጉት እንጂ ከፈለጉ ኃጢአትም ከፋትም ለመሥራት ይችላሉ:: ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ከማዕረጉ የተዋረደው እንደነሱ መልአክ ነበር፣ የነርሱም ወገን የነበረ ነው፣ በራሱ ምርጫ ግን ኃጢአትን ሠራ፣ እርሱም ሠራዊቱም ከክብራቸው ተዋረዱ ማዕረጋቸውንም አጡ:: መላእክት የተፈጥሮ ጠባያቸውን ስላልለወጡ ንጽሕናቸውንም ስለጠበቁ ከእግዚአብሔር ይቀርባሉ፣ የእግዚአብሔርንም ገጽ ያያሉ:: በዚህም ተደስተው ይኖራሉ::

## ፫. የመላእክት ተግባራቸው፣

የመላእክት ተግባራቸው ዓይነቱም ስሙም የተለያዩ ነው:: በመጠኑ ሲገለጥ ግን፣

1. የአምላክ የስሙ ቀዳሽ የክብሩ ወራሽ መሆን ነው፣ ይኸም ከመሠረቱ መላእክት እንደ ሰው ለምስጋና መፈጠራቸውን ያመለክታል::
2. ስማቸው እንደሚያመለክተው መላእክት ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርንም ማገልገል ነው::[20] የሰውን መሥዋዕት ጸሎት ስእለትና አስተበቁዓት ያሳርጋሉ ወደ ፈጣሪያቸው ያቀርባሉ የእግዚአብሔርንም ምሕረተት ወደሰው ያስተላልፋሉ::[21]
3. የመላእክት ሌላው ሥራቸው የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆነውን ሁሉ መጠበቅ ነው፣ በተለየ ግን የሰዎች ጠባቂዎች ናቸው:: በኦርቶዶክስ እምነታችን እያንዳንዱ ሰው የተለየ ጠባቂ መልአክ አለው:: ይኸ ጠባቂ





መልአክ ካላጋለጠው በቀር እያንዳንዱ ሰው አደጋ አይደርስበትም::[22]

የመላእክት ጥበቃ በክርስቲያኖች፣ በዕብራዊያንና በእስላሞች እምነት የተደገፈ ነው፣ በኛም ምዕመናኑ ሳይቀር የሚያምኑት የሚቀበሉት ነው፣ ዐቃቤ መልአክ የሚባለውን ውቃቤ መልአክ እያሉ የሚጠሩትም እርሱን ነው:: ጠባቂ መልአክ ለእያንዳንዱ ሰው እንዳለው ጌታ ራሱ ሲያስረዳ «መላእክቶቻቸው በሰማያት ሁሉ ጊዜ የሰማዩን አባቴን ፊት እንዲያዩ» ይላል::[23]

እነዚህ ጠባቂ መላእክት እያንዳንዱን ሰው ከአደጋ ከመከራ የሚጠብቁ ሲሆኑ ከሰይጣን ፈተና አሽከላም ይጠብቃሉ፣ የሰው ልጅ ግን ፈቅዶ በነፃነቱ በደል ሲፈጽም ሲያዝኑና ያነኑ ሲመዘግቡ ይኖራሉ፣ እንዲሁም ወዶና ፈቅዶም በጎ ተግባር የሠራ እንደሆነ ዕድሜ ሲለምኑት ሲያማልዱት የሚኖሩ ናቸው:: መላእክት የእግዚአብሔር የሆነውን ሰው ሁሉ ይንከባከባሉ ይጠብቃሉ::[24] የታሠሩትን በመፍታት መንገድ በማሳየት ይረዳሉ::[25]

እግዚአብሔር በተቆጣ ጊዜ ደግሞ መዓቱን ጥፋቱን የሚያመጡ መላእክት አሉ::[26] በፍጻሜ ዘመን ደግሞ ጻድቃንን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ኃጥአንን ደግሞ ወደ ዘለዓለም ሥቃይ የሚመሩ መላእክት ናቸው::[27] በዚሁ ሁሉ አገላለጥ መላእክት የእግዚአብሔር ፈጻሚያን ፈቃድ እነደሆኑ እንረዳለን::

## ፬. የመላእክት ነገዳቸው፣

ለመላእክት ብዙ ቁጥር ብዙም ዓይነት የነገድም የማዕረግ ስም ኣላቸው በቁጥር የማይወሰኑ ስለሆነ፣ መጽሐፍ አእላፈ አእላፋት (የብዙ ብዙ) ይላቸዋል እንጂ መላእክትን በቁጥር የወሰነ መጽሐፍ ከቶ የለም::[28] መላእክት የማይቆጠሩ መሆናቸውን ጌታችን ኢየሱስ ሳይቀር ሲናገር «ወይስ የማልችል ይመስልሃልን አሁን ወደ አባቴ እለምን ዘንድ ከመላእክቱም ከ፲፪ቱ ዲቪዢን (ጭፍሮች) የሚበልጥ ይሰድልኛል» ብሏል::[29] ሉቃስም «ብዙ የሰማይ ሠራዊት



www.ethiopianorthodox.org

ከመልአኩ ጋር ነበር» አለ እንጂ ሊቆጥር አልቻለም::[30] አእላፍ መላእክትም ይላቸዋል::[31] በነገድ ግን ሊቃናት መናብርት አጋዕዝት ኃይላት፣ ሥልጣናት ኪሩቤል ሱራፌል እየተባሉ ይጠራሉ::[32] የነገድ ቁጥራቸው በሥነ ፍጥረት ፲ እንደነበር ግን በኋላ አንደኛው ነገድ በፈቃዱ አምላኩን ክዶ ከመዐረጉ እንደተወገደ ከክብሩ እንደተዋረደ፣ አሁን ግን ዘጠና ዘጠኝ ነገድ ብቻ እንዳሉ ይነገራል:: ከነዚህም ውስጥ የጥቂቶቹ ሊቃነ መላእክት ስም የታወቀ ሲሆን ብዙዎቹ አየታወቅም:: በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ስማቸው ተገልጦ ተጽፎ የሚገኙ በጣም ጥቂቶች ናቸው እነርሱም፤ ሊቀ መላእክት ሚካኤል::[33] ገብርኤል::[34] ሩፋኤል በጦቢት መጽሐፍ ላይ ይገኛል::[35] ሱራፌል::[36] ኪሩቤል::[37] የእነዚህ መላእክት ስም ብቻ በዚህ ዓይነት ተመዝግቦ ሲገኝ የሌሎች ፈጽሞ አይገኝም:: በመጽሐፈ ሔኖክ ግን የብዙዎች መላእክት ስም ተጠርቶ ይገኛል:: በዚህም በመጽሐፈ ሔኖክ ውስጥ የብዙዎቹ መላእክት ስም በአንዳንድ የጸሎት መጽሐፍ በመገለጡ የታወቁ ሲሆን የጥቂቶቹ ግን ተሰምቶም የማይታወቅ ነው:: እርሱም እንዲህ እያለ ያመጣዋል፣ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ይለዋል፣ መላልሶም ይጠራዋል፣ ገብርኤል በብዙ ቦታ ከመነሣቱ ሌላ በአበቦች ላይ የተሾመ፣ በገነት ባሉ ጻድቃን ላይም የተሾመ ይለዋል፣ እንዲሁም በኪሩቤል ላይ አለቃ የሆነ፣ በመላእክት ሁሉ ላይ አለቃ የሆነ እያለ ይናገርለታል::[38] ሩፋኤል፣ በብዙ ቦታ ላይ ያነሣዋል፣ ከዚህም በላይ በሰው ቁስል ላይ እንዲሁም በበሽታም ላይ የተሾመ መሆኑን ይናገራል::[39]

ኪሩቤል::[40]

ዑራኤል::[41]

ራጉኤል፣ ዲያብሎስንና ሌሎችንም አጋንንት የሚበቀላቸው ነው ይላል::[42] ዑራኤል፣ በመብራትና በነጎድጓድ ላይ የተሾመ::[43]

ሱርያል::[44]

አፍኒን::[45]





ፋኑኤል::[46] የዘለዓለም ሕይወትን ለሚወርሱ ተስፋ ሲሆን ንስሐ በሚገቡ ሰዎችም ላይ የተሾመ ነው ይላል::

ራሙኤል::[47]

ዛጡኤል::[48]

ሠራቅኤል::[49]

ዑርኤል::[50] በሰማይ ሠራዊት ላይ የተሾመ ይላል::

በዑርኤልና በዑራኤል መካከል ልዩነት ያደርጋል:: እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ሚካኤልን መጋቢ ብሉይ ሲለው ገብርኤልን ደግሞ መጋቢ ሐዲስ ይለዋል እስከ አሁን ድረስም በየክፍለ ሀገራችን ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶላቸው ሕዝብም አውቋቸው ስማቸው ሲጠራ የኖሩ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሩፋኤል ሲሆኑ ኪሩቤል ፬ቱ እንስሳ ሱራፌል ካህናተ ሰማይ ተብለው እነዚህ ብቻ ነበሩ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ራጉኤልና ዑራኤል በአዲስ አበባችን ብቻ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶላቸው ይገኛሉ::

## ፫. የመላእክት ክብራቸው፣

መላእክት ያለ ፍርሃት በባለሟልነት ከፈጣሪያቸውና ከጌታቸው ፊት የሚቆሙ ናቸው::[51] መላእክት ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ንጽሕናቸውን ያላሳደፉ፣ እምነታቸውንም ያላጎደሉ ከሕጉ ያልተላለፉ ስለሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ:: መላእክት የማማለድ የመታደግ ሥልጣን አላቸው ስለዚህ እንዲያማልዱንም እንለምናቸዋለን:: መላእክት የማዳን የመታደግ ሥልጣን እንዳላቸው ዳዊት በመዝሙሩ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል፣ ያድናቸዋልም» ይላል::[52]



www.ethiopianorthodox.org

# ም ዕ ራ ፍ ፳

## አጋንንት በጠቅላላው፣

፩. ህልውናቸው፣ ጋኔን ማለት ውዱቅ ጽሉዕ ማለት ነው፣ በብዛት አጋንንት ይባላሉ፣ በአለቃቸው በሰይጣን ሰይጣናት ይባላሉ:: ሰይጣንም ማለት ተከራካሪ ተቃዋሚ ባላጋራ ማለት ነው፣ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ይቃረናልና:: እንዲሁም ለሰይጣን ዲያብሎስ የሚል የመጠሪያ ቃል ይገኛል፣ ትርጉሙም ከሳሽ ማለት ነው፣ ይኸም የአጋንንት ሁሉ አለቃ እንደሆነ ይነገርለታል፣ ሁል ጊዜ በነጠላ ቁጥር ብቻ ይጠራል፣ እንዲሁም ሣጥናኤል፣ የሚል ጥንታዊ መልአካዊ ስም እንደነበረው ይነገርለታል፣ ትርጉሙም ቅሩብ መለኮት፣ አኃዜ መንጦላዕት ማለት እንደሆነ ይነገራል:: ከፈጣሪው ተጣልቶ ከወረደ በኋላ ግን ውዱቅ ጽሉዕ ርጉም ለማለት ጋኔን ተብሏል፣ ሠራዊቱም አጋንንት እንዲሁም እርሱ ሠይጣን ሁኖ ሠራዊቱ ሠይጣናት ተብለዋል:: በሌላ የማዕረግ ስም ሲጠራ ደግሞ ብኤልዜቡል ይባላል፣ የአጋንንት አለቃ ማለት ነው::

ሠይጣን ወይም፣ ሠይጣናት እያለች ሕልውናቸውን በመግለጥ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች:: ይኸም አስተያየት ጥንታዊም ዘመናዊም ነው፣ ማለት በብሉይ ኪዳን ጊዜ አጋንንት እንደነበሩ ቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው ይነግረናል:: እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ጊዜ እንደነበሩ በብዙ ቦታ እናገኛለ::[1] በተለይም በክርስቶስ ጊዜ ለሠይጣናት ብዙ ሥልጣን በሰው ልጅ ላይ እንደነበራቸው፣ በብዙም መልክ የሰውን ልጅ ያሠቃዩ እንደነበር እናገኛለን::[2] ክርስቶስን ሳይቀር ሠይጣን እንደተፈታተነው እናገኛለን::[3] ክርስቶስ ግን ሰውም ቢሆን ለሠይጣን ፈቃድ አልተገዛለትም::

በአጋንንት ህልውና ብዙ የዘመኑ ሰው አያምንም፣ እንዲሁ ሰው በሐሳቡ የፈጠረው እንጂ አጋንንት የሉም ይላል፣ አንዳንድ ደግሞ እስከ ክርስቶስ ዘመን አጋንንት እንደነበሩ በቅዱስ መጽሐፍ ምስክርነት እየተረዱ ይናገራሉ፣ ግን ክርስቶስ አጥፍቷቸዋል፣ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ የሉም ይላሉ:: እንዲሁም ሌላው አስተያየት አጋንንት ነበሩ አሁንም አሉ፣ ለሰው ልጅ



www.ethiopianorthodox.org



ወጥመድ አሽከላም እየሠሩ በግልጥ በሥጋ በስውርም በመንፈስ ሰውን ያሠቃያሉ፣ ያሰናክላሉ፣ ይላሉ:: የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ግን አሁንም አጋንንት ህልውና እንዳላቸው በግልጥም በስውርም ሰውን እንደሚፈታተኑ ታስተምራለች::

፪. የአጋንንት ተፈጥሮ፣ አጋንንት ወይም እርኩሳን መናፍስት እየተባሉ የሚጠሩ በመጀመሪያ መላእክት የነበሩ ናቸው፣ ስለዚህ ተፈጥሯቸው እንደመላእክት ነው፣ ወይም ከመላእክት ጋር ነው:: ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር እንደሌሎች መላእክት ባለመታዘዛቸው ከአለቃቸው ከዲያብሎስ ጋር ከማዕረጋቸው ተዋርደዋል፣ ከቦታቸው ተወግደዋል፣ ግን አሁንም መናፍስት ናቸው፣ መናፍስትም ይባላሉ፣ ስለዚህ ርኩሳን መናፍስት ወይም መናፍስት ርኩሳን እየተባሉ ይጠራሉ:: ብርሃናቸውም የተገፈፈ ስለሆነ፣ ጨለማ ናቸው፣ ስለዚህም መላእክተ ጽልመት እየተባሉ ይጠራሉ፣ አለቃቸውም የጨለማው አለቃ ይባላል::[4] አጋንንት አንድ ጊዜ ብቻ የተፈጠሩ እንጅ በየጊዜው የሚፈጠሩ፣ ወይም የሚራቡ አይደሉም:: አጋንንት እንደ መላእክት የማይሞቱ የማይጠፉ በመሆናቸው ሁል ጊዜ ያንኑ ቁጥር ይዘው ይገኛሉ:: የአንዱ ሊቀ መላእክት ጭፍራ (ሠራዊት) ብዙ ቁጥር ያላቸው እንደመሆናቸው ሳጥናኤልም ሲወርድ ያለውን ጭፍራ ሁሉ ይዞ ስለሆነ አጋንንት በቁጥር ብዙዎች ናቸው::

፫. የአጋንንት ባሕርይ፣ አጋንንት መንፈስ እንደመሆናቸው የማይራቡና የማይጠሙ ናቸው፣ ስለዚህ የማይበሉና የማይጠጡ ናቸው:: እንደ መላእክትም የማያገቡ የማይጋቡ የማይባዙ ናቸው:: አጋንንት የማይሞቱ የማይጠፉ መናፍስት ናቸው:: በመላእክት ዘንድ መላክተ ብርሃን እንዳሉ የታወቀ ሲሆን፣ ለነዚህ ግን ብርሃንነታቸው ተነስቷቸዋል፣ ስለዚህም መላእክተ ጽልመት ይባላሉ::[5]

፬. የአጋንንት ቦታ፣ አጋንንት ፍጡራን እንደመሆናቸው የተወሰነ ቦታ አላቸው እንጅ በዓለም ምሉዕ ሊሆኑ አይችሉም:: ይሁን እንጂ በዓለሙ ተሰራጭተው ከመገኘታቸውና ሰውን ለማሳት ትጉህ ከመሆናቸው የተነሣ ማንኛውንም ሰው በየት

መገኘታቸውና ሰውን ለማሳት ትጉህ ከመሆናቸው የተነሣ ማንኛውንም ሰው በየትኛውም ቦታ ሲፈታተኑት ይገኛሉ:: ይሁን እንጂ የተለየ ቦታ እንዳላቸው የት እንደሚኖሩ የሚያስረዳ መጽሐፍ የለም፣ ከሰማይ ወደ ምድር ወረዱ ከሚለው በቀር::[6] ሰውየው ለሠይጣን ካልተገዛ በቀር ሠይጣን የሰውን ሙሉ የተፈጥሮ ነፃነቱን የመውሰድ ኃይል የለውም፣ ብቻ ለማሳት ሲፈልግ ያነን ነገር ያስጎመጀዋል፣ ያስመኘዋል፣ እንዲሠራውም ይገፋፋዋል እንጂ በኃይል አስገድዶ ነፃነቱን ወስዶ አያሠራውም::[7] ለሠይጣን ለማሳት ብዙ መንገድ አለው፣ ማለት ውሸት እንዲዋሽ ያደርጋል፣ ይኸም ያማረለት እንዲመስል ያደርጋል::[8] ወጥመድ ያጠምዳል በዚያም ይይዛል፤ ፍላጎቱንም ያነሣሣል ያጓጓዋል:: ሁሉን ለመውጋት መውጊያ ያበጃል::

፭. <u>የአጋንንት ሥራ</u>፣ አጋንንት ነቅተው ተግተው የሚሠሩት ሰውን ለማሳት ወደ ክፋትም ለመምራት፣ ሰውን ለማሠቃየት ወደ ችግርም ለማስገባት ነው፤ ይኸ ዓላማቸው ግብ አለው፣ ይኸም ማንኛውንም ሰው የነርሱ ተገዢ ለማድረግ ነው:: በመሠረቱ የሠይጣን ሥራ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ተቃራኒ በመሆን ነው፣ ማለት እግዚአብሔር ሥሩ የሚለውን አትሥሩ፣ አትሥሩ የሚለውን ሥሩ በማለት፤ በጠቅላላም ሕጉን በማስፈረስ ነው:: አንድን ሰው ሠይጣን ሲፈታተን እስከ ማሳሰር እስከ ማስገረፍ ያደርሳል፣ ከዚያም በላይ ልዩ ልዩ ሥቃይ እንዲደርስበትና ሰውየው ሁሉንም ሰልችቶና ተመርሮ ከሕጉ እንዲወጣ ከመሥመሩ እንዲናወጥ ውጭ እንዲሆን ያስደርገዋል:: ስለዚህ፣ ማንኛውም ክርስቲያን ሁሉ ጊዜ ፈተና መኖሩን አውቆ መኖር ግዴታው ነው፣ እንዲህም ከሆነ ዘንድ የሠይጣን ጦር እንዴት እንደሚመጣ አውቆ ይዋጋል ድልም ያደርጋል:: ቅዱሳን የሚባሉ ሁሉ እንዲሁ ሠይጣንን ተዋግተው፣ ድልም ነሥተው የክብር አክሊልም ስላገኙ ነውና::

፮. <u>የአጋንንት ውድቀት</u>፣ አጋንንት ከክብራቸው የተዋረዱ ከማዕረጋቸው የወረዱ በተለያየ ምክንያት እንደሆነ ጥንታውያን አባቶች አስተያየት ይሰጣሉ::

1. አለቃቸው ሠይጣን አምላክነትን ስለተመኘ ነው፣ አምላክ በአምላክነቱ ሲገቡበት ቀናተኛ ነውና ሠይጣንን እንዲዋረድ አደረገው፣ ስለዚህም ከሠራዊቱ ጋር ወደቀ፣ ከዚህም የተነሣ ሠይጣን ርኩስ፣ ውዱቅ፣ ጽሉዕ እየተባለ ይሰደባል::

2. ሠይጣን ከቅንዐቱ ከምቀኝነቱም የተነሣ እርሱም ሠራዊቱም ወደቁ:: ሠይጣንም የቀናው በሰው ተፈጥሮ ነው፣ ማለት ሰው የሁሉ ገገር የሁሉም አዛዥ ሆኖ፣ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ በመፈጠሩ ቀናበት፣ ተመቀኘውም፣ እግዚአብሔር ግን ቅንዐትንና ምቀኝነትን አይወድምና ሠይጣንን ከማዕረጉ ሻረው ከክብሩ አዋረደው:: ይኸም ይታወቅ ዘንድ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን፤ ከዚህም እስከ ምጽአት ሰልፉንና ውጊያውን ከሰው ሁሉ ጋር እንዳደረገ ነው::

ሌሎችም ይኸን የመሳሰሉ አስተያየቶች ይገኛሉ፣ ይሁን እንጂ በጣም መስሎ የሚታየው የመጀመሪያው ነው፣ ስለዚህም አምላክ ይቅርታ አላደረገለትም:: በቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት ምዕላዶች ጎልቶ የሚነገረው አምላክነቱን ሽቶ ምስጋናም ፈልጎ እንደወደቀ ነውና::[10] እንዲሁም በሰው ተፈጥሮ ቀንቶ ለሰው በተሰጠውም ክብር ተመቅኝቶ እንደወደቀ በመጠኑ ይነገራል፣ ምክንያቱም ሰው ተፈጥሮ በርሱ ቦታ እንደገባ ይነገራልና::[11]

የሆነ ሁኖ ሠይጣን እስከ ክርስቶስ 2ኛ መምጣት ድረስ እንደወደቀ ይኖራል ማለት ሥራውንም እንደቀጠለ ይቆያል:: ከምጽአት በኋላ ግን በተወሰነ የግዞት ቦታ እርሱም ሠራዊቱም እንደሚዘጉ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል::[12]

## ምዕራፍ ፯

## ስለ ሰው በጠቅላላው፣

### ፩. የሥጋ ተፈጥሮ፣

በረቂቁና በግዙፉ ዓለም መካከል ከነፍስና ከሥጋ የተፈጠረ አንድ የተከናወነ ፍጥረት አለ፣ ይኸውም ሰው ተብሎ የሚጠራው ፍጥረት ነው:: ይኸንም ፍጥረት ልዑል እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

በዓይነቱና በቁጥሩ የበዛውን ፍጥረት ሁሉ ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ ለሰውም የሚያሻውን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ወዶና ፈቅዶ ለተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ራስ ወይም ጉልላት አድርጎ ሰውን ፈጠረ::[1] ሰው የተባለው ፍጥረት በሥጋ ምድራዊውን ወይም ግዙፉን ዓለም፣ በነፍሱ ደግሞ ሰማያውዪውን ወይም ረቂቁን ዓለም ወርሶ መስሎም የሚኖር ነው:: በሌላም ቃል ሲገለጥ ደግሞ ሰው የሁለት ዓለማት ባለቤት የሆነ ታላቅ ፍጥረት ነው:: ለዚህም ሁሉ ሊያበቃው የቻለው የመጀመሪያው የአፈጣጠሩ ሁኔታ ነው፣ ማለት ከመሬት የተፈጠረ እንደመሆኑ ሥጋው ምድራዊ ነው፣ ስለዚህም ምድራዊውን ዓለም ወርሶ ምድራዊውንም ዓለም መስሎ ይኖራል::

በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ በመፈጠሩ፣ በታላቁ ፈጣሪም እጅ በመሠራቱ፤ ሕይወተ ነፍስንም በማግኘቱ ደግሞ ሰማያዊ ነው፣ ሰማያዊም ይባላል፣ ስለዚህ ሰማያዊነቱን መንፈሳዊነቱን ይገልጣል፣ ወይም መንፈሳዊውን ዓለም መስሎ መንፈሳዊውን ዓለም ወርሶ እንደሚኖር ያጠይቃል:: ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔር የቃሉ ፍጥረት ነው፣ ማለት «ለይኩን፣» ባለ ጊዜ ሁሉም በየወገኑ እየተሠራ እየተፈጠረም ተገኝቷልና፣ ሰውን ግን እግዚአብሔር ተጠብቦ በእጁ ሠርቶታል፣ ሕያዊት ነፍስንም እምኀበ አልቦ አምጥቶ አሳድሮበታል::[2]

እግዚአብሔር ሰውን ተጠብቦ ተራቆም ይኽ ቀረኽ የማይባል ፍጹም ፍጥረት አድርጎ ይፍጠረው እንጂ ከወርቅና ከብር፣ ከሌሎችም የከበሩ ድንጋዮች እንዲሁም ተወዳጆች ከሆኑ ከልዩ ልዩ ማዕድናት አልፈጠረውም፣ እንዲሁ ከተርታው አፈር (ከትቢያ) አንስቶ ጭቃ አድርጎ ሠራው እንጂ::[3] ይኽም የሚያመለክተው ጥንቱን መሬት ነበርክና ከመሬት እነደ ተነሣህ፤ ደግሞም ወደ መሬት ትመለሳለህ የሚለውን አምላካዊ ቃል በኋላ እንደሚናገር በባሕርዩ አውቆ እንደ ፈጠረው የሚያስረዳ ነው::

እግዚአብሔር ከአፈር አንሥቶ ሰውን ይፍጠረው እንጂ ለስላሳ ሥጋን ጠንካራንም አጥንት አድርጎ ከአንድ አፈር ሠራው:: የነርሱን መገናኛ ወይም መያያዣ ጅማቶችን ሠራ::





ለአካላት ሁሉ ምግብን የሚያመላልሱ የደም ቧንቧዎችንም አስተካክሎ ተጠብቦ ሠራቸው:: የተለያዩ አካሎችን፣ ወይም ሕዋሳትን እንዲሁም፣ ስሜት የሚሰጡትን ክፍሎች በየደረጃቸው ውስጣዊና አፍአዊ አድርጎ በየመልካቸው ፈጠረ:: የተለያዩትን አካላት የሚሸከሙ፣ ቅርጹንም የሚሰጡ አጥንቶችን በየመልካቸው አደረገ፣ በዚህ መልክ ሰውን ያህል ታላቅ ፍጥረት ሠራ አከናወነም:: የመጀመሪያውንም ሰው ሠርቶ ሲጨርስ ስሙን አዳም አለው፣ ትርጉሙም አፈር ማለት ነው፣ ከዚህ በኋላ ነፍስን አሳደረበት::

## ፪. የነፍስ ተፈጥሮ፣

ሰውን እንዲህ አድርጎ መልክ ቅርጽ፣ ያለው የተከናወነ ፍጥረት አድርጎ ከፈጠረው በኋላ ሕያው ነፍስን አሳደረበት:: ማንኛውም ፍጥረት በክብደቱ፤ በመጠኑ፣ በቅርጹ ልዩ ልዩና ታላላቅ ፍጥረት ቢኖርም ሰው በእውቀቱ፣ በሕያውነቱ፣ በተናጋሪነቱ ከሌላው የበለጠ ከፍ ያለ እንዲያውም የሌላው ፍጥረት ሁሉ ባለቤትና ጠባቂ እንዲሆን አድርጎ አምላክ ፈጠረው፤ ሁሉንም ገንዘብ አድርጎ ሰጠው::[4] እንስሳትም ሌላውም ፍጥረት ሁሉ ጊዜያዊ የሆነ ተንቀሳቃሽነት ሕይወት አለው እንጂ ሕያው ነፍስ የለውም፣ ስለዚህ ሁሉም አሁን ይታያል ቆይቶ ይጠፋል፣ ሰው ግን ምንም በሥጋው ኃላፊ ቢሆንም በነፍሱ ሕያው ነው፣ እንዲሁም ሥጋው እነደገና ተነሥቶ አካል ገዝቶ ሕያውነት አግኝቶ ለዘለዓለም እንዲኖር አድርጎ ፈጥሮታል::[5] ከሌላው ፍጥረት ሁሉ ተለይቶ ሰው የእግዚአብሔር የስሙ ቀዳሽ፣ የክብሩም ወራሽ ሆኖ ሕያውነትን አግኝቶ እንዲኖር አድሎታል:: ሰው ከሥጋና ከነፍስ ከተለያዩ ባሕርያት ይፈጠር እንጂ አንድ ሰው ተብሎ መጠራቱን ቤተ ክርስቲያን ዶግማ አድርጋ ታስተምረዋለች:: ሰውም ፍጹም ፍጥረት ነው የሚባለው ወይም ሙሉ ሰውም የሚባለው ነፍስና ሥጋ ተዋህዶለት አንድነት ያላቸው፣ ነባቢነት፣ ለባዊነት፣ ሕያውነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው:: ሰውንም ሰው የሚያሰኙት ወይም የሚያስደርጉት እነዚህ ናቸው:: ከነዚህም አንደኛው ያልተስተካከለ ከሆነ፣ ሙሉ ሰው ሊሆን ወይም ሊባል አይችልም:: የእግዚአብሔርን አርአያነት የሚያጸድቁ እነዚህ ናቸው፣ ማለት አዋቂነቱ፣ ገዢነቱ፣



www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር በታች የሁሉ አስተዳዳሪ መሆኑ ነው:: በዚህም አነጋገር ሴቷም ከሌላ አካልና ባሕርይ ሳይሆን ሁሉም ከተፈጸመለት ነፍስና ሥጋ ከተዋሐደለት፣ ሰው ተብሎ ከሚጠራው ከአዳም ከአካሉ አካልን ከነፍሱም ነፍስን ነስታ የተገኘች እንደመሆኗ እርሷም ሰው ናት፣ ሰውም ትባላለች:: ስለዚህ በወንድና በሴት አካል ልዩነት ቢኖርም ሁሉም እኩልነት ያላቸው ፍጥረታት መሆናቸውን እንረዳለን፣ ማለት እግዚአብሔር ተጠብቦ ሥጋውን ከፈጠረለት ነፍስንም ከአሳደረበት አካል ላይ አንድ አጥንት ወስዶ፣ አሁንም ተጠብቦ ሌላ ሥጋ ሌላም ነፍስ ሳያወጣ ሙሉ አካልና ነፍስ ያላት ሰው አድርጎ ሴትን አቅርቧታልና::[6] እንግዲህ ወንድና ሴት ከእኩልነት ደረጃ አልፎ አንድ አካል ናቸው የሚባለው ከሥጋው ሥጋን ከአጥንቱም አጥንትን ከነፍሱም ነፍስን የነሣች ስለሆነች ሙሉ ሰው ስለሆነች ነው:: ይህም አገላለጥ በተጋቡት ወንድና ሴት ብቻ ሳይወሰን በጾታ በተለያዩ ወንዶችና ሴቶች መካከል በማንኛውም ሁሉ የሚጸና ቃል ነው:: ወንድም ሴትም ሰው ተብለው ይጠሩ እኩልነትም ይኖራቸው ዘንድ አምላክ የሁለቱንም መገኛ አንድ ግብር አደረገው::[7]

የነፍስ ተፈጥሮን ከአነሣን ዘንድ ስለነፍስ ተፈጥሮ ስለነፍስም ህልውና በየጊዜው ከቀረቡት አስተያየቶች እውነተኛ የሆነውን ትምህርት እንገልጣለን፣ በየጊዜው የቀረቡ አስተያየቶች እንደሚከተለው ያሉ ናቸው::

1. ነፍስ ቀድሞ የነበረች ናት፣ መዝገበ ነፍሳት አለ በዚያ ትኖራለች፣ አንድ ሰው በተወለደ ጊዜ ግን አንድ ነፍስ ይሰጠዋል::
2. ነፍስ በየጊዜው ትፈጠራለች፣ አንድ ሰው ሲወልድ አዲስ ነፍስ ይፈጠርለታል::
3. ነፍስ አንድ ጊዜ የተፈጠረች በሥጋም ያደረች ናት የሚሉ ናቸው::

ከነዚህም ውስጥ የመጨረሻው አስተያየት ኦርቶዶክሳዊ አስተያየት ነው ማለት ነፍስ አንድ ጊዜ ተፈጥራለች ከዚያ በኋላ ግን ትራባለች፣ ትባዛለች እንጂ አስቀድማ ተፈጥራ



www.ethiopianorthodox.org



የቆየች፣ በኋላ በሥጋ የምታድር አይደለችም፤ እንዲሁም በየጊዜው የምትፈጠር አይደለችም:: ነፍስ ቀድማ የነበረች ናት ከዚያ በኋላ ለየሰዉ ትታደላለች የሚለው አስተያየት ስሕተት ነው፣ ነፍሰ ቀድማ አልነበረችም፣ ቀድሞ የተገኘ፣ ነገር ከቶ የለምና፣ ሁሉም በዘመን የተፈጠረ ነው እንጂ:: ነፍስ በየጊዜው ትፈጠራለች፣ የሚለው ደግሞ አምላክን በየጊዜው እንደሚፈጥር እንደሚሠራ የሚያደርገው ነው፤ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ግን ፍጥረቱ ሁሉ በ6 ቀናት ተጠቃሎ እንዳበቃ ነው፣ ስለዚህ ይህ ዓይነት አስተያየት ቀዋሚ አይደለም፣ በቅዱስ መጽሐፍም አይደገፍም::[8] ነፍስ አንድ ጊዜ ከተፈጠረች በኋላ ከሥጋ ጋር እንደ ሥጋ ትራባለች ትባዛለች የሚለው ግን ቀዋሚ ትምህርት በቅዱስ መጽሐፍም የተደገፈ ነው «ወለእመ ተፈጥረ ነፍሰሙ ለአበው እምነነፍሱ ለአዳም በከመ ተፈጠረ ሥጋሆሙ እምነ ሥጋሁ፤ በአማን አዕረፈ እግዚአብሔር:: ወለእመ ኢተፈጠረ ነፍሶሙ ለእለ አቤል እምባሕርየ ነፍሱ ለአዳም አላ ይፈጥሮ በበጊዜሁ እምካልዕ÷ ኢፈጸመ እግዚአብሔር ግብሮ ወኢያዕረፈ በሰንበት ኦዲሁ ሀሎ በፈጢረ ነፍሳት፤ እምሰ ሀሎ በፈጢረ ነፍሳት ዓዲሁ ሀሎ በፈጢረ ሰማያት ወመላእክት::»[9] ማንኛውም ፍጥረት አንድ ጊዜ በአምላክ ፈጣሪነት ከተፈጠረ በኋላ መሰሉን አካሉን ማስገኘት እንዳለበት ሁሉ እንደ ሥጋችን ነፍሳችንም ከአባትና ከእናት ዘር ይገኛል አንድ ፍጹም ሰው ሆኖ ይኸ ጎደለው ሳይባል ይወለዳል:: አንድ ዛፍ ፍሬውን ወስደው ቢተክሉት በቅጠሉ፣ በቅርፊቱ በቅርንጫፉ በጠቅላላው በሌላው ሁኔታው ሁሉ ያንኑ የመጀመሪያውን ዛፍ መስሎ እንዲገኝ ነፍስና ሥጋም በአንድ ጊዜ ከአባትም፣ ከእናትም በሔደው ዘር አብረው ይሔዳሉ ከዚያ በኋላ ያኑ የመጀመሪያውን ሰው መስሎ ሥጋው ተቀርጾ አካል ለይቶ ሰው ሆኖ ሲገኝ ነፍሱም አብራ ተቀርጻ ባሕርይዋን ይዛ ትገኛለች:: ሥጋ በቅርጹም በመጠኑም ያደገውን ያህል ነፍስም አብራ ታድጋለች ማለት ዕውቀቱ ይዳብራል፣ አእምሮው ይሰፋል::

ስለዚህ ጥንታዊ በደልን ከአባቱና ከእናቱ በዘር ይወርሳል የሚባለው ስለዚህ ነው፣ ነፍሱም ሥጋውም በዘር ስለሚሄድ የኃጢአትም ቁራኝነት ከነፍሱ ጋር አብሮ በዘር ስለሚወርድ

ለባዊነት፣ ሕያውነት፣ ግን እነዚህ ሁሉ የአንዲት ነፍስ ጠባይ መሆናቸውን ይናገራሉ። ከዚህም ላይ ነፍስ መንፈስ የሚለው የአንዲት የነፍስን ሁኔታ ለመግለጥ እንደሆነ የታመነ ነው።

፬. <u>የሰው ነገድ ሁሉ ከ፩ ዘር መሆኑ፣</u>

የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት በጠቅላላ የሰው ነገድ ሁሉ ከነዚህ ከመጀመሪያዎቹ ፍጥረቶች ከአዳምና ከሔዋን የተገኘ መሆኑ ነው። በቀለም፣ በቋንቋ፣ በዜግነት፣ በሌላም ይኸን በመሳሰለ አኳኋን የሰው ነገድ የተለያየ ይምሰል እንጂ ከአንድ አባትና እናት የተወለደ ከአንድ ምንጭ የተቀዳ፣ ከአንድ ምንጭ የተቀዳ እንደሆነ የታመነ ነው። ይኸንም ቤተ ክርስቲያን ዶግማ አድርጋ እንደሆነ የታመነ ነው። ይኸንም ቤተ ክርስቲያን ዶግማ አድርጋ የምታስተምረው፣ በቅዱስ መጽሐፍም የተደገፈ ትምህርት ነው።[16] ሰው ሁሉ ከአዳምና ከሔዋን የተገኘ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ «አዳምም የሚስቱን ስም ሔዋን ብሎ ጠራት፣ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና» ሲል ያስረዳናል።[17] በብሉይ ኪዳን ይኸን የመሰለ ምስክር ሲኖር በሐዲስ ኪዳን ደግሞ «እርሱም ከአንድ ደም አሕዛብን ሁሉ ፈጠረ፣ በምድር ሁሉ ይኖሩ ዘንድ ሲል ያስረዳል።[18] ከአንድ ደምና ሥጋ ሰው ሁሉ የተፈጠረ እንደመሆኑ በአንድ በአዳም በደል ሰው ሁሉ ለኩነኔ ተዳርጎ ነበር፣ እንዲሁም በአንድ ክርስቶስ አዳኝነት ደግሞ የሰው ልጅ ሁሉ ነፃ ሊወጣ ቻለ።[19]

ምንም ቤተ ክርስቲያን የሰውን ነገድ አንድ አድርጋ ብታስተምርም፣ ቅዱስ መጽሐፍም ይኸነኑ ቢደግፍም ስለ ሰው ዘር ልዩነት በየጊዜው ልዩ ልዩ አስተያየት ከሰው ዘንድ መስንዘሩ ሐሳብም መቅረቡ አልቀረም፣ ይኸውም የሰው ነገድ ሁሉ የተለያየ እንደሆነ የሚገልጥ ነው። ለዚህ ማስረጃ የሚያደርጉት ይኸው ነገድ ሁሉ በቅርጹ፣ በቀለሙ፣ በአስተሳሰቡ፣ በሌላም ይኸን በመሳሰለው ሁሉ የተለያየ መሆኑን በመመርኮዝ ነው። ቤተ ክርስቲያን ግን በበኩሏ የቀለምን፣ የቅርጽን መለያየት እንዲሁ ያለፈችው አንድም የረሳችው ያልተገነዘበችውም ሆኖ አይደለም፣ ግን ለዚህ ሁሉ መነሻ የሚሆነው የአየር መለዋወጥ፣ የኑሮ ምቾትና ጉስቁልና የሌላም ልዩ ልዩ ለውጥ ይኸን የሰው ነገድ በመካከሉ ሊያመጣ እንደሚችል በመገንዘቧ ነው።





ካለው ልዩነት ይልቅ የሚያገናኘው ብዙ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች እንዲሁም በጠቅላላው ሰው መሆኑን የሁሉንም ዝምድና ወይም ግንኙነት የሚገልጽ አስረጅ በመስጠት ታስተምራለች። ይኸም ሰው በነገድ ቢለይም ከ፩ አባት መገኘቱን አንድ መሆኑንም የሚመሰክሩ ፫ ነገሮች አሉ፣

1ኛ. የቋንቋ ሁኔታ፣ የልዩ ልዩ ሀገር ሕዝብ ቋንቋ ከአቅራቢያው ሕዝብ ጋር የተመሳሰለ ነው። ይኸም ጥንታዊ አንድነቱን ያመለክታል። ምንም በጣም ከተራራቀው ሀገር ሕዝብ ቋንቋ ጋር በጣም የተራራቀ መስሎ ቢታይም አንዳንዱን ነገድ በአቅራቢያው ከአለው ሕዝብ ቋንቋ ጋር ማነፃፀሩ ጠቃሚ ነው።

2ኛ. በዕምነት በኩል የተመለከትን እንደሆነ እያንዳንዱን ሕዝብ በአንድ አምላክ ሲያምን እርሱንም ሲያመልክ ይገኛል፣ በዚህም አንድነቱን ይገልጣል፣ ማለት ፈጣሪ መኖሩን ሲያምን እርሱንም፣ ሲያመልክ መቆየቱን ያመለክታልና።

3ኛ. በኤትኖግራፊ በኩል የተመለከትን እንደሆነ የማንኛ ውም ሕዝብ መነሻ አንድ ሆኖ ይገኛል፣ ከዚያ በኋላ እያንዳንዱ ነገድ ወደ ተለያዩ አህጉሮች እንደሔደ ይገልጣልና። በመሠረቱ ግን ሰው ሲባል አንድ ነገድ፣ አንድ ትውልድም መሆኑን በትክክል ይገልጣል።

፭. <u>የሰው የመጀመሪያው ዕድል፣</u>

እውነተኛው ፈጣሪ እግዚአብሔር ሰውን ከተለያዩ ባሕርያት ይፍጠረው እንጂ ይኸ ቀረው ወይም ይኸ ጎደለው እንዳይባል አድርጎ ፈጠረው። ፈጥሮም እንዲሁ የጣለው የተለየውም አልነበረም፣ ይኸ ቀረበት ይኸም ጎደለው እንዳይባል አድርጎ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አሟልቶ ሰጥቶት ነበር። ስለዚህም ቅዱስ መጽሐፍ የሰውን ታላቅነት ሲገልጥ የእግዚአብሔር አርአያና አምሳል አድርጎ በመፍጠሩ የሁሉ ገዢ የሁሉም



www.ethiopianorthodox.org

ባለቤት በመሆኑ እንዲታወቅ አድርጓል፣ እርሱም እንዲህ ሲል ይገልጥልናል «እግዚአብሔር ባረካቸው፣ እግዚአብሔርም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፣ ግዟትም፣ የባሕሩንም አሣ ግዙ፣ የሰማዩንም አዕዋፍ በምድር ላይም የሚንቀሳቀሰውንም እንስሳ ሁሉ።»[20]

በእግዚአብሔር አርዓያና ምሳሌ መፈጠሩን ለመተርጎም በእግዚአብሔርንና ሰውን አንድ ያደርጉት በነፍስ አማካይነት እግዚአብሔርንና ሰውን አንድ ያደርጉት ነበር፣ ማለት ነፍስ ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የተገኘች እነደመሆኗ፣ የእግዚአብሔር አካልነት ያላት ወይም አምላካዊ ጠባይ ያላት ናት ይሉ ነበር፣ ስለዚህም የርሱን ምሳሌና አርዓያ እንደያዘች የሚናገሩ ነበሩ። እግዚአብሔር ጥበበኛ ፈጣሪ እንደመሆኑ ነፍስን ፈጥሮ በሰው ሥጋ ውስጥ አሳደራት እንጂ ከአምላክነቱ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላት ፍጥረት ናት። ሰው የእግዚአብሔር አርዓያና ምሳሌ የተባለውን ሊቃውንት ሲተረጉሙ፣

1. <u>በገዥነቱ፣</u> ሰው ከእግዚአብሔር በታች የሁሉ ገዢ የሁሉም ባለቤት በመሆኑ የእግዚአብሔር አርዓያና ምሳሌ ነው።[21]
2. <u>በአዋቂነቱ፣</u> ከእግዚአብሔር በታች እንደ ሰው ያለ አዋቂ ተናጋሪ አሳቢ ያለፈውን የሚመጣውንም ይገነዘብ ዘንድ ችሎታ ያለው ፍጥረት ከቶ የለምና።[22] ስለዚህ በአዋቂነቱ ሰው እግዚአብሔርን ይመስላል።
3. <u>በቅድስናው፣</u> ሰው በንጽሕናው በቅድስናው በክብሩ እግዚአብሔርን ይመስላልና፤ ንጹሕ ጠባይ ያለው ሰው ልጅነቱም ያልተወሰደበት፣ የመጀመሪያው ሰው ክብር ጸጋ ስለነበረው በአርዓያችን በምሳሌያችን የተባለ እርሱ ነው። ዛሬም ቅዱሳን ሁሉ በቅድስናቸው እንደ እግዚአብሔር የሆኑ ጸጋ ያላቸው ናቸው።[23]
4. <u>በሕያውነቱ፣</u> ሰው በሕያውነቱ እግዚአብሔርን ይመስላል፤ ሰው ቢሞትም ቢፈርስም እንደገና ተነሥቶ አካል ገዝቶ ሕያው ሆኖ የሚኖር ነው፣ እንደገናም ሞት የሌለበት ሁል ጊዜ ኗሪ ስለሆነ፣ እግዚአብሔርን ይመስላልና።[24]





ሰው በመጀመሪያ ጊዜ ይኸን የመሰለ ዕድል ይኸንም ያህል ክብር ተሰጥቶት ነበር፣ ሰው በአራዊት ዘንድ ተፈሪ፣ በመላእክት ዘንድ ተከባሪ ነበር፣ ሰው በጠቅላላው በምድር ያለው ፍጥረት ሁሉ ገንዘቡ የሆነ፣ ሰማያዊ ክብርንም በኋላ የሚወርስ ፪ቱም ዓላማት ባለቤት የሚሆን ነበር። ለሰው ይኸ ሁሉ ክብር በመስጠቱ የሰው ጥንታዊ ጠላት ሰይጣን ቀናበትና የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲያፈርስ አደረገው፣ ከዚያ በኋላ ግን የርሱ ተገዢ የፈቃዱም ፈጻሚ አደረገው።

## ም ዕ ራ ፍ ፫

### <u>ጥንተ አብሶ (ጥንታዊ በደል)፣</u>

ቤተ ክርስቲያናችን እንደምታስተምረው የሰው ነገድ አባት የሆነው አዳም በተፈጠረበት ንጽሐ ጠባይዕ ለብዙ ጊዜ አልቆየም፣ ወዲያው ሕግ አፍራሽ ሆኖ ወደቀ እንጂ። እንዲሁም የነገድ ሁሉ አባት እንደመሆኑ በርሱ መውደቅ ምክንያት ልጁን የልጅ ልጁን ሁሉ ይዞ ወደቀ፤ ይኸ የሰው ነገድ አባት የተባለው ከስህተት በኋላ ባሕርዩ ወደ ኃጢአት ያዘነበለ ስለሆነ ከርሱ የተገኙት ሁሉ በጠባያቸው ሕግ አፍራሽ ስለሆኑ በእግዚአብሔር በኩል ለቅጣት የተዘጋጁ ሆኑ። ይኸን የመሰለውን ቅጣት ያመጣው ጥንተ አብሶ የተባለው የአዳም ስሕተት ነው፣ ይኸም ጥፋት እንዴት እንደመጣ ለማጥናት ፫ ዓይነት መልክ እንሰጠዋለን፣

1. ኃጢአት እንዴት ተጀመረ?
2. የኃጢአትስ ጠባይዕ እንዴት ነው?
3. ለዚህ ጥፋት የተሰጠው ቅጣትና ቀጥሎ ያለው ውጤት ምንድን ነው? የሚል ነው።

1. <u>የጥንተ አብሶ አመጣጥ፣</u> አዳም አባታችን ሲፈጠር በመሠረቱ ንጽሐ ጠባዕይ የነበረው ሆኖ ያንንም እስከ ፍጻሜው ጠብቆ ቆይቶ ቢሆን፣ ከብዕዕና ማዕረግ ደርሶ እነደ መላእክት በቅዳሴ በምስጋና እንዲኖር ወደ እግዚአብሔርም ፈቃድ ብቻ እንዲያዘነብል አድርጎ ነበር የፈጠረው። አዳም በተፈጥሮ ጠባዩ



www.ethiopianorthodox.org

ጸንቶ የተሰጠውን ሕግ ጠብቆ ቆይቶ ቢሆን ኑሮ የሥጋዊውም የመንፈሳዊውም ዓለም ባለቤት ሁኖ ሕማም ሞት ሳያገኘው ለመኖር በቻለ ነበር፣ የኃጢአት ዋጋ ሞት ነውና፣ ስለዚህ ለሠራው ጥፋት ሁሉ የተከፈለው ዋጋ ሞት ሆነ::[1] ዲያብሎስ ከቅንዓቱ የተነሣ በእባብ አካል ተሠውሮ አዳምን ተፈታተነው፣ ስለዚህም ወደርሱ ፈቃድ ስቦ ኅትቶም አስገባው፣ የእግዚአብሔር ሕግን እንዲያፈርስና ቅጣት እንዲቀበል አስደረገው፣ ትልቁ ፍጥረት አዳም ከእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይልቅ የዲያብሎስን ፈቃድ መፈጸም አስደሰተው፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ የራሱን የግሉን ፍላጎት ማሟላት ጠቃሚ መስሎ ታየው፣ ስለዚህ እርሱም ሚስቱም አትብሉ የተባሉትን የዛፍ ፍሬ በሉ፣ በዚህም ጊዜ ከክብራቸው ተዋረዱ::[2]

አዳም ለጊዜው ኃጢአት መሥራቱ ብቻ ሳይሆን ባሕርዩም ወደ ኃጢአት ያዘነበለ ሆነና በእርሱ ጠባይዕ የሚወለደው ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ሆነ፣ ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ የነበረው አካሉ ከኃጢአቱ ብዛት የተነሣ ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ ከመሆን ራቀ፣ እግዚአብሔርን ከሚያስደስት ፈቃዱንም ከሚፈጽም ይልቅ የሰው ልጅ ከራሱ ጋር የሚነጋገር የራሱንም ፈቃድ የሚፈጽም ሆነ፣ ይኸም የኃጢአቱ ውጤትና የቅጣቱም ተከታታይ ነበር:: ክርስቶስ ሰው ሆኖ የኛን ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ የሰውን ባሕርይ እስከ አደሰው ድረስ የሰው ነገድ ሁሉ ባሕርዩ አንድ እንደመሆኑ ኃጢአቱም የወል ሆኖ ከባሕርዩ እየወረሰ የኃጢአተኛ ልጅ ኃጢ አተኛ እየተባለ ኑሯል:: ከዚህም ከጥንተ አብሶ ከተባለው ኃጢ አት ማንም የሰው ልጅ የሆነ ሁሉ ሊያመልጥ አልቻለም፣ ሁሉም በደለኛ ተባለ::

በአዳም በደል የሰው ልጅ ሁሉ በደለኛ እንደተባለና በበደሉ ሁሉም እንደገባ፣ ስለዚህም ቅጣቱ በሁሉ ዘንድ የተላለፈ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ ትውፊትም በሰፊው ያስረዳሉ::[3] ከሰው ወገን ምንም ጻድቅ እንደማይገኝ ሁሉም በደለኛ እንደሆነ፣ ጻድቅ ኢዮብ እንዲህ ሲል ይመሰክራል «ከርኩስ ማነው ነጽሕናን የሚያወጣ? አንድም የለም፤ የሰው ዕድሜ በምድር ላይ ፩ ቀን ቢሆንም»[4]::





ሰው በመሠረቱ በኃጢአት መወለዱን ኃጢአቱን ከዘሩ ጋር አብሮ እንደሚወርሰው ንጉሡ ዳዊትም እንዲህ ይላል «እስመ ናሁ በኃጢአት ተፀነሥኩ ወበአመፃ ወለደተኒ እምየ::[5]» ዳዊት በዘር ቁራኝነት ከያዘው ኃጢአት እግዚአብሔር እንዲያላቀው ጸለየ:: ከወላጆቻችን ከወረስነው የዘር ቁራኝነት ካልወጣንና ከእግዚአብሔር ካልተወለድን በቀር መንግሥተ ሰማያትን ልንወርስ እንደማንችል ወንጌላዊው ዮሐንስ ገልጦ አስረድቶናል::[6] እንደርሱም አገላለጥ ከሥጋ ወላጆቻችን ኃጢ አትን ወረስን ኃጢአተኞች እንደምንሆን ኃጢአተኞችም እንደምንባል ከውሀና ከመንፈስ ተወልደን የእግዚአብሔር መንግሥትን መውረስ እንዳለብን ገልጦ አስተምሯል::[7] በፍጥረታችን ንጹሕ ስንሆን ከዘር በወረስነው ኃጢአት የእርግማን ልጆች እንደሆን ሐዋርያው ጳውሎስ ገልጦ ጽፎልን እናገኘዋለን::[8]

ከአዳም ውድቀት የተነሣ ኃጢአት የሰው ሁሉ ውርስ እንደሆነ፣ ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደሆን አንድም እንደተባልን፣ ኃጢአትም ሁሉን እንደገዛ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው ልንረዳ እንችላለን::[9] እንግዲህ ኃጢአት ከአዳም የተነሣ ተገኘች፣ የሰውም ዘር ሁሉ ከእርሱ እንደሆነ፣ ኃጢአትም ከእርሱ የተነሣ ለሰው ልጅ ሁሉ የወል ሆነ:: የሰው ልጅ ሁሉ ከአዳም እንደመወለዱ ኃጢአትን ቢወርስም ክርስቶስ ግን ከአዳም ዘር ቢወለድም የኃጢአትን ቁራኝነት አስቀድሞ ሽሮና አጥፍቶ ነው ሥጋን የተዋሃደ «እንዚሖ ሥጋሃ ላዕሌሃ ኀደረ፣ ቀዲሶ ኪያሃ ኀበ ማርያም ኀደረ»[10] ይላልና:: የመጀመሪያው አዳም ለኃጢአት መነሻ ምክንያት እንደሆነ፣ ፪ኛው አዳም ክርስቶስ ደግሞ የሥርየት መገኛ ሁኖናል::[11] በአዳም ምክንያት የሰው ልጅ ሁሉ ከተስፋው ውጭ እንደነበር፣ በአዳምም የሆነውን ሁሉ እንደወረሰ እንዲሁም በክርስቶስ ጽድቅ ስለሆነ፣ በፍቅርና በሃይማኖት እርሱን የተቀበሉ ሁሉ፣ የርሱ ልጆች ናቸው፣ ስለዚህም የርሱ የሆነውን ሁሉ ይወርሳሉ::[12]

፪. <u>የኃጢአቱ ጠባይዕ</u>፣ የበደለውም ያልበደለውም የአዳም ልጅ በመሆኑ ብቻ ኃጢአተኛ ተባለ፣ ስለዚህ ሁሉም ከእግዚአብሔር ጽድቅ ውጭ ሆነ:: አእምሮውም ፈጽሞ



www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር ህልወት ውጭ ሆነ፣ ሰውም ፈጽሞ ወደራሱ ፍላጎት ብቻ አዘነበለ፣ ይኸም ከቅጣቱ ከፍተኛው ገጽታ ነበር፣ የመጀመሪያው የሰው በደል ያመጣው ቅጣት ተገቢና ሕጋዊ መሆኑን ሁሉ ይገነዘባል:: የኃጢአቱም ጠባይዕ ከብዙ አቅጣጫ ይታያል፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን ማጣት፤ ብልየትን ማግኘት (ማርጀት) ከፍተኛው ቅጣት ነበር:: እንዲሁም የመንፈስ ማኅደር ከመሆን ፈጽሞ የሰው ልጅ መለየት፣ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር መራቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ጥብቅ ግንኙነት ማቋረጥ የመጨረሻው የሰው ቅጣት ነበር:: እግዚአብሔር ከኛ ፊቱን መመለስ ከጸጋውም ፈጽሞ መራቆት፣ ከዚሁም የቀጠለና የቅጣቱ ውጤት ነበር:: ለሰው ወገን ሁሉ በሥጋዊ ዓለም መዋጥ የእግዚአብሔር አርዓያንና ምሳሌነትን ማጣት የሞት ሞት ነበር:: በጥንተ ተፈጥሮ የነበረው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር አርዓያና ምሳሌነት በእርግማን ጠፍቶ ትርጉሙም ተለውጦ መቅረት ከስሕተት የተነሣ ነው:: የስሕተቱ ከባድነት የአእምሮ መጨለምን ማለት ፈጣሪን አለማወቅ ወይም መርሳት፣ ፍጡራንን ማምለክና የፍጡ ራን ተገዥ መሆንን አስከተለ:: በጠቅላላም የሰው ወገን ሁሉ የተፈጥሮው ነፃነት ተወስዶበት በሥጋ ምኞት ብቻ መሳብ መነኀተት ዕድሉ ሆነ:: እነዚህ ጸጋዎች ሁሉ ከሰው ልጆች ተወግደው ሰው ከመንፈስ ተራቁቶ ነፃነቱን አጥፍቶ ለብዙ ዘመናት በሰይጣን ባርነት ይኖር ነበር:: ከሊቃውንት ውስጥ ግን ከላይ የዘረዘርናቸውን በሰው ልጅ ላይ የደረሱትን ጉዳቶች በ፪ እና በ፫ መልክ አጠቃልለው የሚናገሩ አሉ፣ ይኸንም ሲሉ ሌላው ሁሉ በነዚህ ይጠቃለላል፣ እነዚህንም ከማጣት የተነሣ ሌሎች ችግሮች በሰው ልጅ ላይ ሊመጡ ቻሉ ይላሉ::

እነዚህም ፫ቱ የቅጣት ዓይነቶች የተባሉት ለአዳም በጥንተ ፍጥረት የተሰጠው ልጅነት መወሰድ፣ በመንፈስ ማርጀት /ብሌት ማግኘት፣ ከመንፈስ ቅዱስ ማኅደርነት መውጣት ናቸው፤ በነዚህም ምክንያት ብዙ ጉድለቶች በሰው ሕይወት ላይ መድረሱ የታወቀ ነው::

ሌሎች ደግሞ ሙሉ ነፃነቱን፣ በተፈጥሮ የተሰጠውን ዕውቀቱን ማጣቱን ልጅነቱን ማጥፋቱን ከፍተኛ አድርገው





አጉልተው ይናገራሉ:: እንግዲህ የሰው ልጅ በጥንተ ተፈጥሮ የተሰጠው ጸጋ ሁሉ በስሕተት ምክንያት መጥፋቱ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ የኃጢአቱ ጠባይዕ በመላ በሰው ልጅ ባሕርይ የተዋሃደ መሆኑ በአንደኛው ጸጋ ማጣት ብዙ ክብርና መብት መጉደልን ሊያስከትል ይችላል፣ ይኸም ከሆነ የሰው ልጅ በመላ ሕይወቱ በግብርናት ዲያብሎስ መያዙ ሙሉ መብቱ ሙሉ ነፃነቱ መጥፋቱ የታወቀ ነው:: ሁሉንም የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ፣ ከመንፈስ ቅዱስ መለየቱ ሁሉንም ሊያሳጣ ይችላል:: እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር የሰው ልጅ በመታረቁ ይኸ ሁሉ እንደ ተመለሰለት የሰው ልጅ በሐዲስ ተፈጥሮ እንደ ጥንተ ተፈጥሮው እንደሆነ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ:: ይኸም የሆነ በጥንተ አብሶ በደረሰው በደል የሰው ልጅ ያጣውን ጸጋ ሁሉ ለመመለስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆኑና በሰው በደል ገብቶ በመሰቀሉ ነው::

አዳም የሁሉ አባት እንደመሆኑ ኃጢአቱ ለሁሉ ደርሷል፣ ክርስቶስ በጥንተ አብሶ ለበደሉ ተሰቀለ ብንልም የአዳም ኃጢአት ሁሉን ከአደረሰ ክርስቶስም በምልዐት ኃጢአት ተሰቀለ ለማለት ያስችላል:: የመጀመሪያው አዳም በስሕተቱ ሁሉን እንደሚይዝ ለሁሉም እንደሚወክል ፪ተኛው አዳም ክርስቶስ በማዳኑ ሁሉንም ይይዛል ማዳኑም ለሁሉ ነውና:: ክርስቶስ የካሰው ለአዳምና ለልጆቹ ነው፣ በጠቅላላም ለዓለም ሁሉ ነው፣ ኃጢአት በአንደኛው ሰው ምክንያት ለዓለም ሁሉ ደርሳ እንደነበረች የጌታችን የኢየሱስም የማዳን ሥራ ለሰው ልጅ ሁሉ ደረሰች::[13] ክርስቶስ ሰው እንደመሆኑ ለኃጢአተኛው ሰው ሁሉ እንደሚወክል የማዳን ሥራውም እንደ አምላክነቱ ሁሉን የሚመለከት ሁኖ ይገኛል፣ ስለዚህም የሰው ወገን ሁሉ ለድኅነት ተመዘገበ፤ ክርስቲያኑ ሕዝብ ሁሉ የዳነው ሕዝብ ተብሎ ይጠራል::

፫. <u>በጥንተ አብሶ ምክንያት የመጣው ቅጣትና ቀጥሎ ያለው ችግር</u>፣ አምላካዊ ሕግን በራሱ ፈቃድ የሰው ወገን ስለተላለፈ የመተላለፉ ውጤት የማያቋርጥ ቅጣትን አስከተለ፤ ማለት አጥፊውንም ያላጠፋውንም የሰው ወገን የሆነውን ሁሉ ከአዳም እስከ ሙሴ፣ ከሙሴም እስከ ክርስቶስ ድረስ ሞት ገዛው:: በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ቅዱሳን እንዲሁም የአባቶች



www.ethiopianorthodox.org

አባት የተባለውን አብርሃምን ሳይቀር ሞት ገዛው:: እንዲሁም ራሱን የሕግ ባለቤት የነበረውን ሙሴንም ሳይቀር ሌሎችንም ቅዱሳን ሁሉ ሞት ገዛቸው::[14]

የበደለውንም ያልበደለውንም ሞት ገዛው አለ እንጂ እገሌንና እገሌን ብቻ አላለም፣ ወይም ከእገሌና ከእገሌ በቀር ብሎ ለይቶ የተነገረለት የለም:: የሰው ወገን ምሕረት የሚተላለፍበትን አምላካዊ ሕግን በመጣሱ ያ ምሕረታዊ ሕግ በሰው ላይ ፈራጅ ሕግ ሁኖ ቀረበ፣ ስለዚህ በዘር ቁራኝነት ብቻ የበደለውንም ያልበደለውንም ሞት ገዛው:: በስሕተት ምክንያት የመጣው ቅጣት ጊዜያዊና ዘለዓለማዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፣ እንዲሁም ሥጋዊና መንፈሳዊ ሊባል ይቻላል:: ይኸውም ከጊዜያዊና ሥጋዊ ሞት ጀምሮ ዘለዓለማዊና ነፍሳዊ ሞት በማስከተል ሰውን ሊገዛው የቻለው ነው:: በስሕተት ጊዜ አምላክ ለአዳም ከአሰማው ድምፅ «ወደ ተፈጠርክባት ምድር እስክትመለስ ድረስ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ» የሚል ነበር::[15] ነፍስ ከሥጋ በምትለይበት ጊዜ ሥጋ ወደ መቃብር ነፍስ ደግሞ ወደ ቁራኝነት ይሄዳሉ፣ በዚህ መልክ የሰው ልጅ ወዶም ሳይወድም የኀጢአት ባሪያ ሁኖ መኖር ግድ ሆኖበት ነበር:: ሰው በጥፋቱ ምክንያት የመጣበት ቅጣትና የሚቀጥለው ችግር የተባለው ይኸ ነበር:: እንዲህ ሁኖ የሰው ወገን መንፈሱ ከእግዚአብሔር ተለይቶት፣ በሥራውም ሁሉ ሳይደሰት ረድኤት ርቆት ለብዙ ዘመን ኖረ:: ማንኛውም ሥጋዊ ሕማም ቢሆን በሕግ አፍራሺነት ከመጣው ቅጣት የተነሣ እንደሆነ የታወቀ ነው:: ሰው በመጀመሪያ ባይበድል ኑሮ ከሕይወት ዛፍ ፍሬን እየበላ ለዘለዓለሙ እየታደሰ ሞትን ሳያይ ይኖር ዘንድ የአምላክ ውሳኔ ነበር::[16] ለዚህም ከአዳም ጥፋት በኋላ ወዲያው በሰው ላይ ሞት የሞት ሞት ታዘዘ፣ ማለት የሥጋም የነፍስም ሞት በሰው ሁሉ መጣ፣ የኀጢአት ዋጋው ሞት ነውና::[17] ይኸ ሁሉ ቅጣት ይኸም ሁሉ ሥቃይ እንደገና ከሰው ወገን ሊነሣ የቻለውና በዚህም ፈንታ ጸጋ ምሕረት ለሰው ልጅ የተሰጠው ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረትና ዓለምን በማዳን ሥራው ነው:: ከአዳም ጥፋት የመነጩ ወደሰውም ዘር የተላለፉ ዓይነታቸው ስማቸው





የተለያዩ ሥቃዮች ሁሉ በኢየሱስ አዳኝነት ሊጠፉ ቻሉ:: ከዚህ በኋላ ሰው የጸጋ ባለቤት ሆነ፣ በአንድ ሰው ኀጢአት ሞት በሰው ሁሉ ላይ እንደሰለጠነ እንዲሁ በአንድ ሰው ጽድቅ ምክንያት በሁሉ ላይ ጸጋ ጽድቅ መጣ:: ኀጢአት የበዛውን ያህል በኢየሱስ አዳኝነት ጽድቅ ሰላም ሞገስ ለሰው ልጅ ሁሉ ሆነ::[18] የሕይወታችን አስገኝ አዳኛችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን:: ሥጋዊው ሞት እንዳለ ቢቀጥልም እንኳን አስፈሪነቱን አስደንጋጭነቱን አጥቷል፣ ምክንያቱም ማንም በሥጋ ቢሞት ኢየሱስ ክርስቶስ የባረከው ስለሆነ፣ ወደርሱ በነፍሱ ለመዛወር ይችኩላል፣ ደስም ይለዋል እንጂ አይፈራም፣ የሞት ሞት የለበትምና:: «የታለ መውጊያህ ሞት ሆይ ማቸነፍህ የታለ ሲኦል ሆይ»[19] እያለ ማንም ክርስቲያን ሊናገር በክርስቶስም ሊመካ ችሏልና::

## ክፍል ፫

## ድኅነተ ዓለም::

## ም ዕ ራ ፍ ፩

### ምሥጢረ ሥጋዌ በጠቅላላው÷

### ፩. የድኅነተ ዓለም ዕቅድ÷

በአለፉት ምዕራፎች እንደተገለጠው ይኸ ዓለም ተከናውኖ ይኸ ቀረህ÷ ይኸም ጎደለህ በማይባል መልክ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ተፈጥሯል፤ የፍጥረቱም ራስ ወይም ጉልላት የሰው ልጅ ሆኗል:: ቢሆንም በሰው ልጅ መውደቅ ምክንያት ደግሞ ሁሉም አቅጣጫውን ለውጧል÷ ማለትም ሁሉም ለጥፋት የተዳረገ ሆኗል:: ለብዙ ዘመናትም የፍጥረቱ ሁሉ ዕድል ሞትና ተስፋ መቁረጥ ሆነና የሰው ልጅ በራሱ ጥረት ሊድን ከጥፋቱም ሊመለስ ሳይችል ኑሯል÷ ስለዚህም የሰው ልጅ ሁሉም የተፈጠረበትን (የተወለደበትን) ዕለት ሲረግም ኖሯል::[1]

ብዙ አባቶች ነቢያትም ስለድኅነታቸው የብዙ እንስሳትን ደም ቢያፈሱ÷ ስብም ቢያጤሱ ልዩ ልዩ መሥዋዕትም ቢሠዉ



www.ethiopianorthodox.org

ሥራቸው ወደእግዚአብሔር ደርሶ የተፈለገውን ዓላማ ሊያስገኝ፥ ከተፈለገውም ግብ ሊያደርስ አልቻለም፥ ምክንያቱም አምላክ ሁሉንም ለሞት ዳርጎት ነበር፤ የምህረትም ፊቱንም አልመለሰውም ነበርና::

የዓለም ድኅነት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንና ራሱንም መሥዋዕት አድርጎ ከመስጠቱ ጋር የተያያዘ ነበር፥ ማለትም ያለርሱ ንፁሕ ደም ዓለም ሊድን አይችልም ነበርና:: እግዚአብሔር አብ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን ፩ ልጁን ወደዚህ ዓለም ላከ፥ ከሰማየ ሰማያት እንዲወርድ ሰውም እንዲሆን ፈቀደ፥ ማለት ለሕማም ለሞት ለመስጠት ቅዱስ ፈቃዱ ሆነ:: ስለዚህም በአባቱ ፈቃድ በራሱም ፈቃድ፥ በመንፈስ ቅዱስም ሥምረት ወልድ ዋሕድ የአብ ቃል ሰው ለመሆን ወደዚህ ዓለም መጣ:: ነቢያትም ወልድ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱና ዓለምንም የማዳኑ ዕቅድ ተገልጦላቸው "ፈኑ እዴከ፥ አንሥእ ኃይለከ ወነዓ አድኅነነ" እያሉ ትንቢት ተናገሩ ሱባዔም ቆጠሩ:: የክርስቶስን መምጣትና የዓለሙን የማዳን ሥራ በትንቢታዊ ቃላቸው አበሠሩ:: ይኸንን ምሥጢር ራሱ ክርስቶስ ገልጦ "አብርሃም አቡክሙ ተመነየ ከመ ይርአይ ዕለትየ፥ ርእየ ወተፈሥሐ" ሲል በመናገሩ ያረጋግጥልናል::[2] እያንዳንዱ ነቢይ ደግሞ ልክ ክርስቶስ አሁን የተወለደ ዓለምንም ያዳነ እየመሰላቸው እየተደሰቱ ትንቢት የተናገሩ አሉ፥ እንዲሁም ደግሞ ሁኔታው የዘገየም እየመሰላቸው በቶሎ ላከው፥ በቶሎ ና እያሉ የጸለዩ፥ ያመለከቱ ጩኸታቸውን ከፍ አድርገው ያሰሙ ብዙዎች ናቸው::[3]

ጊዜው ሲደርስ ግን የዓለሙ መድኃኒት የሕዝቡን በደል የሚያስተስርየው ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልደ፥ በዚህም ዓለም ተገለጠ፥ ኢየሱስ ብሎ ስሙን እንዳመለከተው በርግጥም የዓለሙ መድኃኒት እርሱ ሆነ::

ጌታችን ኢየሱስ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከሚፈጽመው ቅዱስ ተግባር ጋር እየተገለጠላቸው ነቢያት በተለያየ መልክ ሰይመውታል:: ስሞችም ከግብሩ ጋር የተያያዙ ወይም ሥራውን የሚተረጉሙ ስለነበሩ በፍጻሜ ዘመን





ስሞችና ትርጓሜዎች የኢየሱስን ሕይወት ገላጮች ሁነው ተገኝተዋል:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው::

ከሦስቱ አካላት አንደኛው አካል እግዚአብሔር ወልድ ነው:: እግዚአብሔር ወልድም የአብ የባሕርይ ልጁ ስለሆነ፥ ወልደ እግዚአብሔር ይባላል::[4] ቃሉም ስለሆነ፥ ቃለ እግዚአብሔር ይባላል::[5] መድኃኒትም ስለሆነ ኢየሱስ ይባላል::[6] መሢህ ወይም ንጉሥ ስለሆነ ክርስቶስ ይባላል::[7] የእኛን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ በእኛ የተፈረደውን ፍዳ ራሱ ተቀብሎ ስላዳነንና ሁል ጊዜም እኛን ተዋህዶ አንድነቱን ከእኛ ጋር አድርጎ ስለሚኖር አማኑኤል ይባላል::[8] የሥጋም የነፍስም ፈጣሪያችን ገዢያችን እርሱ ስለሆነ፥ በተለይም ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ አውጥቶ ከፍዳ ከመርገም አድኖ ስለሚገዛን ጌታ እግዚእ ይባላል:: ይህንም የመሰለ ከግብሩና ከባሕርዩ ጋር የተስማሙ ብዙ ስሞችና ቅጽሎች አሉት::

## ፪. ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ መሆኑ፤

እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ተፈናዊ፥ በተለየ ስሙ ወልድ፥ በተለየ ኩነቱ ተወላዲ፥ በባሕርዩ ደግሞ ነባቢ ይባላል::[9] ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል፥ ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወለደ፥ ተወለደ እንጂ አልተፈጠረም፥ ስለዚህ "ዘተወልደ ወኢኮ ዘተገብረ" ሲሉ ሰለስቱ ምዕት አስረድተዋል::[10]

እንዲህም ስለሆነ፥ ፍጹም አምላክ ነው፥ ከአባቱም ጋር ትክክል ነው፥ በመለኮት አንድ ነውና:: ሁሉ በርሱ ሆነ ያለርሱም ምንም የሆነ የለም::[11] የክርስቶስን አምላክነት፥ የርሱንም ብቻ ንጉሥነት ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ "አሁንም የዘለዓለም ንጉሥ የማይጠፋ ብርሃን፥ የማይታይም አንድ አምላክ ክብር ምሥጋና ይገባዋል ለዘለዓለሙ አሜን" ሲል አስረድቷል::[12] እግዚአብሔር ወልድ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው:: እርሱ ቀዳማዊ አምላክ ነው፥ እርሱን የሚቀድም የሚበልጥም ከቶ የለም እርሱ የመጀመሪያውና የመጨረሻው አምላክ ነው::[13] ያ ቀዳማዊ አምላክ ቃለ አብ በፍጻሜ ዘመን ሰው ሆኖ ሥጋንም ለብሶ ለሰው ልጅ ተገለጠ፥ አንድነቱንም ከሰው ጋር አደረገ፥



www.ethiopianorthodox.org

ይላል፥ "የእሥራኤል ንጉሥ የሚያድነውም እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ፥ እኔ በፊት ነኝ፥ እኔም በኋላ ነኝ፥ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም"::[22] ይኽንም የመሰለ በሌላ ምዕራፍ "ያዕቆብ ሆይ እኔን ስማኝ፥ አንተም ፳ኤል እኔ ነኝ የጠራሁህ:: እኔ የፊተኛው ነኝ የኋለኛውም እኔ ነኝ እጄም ምድርን መሠረተች፥ ቀኜም ሰማዮችን ዘረጋች እኔ እጠራቸኋለሁ በአንድነትም ትቆማላችሁ" ይላል::[23] ይኽ አገላለጥ በጠቅላላው ለአብ ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ይተባበራል፥ እርሱም እንዲህ ይላል "አሉትም አንተ ማነህ? ኢየሱስም አላቸው፥ እኔ ነኝ ያ ከጥንቱ ጀምሮ እነግራችሁ የነበርኩት"::[24]

ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥንት ጀምሮ የነበረ፥ የሠራ የተናገረ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ፥ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ያልተለየና በ፩ነት የሠራ፥ የፈጠረ የተናገረ እርሱ ነው:: የወልድን አምላክነት ለማስረዳት በተለይ ስለ ወልድ ዮሐንስ ወንጌላዊ ሰፋ አድርጎ ተናገረ እንጅ በመለኮት በአገዛዝ በህልውና ፫ቱም አካላት ፩ ስለሆኑ ለ፩ኛው ብቻ አስፍቶ አጉልቶ መናገር ስለማያስፈልግ ከዚህ ላይ እንወሰናለን::

፬. <u>የእግዚአብሔር ልጅነቱ፥</u>

የክርስቶስን አምላክነት በመግለጥ አንዳንድ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ ስም ተጠቅመው ይገኛሉ፥ አንዳንዱ ስም በትክክል አምላክነቱን ይገልጣል፥ ከዚህ በመጀመሪያ የምናሳየው ወልድ (ልጅ) በሚለው ስም ነው:: ይህ ወልድ የሚለው ስም ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደ መሆኑን መለኮቱን መለኮትነቱን ያስረዳል:: ይኽንም ቃል ተከትሎ ወንጌላዊ ሉቃስ ሲገልጥ "ወይቤልዎ ኩሎሙ አንተኑ ወልደ እግዚአብሔር ወይቤሎሙ አንትሙ ትብሉ ከመ አነ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር" ብሏል::[25] በዚህ ስም ፺ ጊዜ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ተገልጦ እናገኘዋለን፥ ይኽም አገላለጥ በቀጥታ ለክርስቶስ ሆኖ እናገኘዋለን::





ገና ከጽንስ በፊት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለቅድስት ማርያም ሲያበሥራት "መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፥ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ፥ ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል"::[26] ብሎ ገልጦ ተናግሮ ነበር:: አብም በዮርዳኖስ የመሰከረው "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር" በሚል አገላለጥ ነው::[27] ራሱ ክርስቶስም ሲመሰክር አብን አባቴ እያለ ብዙ ጊዜ ይጠራ ነበር:: አይሁድም ሳይቀሩ ክርስቶስን ለመግደል ከተነሣሡበትና ለሞቱ ምክንያት ካደረጉበት ፩ኛው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ በማለቱና ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለ ብለው ነውና::[28] የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መሆኑ አምላክ ነው፥ ከአምላክ የተገኘ የተወለደም ነው:: ስለዚህም "አምላክ ዘበአማን ዘእምአምላክ ዘበአማን" ይባላል::

ምዕመናን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ቢባሉም ክርስቶስን በተለይ "ወልድ ዋህድ" ይለዋል፥ ከሌሎች ጋር አያገናኘውም:: ስለዚህም ወንጌላዊ ዮሐንስ "ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ አላ ወልድ ዋህድ ዘሀሎ ውስተ ሕጽነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ" ሲል ተቀዳሚም ተከታይም የሌለው ብቸኛ ልጅ እርሱ ብቻ መሆኑን ይገልጣል::[29] እርሱ የባሕርይ ልጅ ነው፥ ከባሕርይ አባቱ ይወለዳልና:: እኛን ግን በምሕረቱና በቸርነቱ በጸጋው ብቻ ይወልደናል፥ ግን አሁንም ልጆቹ እንባላለን ሁኖም የባሕርዩንና የጸጋውን ልጅነት መለየት አለብን፥ ማለት የባሕርይ ልጅ ስንል አብን መስሎ አብንም አክሎ ምንም ልዩነት የሌለበት ሆኖ መወለዱን ያስረዳል:: የጸጋው ልጅ ግን ከርሱ በባሕርይ ሳይወለድ እግዚአብሔር በቸርነቱ በጸጋው ብቻ ልጅ ሲያደርገው ነው::

ሰውን ከመውደዱና ከማፍቀሩ የተነሣ እግዚአብሔር አብ ለዓለም ቤዛ መድኃኒት አድርጎ የላከው የርሱን የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው እንጂ መላእክትን ወይም ሰዎችን አይደለም:: ዓለም የዳነውም በእርሱ አንድ ልጅ ደም ብቻ ነው፥ ይኽንም ወንጌላዊ ዮሐንስ "እስመ ከመዝ አፍቅሮ እግዚአብሔር፥ ለዓለም እስከ ወልዶ ዋህዶ ወሀበ ቤዛ ኩሉ



www.ethiopianorthodox.org

ዘየአምን ቦቱ ኢይትሐጎል አላ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም" ሲል ገልጦልናል::[30] ወልድ ዋህድ የሚለው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ የአብ ልጅ እርሱ ብቻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል ነው:: በዚህም አገላለጥ ሰው የተባለው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ቢባልም የባሕርይ ልጅ ሊሆን አይችልም፥ ምክንያቱም ወልድ ዋህድ የሚለው ቃል እንደ አጥር ይጋርደናል:: ስለዚህ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ብቻ ነው:: እንዲህ ባለው ሁናቴ የክርስቶስን አምላክነት ስንረዳ ለሰው ልጅ ደህንነት ደግሞ ሰው መሆኑን እንደሚከተለው እንገልጣለን:: ያው አምላክ ሰውን ከማፍቀሩ የተነሣ በፍጻሜ ዘመን ሰው ሆነ፥ ሰውም የመሆኑ ገብር እንደሚከተለው ነው::

፩. <u>ፅ ን ሰ ቱ፥</u>

ቃል ሥጋን ለመልበስ የሰው ነገድን ለመጎብኘት እንደወሰነ ቅዱሱን መልአክ ገብርኤልን ወደ አንዲት ድንግል፥ ማርያም ወደ ምትባል ላከው፥ እርሱም "ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ" ሲል ለድኅነት ሥራ መነሻ መሸጋገሪያ ለመሆን የበቃችውን ድንግል ማርያምን አበሰራት::[31] እርሷም ከሰው እንደምትፀንስ ወይም ሰውን እንደምትፀንስ ስለመሰላት በከንቱ ውዳሴ አልጠለፍም፤ ዘለዓለማዊ ድንግልናየንም አልለውጥም በማለት ለብዙ ጊዜ ከመልአኩ ጋር የቃል ልውውጥ አደረገች:: በኋላ ግን መልአኩ "እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር" ብሎ ነገሩን ስለወሰነባት "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ" ብላ የምሥራቹን ቃል አምና አክብራም ተቀበለችው:: ወዲያውኑም አካላዊ ቃል በማኅፀኗ ተቀርጾአል፥ ሥጋንም ለብሷል::

ይኩነኒ ያለችውን የማርያምን የእምነት ቃል በመከተል ሰማይና ምድር የማይወስኑት አካላዊ ቃል በማኅጸኗ ተወሰነ፥ ተጸነሰ፥ በዚሁ ዕለት በዚሁም ሰዓት ቃል ~~ከሥጋ ጋር~~ ሥጋም ከቃል ጋር በፍጹም ተዋሕዶ ተዋሐደ፤ ይኩነኒ ያለችው የቅድስት ማርያም ቃለ ተአምኖ ለቃልና ለሥጋ ተዋሕዶ ትልቅ ምክንያት ሆነ::



www.ethiopianorthodox.org



የዓለሙ ፈጣሪ ቃል ስማያዊነቱን ሳይለቅ በድንግል ማኅፀን አደረ፥ ፱ ወር ከ፭ ቀንም ተፀነሰ፥ ቀዳማዊ ቃል ደኃራዊ ሥጋን ስለተዋህደ ተፀነሰ ተባለ:: በቀዳማዊ ልደቱ ጊዜ እናት ያላስፈለገው ቃል፥ ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደ ወልድ፥ በዚህ ጊዜ ደግሞ እንበለ ዘር፤ ያለ አባትም ምንም ምክንያት ሳያስፈልገው ከቅድስት ማርያም ለመወለድ ተፀነሰ:: ይኸንም ወንጌላዊው ማቴዎስ እንዲህ ሲል ይገልጥልናል "የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበር እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች"::[32] በመለኮታዊ ግብር በተአምራታዊ ሁኔታ ብቻ ቅድስት ማርያም አምላክን በማኅፀኗ ለመወሰን በቃች፥ ማለት ጸነሰችው:: ይኸም ሁናቴ ቅድስት ማርያምን ከሴቶች የተለየሽ ነሽ አሰኝቶ ለመመስገን አብቅቷታል፥ ስለዚህም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደርሷ ገብቶ "ደስ ይበልሽ ጸጋን ያገኘሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፥ ከሴቶችም ዘንድ የተባረክሽ ነሽ" ሲል በእውነት መስክሯል::[33] ወዲያውኑ ምስክርነቷን አንድ በማድረግ ቅድስት ኤልሳቤጥ ይኸንኑ ቃል በመድገም ተናግራለች::[34] አካላዊ ቃል ወልድ ግዕዘ ሕፃናትን ሳያፋልስ ማንም ሕፃን እንደሚጸነሰው ተፀንሶ ተወለደ፥ ልደቱም እንደማንኛውም ሕፃን ሆነ::

ቅድስት ማርያምን መንፈስ ቅዱስ አነፃት ቀደሳትም፤ እንዲሁም አካላዊ ቃልን በማኅፀኗ ትሸከመው ዘንድ አጸናት፥ አስቻላት፥ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነውና ጸለላት፤ ማለትም በድንግልና ፀንሣ በድንግልና እንድትወልድ አደረጋት:: መንፈስ ቅዱስ ጸለላት፥ መንፈስ ቅዱስ አነፃት፥ መንፈስ ቅዱስ ቀድሳት ማኅደረ መለኮት እንድትሆን አዘጋጃት::

እንግዲህ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከድንግል ማርያም ተወለደ፥ ፍጹም ሰውም ሆነ ስንል ምነው አብም መንፈስ ቅዱስ ሥጋን ያልለበሱ ሰውም ያልሆኑ ቢያሰኝ ከዊነ ወልድ የግሉ የወልድ ነውና እንላለን:: ስለዚህ እርሱ ብቻ

በተለየ አካሉ ሰው ሆነ፥ ሥጋንም ለበሰ። እንዲህስ ባይሆን ኖሮ የአካል የግብር የስም ልዩነት በሥላሴ ዘንድ በተፋለሰ ነበር። የባሕርይ ተዋህዶ የተዋሃደውን አካል በተዋሀደው ስም በተዋሃደው ግብር፥ በተዋሃደውም አካል ሰው አሰኝቶ ወላዲም ሠራጺም ሆነ በተባለ ነበር። የተዋሃደውን አካል በተዋሀደው ስም በተዋሃደው ግብር በተዋሃደው አካል አምላክ ሳያሰኝ አይቀርም ነበር። ይኸንንም "ወኢተዋሃደ በመንፈቀ ህላዌ" ሲል ኤፍሬም አፈ በረከት አስረድቷል።[35] ወልድ ግን ምስጋና ይግባውና የአብ የመንፈስ ቅዱስ እንዲህ እንዳይሆን መወለድ ሥጋንም መልበስ የወልድ ብቻ እንዲሆን በተለየ ስሙም ለመጠራት፥ በተለየ ግብሩና አካሉ ለመጽናት በአብ በመንፈስ ቅዱስ በእርሱም ፈቃድ ሰው ሆነ፥ ሥጋንም ለበሰ በቤተ ልሔምም ተወለደ።

፮. ልደቱ፥

ዘመኑ ሲፈጸም እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ማርያም በኅቱም ድንግልና ተጸንሦ በኅቱም ድንግልና ተወለደ። አምላክ ጽንሰቱን በማንኛውም ሰው ልክ እንዳደረገው ልደቱንም እንዲሁ አደረገው። እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከቅድስት ማርያም ተወለደ፥ ፍጹም ሰው ሆነ፥ ሥጋንም ለበሰ፥ ይኸም ማለት ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ ሰው መሆኑን፥ ሥጋን መዋሐዱን ያጠይቃል "በእንተ ተዋህዶተ መለኮት ዘንትናገር በዝየ ዘህልው ወአኮ በእንተ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢ ንቤ ከመ እሙንቱ ኃደሩ ለተሰብአ ውስተ ከርሣ ለድንግል ዘእንበለ ዳዕሙ ወልድ ባሕቲቱ አሐዱ እምስለሥቱ አካላት ተወልደ እምኔሃ ኢይፈልስ አብ ለከዊነ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ ወኢወልድ ለከዊነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፥ ወኢመንፈስ ቅዱስ ለከዊነ አብ ወወልድ" ሲል አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ያስረዳናል።[36] መለኮት ከሥጋ ጋር ተዋሐደ ባልን ጊዜ ከኃጢአት በቀር በባሕርየ ሥጋ በአካለ ሥጋ ሰው ሆኖ በባሕርየ መለኮቱ በአካለ መለኮቱ ሥጋን ክቡር አደረገ ስለሥጋም እንግድነት ቃል ከበረ መባልን ገንዘብ አደረገ "አኮ ሐይጾ ዘኮነ እግዚአብሔር አላ አትሒቶ ርእሰ ነሥአ አርአያ ገብር" ሲል





ቅዱስ ጳውሎስ ያስረዳናል።[37] እንዲህ ባለ ምሥጢር በማይወሰን አካል በማይመረመር ግብር አካላዊ ቃል በምልዓት በጌትነት ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አንድነቱን ሳይለይ ብቻውን ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ግብር የዕለት ጽንስ ሆኖ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን፥ ነሥቶ ሰው ሆነ ማለት ተወለደ።[38] ስለዚህ ክርስቶስ መባልን ገንዘብ አደረገ ክርስቶስም ተባለ። ይኸም ስም በሥጋዌ ምክንያት የወጣለት ስም ነው ትርጉሙም ቅቡዕ ማለት ነው። ይኸም ስም የመለኮት ባሕርይና የትስብእት ባሕርይ አንድ በመሆኑ ባለመለያየት፥ ባለመቀላቀል በፍጹም ተዋህዶ ስለተዋሐደ የወጣለት ስም ነው እንጂ ብቻ የትስብእት፥ ብቻም የመለኮት ስም አይደለም። ይኸም ስም የሥጋንና የመለኮትን ተዋህዶ በትክክል ያመለክታል። ስለዚህም ክርስቶስ ከሁለት አካላት አንድ አካል ከሁለት ባሕርያት አንድ ባሕርይ በመሆን ስለተዋሐደ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክም ሆኖ አምላክ ወልደ አምላክ፥ አንድም ወልደ እጓለ እምሕያው እንዲሁም አምላክ ወሰብእ ተብሎ ሲመሰገን፥ ሲቀደስ ሲወደስ ይኖራል። ክርስቶስ በዚህ መልክ ሰው ሆኖ ተወለደ፥ በየጥቂቱም አደገ ማለት ግዕዘ ሕፃናትን ሳያፋልስ አደገ በዚህም ዓለም ዞረ ተመላለሰ፥ የማዳን ሥራውን እስከ ሠራበት ዕለት ድረስ እንደማንኛውም ሰው ኖረ።

፯. የክርስቶስ የዚህ ዓለም ሕይወቱ፥

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ሰው ሆኖ በሰው የተፈረደውን ፍርድ ራሱ ተቀብሎ ለማዳን ብቻ ነው። ስለዚህ እንደ አንድ ዝቅተኛ ሰው ሆኖ ሊያገለግል እንጂ፥ እንዲገለል የመጣ ሳይሆን በዚህ ዓለም ኖረ።[39] እንዲያውም የሰው ልጅ ሁሉ መኖሪያ ጎጆ እንደየአቅሙ ሲኖረው ይኸንም ለማግኘት ሁሉ ሲጣጣር ክርስቶስ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት ጎጆ እንኳን አልነበረውም።[40] ቀን በአደባባይ ሕዝብ በብዛት ሲያስተምር ይውል ነበር፥ ሌሊት ግን ወደደብረ ዘይት ተራራ እየወጣ ያድር ነበር።[41] ክርስቶስ እየዞረ ሲያስተምር ምግብ አዘጋጅቶ የሚጠብቀው ዘመድ አልነበረውም፥ በዚህም መልክ ይርበው ይጠማው ነበር፥ እህልም ውሀም የለመነበት ጊዜና ቦታ ነበር።[42]



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም የሚበላ ነገር አላችሁን እያለ ደቀመዛሙርቱን የጠየቀበት ጊዜ የጠየቀበትም ቦታ ነበር::[43] ስለእግዚአብሔር መንግሥት ራሱን ዝቅ በማድረግ መራብ፥ መጠማት አስፈላጊ መሆኑን "በመንፈሳቸው የተቸገሩ ብፁዓን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የርሳቸው ናትና:: ገሮች የተመሰገኑ ናቸው እርሳቸው ምድርን ይወርሳሉና:: ጽድቅን የሚራቡ የሚጠሙም የተመሰገኑ ናቸው እርሳቸው ይጠግባሉና፥ ........" እያለ ፍጹም የብዕዕና ትምህርት አስተምሯል::[44] እንዲህም እያደረገ እውነተኛው ክርስቲያናዊ ሕይወት ምን ዓይነት እንደሆነ፥ በመግለጥ ትምህርት ይሰጥ ነበር:: የክርስትናውን ትምህርት ፍጹም ልዩ የሚያደርገውና ሰውንም ሁሉ የሳበው በዚህ ዓይነት ስለቀረበ ነው:: ክርስቶስ ሐዲሱን የክርስትና ትምህርት በሐሳብ ብቻ ሳያስቀር በሥራ ይተረጉመው፥ ምሳሌነቱንም ይሰጥ ነበር::

ክርስቶስ በግላዊ ሕይወቱ፥ ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ የሰጠው ብዙ ምሳሌነት ያለው ትምህርት ነው::

ሀ. <u>ክርስቶስ በግላዊ ሕይወቱ</u>፥ ክርስቶስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ በቤተ መቅደስ መገኘትን መርጧል::[45] ክርስቶስ ለብቻው ይጸልይ ነበር፥ ክርስቶስ ለብቻው ስለሰው ልጅ ሕይወት ይቆዝም ነበር:: ክርስቶስ ለብቻው በባሕር ይጓዝ ነበር::[46] ይኸን በመሰለው ሁናቴ ብቻውን የሠራበት ቦታና ጊዜ ይገኛል::

ለ. <u>ክርስቶስ በማኅበራዊ ኑሮ</u>፥ ክርስቶስ ሰውን ለማስደሰት እውነተኛውንም ማኅበራዊ ኑሮ ለመመሥረት በሠርግ ቤት ተገኝቷል፥ በዚህም የመጀመሪያውን ታምራት አሳይቷል::[47] ክርስቶስ በግል ሰዎች ቤት እየተጋበዘ ተገኝቷል[48] ክርስቶስ በሽተኞችን ይጎበኝ ፈውስንም ይሰጥ ነበር::[49] ወገን የሌለውን ችግረኛውን፥ በሽታም የጸናበትን ሁሉ ሳይጸየፍና ሳይጠላ ሁሉንም ያነጋግር፥ ሁሉንም እንደየእምነቱ እንዲድን ጥያቄ ያቀርብ ነበር::[50] በዚህ መልክ ክርስቶስ ሲሠራ አንድ ካህን ለምእመኑ ምን ማድረግ እንደሚገባው ምሳሌነቱን በግልጥ አሳይቷል:: እርሱም ሰው የሆነበት ዋናው ዓላማ ለሰው ልጅ አዲስ ማኅበራዊ ኑሮን ለመመሥረት ሕዝብንም በዚያም





ለመምራት ነው:: ክርስቶስ በኀዘን ቤት ተገኝቶ አልቅሷል፥ ማኅበራዊ ኑሮን በማክበር የኀዘን ተካፋይ ሆኗል::[51] ስለሀገር ፍቅርም እንደሚከተለው ሠርቷል፤ ክርስቶስ ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት አዝኗል፥ ብትመለስ ግን እንደምትድን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል::[52]

ክርስቶስ ታላላቆችንም ሕፃናትንም ያፈቅራል፥ እንዲያውም "ሕፃናትን አትከልክሏቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ" ሲል ለሕፃናት ደንብ አውጥቶላቸዋል::[53]

እንዲሁም በመንግሥተ ሰማያት ትልቅ የሚባለው ራሱን እንደ ሕፃናት ያዋረደ ሰው እንደሆነ በአንድ ሕፃን ምሳሌ አድርጎ አስተምሯል::[54] ክርስቶስ ወንድ ሴት ሳይል ያታንም ሳይለይ ሁሉንም ይወዳል፥ እንዲያውም ሴቶች ከገሊላ አንስተው እስከ ቀራንዮ አልተለዩትም፥ በገንዘባቸውም ያገለግሉት ነበር::[55]

እንዲሁም በመስቀሉ አንፃር ሳይለዩ ቆመው ሲያለቅሱ የዋሉ ሴቶች የርሱን ፍቅር በማወቅ ነበር::[56] በትንሣኤውም ጊዜ በመጀመሪያ ያገኙት ለደቀመዛሙርቱም ሄደው የነገሩ ሴቶች ናቸው::[57] ይኸንንም የሚያደርጉት የክርስቶስ ውለታ አስገድዷቸው ነው:: ክርስቶስ ለሰው ልጅ ማኅበራዊ ኑሮ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጥ ከፍተኛ ምሳሌነቱን የሰጠ ፍጹም ሰው እንደመሆኑ ነው፥ ሕግንም ጠብቆ የኖረ የሰውን ዜግነት በማክበሩ ነው::

ግብር መገበር ይገባል አይገባም ብለው ሲጠይቁት የቄሣርን ለቄሣር፥ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር መስጠት ተገቢ መሆኑን ገልጦ አስተምሯል::[58] ይኸውም ማንም ሰው በምድራዊ ሕይወቱ ግብር ሳይገብር ሊኖር እንደማይችል የሚያስረዳ ትምህርት ነው:: ከግብር እንኳን ነፃ መሆን ሲገባውና ሲችልም ምሳሌነቱን ለመስጠትና ለሌሎች የጥፋት አብነት እንዳይሆን ጴጥሮስን ዓሣ አምጥቶ ሆዱን ሰንጥቆ ያገኘውን መኀልቅ ስለ ክርስቶስና ስለራሱ ግብር እንዲከፍል አዘዘው::[59]

ሐ. <u>ክርስቲያናዊ ትምህርቱ</u>፥ ክርስቶስ የመጣው ለራሱ ክብር ስላይደለ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንም ለያንዳንዳችን



www.ethiopianorthodox.org

ለራሳችን ብቻ አለመሆኑን ይገልጥልናል፥ ማለት አንዱ ክርስቲያን ሌላውን ወንድሙን በማስተማር በመርዳት አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ራሱን ሳይቀር መስጠት እንዳለበት አስተምሯል::[60] ክርስቲያን ሁሉ ጨው ሆኖ የሌላውን ሕይወት፥ የሌላውንም ማኅበራዊ ኑሮ ማጣፈጥ እንዳለበት አስተምሯል::[61] እንዲሁም ክርስቲያናዊ ሕይወት ለሌላው ብርሃን እንዲሆን፥ ሌላውን ከእንቅፋት ሊያድን እንዲገባው ክርስቶስ ምሳሌ መስሎ ተናግሯል::[62] ክርስቲያናዊ ሕይወት ለወንድሜ እንጂ ለእኔ እንደማያስኝ ራሱን ምሳሌ አድርጎ አስተምሯል:: ክርስቲያናዊ ትምህርት ፍጹም የመጨረሻው ትምህርት ነው፥ የሰው ልጅም የሕይወቱ ብርሃን ክርስቶስ ነው፥ የላከልን አብንና የተላከልን ወልድን ማመን ዘለዓለማዊ ሕይወት ነውና::[63]

ክርስቲያን ከሆነ፥ ክርስቶስን መከተል በክርስቲያናዊ ትምህርትም መጽናት የእያንዳንዱ ግዴታ ነው፥ ፍጹም እምነትን ይዞ በዚህ ስም እየተጠራ ክርስቶስን ባይከተል በትምህርቱም ባይጸና የሚፈርድበት እርሱ ሳይሆን ያ አስቀድሞ እርሱ የተናገረው ቃል ነው::[64]

መ. <u>እንደክርስቶስነቱ</u>፥ ምንም መለኮትን የተዋሀደ ሰው ሆኖ ስለሰውነቱ፥ ስለ ምድራዊ ሕይወቱ ሰፋ አድርገን ብናትት፥ ሰማያዊ ሕይወቱ መለኮትነቱ ወይም አምላክነቱ እንዲሁ የሚተው የሚታለፍም አይደለም፥ ለዚህም ክርስቶስ የሚለው ስሙ ያስተባብርልናል፥ ማለት ክርስቶስ ማለት ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነውና::

ክርስቶስ የተባለው ኢየሱስ በምድር እኛን መስሎ እንደ እኛም ሆኖ ሁሉን ሠራ፥ እንደሁሉም ሆነ፥ ከኃጢአት በቀር:: ስለዚህ ለኛ ለክርስቲያኖች ምሳሌያችን ኃላፊያችን አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::





# <u>ም ዕ ራ ፍ ፪</u>

## <u>ስለ ክርስቶስ አምላካዊ ባሕርይ</u>፥

1. <u>ቅድስናውን መግለጥ</u>፥ ጌታችን ኢየሱስ ቅዱስ መሆኑን፥ ቅድስናም የባሕርዩ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ገልጠው ይናገራሉ ይመሰክራሉ:: ከሁሉ በፊት ክርስቶስ ገና ሲጸነስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለቅድስት ማርያም "ስለዚህም ደግሞ ቅዱሱ ከአንች የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ፥ ይባላል" ሲል አብሥሯታል::[1] በሐዋርያት ሥራም "አንትሙሰ ከሕድክምዎ <u>ለቅዱስ ወለጻድቅ</u>" ሲለው እናገኘዋለን:: ይኸን የመሰለ በነቢዩ በሆሴዕ መልእክት እናገኛለን፥ እርሱም እንዲህ ይላል "የቁጣየን መቅሠፍት አላደርግም ኤፍሬምን ለማጥፋት አልመለስም፥ እኔ በመካከልህ <u>የተቀደስኩኝ አምላክ</u> ነኝና ሰው አይደለሁም፥ ስለዚህ በቁጣየ ትኩሳት አልመጣም"::[2] አምላክ ስለሆነ ከሁሉ የራቀ፥ የተለየም ቅዱስ ነው:: ቅዱስ ጻድቅ እየተባለ በብሉይም በሐዲስም የሚመሠከርለት ቃሉ አንድ ሆኖ የተነገረለት ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው::

2. <u>ክርስቶስ ጌታ መሆኑ</u>፥ ጌታ የሚለው ቃል ሊውል የሚችለው ለጌታችን ለአምላካችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው፥ ምክንያቱም ከዲያብሎስ አገዛዝ ከባርነትም ቀንበር ነፃ አውጥቶ በነፍስም በሥጋም የሚገዛን የሚመራን እውነተኛው ጌታችን እርሱ ብቻ ነውና::

የክርስቶስ ጌትነት በሐዲስ ኪዳን ብቻ የተገለጠ ሳይሆን አስቀድሞ በትንቢተ ነቢያት የተነገረ የታወቀና የተረዳ ነው:: ከተነገረው ትንቢት ውስጥ በከፊል እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፥ ነቢዩ ዳዊት "የምድር ነገሥታትና መኳንንትም ተሰብሰቡ፥ በጌታና በመሢሁ" ሲል ተናግሯል::[3] ይኸም ቅጥል ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ መነገሩን የሚያስረዳ ሉቃስ ወንጌላዊ እንዲህ ሲል ይጽፋል "የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በአንድነት ተማከሩ በጌታ ላይ በመሢሑም ላይ"::[4] እንደገናም ነቢዩ ዳዊት "ጌታ ጌታየን አለው በቀኜ



www.ethiopianorthodox.org

ተቀመጥ ጸላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ"::[5] ይኸ የዳዊት ትንቢት ለክርስቶስ የተነገረ መሆኑን ወንጌላዊ ማቴዎስ በአድናቆት ተቀብሎ ለጌትነቱ ማስረጃ አድርጎ አቅርቦት እናገኛለን::[6]

ጌታ የሚለው ቅጥል ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ መሆኑን ከተረዳን ዘንድ ሌላ ሰው ሊጠራበት ለሌላም ስም ሊውል የማይገባው መሆኑን ተረዳን፥ ይኸም ከሆነ ስሙንም ክብሩንም ለባዕድ ልንሰጥ ከቶ አይገባንም:: ጌታችን ኢየሱስ የጌቶች ጌታ ነው፥ የአማልክትም ሁሉ አምላክ ነው፥ የማዳንም ኃይል ያለው እርሱ ብቻ ነው:: የጌቶች ጌታ የአማልክት አምላክ መሆኑን ሊቀ ነቢያት ሙሴ "እግዚአብሔር አምላካችሁ የአማልክት አምላክ ነውና፥ የጌቶችም ጌታ ነውና፤ ታላቅ አምላክ ኃይለኛም የሚያስፈራራም ፊት አይቶ የማያዳላ መማለጃም የማይቀበል" ሲል አምላካችን እግዚአብሔር እንዴት እንደሆነ ገልጦ ተናግሯል::[7] እግዚአብሔር አንድ ከሆነ አምላክም አንድ ስለሆነ ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን::

የኛ የክርስቲያኖች ጌታ ክብርና ምስጋና የሚገባው እርሱ መሆኑን በሐዲስ ኪዳንም እንደዚሁ ያለ ማስረጃ እናገኛለን:: ከብዙ ማስረጃዎች ውስጥ ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስረዳል፥ "ከዚህ ዓለም አለቆች ማንም ያላወቀው አውቀውስ ቢሆን የምስጋና ጌታን የክብርም ባለቤትን ባልሰቀሉትም ነበር" ሲል ጽፏል::[8] የምስጋና ጌታ፥ የክብርም ባለቤት የሆነ ሌላ ሰው ማንም የለም ከአምላካችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ በቀር::

የወንበዴውም አለቃ በመስቀል ላይ ሆኖ በጌታችን ፊት ኑዛዜ ሲያደርግ "የክርስቶስን ጌትነት በመመስከር ነው"::[9] እንግዲህ አንድ ጌታ ብቻ አለን፥ ስለዚህ ለእርሱ ብቻ እንገዛለን፥ እርሱንም ብቻ እናመልካለን፥ እርሱም ብቻ ጌታ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ "ለኛ ግን አንድ አምላክ አለን እግዚአብሔር አብ፥ ሁሉ ከእርሱ የሆነ፥ እኛም ለእርሱ:: አንድ ጌታም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉም በእርሱ የሆነ፥ እኛም በእርሱ" ሲል ገልጦ አስረድቷል::[10]





ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋንም ለብሶ ሲወለድ መላእክት ክርስቶስን ጌታ ብለው ጠርተውታል ጌትነቱንም ጠቅሰው እንዲህ ሲሉ አስረድተዋል."......ዛሬ መድኅን ተወልዶላችኋልና እርሱም ክርስቶስ ጌታ በዳዊት አገር"::[11] ክርስቶስ ብለው ጠርተው ቅጥሉንም ጌታ ሲሉ ጌትነቱን አረጋግጠው ተናግረዋል::

ሐዋርያው ቶማስም እንደ ቃለ ተአምኖ አድርጎ ስለክርስቶስ የሰጠው የምስክርነት ቃል "ጌታዬ አምላኬም" በማለት ነው::[12] እንዲሁም ገና በጽንስ ላይ እንዳለ ቅድስት ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ "የጌታዬ እናት ስትሆኚ ወደኔ እንዴት ትመጫለሽ?" ስትል ጌትነቱን አስቀድማ ተናግራለች::[13]

የኢየሱስን ጌትነት፥ መድኃኒትነት፥ አምላክነት በዚህ መልክ ተረድተናል፥ በዚህም መልክ መመስከር ይኖርብናል:: በመጨረሻው ሕይወታችን ወደ ክርስቶስ ቀርበው ሰዎች ክርስቶስን ጌታ እያሉ እንደሚጠሩ ጌትነቱንም እንደሚመሰክሩ አቤቱ አቤቱ በማለት እንደሚጮኹ ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረው አስረድተውናል::[14]

ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስ በመጨረሻ ሕይወቱ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ የተናገረው የመጨረሻው ቃል "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበላት" በማለት የኢየሱስን ጌትነት በማመንና በመመስከር ነው::[15] በመላም ቅዱሳን ሐዋርያት መምህራቸውን ኢየሱስን ጌታ፥ ጌታችን እያሉ ይጠሩት ነበር:: "እርሳቸውም አሉት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ትድናለህ ቤተ ሰብህም ሁሉ" ሲል ቅዱስ ሉቃስ ጠቅሶ ያስረዳናል::[16]

3. <u>የክርስቶስን አምላክነት በመግለጥ፤</u> ክርስቶስ የአብ ቃል እንደመሆኑ ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ይወለዳል፤ ስለዚህም ፍጹም አምላክ ነው:: ይኸንንም እውነት ወንጌላዊ ዮሐንስ "አስቀድሞ ቃል ነበር፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፥ እግዚአብሔርም ቃል ነበር" በማለት ቀዳማዊ አምላክ እንደሆነ በማያጠራጥር መልክ መስክሮ ተናግሯል::[17] እንደገናም ይኸው ወንጌላዊ የቶማስን ምስክርነት በመግለጥ



www.ethiopianorthodox.org

"ቶማስም መለሰ አለም ጌታዩ አምላኬም" ሲል ተናግሯል::[18] ይኸም ትክክል ቃል ነው፥ ምክንያቱም ክርስቶስ ጌታም ነው፥ አምላክም ነውና፤ ስለዚህ እውነቱን ገልጦ መስክሯል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስን አምላክነት ሲገልጥ ከሁሉ የሚበልጥ አምላክ እንደሆነ በመግለጥ፥ ለእርሱም ምስጋና የሚገባው መሆኑን በማስረዳት ተናግሮ እናገኘዋለን::[19] ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ አምላክነት ሲል በሥጋው ከእሥራኤል መወለዱን በጉልህ አሳይቷል፤ ግን ምንም ሰው ቢሆን ሥጋንም ቢለብስ መለወጥ የሌለበት ስለሆነ ታላቅ አምላክ፥ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው በማለት አጎልቶ ገለጠው::

የአብ ቃል ወልድ ሰውም ቢሆን ሥጋንም ቢለብስ ከኛ ከሰዎች ያልራቀ ያልተለየም መሆኑን ነቢዩ ኢሳይያስ "እንግዲህ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ብሎ ተናግሯል::[20]

አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋር ማለት ነው፥ እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራው ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ክርስቶስ ሰው በመሆኑ ባሕርያችን ባሕርይ አድርጓል:: ይኸንንም አረጋግጦ ወንጌላዊ ማቴዎስ ጽፎልናል::[21] እንደገናም ይኸው ነቢይ ጌታችን ኢየሱስን ብርቱ አምላክ የዘለዓለም አባት ሲል ተናግሯል:: አምላክነቱንም ዘለዓለማዊነቱንም ገልጦልናል::[22] አምላክ አንድ ብቻ ነው፥ ብርቱ አምላክ ሲልም ሌላ ፪ኛ ፫ኛ አምላክ ሆኖ ከነዚያ የበረታ ማለት አይደለም፥ እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን እርሱም የበረታ አምላክ መሆኑንና አምላክነቱም የባሕርይ መሆኑን ለመግለጥ ነው::

"እኔ ነኝ እግዚአብሔር ከኔ ሌላ የለም፥ ከኔ በቀር አምላክ የለም...." ሲል ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::[23] ሐዋርያው ጳውሎስም የክርስቶስን አምላክነት አምኖ ሰው ሲሆን አምላክ፥ አምላክም ሲሆን ሰው መሆኑ አስደንቆት "በእውነት ታላቅ ነው የአምልኮት ምሥጢር:: አምላክ በሥጋ ተገለጠ፥ በመንፈስ ጸደቀ፥ ለመላእክት ታየ፥ በአሕዛብም ተሰበከ፥ ከዓለም ታመነ፥ በምስጋና ዐረገ" በማለት የተአምኖውን ቃል ሰጥቷል::[24]





ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን፥ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እያለ ቅዱስ ሉቃስ ይጠራታል፥ ይኸም እግዚአብሔር ወልድ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው::[25]

ከሦስቱ አካላት ፩ኛው አካላዊ ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፥ እርሱም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል መሆኑን በአምላክነት፥ በመለኮትነትም አንድ መሆኑን ራሱ ጌታ ሲናገር "እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፥ አጥምቋቸውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም በማለት ደቀ መዛሙርቱ አዟቸዋል::[26]

ሐዋርያው ጳውሎስ በመላእክትና በወልድ መካከል ያለውን ልዩነት እያነጻጸረ መጥቶ ወልድ የመላእክት አምላክና ፈጣሪ መሆኑን ሲያስረዳ "ማንን ነው ከመላእክት ያለው ከቶ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔም ዛሬ ወለድኩህ .... ደግሞም በኩር ወደ ዓለም በገባ ጊዜ አለ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ለእርሱ ይሰግዱሉ:: ስለ መላእክትም አለ መላእክቱን ነፋሳት ያደረገ፥ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባሎች:: ስለ ልጁ ግን አለ ዙፋንህ አምላክ ለዘለዓለም ነው፥ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው::[27]

ወንጌላዊ ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ አምላክነት በመልእክቱ እንዲህ ሲል ያስረዳል "እኛም በእውነት እንናገራለን፥ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ:: ይኸ ነው እውነተኛው አምላክ የዘለዓለሙም ሕይወት"::[28] እውነተኛው አምላክ የዘለዓለሙም ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: እውነተኛው የሰው ልጅ ተስፋና ሕይወት እርሱ ብቻ ነው:: ክርስቶስ ስለ እውነተኛው ሕይወት ሲያስተምር "በወልድ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አለው" ብሏልና::[29] እንዲሁም በሌላ ምዕራፍ "እኔ መንገድ ነኝ እውነትም ሕይወትም" ሲል አስረድቶ ተናግሯል::[30]

እንግዲህ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን መሆኑን አዳኛችንም እርሱ ብቻ መሆኑን አምነን ወደ እርሱ እንቅረብ::



www.ethiopianorthodox.org

4. <u>ሁሉን አዋቂ መሆኑ</u>÷ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ ማንኛውንም ነገር ሁሉ ያውቃል÷ የሚሆነውን ሁሉ ሊነገረው እንደማይሻ ዮሐንስ እንዲህ ይላል "ማንም ይመሰክርለት ዘንድ አይሻም ነበር÷ እርሱ በሰው ዘንድ ያለውን ያውቅ ነበርና::[31] የያንዳንዱን ሰው ታሪክ ይተርኩለት÷ ክፉቱንም ደግነቱንም ይነግሩት ዘንድ ከቶ አይሻም÷ እርሱ ራሱ ኩላሊት ያጤሰውን ልቦና ያመላለሰውን መርምሮ የሚያውቅ አምላክ ነውና:: የሚሆነውን ሁሉ ከመሆኑ ከመደረጉም አስቀድሞ ያውቃል::[32] ናትናኤል የሠራው በጠቅላላም ሕይወቱ ምን እንደነበረ ክርስቶስ አስቀድሞ እንደማወቁ መስክሮ ተናግሯል::[33] ይኸም ሰዎች ምን እንዳደረጉ ወደፊትም ምን እንደሚያደርጉ ማወቁን ያመለክታል:: ቅዱስ ጴጥሮስ ክርስቶስ ሁሉን እንደሚያውቅ የሚሰወረውም አንዳች እንደሌለ "አቤቱ አንተ ሁሉን ታውቃለህ÷ አንተ ታውቃለህ÷ እንደምወድህ" ሲል ይመሰክራል::[34]

5. <u>ክርስቶስ በዓለም ምሉዕ መሆኑ</u>÷ ክርስቶስ ሰውም ቢሆን ሥጋንም ቢለብስ እንደ አምላክነቱ በዓለም ምሉዕ ነው:: ስለዚህ በየትኛውም ቦታ ሁነው ቢለምኑት ይሰማል ይሰጣል ቢፈልጉት ይገኛል:: ስለዚህም እርሱ ራሱ ሲመሰክር "... ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ ወደ ተከማቹበት ከዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ" ሲል ተናግሯል::[35]

በዚህ አገላለጥ መሠረት የትም ብንሄድ የትም ብንኖር ኢየሱስ ክርስቶስ ከኛ ጋር ነው÷ ከአለንበትም ሁነን ብንጠራው ይሰማናል÷ ይረዳናል÷ በዓለም ምሉዕ ነውና:: በሰማይም ያለ በምድርም ያለ እርሱ ነው÷ ከሰማይ ወደ ምድር የወረደው ሰው የሆነውም እርሱ ነው÷ ከመሬትም ወደ ሰማይ ያረገው እርሱ ነው÷ እርሱ በዓለም ምሉዕ ነውና::[36] የሰው ልጅ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በኖረ ጊዜ ከሰማያዊ መንግሥቱ አልተለየም÷ ከባሕርይ አባቱ ከአብ÷ ከበሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አልተለየምና:: እርሱ በአብም በመንፈስ ቅዱስም ህልዉ ነው፤ አብም መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ሕልዋን ናቸውና::[37]

6. <u>ክርስቶስ ዘለዓለማዊ መሆኑ</u>÷ ኢሳይያስ የክርስቶስን አምላክነት ዘለዓለማዊነት የሁሉ አጽናኝ የነበረ ያለ የሚኖር





መሆኑን በጎላና በተረዳ "ሕፃን ተወልዶልናልና÷ ወንድ ልጅም ተሰጠን÷ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል÷ ስሙም ድንቅ ተብሎ ይጠራል÷ መካርም ብርቱም አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ" ሲል ገልጦልናል::[38] በባሕርዩ ሞት በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት ዘለዓለማዊ አባት ነው::

ራሱ ክርስቶስም ጥንታዊነቱን ዘለዓለማዊነቱንም ሲገልጥ ለአባቱም ሲያስረዳ "አሁንም አመስግነኝ አንተ አባት ሆይ ከአንተ ዘንድ ከጥንት በነበረኝ ምስጋና ዓለም ሳይፈጠር" ብሏል::[39] እንዲሁም በድጋሜ ጥንታዊነቱን አምላክነቱን ለአይሁድ ሲገልጥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነኝ ብሏቸዋል::[40] ይኸም ማለት የሰው ነገድ ሳይፈጠር÷ ዓለምም ራሱ ሳይፈጠር የነበረ ቀዳማዊ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: ክርስቶስ የትናንትናው÷ የዛሬው÷ ለዘለዓለሙም የሚኖር አምላክ ነው::[41] ክርስቶስ ቀዳማዊ ነበር÷ ዛሬም አለ÷ ወደፊትም ለዘለዓለም ነግሦ የሚኖር ኅልፈት ውላጤ የሌለበት አምላክ ነው:: ሁሉ ያልፋል÷ ይጠፋል ይለወጣል እርሱ ግን ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኖራል::[42] ሥጋም ቢለብስ ሰውም ቢሆን እርሱ ያው አምላክ ነው÷ አምላክነቱም የባሕርዩ ነው አይለወጥምና÷ ዘለዓለማዊነቱም ከቶ አይጠፋምና:: አምላክነቱ የባሕርዩ ገንዘቡ እንጂ እንዲሁ ሽቶ ወይም ተመኝቶ ወይም ለምኖ ወይም በብድር የአገኘው አይደለም÷ ወይም ቀምቶ የወሰደው አይደለም::[43] ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት አምላክ ነበር÷ ሰውም በሆነ ጊዜ ሰውም ከሆነ በኋላ አምላክ ነው÷ ፍጹም መለኮቱ ከሥጋ ጋር ተዋሕዷል መከፈልና መለየት የለበትም::[44] ቃል ፍጹም አምላክ እንደመሆኑ የተከፈለ ሳይሆን በምልዓት ሥጋን ተዋሕዷል÷ ፍጹም መለኮቱ ከሥጋ ጋር ተዋሕዷል÷ ውላጤም የለበትም ስለዚህም ዘለዓለማዊ አምላክ ነው::

7. <u>በፈጣሪነት መሥራት</u>÷

ክርስቶስ ከጥንት ምድርን የመሠረታት÷ ዓለምንም የፈጠራት እርሱ ነው ስለዚህም "...... አንተ አቤቱ ከጥንት ምድርን መሠረትካት ሰማዮች የእጅህ ሥራዎች ናቸው:: እርሳቸው ይጠ



www.ethiopianorthodox.org

ፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ .....” ሲል ነቢዩ ዳዊት ይገልጥልናል::[45]

ወንጌላዊ ዮሐንስም “ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱስ ከሆነው ሁሉ ምንም የሆነ የለም” ሲል ይገልጥልናል::[46] ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስን ፈጣሪነት ከሁሉ በበለጠ አጉልቶ እንዲህ ሲል ይገልጣል፥ “ነገር ሁሉ በርሱ ተፈጥሯል፥ በሰማያት ያለ ሁሉ በምድርም ያለ የሚታይም የማይታየውም፥ መናብርትም አጋዕዝትም ሊቃናትም ሥልጣናትም፥ ሁሉ በርሱ ለርሱም ተፈጠረ፥ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው፥ ዓለሙም ሁሉ በርሱ ጸና::”[47]

የሰው ልጅ ክርስቶስ የዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ ነው፥ ዘመን የማይቆጠርለት ቀዳማዊ አምላክ ነው:: በፍጻሜ ዘመን ደግሞ ስለሰው ድኅንነት ሰው ሆነ፥ ሥጋንም ለበሰ፥ በዚህም ጊዜ ፍጹም አምላክ ነው፥ አልተለወጠም:: በዚህም ጊዜ ፍፁም ሰው ነው ምንም ጉድለት የለበትም፥ ስለዚህ አምላክ ወሰብእ እየተባለ ይመሰገናል:: ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው አምላክ ስለኛ በደል ደካማ መስሎ ታየ ኃጢአተኛም ተብሎ ተጠራ፤ በበደላችንም ገባ፥ ነገር ግን ራሱን ክሶ ደሙን አፍስሶ የማዳን ሥራውን ፈጸመ:: በክብርና በምሥጋና ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀምጦ ዓለምን ያስተዳድራል::[48]

8. <u>እንደ አምላክነቱ ኃጢአትን ማስተሥረዩ</u>፥ ክርስቶስ ሰው የሆነው ሥጋንም የለበሰው ኃጢአትን ለማስተሥረይ ስለሆነ፥ ወንድና ሴት ልጅና ሽማግሌ ሳይል ወደርሱ ለመጡት ንስሐም ለገቡት ሁሉ በደላቸውን ሁሉ ይቅር ይላቸው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ከአይሁድ ውስጥ ይቃወሙት ነበር፥ እንዲህ ሲሉ “ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ይቅር ይል ዘንድ ማን ይችላል::[49] በአንድ በኩል ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለ አምላክ ነኝ አለ” ብለው ይከሱት በሌላ በኩል ደግሞ አምላክን ይመስል እንደ አምላክ ኃጢአትን ያስተሠርያል እያሉ ይከሱት ነበር:: በእርግጥም ኃጢአት ማስተሥረይ አምላካዊ ግብር ነው ክርስቶስም ሰው የሆነ አምላክ እንደመሆኑ ኃጢአትን ያስተሠርይ ነበር::





9. <u>በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር አብ የተነገረ የሚመስለው በሐዲስ ኪዳን ግን እነዚሁ ቃላት እየተጠቀሱ ለክርስቶስ እንደተነገሩ</u>፥

የዓለም ፈጣሪ ክርስቶስ እንደሆነ በሐዲስ ኪዳን የተነገሩትን እየጠቀስን ባለፈው ተናግረናል፥ አሁን ግን ከብሉይ ኪዳን ጥቅስ ጋር በማነፃፀር እንመልከት “አልሁም አምላኪየ በዘመኔ እኩሌታ አታንሣኝ ዓመታትህ ለልጅህ ልጅ ናቸውና:: አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትካት፥ ሰማዮች የእጅህ ሥራዎች ናቸው:: እርሳቸው ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትቆማለህ፥ ሁሉም እንደልብስ ያረጃሉ እንደመጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ ይለወጣሉ አንተ ግን እንዲሁ አንተ ነህ ዓመታትህ ከቶ አያልቁም”::[50] ይህንን ጥቅስ እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ለክርስቶስ አድርጎ በሐዲስ ኪዳን ያቀርብልናል::[51]

እንዲሁም ነቢዩ ኢሳይያስ “የአዋጁ ነጋሪ ቃል በምድረ በዳ የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ፥ በምድረ በዳ የአምላካችን መንገድ አስተካክሉ:: ዝቅ ያለው ሁሉ ከፍ ይበል ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይበል፥ ጠማማው ይቅና አቀበቱም ሜዳ ይሁን፥ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጣል፥ ሥጋም የለበሰ ሁሉ በአንድ ያዩታል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይኸን ሁሉ እንደተናገረ”::[52] ሲል የተናገረውን ቃል እንዳለ ለክርስቶስ ተነግሮለት እናገኛለን፥ ይኸንም ወንጌላዊያን እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ተናግረውት ሁሉንም በቀጥታም ለክርስቶስ አውለውት እናገኘዋለን::[53] ክርስቶስ ቀዳማዊ ነበርና አስቀድሞ ትንቢት አናገረ ቀጥሎም አዋጅ ነጋሪ አስነሣ፥ በፍጻሜ ዘመን ግን ራሱ ሰው ሆኖ ተገልጦ ታየ ሁሉም ለርሱ መሆኑ ተገልጦ ተረዳ::

እንዲሁም ነቢዩ ኤርምያስ “አንተ ግን የሠራዊት ጌታ በእውነት የምትፈርድ ኩላሊትንና ልብን የምትፈትን፥ ከእርሳቸው በቀልህን ልመለከት ምክንያቱን ገለጥኩልህም” ሲል ተነግሯል::[54] ይኸን የመሰለ ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ስንመለከት ተመሳሳይ ሆኖ ለክርስቶስ እንደተነገረ እናገኘዋለን::[55] በዚህ መልክ የተገለጠው ብዙ ነው፥ ለአብነት ያህል ብቻ ይኸን እንጠቅሳለን::



www.ethiopianorthodox.org

10. <u>እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር ወልድ በአምላክነት አንድ እንደመሆናቸው በእኩልነት በተነፃጻሪነትም ሲገኙ</u>÷

ቅዱስ ጳውሎስ በጽሑፍ እንደተለየ መታወቂያ አድርጎ አባታችን እግዚአብሔር አብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማለት በአንድ አረፍተ ነገር እያስገባ እንዲህ እያለ ያቀርብልናል÷ “የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ÷ የእግዚአብሔር ፍቅር÷ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት በሁላችሁ ላይ ይሁን”::[56] ይህንም አዘውትሮ የሚጽፈው ከክርስቶስ ትምህርት አብነት ነስቶ መሆኑ ግልጥ ነው÷ እርሱም “ሑሩ ወመሐሩ ኩሎ አሕዛበ÷ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በሰመ አብ÷ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ”::[57] ይኸን አገላለጥ በአንድ አምላክ ከሚያምኑት ወገኖች ሁሉ ክርስቲያኑ ወገን የሚለይበት ሥላሴነትን የሚገልጥበት ምክንያት ነው:: ይኸንም አብነት አድርጎ ክርስቲያኑ ሁሉ በድርሰቱ መጀመሪያና መፈጸሚያ ላይ የሥላሴን ስም እያስገባ ይጽፋል::

ቅዱስ ጳውሎስ በተጨማሪ “እግዚአብሔርም አባታችን ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እናንተ መንገዳችንን ያቅናልን” እያለ ያቀርብልናል::[58] ሁሉን ያደረገ ሁሉንም ለማድረግ የሚችል እግዚአብሔር አንድ ነው ብሎ ስለ አብ ሲናገር በወልድ ህልው ስለሆነ÷ አብም አብሮ አለ÷ ወልድ ብሎ ቢናገር አብ በወልድ ህልው ስለሆነ አብም አብሮ አለ÷ ከቶ ልዩነት በመካከላቸው የለባቸውም÷ በአካልና በስም ፫ ብለን የምንናገረውን አንድ እግዚአብሔር አንድ አምላክ አንድ ህልውና አለው ብለን እናምናለን::[59] ሐዋርያው ያዕቆብ መልዕክቱን ሲጀምር “ያዕቆብ ገብሩ ለእግዚአብሔር ወለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ” ብሎ ነው::[60] ክርስቶስ ራሱ ደግሞ ግልጥ አድርጎ እርሱ በአብ ህልው እንደሆነ አብም በእርሱ ህልው እንደሆነ “......... የሚወደኝ ቢኖር ነገሬን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል÷ ወደርሱ እንመጣለን÷ በርሱም ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን” ሲል አንድነታቸውንና እኩልነታቸውን ገልጧል::[61]





እንዲሁም ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል ብሎ አንድነታቸውን ተናገረ::[62] “አነ በአብ ወአብ ብየ÷ ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ÷ አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ” እያለ ራሱ ክርስቶስ እየመላለሰ አስረድቷል::

ቅዱስ ጴጥሮስም ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ እንደማይለይ አብሮ እንደሚሠራ “በአምላካችን ጽድቅ በመድኃኒታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ” ሲል ተናግሯል::[63] በአንደኛው መልዕክቱ ደግሞ እንዲህ ሲል ይመሠክራል “ቀድመው የተመረጡት እንደ እግዚአብሔር አብ እውቀት÷ በመንፈስ ቅዱስም÷ ለኢየሱስ ክርስቶስም በደሙ መረጨት::”[64] ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔር አብንና የክርስቶስን ምሥጢር ወደማወቅ ምእመናንን ሲመራ ሁለቱን አጫፍሮ ገልጦ ጽፎ እናገኘዋለን::[65] ራሱ ክርስቶስ ደግሞ እውነተኛ ሕይወት ለሰው ልጅ ሊኖረው የሚገባው እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔር አብንና የላከውን ክርስቶስን ማወቅ እንደሆነ ገልጦልናል::[66]

እንዲሁም “ልቦናችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በኔም እመኑ” ሲል እኩልነታቸውን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ይገልጥልናል::[67] ዮሐንስ በራእዩ ደግሞ “በታላቅ ድምፅ ጮኸ እንዲህ ይላል መድኃኒት በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠ÷ ለአምላካችንና ለበጉ” ሲል መድኃኒታችን የሚገኘው ከክርስቶስና ከባሕርይ አባቱ ከአብ ዘንድ እንደሆነ መስክሯል::[68]

ዮሐንስ በወንጌሉ በአብና በወልድ መካከል ያለውን እኩልነት÷ አንድነት በድጋሚ ሲገልጥ ክብር ለሁሉም እንዲገባ ሁሉንም ማክበር እንዳለብን እንዲህ ሲል ይናገራል “ሰዎች ሁሉ ወልድን እንዲያከብሩ አብን እንደሚያከብሩ ወልድን የማያከብር የላከውን አብንም አያከብርም” ብሏል::[69] ይኸንንም የመሰለ በራእዩ ገልጦልን እናገኘዋለን÷ “በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ በምድርም በታች በባሕርም በአሸዋም ያሉ ሁሉ ሁሉንም ሰማኋቸው እንዲህ ሲሉ÷ በረከትና ክብር ምስጋናም ችሎታም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ይገባዋል ለበጉም::”[70]



www.ethiopianorthodox.org

የወልድን አምላክነት ለማሳወቅ በጎላም ለማስረዳት ሲል ከአብ ጋር በማነጻጸር በማስተባበር አመጣው እንጂ የሌላ የማንንም ስም ከአብ ጋር በማጫፈር በማያያዝም ያመጣው የለም፥ እንግዲህ በዚህ መልክ የተነገረው የተጻፈው በብዙ መልክ ይገኛል።

11. <u>ለክርስቶስ አምልኮትና ስግደት እንዲገባው</u>፥ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፥ ቅዱሳት ሴቶች በመንገድ አገኙና ሰገዱለት።[71] ክርስቶስ በዐረገ ጊዜ አምላክነቱን በመረዳት ቅዱሳን ሐዋርያት ሰገዱለትና በፍጹም ደስታ ወደኢየሩሳሌም ተመለሱ።[72] ክርስቶስ በመርከብ ሳለ ነፋሱን ስለገሠጸ ባሕሩን ጸጥ ስላደረገ ሕዝቡ እንደሰገዱለት ማቴዎስ እንዲህ ሲል ይገልጥልናል "በመርከብ የነበሩ መጥተው ሰገዱለት እንዲህ ሲሉ አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ"።[73] አምልኮትን ስግደትን ተቀብሏል፥ ለእግዚአብሔር ብቻ መስገድ እርሱንም ብቻ ማምለክ እንዲገባ አስቀድሞ ተጽፎልናልና።[74]

የሰው ነገድ ብቻ ሳይሆኑ መላእክትም እንደሚገዙለት እንደሚታዘዙለት እንደሚሰግዱለት እንዲህ ሲል ተጽፎ እናገኛለን "ደግሞም በኩር ወደ ዓለም በገባ ጊዜ አለ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ለእርሱ ይስገዱለት"።[75]

የሚታየው የማይታየውም ፍጥረት ሁሉ ለክርስቶስ እንዲገዛ እንዲታዘዝ ጉልበት ሁሉ ለክርስቶስ እንዲበረከክ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይገልጥልናል "ለኢየሱስ ስም ጉልበት ሁሉ ይንበረከክ ዘንድ በሰማይም በምድርም ከምድር በታች ያለ ሁሉ"።[76] ይኸ ዓይነት አምልኮትና ስግደት ለኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር እንዲገባ አስቀድሞ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ተናግሯል "ይናገሩ ይቅረቡም ባንድነትም ይማከሩ። ይኸን ከጥንቱ ማን አሰማ? በዚያ ዘመን የተናገረ ማነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁንም? ከኔ ሌላም አምላክ የለም፥ ጻድቅ አምላክ የሚያድን ከኔ በቀር ሌላ የለም ወደኔ ተመለሱ ትድኑማላችሁ እናንተ በምድር ዳር ያላችሁ ሁሉ። እኔ እግዚአብሔር ነኝና ሌላም የለም። በራሴ ማልሁ ከጻድቅም አፍ





ነገር ወጣች አትመለስም። ጉልበት ሁሉ ለኔ ይሰግዳሉና ምላስም ሁሉ በኔ ያምናልና"።[77]

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እያለ ፍጹም አምላክነቱን ፍጹም መለኮቱን ይገልጥ የነበረው በሐዲስ ኪዳን ተገልጦ ለክርስቶስ እንደሆነና ስለ ክርስቶስ አምላክነት ቀጥታ ገላጭነት ያላቸው አዳዲስ ዐረፍተ ነገሮች እንደተሳለፉ የታወቀ ነው። ይኸንንም በመጠኑ የገለጥነው ለአንዳንድ ተጠራጣሪዎች መመሪያ እንዲሆን እንጂ ሁሉን የገለጥነው አይደለም። ይሁን እንጂ ይኸን ሁሉ እየተረዳ የክርስቶስን አምላክነት የሚክድ ቢኖር የአባቱንም ህልውና የካደ ነው፥ እውነትንም ለማወቅ ችሎታ የሌለው መሆኑ ግልጥ ነው።

## ም ዕ ራ ፍ ፫

### ምሥጢረ ተዋህዶ፥

የአንድ አካልንና የአንድ ባሕርይን ነገር ለመረዳት ሲፈለግ የቃልንና የሥጋን ተዋሕዶ ማመን ተገቢ ነው፥ ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአምላክ የተገኘ ፍጹም አምላክ እንደሆነ እንዲሁም ፍጹም ሰው መሆኑን በማመን ይፈጸማል። ዓለም ሳይፈጠር ከአብ የተወለደው አካላዊ ቃል በኋለኛውም ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፥ ልደቱም ማንኛውም ሰው እንደሚወለደው ሆኖ አንድም ነገር የጎደለው አንድም የተጨመረለት ሳይኖረው ነው። ስለዚህም ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው፥ ምንም የጎደለበት የለም፥ ጭማሪም የለበትም። ከአብ ቅድመ ዓለም እንደመወለዱ ደግሞ ፍጹም አምላክ ነው ምንም ሕፀፅ የለበትም፤ ስለዚህ ከአብ ጋር በመለኮት ትክክል ነው ዕሩየ መለኮትም ነው። ሰውም እንደመሆኑ ፍጹም ሰውነት አለው ውሳጤ የለበትም፥ ይኸም ሊሆን የቻለው ከ፪ ባሕርያት አንድ ባሕርይ ከ፪ አካላት አንድ አካል ሆኖ ስለተዋሐደ ነው። ተዋሕዶውም መለወጥ መከለስ ወይም መጨመር የሌለበት ሊለወጥም በማይቻል አምላካዊ ምሥጢር ነው። ስለዚህም ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ከቶ አይባልም፥ አንድ አካል፤ አንድ ባሕርይ፤ እንጂ



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም የተነሣ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አንድ ፈቃድ ለክርስቶስ አለው ብለን እናምናለን፥ እንዲሁም እንናገራለን። አሁንም አንዱን ጌታ አንዱን አምላክ አንዱን ኢየሱስን እናመልካለን፥ ለእርሱም እንሰግዳለን፥ ከአባቱ ጋር ከመንፈስ ቅዱስም ጋር።

የቃልና የሥጋ ተዋሕዶም በዚህ መልክ የተፈጸመ ነው፤ ማለት አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን በተቀረፀ ሥጋንም በለበሰ ጊዜ ነው። በዚህም ጊዜ የቃል አካል ከሥጋ አካል ጋር፥ የሥጋም ባሕርይ ከመለኮት ባሕርይ ጋር ሊለይ በማይቻል ምሥጢር ፈጽሞ ተዋሕዷል፥ አንዱ ባሕርይ አንዱን ሳያጠፋው አንዱም አንዱን ሳያዋርደው ተዋሐደ። ስለዚህም ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ቄርሎስ የሥግው ቃለ እግዚአብሔር ባሕርይ አንድ ነው ሲል ጽፏል።[1] በማሕፀን የተደረገው ተዋሕዶ ፍጹም ተዋሕዶ እንደሆነ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ "ቃል ሥጋ ሆነ፥" ሲል የረቂቁን የቃልንና የግዙፉን የሥጋን ፍጹም ተዋሕዶ አስረዳ። ይኸም ማለት ጥንትነት ያልነበረው ሥጋ ቃልን ተዋሕዶ ቀዳማዊ አምላክ ሆነ፥ ዘመን የማይቆጠርለት ቃል ደግሞ ሥጋን ተዋሕዶ ዘመን ተቆጠረለት፥ "ወየአክል ፴ ክረምቱ ለእግዚእ ኢየሱስ" ሲል ወንጌላዊ ሉቃስ ጽፏልና።[2] በዚህም ጊዜ የሥጋ ገንዘብ ለቃል፥ የቃልም ገንዘብ ለሥጋ ሆነው፥ ፍጹም ተዋሕዶም በዚህ መልክ ተፈጸመ። አምላክ ሰው ሲሆን ሰውም አምላክ ሲሆን የትስብእትም ሆነ የመለኮት ባሕርይ ውላጤ ከቶ አላገኘውም፥ በተዋሕዶ ምሥጢር ብቻ አንድ ሊሆን ቻለ እንጂ፥ ስለዚህ ለክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይም እንዳለው እናምናለን። ይህንንም ስንል በተዋሕዶ ነው እንጂ ብቻ የመለኮት ባሕርይ፥ ወይ ብቻ የሥጋ ባሕርይ እንዳለው አድርገን መናገራችን አይደለም። የሥጋ አካልና የሥጋ ባሕርይ ከመለኮት አካልና ከመለኮት ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ አንድ ሆነ፤ ከዚህም የተነሣ ሞናፌሲት የሚሉት ስም የጠላት አሰጣጥ ነው፥ ፍጹም አንድ ባሕርይ ብቻ ማለት ነው። እኛ ግን አንድ ብቻ የሚለውን አንቀበልም፥ ከሁለት ባሕርያት በተዋሕዶ አንድ ሆነ እንላለን እንጂ ብቻ የመለኮት ወይም ብቻ የትስብእት ባሕርይ ነው አንልም። መለኮት ሥጋን



www.ethiopianorthodox.org



ሲዋሐድ የሥጋን ባሕርይ መጠጠው አጠፋው ስለዚህም ለክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ አለው የሚሉትን እናወግዛለን። እንዲሁም ከተዋሕዶ በኋላ ለክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ሁለት ፈቃዶች አሉት አንልም፥ ሰው የሆነው አምላክ፥ አምላክ የሆነው ሰው በተዋሕዶ ነውና፥ ይኸውም ፈጣሪ መለኮት ፍጡር ሥጋን ስለተዋሐደ፥ ፍጡር ሥጋም ፈጣሪ መለኮትን ስለተዋሐደ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ። ስለዚህ ሰማያዊ ምድራዊ ሆነ ምድራዊውም ሰማያዊ ሆነ። የእኛ ነፍስ ነባቢነቷን፥ ለባዊነቷን፥ ሕያዊትነቷን ሳትለቅ ሥጋን በተዐቅቦ እንደተዋሐደች አካላዊ ቃልም አምላክነቱን ምልዓቱን ስፋቱን ርቀቱን ሳይለቅ ምንም ውላጤ ሳይኖርበት ሥጋን በተዐቅቦ ተዋሕዷል። የእኛም ሥጋ ጥበቱን ግዙፍነቱን ውሱንነቱን ሳይለቅ አካላዊ ቃልን ተዋሕዷል። ስለዚህም በሰውነቱ የአምላክነቱን ሥራ፥ በአምላክነቱም የሰውነቱን ሥራ ይሠራል። የሥጋ ገንዘብ ለቃል፥ የቃልም ገንዘብ ለሥጋ ነውና፥ ይገናዘባሉና፤ የተዋሕዶውም ምሥጢር ይኸው ነውና።

የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ፥ አንድም የአንድ አካልና የአንድ ባሕርይ ምሥጢር በአሳብ ብቻ ሳይሆን በሥራ ተገልጧል፥ ይኸም ማለት በመስቀል የተሰቀለው ያው ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፥ ማለት ምንም በሥጋ ባሕርይ ቢሰቀል መለኮት ፈጽሞ አልተለየውም፥ ምክንያቱም ሥጋን ያልተዋሐደ መለኮት ብቻ ሊሰቀል አይችልም ረቂቅ ነውና፥ ግን ሥጋን ስለተዋሐደ ተሰቀለ። እንዲሁም መለኮትን ያልተዋሐደ ሥጋ ብቻ ተሰቅሎ ቢሆን ዓለምን ሊያድን ከቶ አይችልም ነበር፥ ብዙ ሰው ተሰቅሏል፥ ግን ዓለምን ያዳነ ከክርስቶስ በቀር ማንም የለም። በዚያውስ ላይ ድንቁ ምንድን ነው? መለኮት በለበሰው ሥጋ በተዋሐደውም በሥጋ ባሕርይ ተሰቀለ ካላልን "እንዘ ቅንው አንተ ዲበ ዕፀ መስቀል ኢአረቀ እምነ መንበርከ ወኢተፈለጥከ እምነ መለኮትከ ወእምነ መንፈስ ቅዱስ" ሲል ሊቁ አርካቦስ ተናግሯልና።[3]

ክርስቶስ ተሰቀለ ባልን ጊዜ በፍጹም ተዋሕዶ ሥጋም መለኮትም በአንድ ላይ ያለ መለያየት እንደሆነ፥ ማመን አለብን፥ ምክንያቱም ከላይ እንደተናገርነው ሥጋን ያልተዋሐደ

መለኮት ረቂቅ ስለሆነ ብቻውን ከቶ ሊሰቀል አይችልም፥ መለኮትንም ያልተዋሐደ ሥጋ ብቻውን ቢሰቀል ደግሞ ግዳጅ አይፈጽምም ነበርና፡፡

መለኮት ሥጋን ሲዋሐድ ርቀቱን ምልዓቱን ሳይለቅ ነው፥ ሥጋም መለኮትን ሲዋሐድ ግዙፍነቱን ሳይለቅ ውሱንነቱን ሳይተው ነው፥ ማለት በተዐቅቦ ነው፥ ይኸም እንዴት ይቻላል ያልን እንደሆነ የነፍስንና የሥጋን ተዋሕዶ እንመልከት፥ ማለት ነፍስ ረቂቅነቷን ሳትተው ከግዙፍ ሥጋ ጋር ተዋሐደች፥ ሥጋም ግዙፍነቱን ሳይተው ከረቂቁ ከነፍስ ጋር ተዋሕዶ ይገኛልና፡፡ "አንተ ምስለ አብ በውስተ ሰማይ፥ ወአንተ ስቁል በዲበ ዕፀ መስቀል፥ አንተ ዘኢትሐምም በመለኮት ወአንተ ሐማሚ በሥጋ" ይላልና፡፡[4] ይህም ማለት ኢሐማሚ መለኮት ሥጋን ተዋሕዶ ተሰቀለ፥ ሐማሚ ተባለ፥ ይሁን እንጂ ቢሰቀልም ከቶ ሕማመ ሥጋ ድካመ ሥጋ አላገኘውም አልተሰማውም፥ ምክንያቱም መለኮት አይታመም አይሞትምና፤ ይኸንም ታላቁ ሊቅ ቄርሎስ በእሳትና በብረት ተዋሕዶ ሲመስል ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፥ የጋለውን ብረት በመዶሻ በሚቀጠቅጥበት ጊዜ የሚመታው እሳቱና ብረቱ ቢሆንም ስሜቱ ለብረት ብቻ እንጂ ለእሳቱ እንዳይደለ መስሎ ተናግሯል፡፡[5] ሐማሚ ሥጋም ኢሐማሚ መለኮትን ተዋሕዶ ስለተሰቀለ ለዓለም ድኅነትን ለመስጠት ቻለ፥ ለሰውነት ሞት ለመለኮት ሕይወት ገንዘቡ ስለሆነ በተዋሕዶ የሥጋ ገንዘብ ለቃል፤ የቃልም ገንዘብ ለሥጋ ሆነ ስለዚህ "ሞተ ዘኢይመውት" እንላለን፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም የተዋሕዶን ነገር አጉልቶ ሲናገር፥ "ሞተ በሥጋ" ብሎ የመለኮትን ሥራ በሥጋ ባሕርይ፥ "ወሐይወ በመንፈስ" ብሎ የሥጋን ሥራ በመለኮት ባሕርይ የገለጠውን ተናገረ፡፡ ሞተ በሥጋ የተባለው መዋቲ ሥጋን የለበሰ መለኮት ነው፥ ወሐይወ በመንፈስ የተባለ ደግሞ ሕያው መለኮትን የተዋሐደ ሥጋ ነውና፡፡[6] ይኸን በመሰለ አገላለጥ፥ ቅዱስ ጳውሎስም "እምከመ ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ" ብሎ የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን እንደሞተ በርሱም ሞት ደግሞ እኛን ይቅር እንዳለን ተናግሯል፡፡[7]





ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ፍጹም ሰው እንደመሆኑ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በሥልጣኑ ለያት፥ ይሁን እንጂ መለኮት ከሥጋም ጋር በመቃብር፤ ከነፍስም ጋር በሲኦል ነበር፥ ነፍስ ተለየች ይባላል እንጂ መለኮት በምንም ጊዜ ከሥጋ ተለየ አይባልምና፡፡ ሥጋም አንድ ጊዜ ከተዋሐደ በኋላ በምንም ምክንያት ከመለኮት ሊለይ አይችልም፥ መለኮት እንደሆነው ይሆናል እንጂ፡፡ በፍጹም ተዋሕዶ መለኮት ከሥጋ ጋር ስለተዋሐደ ሞት እንኳን አልለየውም፥ ይህንም ቅዱስ ፊላታዎስ ሲያስረዳ "ሶበ ተፈልጠ ነፍስ እምነ ሥጋ ወኢእምነ ነፍስ ዘትትፈለጥ እምነ ሥጋ" ብሏል፡፡[8]

ሥጋ መለኮትን ተዋሕዶ በመቃብር በነበረ ጊዜ እንዲሁ ሥጋ መለኮትን ሰለ ተዋሐደ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ተቀምጠ ዓለምን ይገዛ ያስተዳድር ይመግብ ነበር "አንተ ውእቱ ንቡር በውስተ መቃብር ወአንተ ንቡር በዲበ ኪሩቤል፥ ወአንተ ምውት ሠሉሰ መዋዕለ ወአንተ ሀለዉ ምስለ አብ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ በኩሉ አዝማን" ሲል ይኸው ሊቅ እንደገና አስረድቷል፡፡ ምንም ክርስቶስ አምላክነቱን እንደዚህ አድርጎ ቢገልጽ ወዲያውኑ ቤተ ክርስቲያን እንደተቋቋመች ስለ ክርስቶስ አምላክነት ሰለባሕርዩም ሁናቴ ጥርጥር ስለመጣ የመናፍቃን ክርክር ቀጠለ፥ የክርስቶስንም መንጋ በተኑት፥ ለያዩት፥ ከፋሉትም፡፡ ኦርቶዶክሳዊያን አባቶች ግን የቀናውንና እውነተኛውን ሃይማኖት በጉባዔ እየወሰኑ መናፍቃኑን እያወገዙ በመላ ዓለም ሊያምንበትና ሊቀበለውም የሚገባውን የሃይማኖትን ትምህርትና አንቀጽ በየጊዜው ወሰኑ እንጂ እንዲሁ የምንግዴ አልተውትም፥ በመፍራትም ቸል አላሉትም፥ ለምሳሌ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የመጀመሪያው ጉባዔ እየተባለ የሚጠራው በኒቂያ የተደረገው ጉባዔ በአርዮስ ምክንያት የተናወጠውን ቤተ ክርስቲያን ጸጥ ለማድረግ ነበር፥ እነርሱም ተሰብስበው ከዚህ የሚከተለውን ወሰኑ፥ "ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ አንድ የአብ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፡፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በባሕርዩ ከአብ ጋር የሚተካከል(አንድ የሚሆን)፡፡ ሁሉ በርሱ



www.ethiopianorthodox.org

የታዛዥነት ምሳሌ ነው፥ እስከ ሞት ድረስ እሽ አለ፥ ታዘዘ፥ ሞቱም በመስቀል ሆነ ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ ገልጦ ተናግሮለታል::[13] እንዲሁም የመስቀሉ ሞት ከሰው ፍቅር የተነሣ እንደሆነ ግልጥ ነው፥ የሰው ፍቅር እንዲሁ ከሞት አደረሰው::[14]

በመስቀል መሞቱ ዘለዓለማዊ መሥዋዕት ስለኛ ለማቅረቡ፥ ለሁሉ ጊዜ ድኅነተ ሥጋንም ድኅነተ ነፍስንም የሚሰጥ እንደሆነ ያመለክታል::[15] ይኸንም ሁሉ ለመግለጥ "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም" ሲል ይገልጥልናል::[16] ሕዝብ ሁሉ ከሚጎዳ እርሱ ለሁሉ ቤዛ ሆኖ መሞትን መርጧልና:: በኦሪት ከነበረው መሥዋዕት የተለየ የከበረና የማዳን ኃይል ያለው መሥዋዕት ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ ቀረበ:: በተለይም በዓመት አንድ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ያቀርበው ከነበረው መሥዋዕት የበለጠ ሆኖ ተገኘ:: ያ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ሁሉ ምሳሌ እንጂ የማዳን ኃይል ከቶ አልነበረውም፥ በዚያን ጊዜ ብዙ ደም ቢፈስም ከቶ ያዳነው የለም:: የእውነተኛ መሥዋዕት የክርስቶስ ደም ግን ዓለሙን ሁሉ አዳነ፥የሰውን ልጅ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ::

## ፪ <u>የክርስቶስ የነቢይነቱ ማዕረግ፥</u>

የክርስቶስ የነቢይነቱ ማዕረግ የሚገለጠው ወይም የሚታወቀው ከፍተኛና እውነተኛ የሆነውን ትምህርት ማስተማሩ፥ ለሰው ልጅ በሚሰጠው ጸጋ ሁሉ በቂ ሆኖ እንዲገኝ ለማዘጋጀት የሆነውን ትምህርት ነው::

የብሉይ ኪዳን ነቢያት የማንቃት የማትጋት የመቀስቀሻ ትምህርት ለእሥራኤላውያን ቢሰጡም ከእግዚአብሔር ተልከው በርሱም ገላጭነት ነው፥ ክርስቶስ ግን በራሱ ፈቃድ በአባቱም ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስም ሥምረት ተልኮ እውነተኛውን የድኅነት ወንጌል ለሁሉም ሰበከ:: ይኸንንመ በገጠር በመንደር በመቅደስ ሕዝብ በተሰበሰበበት መስከረ፥ ነገረ፥ አስተማረ፥ ይኸም ሁሉ ሲሆን በመናገር ብቻ ያስተማረ አይደለም በሥራም እየገለጠ እያሳየ አስተማረ እንጂ:: የክርስቶስ የራሱ ኑሮ ሳይቀር ግልጥ ምስክርና ማስተማሪያ ነበር፥ እርሱም ሰውን ለማቅረብ፥ ሰውን



www.ethiopianorthodox.org



ለመሰብሰብና አንድ ለማድረግ "አነ ውእቱ ፍኖት፥ ወጽድቅ፥ ወሕይወት ወዘይተልወኒ ኢየሐውር ውስተ ጽልመት አላ ይረክብ ብርሃነ ሕይወት" እያለ ያስተምር ነበር::[17]

ነቢያት ተግባራቸውን ለመፈጸም ምልክት በማሳየት ተአምራት በማድረግ ትንቢት በመናገር ይሠሩ ነበር፥ ክርስቶስም በዚህ መልክ ይሠራ ነበር::[18] እንደ ነቢይነቱ፥ የኢየሩሳሌምን ጥፋት ቀደም አድርጎ ተናገረ፥ በምድርም ሰላም እንዲመሠረት የመንግሥቱም ሕግ የሚነገርባት ቤተ ክርስቲያን ጸንታ እንድትኖር አስቀድሞ ተናገረ:: በዚህ ሁሉ ምክንያት ክርስቶስ ሊቀ ነቢያት ነው፥ ስለ እርሱም የተነገረው ትንቢት ሁሉ ተፈጸመ፥ ስለዚህም ክርስቶስ የሰው ነገድ ሁሉ የበላይ መምህር የበላይም ነቢይ ነው፥

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ እግዚአብሔር ቃል ከመንፈስ ቅዱስ የተገለጠላቸውን የታዘዙትን ይናገራሉ፥ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው መንፈስም ተአምራት ያደርጋሉ፥ ጌታችን ኢየሱስ ግን ራሱ የአብ ቃል እንደመሆኑ፥ ከአብ ጋር አንድ እንደመሆኑ የራሱንም የአባቱንም ፈቃድ ይናገራል፥ ያንንም ያስተምራል፥ ከአባቱ ጋር ያለውን አንድነታቸውን ይገልጣል እውነትን ይናገራል:: የሚያሳየው ተአምራት ደግሞ አምላክ እንደመሆኑ ከባሕርዩ ከአምላክነቱ የመነጨ ነው[19]:: የክርስቶስም ትምህርት የነቢያት ትምህርት ሁሉ ማጠቃለያ ነው፥ ከርሱ በኋላ ነቢይ አልተነሣምና:: ሐዋርያት ግን በሌላ መንፈስ ተቃኝተው በሌላ መልክ ሲያስተምሩ ኑረዋል፥ አሁንም ያ መንፈስ ይቀጥላል:: ይኸንም ሁሉ ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል ማለት የክርስቶስ ትምህርት ምን ዓይነት እንደሆነ ይገልጣል::

በመጀመሪያ ደረጃ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ መሢሕ የተናገሩ፥ የመሰከሩ ብዙዎች ናቸው፥ ክርስቶስም ነቢይ እንደሆነ፥ ከእግዚአብሔርም የተላከ እንደሆነ ሙሴ እንዲህ አለ "ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እግዚአብሔር አምላክ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል እርሱን ስማው[20]:: ይኸውም ወደፊት በጨለማ የሚኖረውን ሕዝብ ወደ ብርሃን የሚመራ ቃል ነው" [21]:: ሐዲስ ኪዳን ይኸኑ ተከትሎ እንዲህ አድርጎ ይገልጣል በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህም አለ" እርሱ በዚህ በኋለኛው ዘመን በልጁ ነገረን ሁሉን ወራሽ ባደረገው ዓለሙንም በርሱ

ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ እንዲህ ይላል "ክርስቶስም አንድ ጊዜ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ሞተ"[32]። እንዲሁም ክርስቶስ ወደሲኦል ወርዶ መበርበሩን አሁንም ቅዱስ ጴጥሮስ በትክክል ደግሞ ይመሰክራል[33]። የክርስቶስ ንጉሥነት በመስቀል ላይ የተገለጠ ሲሆን ቅድስት ነፍሱን በሥልጣኑ ከቅዱስ ሥጋው ሲለይ፥ ነፍሱ ደግሞ ወደሲኦል ወረደች ለነፍሳትም ነፃነትን ሰበከች፥ ይኸንንም ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጴጥሮስ በርሱም በግዞት ወዳሉት ነፍሶች ሔዶ ሰበከላቸውም ሲል ያስረዳናል[34]።

ይኸን በሲኦል ወርዶ መሰበኩን ቅዱስ ጴጥሮስ ከመንገሩ በቀር ሌላ ሐዋርያ ወንጌላዊም አይተርክልንም። የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ዝም ብለው አልፈውት ይገኛል፥ መጽሐፈ ኪዳንም ከሚባለው አንደኛው ክፍል ትምህርተ ኅቡዓት ላይ ግን ሰፋ ያለ አገላለጥ እናገኝበታለን[35]።

ይኸን ወደ ሲኦል ወርዶ የሰበከበትን ዓላማ ደግሞ ሊቃውንት በየበኩላቸው እንደሚከተለው አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

1. ከክርስቶስ በፊት የሞቱትን ነፍሳት ለማብሠር፥ ማለት ሞት እንደጠፋላቸው ክርስቶስ እንደነገሠላቸው ለመንገር፥
2. መሢሕነቱን ለመግለጥ፥ ግዛቱ፡ መንግሥቱ፡ ወሰን የሌለው እንደሆነ፥ በሲኦል ያሉት፥ ራሱ ሲኦልም የርሱ ግዛት እንደሆነች ለማስረዳት፥
3. ልጅነትን አጥተው ተፈርዶባቸው ሲኦል የገቡትን ሰብኮ ያመኑትንና እርሱን የተቀበሉትን ነፃ ለማውጣት ነው። ይኸንም የመሳሰሉ ሌሎች አስተያየቶች አሉ፥ ሁኖም የሁሉ ጠቅላላ አስተያየት አንድ ነው ክርስቶስ እውነተኛው ንጉሥ የሁሉም ገዥ የሁሉም አስተዳዳሪ መሆኑን የሚገልጥ ነው።

በእርግጥም በሥጋው ለሦስት ቀናት ያህል በመቃብር በአረፈበት ጊዜ ነፍሱ ደግሞ በሲኦል እየሰበከች ቆይታለች። በ፫ኛው ቀን ሲነሣ ግን ነፍሳትን ሁሉ ይዞ እንደወጣ ወደ ገነትም እንዳሸጋገራቸው ቤተ ክርስቲያን ትናገራለች።





# ም ዕ ራ ፍ ፭

## የክርስቶስ ሞት፥

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም እንደመጣ በሰውም እግር ገብቶ በደለኛ ተብሎ መከራን እንዲቀበል፥ እንዲሞትም አስቀድሞ ምሳሌ ተመስሏል፥ ትንቢትም ተነግሯል። እርሱም ሰው የሆነበት ዋናው ዓላማ ሞትን ለመቅመስና የሰውን ልጅ ለማዳን ብቻ ነበር፥ ይኸም ስለሆነ የክርስቶስ ሞት ድንገተኛና ሳይታሰብ የሆነ አደጋ አይደለም። ስለሰው ድኅነት በሰው በደል ለመግባት በደለኛ ተብሎ ለመቆጠር ብቻ ሰው ሁኗልና። ስለዚህም ሞተ እንጂ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ "ልጆችም በሥጋ በደም ተገናኝተውታልና እርሱም ደግሞ በዚህ ተገናኛቸው፥ በሞቱ የሞትን ሥልጣን ይሰብር ዘንድ እርሱም ሰይጣን" ሲል ሐዋርያዊ ትምህርቱን ያስተላልፍልናል[1]።

ክርስቶስ የሰው ሕይወት (ኑሮ) አስደስቶት አታሎትም ሰው የሆነ አይደለም፥ ደግሞም በሰው እጅ ለመገልገል ከሰውም ጋር ለመኖር ብሎ ሰው የሆነ አይደለም፥ ራሱን ለሰው ቤዛ አድርጎ ለመስጠት ብቻ ሰው ሆነ እንጂ ይኸንም ወንጌላዊው ማቴዎስ "የሰው ልጅ ሊያገለግል እንጂ ሊያገለግሉት እንዳልመጣ፥ ነፍሱንም ለብዙ ቤዛ ሊሰጥ እንጂ" ሲል አስፋፍቶ ክርስቶስ ሰው የሆነበትን ዓላማ ዘርዝሮ አስረድቷል[2]። ክርስቶስ ቤዛችን ነው፥ ስለዚህ ለኛ ለውጥ ሆኖ በኛም ዕዳ ገብቶ ሞተ።

እንደገና ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ሞትና መቃብር በጠቅላላም ስለ ሰው ልጅ የተቀበለውን መከራ በመግለጥ እንዲህ ሲል ይመሰክራል "ወንድሞች ሆይ እነግራችሁ አለሁ ያስተማርኳችሁ ወንጌል የተቀበላችሁትም በርሱ የጸናችሁበት በርሱም ትድናላችሁ፥ በምን ነገር አስተማርኳችሁ ታስቡት እንደሆነ በከንቱ ያመናችሁ ሳትሆኑ አስቀድሜ ሰጥቻችኋለሁና እኔ ደግሞ የተቀበልኩትን ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን እንደሞተ እንደተጻፈ። እንደተቀበረም፥ በሦስተኛውም ቀን እንደተነሣ እንደተጻፈ[3]።

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለሕማም ለመከራ ለሞት ነው ብለናል፥ ግን ከሞት ያደረሰው ምንድን ነው ያልን



www.ethiopianorthodox.org

እንደሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ይነግረናል "እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ተወጋ ስለ አመፃችን ደቀቀ፥ የድህንነታችን ተግሣፅ በርሱ ላይ ነው፥ በርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን[4]:: ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት ሲሆን ስለ ኃጢአታችን ሞተ ስለዚህም ክርስቶስ የርሱ ሞት ተገቢ መሆኑን ተቀብሎ በአባቱ ፈቃድ በራሱም ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስም ሥምረት እሺ በጄ ብሎ ለሞት ደረሰ::

እንዲሁም የክርስቶስ ሞት ካሣ እንደሆነ፥ የርሱም ደም ንጹሕ ወርቅ ሆኖ ለኛ ሞት ዋጋ ወይም ለውጥ ሁኖ የተሰጠ ነው፥ ይኸንንም ቅዱስ ጴጥሮስ በመመስከር "ታውቃላችሁ በሚጠፋ በወርቅና በብር ከከንቱ ሥራችሁ እንዳልተለያችሁ፥ ከአባቶቻችሁ ለተቀበላችሁት፥ ነገር ግን በከበረው በበግ ደም፥ ነውር ርኩሰትም የሌለበት እርሱም ክርስቶስ"[5]:: እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፥ ስለዚህም ኃጢአትን ይጠላል፥ ስለዚህም ኃጢአትን ለማጥፋት ንጹሕ የሰው ልጅ ደም እንዲፈስ አስፈለገ:: ስለዚህ ያልበደለው ክርስቶስ በደለኛ ተባለ፥ በበደለው በሰው ልጅ እግር ገባና ሞተ፤ ይህንም ነቢዩ ኢሳይያስ ሲመሰክር "እኛ ሁላችን እንደበግ ጠፋን ሁሉ ወደ መንገዱ አዘነበለ:: የሁላችንንም ኃጢአት እግዚአብሔር በእሱ ላይ አኖረበት"[6] ብሏል::

ክርስቶስ በጾታ፥በዕድሜ፥ በዘር በሌላም ይኸን በመሳሰለ በሰው ልጅ መካከል ልዩነት ሳይደርግ ሁሉን ለማዳን ብቻ ሰው ሆነ:: ስለዚህም እንደዓላማው ለመፈጸም በመስቀል ተሰቅሎ ንጹሕ ደሙን ስለሁሉ አፈሰሰ፥ ሁሉንም አዳነ ስለዚህም መድኃኔዓለም ተብሎ ይጠራል:: ስለ ሁላችን ልጁን ለሕማም ለሞት ከሰጠው ለኛ እግዚአብሔር ሁሉንም ይሰጠናል፥ ከዚህ የበለጠ ሌላ ነገር የለምና[7]:: በክርስቶስ ሞት ሁሉም ወደ ሕይወት ተሳበ ሁሉም ከሞት ዳነ[8]:: ክርስቶስ በሞቱ ኃጢአትን ከዓለም አራቀ ስለዚህ ይቅርታ ለሁሉ ሆነ በዚህን ጊዜም ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነ[9]::

ክርስቶስ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል እንደ ግድግዳ የነበረውን ኃጢአት አፈረሰ፥ኃጢአትን በመስቀል ቀጣው ቸነከረው፥ ስለዚህም የዳነው ሁሉ የሰው ልጅ ተብሎ ሊጠራ ቻለ:: ይኸንንም ቅዱስ ጳውሎስ አስፋፍቶ ሲገልጥ "በኛ ላይ የተጻፈውን ጽሕፈት ባጠፋ ጊዜ ለኛ ጠላት የነበረውን ከመካከላችን አወጣው በመስቀሉም ቸነከረው" ብሏል[10]::





# ም ዕ ራ ፍ ፮

## የክርስቶስ ትንሣኤ፥

ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ ድኅነት፥ ስለ ኃጢአት ሥርየት ከመስቀል መከራ በኋላ ሞተ፥ፍጹም ሰው እንደመሆኑም ተቀበረ፥ እንደ አምላክነቱ ግን በሦስተኛው ቀን መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ሌላም ረዳት ሳይሻ በኃይሉ ተነሣ:: አብ አንሥአ፥ መንፈስ ቅዱስ አንሥአ፥ ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ፥ ወተንሥአ እያለ በተለያየ መልክ ይገኛል፥ ሁሉም አንድ ነው፥ በአምላክነት ሦስቱም አካላት አንድ ናቸውና:: እንዲሁም ወልድ በሥልጣኑ ቢነሣ ራሱ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው ነውና በሥልጣኑ በኃይሉ ተነሥቷል::

ነቢዩ ዳዊት "ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም፥ ወከመ ኃያል ወኅዳገ ወይን፥ ወቀተሎ ፀሮ በድኅሬሁ" ሲል ራሱ በሥልጣኑ መነሣቱን ቀደም አድርጎ ተናግሯል[1]:: በብዙ ቦታ ደግሞ እግዚአብሔር አሥነሣው እያለ ይመሰክራል[2]::

እምነታችን ግን የክርስቶስ መነሣትን ሞት ይዞ ሊያስቀረው አለመቻሉን መቃብርም በርሱ ላይ ሥልጣን አለመኖሩን ማወቅና ማመን ብቻ ነው::

ስለዚህ ክርስቶስ ተነሣ ብለን እናምናለን እንናገራለንም፥ የክርስቶስ ትንሣኤ የትምህርታችን የእምነታችን ሁሉ ማኅተምና ምስክር ነው:: የወንጌሉ ትምህርት ማጠቃለያ እርሱ ነውና ማለት ክርስቶስ ወረደ ተወለደ ሲባል፥ እንዲሁም ዞረ አስተማረም፥ ተሰቀለም ሞተ ሲባል እንደ ተራ ሰው ያሰኛል፥ ትንሣኤው ግን አምላክነቱን ኃያልነቱን የሁሉም ገዥ መሆኑን አስተዳዳሪነቱን ያመለክታልና:: ስለዚህ በእርሱ የሚያምኑት እርሱንም የሚከተሉት ሁሉ አያፍሩም:: ክርስቶስ ባይነሣ ግን እምነታችን ትምህርታችን ሁሉ ከንቱ በሆነ ነበር ይኸንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር "ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችን ከንቱ ነው ብሏል"[3]:: የክርስቶስ ትንሣኤው የእምነታችን ማኅተም መሆኑን



www.ethiopianorthodox.org

ሁኖ አንዳንድ ጊዜ በተራ አቀማመጥም ሳይቀር ይዘዋወራል፥ ለምሳሌ ሐዋርያው ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ፪ኛ ተራ ሰጥቶ እንዲህ ሲል ይጽፋል "ቀድመው የተመረጡት እንደ እግዚአብሔር አብ እውቀት በመንፈስ ቅዱስም ለመታዘዝ ለኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ መረጨት"[6]:: በዚህ መልክ ሌላም ብዙ ይገኛል፥ ይሁን እንጂ ስመ ተፋልሶ በሥላሴ የለባቸውም:: አብ አብ ይባላል እንጅ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም፥ ወልድም መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በየስማቸው ይጠራሉ እንጂ ምንም በመለኮት አንድ ቢሆኑም በተራ አቀማመጥም ቢዘዋወሩ ስማቸው ግን ሳይፋለስ እንደ ተጠበቀ ይኖራል::

፪. የመንፈስ ቅዱስ ብሂል፥ የቅዱስ መንፈስ ስም በልዩ ልዩ መልክ ይነገራል ልዩ ልዩ ትርጉምም ይሰጠዋል ስለዚህ መንፈስ ማለት እስትንፋስ ነፈስ ማለት ነው ይኸንም ዮሐንስ ወንጌላዊ እንዲህ ሲል ይገልጥልናል "ይኸንንም ብሎ እፍ አለባቸው አላቸውም፥ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ..."[7]:: እንዲሁም ሊቀ ነቢያት ሙሴ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፥ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለበት ሆነ" ሲል ይገልጥልናል[8]:: መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አብና ወልድ የባሕርይ ሕይወት ነው፥ ራሱን የቻለ አካል አለው፥ ሁኖም በልዩ ልዩ መልክ በተለይም በነፋስ መልክ ስለሚታይ መንፈስ ይባላል::

"ድንገትም ከሰማይ ድምጽ ሆነ እንደ አውሎ ነፋስ፥ ተቀምጠውበት የነበረውንም ቤት መላው" ሲል ሊቃስ ይነግርናል[9]:: መንፈስ ረቂቅ ነው አይያዝም አይጨበጥም፥ እንዴት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሔድ አይታወቅም[10]:: እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚባለው ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው[11]::

ሀ. የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ይባላል ይኸንንም ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ይገልጣል የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ያርፍባት የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኃይል፥ መንፈስ፥ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ"[12]:: ቅዱስ ጳውሎስም ይኸንኑ አስተያየት በመደገፍ እንዲህ ሲል





ይናገራል "እናንተ ግን በሥጋ አይደላችሁም በመንፈስ እንጂ የእግዚአብሔር መንፈስ ከአደረባችሁ የክርስቶስ መንፈስ ግን የሌለበት ያ እራሱ ለእርሱ አይደለም"[13]::

ለ. የክርስቶስ መንፈስ ይኸም አገላለጥ በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ግንኙነት በበለጠ ያጎላዋል "ልጆችም በሆናችሁ ጊዜ እግዚአብሔር የልጁን መንፈስ በልባችሁ ላከ እንዲህ የሚጠራ አባታችን አባት"[14]::

ሐ. የተስፋ መንፈስም ይባላል መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ የተስፋ መንፈስ ነው፥ ይኸንንም ራሱ ክርስቶስ ለሐዋርያት የተስፋ መንፈስ እንደሆነ እንዲህ ሲል ተናግሯቸዋል "እኔም እነሆ የአባቴን ተስፋ እልክላችኋለሁ፥ እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ከተማ ተቀመጡ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ ከላይ"[15]:: ቅዱስ ሉቃስም ይኸንኑ በማጽናት ሲመሰክር "ነገር ግን ኃይልን ትቀበላላችሁ መንፈስ ቅዱስ በወረደባችሁ ጊዜ..."ብሏል[16]::

መ. የእውነት መንፈስ ይባላል፥ መንፈስ ቅዱስ በባሕርዩ እውነት ነውና፥ እውነትም ሁኖ ይሰጣቸዋል፥ እውነቱን ይገልጥላቸዋል እውነቱን ያሠራቸዋልና "ይኸነው በውሀና በደም የመጣው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውሀ ብቻ አይደለም በውሀና በደም እንጅ መንፈስ የሚመሰክር ነው፥ መንፈስ እርሱ እውነት ነውና"[17]::

ሠ. የሕይወት መንፈስ ይለዋል፥ እንዲሁም መንፈስ ጥበብ ነው፥ የጸጋ መንፈስ ይለዋል፥ በዚህም ሁሉ ሌላም ይኸን የመሳሰለ ለሰው ልጅ ሀብት ሙብት እውቀት ሁኖ በሚሰጠው ሁሉ ይመሰላል ይጠራል::

፫. የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረፀ፥ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል የሆነ፥ አምላክነቱ የባሕርዩ የሆነ ህልውና ያለው ዘለዓለማዊ አምላክ ነው:: ዘለዓለማዊ መንፈስ መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጥ "እንዴት ይልቁን የክርስቶስ ደም ለዘለዓለም በሚኖር መንፈስ ራሱን ያቀረበ ያለ ነውር ለእግዚአብሔር ሕሊናችሁን ያነፃል ከሞት ሥራ ሕያው እግዚአብሔርን ታገለግሉ ዘንድ"[18]:: መንፈስ ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ፈጣሪ ሁኖ እንደሠራ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ የሁሉንም ቻይ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ" ሲል ኢዮብ ተናግሯል[19]:: ዳዊትም "እስትንፋስህን ትልካለህ ይፈጠራሉ የምድርንም ፊት ታድሳለህ" ሲል ይናገራል[20]:: እንዲሁም መንፈስ አንድ ሲሆን ሥጦታው የተለያየ ነው፥ ለያንዳንዱ ሰው እንደሃይማኖቱ ጽናት እንደ ምግባሩ ብዛት እንደ ትሩፋቱም ስፋት ይሰጠዋልና፥ ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ሰፋ አድርጎ ጽፏል[21]:: ይኽንን ሁሉ ለማድረግ የሚችለው አምላክ ስለሆነ ነውና::

የመንፈስ ቅዱስ አምላክነትን ማቴዎስ ሲጽፍ "ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ብሎ መንፈስ ቅዱስን ከአብና ከወልድ ጋር አስተካክሎ ዕሩየ መለኮት ዕሩየ ሥልጣን አድርጎ አቀርቦልን እናገኘዋለን:: ይኽን በመሰለ አቀራረብ ሐዋርያው ጳውሎስ የእምነቱ መደምደሚያ አድርጎ ሦስትነትን ገልጦ ወዲያውም የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ገልጦ ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን እኩልነት አስረድቶ እንደሚከተለው ተናግሯል "የጌታችን የኢየሱስ ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን"[22]::

ለመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ሰጥቶ አምላክነቱን አረጋግጦ ራሱንም የቻለ አካል እንዳለው ገልጦ የተናገረና፥ የጻፈ ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ነው እርሱም የቅዱስ ጴጥሮስን ንግግር አስረጅ በማድረግ እንዲህ ይላል "ጴጥሮስም አለው፥ ሐናንያ ሆይ ለምን ሠይጣን መላብህ በልብህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ትዋሺ ከመሬትህም ሽያጭ ትሠርቅ ዘንድ በሰው ሐሰተኛ አልሆንክም በእግዚአብሔር እንጂ"[23]:: እግዚአብሔር እያለ በብሉይም በሐዲስ ኪዳንም የሚጠራው ለእግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድም ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ሊሆን ይችላል፥ በባሕርይ በመለኮት በእግዚአብሔርነት አንድ ናቸውና:: ግን ስም ግብርም ለይቶ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረውን ብቻ ለህልውናው፥ ለአምላክነቱም የተለየ ማስረጃ አድርገን





በመጠኑ ገለጥን:: እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ይመጣል፥ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፥ ሲል ይናገራል[24]:: ፫ቱ ደቂቅም ንባርከ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እያሉ ሦስትነትን ይገልጣሉ፥ ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ አካል ያለውና ከአብና ከወልድ ጋር እኩል እንደሆነ አምልኮትም ስግደትም በትክክል እንዲገባው ገልጠው በማመስገን አስረድተዋል[25]::

፬ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለው እኩልነት፥ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ ህልውና ስላለው በተለየ አካሉ ሲሠራ ይገኛል፥ ለዚህም የሚከተለውን አስረጅ እንመልከት "... ሕዝብም ሁሉ በተጠመቁ ጊዜ እርሱም ተጠመቀ፥ ሆነም እርሱ ሲጸልይ ሰማይ ተከፈተ መንፈስ ቅዱስም በአካል ምሳሌ፥ እንደ እርግብ ወረደበት ድምጽም ከሰማይ መጣ እንዲህ ሲል አንተ ነህ ልጄ የምወድህ በአንተ ደስታዬን አያለሁ"[26]:: በዚህም የምንረዳው ለመንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ አካል የተለየም ግብር እንዳለው ነው፥ ማለት ወልድ ፍጹም ሰው እንደመሆኑ በባሕር ላይ ለመጠመቅ ቀርቧል፥ አብ በሰማይ ሁኖ ድምፅ ያሰማል፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አካል ባለው ቅርጽ በርግብ አምሳል በወልድ ላይ ታይቷል:: ይኸም አንድነት በትክክል ሲገለጥ የክርስቲያንን ዕምነት ያረጋግጣል በተለይም የራሱን የአብን የመንፈስ ቅዱስን ህልውና ሲገልጥ ፫ቱም አካላት በስም በግብር በአካል የተለያዩ መሆናቸውን እንዲህ ሲል ያስረዳል "አብን እለምናለሁ ሌላ አጽናኝ ይሰጣችሁ ዘንድ፥ እርሱም ለዘለዓለም በእናንተ ላይ አድሮ የሚኖር"[27]:: እንግዲህ የሚለምን ወልድ ራሱን የቻለ አካል ያለው ነው፥ የሚለመን አብም ራሱን የቻለ አካል ያለው ነው፥ ግን ሁሉንም የሚያገናዝብ የአብም የወልድም ሕይወት የሆነ አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ የተባለ አካል ያለው መሆኑን ገልጦ ተናግሯል:: ሦስት ራሱን የቻለ የተለየ አካል ነገር ግን አንድ ባሕርይ፥ ሦስት የተለየ ስም ነገር ግን አንድ መለኮት ሦስት የተለያየ ግብር ነገር ግን አንድ ህልውና ያላቸው አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ



www.ethiopianorthodox.org

አምላክ የሚሆን በአንድነትም በተለያየ መልክም ቅዱስ መጽሐፍ ያቀርብልናል፥ ሁኖም እንደ ግብራቸው እንደ ስማቸው እንደ አካላቸው ፫ ብለን በህልውና በባሕርይ፥ በመለኮት አንድ ብለን በአንድ አምላክነት እምነትና ትምህርት ጸንተን እንኖራለን።

## ም ዕ ራ ፍ ፪

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥

፩ <u>መንፈስ ቅዱስ ከዓለም ጋር ስለአለው ግንኙነት፥</u> ይኸ የሚታየው ግዙፉ ዓለም በመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ተፈጥሯል፥ ይኸም ማለት ፫ቱ አካላት በአንድነት ቢፈጥሩም ለያንዳንዱ ጎልቶ የተነገረውን የምንጠቅስበት ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ሕፁጽ አለመሆኑን በመለኮቱ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል መሆኑን ለማጠየቅ ነው፥ ይኸንኑም ነቢዩ ዳዊት "ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዓ ሰማያት ወእምስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኃይሎሙ" ብሎ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ እንድተፈጠሩ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ተካፋይ እንደሆነ ያስረዳል[1]። ኢዮብም በበኩሉ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ የሁሉም ቻይ እስትንፋስም ሕይወት ሰጠኝ"[2] ይላል። ሁሉም በርሱ ተፈጥሯል ይህም ማለት በመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ተፈጥሯል ማለት ነው። ይሁን እንጂ ፈጣሪነቱ በብዙ ቦታ ለእግዚአብሔር አብ ብቻ ይነገራል፥ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ወልድም ቦቱ ኩሉ ኮነ ወዘእንበሌሁ አልቦ ዘኮነ" ሲል ሁሉ በርሱ ፈጣሪነት እንደተፈጠረ ያለርሱም ፈጣሪነት አስገኝነትም ምንም የተገኘ እንደሌለ ይገልጣል። ከዚህም የተነሣ መንፈስ ቅዱስ ከፍጥረት ሥራ ውጭ እንደሆነ የሚገምቱ እንደ ሕፁዕም የሚያደርጉት አሉ። ከዚህ እንደምናየው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ዓለም እንደተፈጠረ እናገኛለን። ዋናው ምሥጢር ግን ሥላሴ በባሕርይ በፈጣሪነት፥ በመለኮት አንድ ስለሆኑ እያንዳንዳቸው በፍጥረት ሥራ በአንድነት የሠሩ መሆናቸውን ማወቅና ማመን ተገቢ ነው። በተለያዩ መጻሕፍት የሦስቱንም አካላት ፈጣሪነትን





አምላክነትን በማሳየት ለይተው ተናግረዋል አስረድተዋልም፥ ለምሳሌ "አብ ይሄሊ ፥ ወልድ ይትናገር፥ ወመንፈስ ቅዱስ ይሠምር እያለ የ፫ቱንም ተግባር ይናገራል[3]። ከላይ ከገለጥነው ትንሽ ለየት ባለ መልክ የሚገኘው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ለፍጥረት ሁሉ ጽናትን፥ ሕይወትን የሚሰጥ የሚጠብቅ የማይለይ መሆኑን በመግለጥ ነው። ይኸም መንፈስ ቅዱስ ከዓለሙ ጋር ምን ያህል ግንኙነት እንዳለው የሚያጠይቅ መግለጫ ሁኖ የሚቀርብ ነው። እርሱም እንደሚከተለው ነው፥ "ወመንፈስ እግዚአብሔር ይጼልል፥ ዲበ ማይ፥" ይላል[4]። እንዲሁም ከፍጥረቱ በኋላ ለሰው ልጅ ሕይወትን፥ ዕውቀትን ለመስጠት "በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፥ ሰውም ሕይወት ያለበት ነፍስ ሆነ"[5]። እያለ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ፥ ጠባቂነት፥ ሕይወት ሰጭነት፥ ዓለሙን ከክብር ወደ ክብር ከማዕረግ ወደ ማዕረግ ያደረሰ ርምጃን የሰጠ፥ ለውጥን ያስገኘ እንደ ዓላማውም የሚመግብ የሚጠብቅ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ይገልጣል።

፪ <u>መንፈስ ቅዱስ ከሰው ጋር ስለአለው ግንኙነት፥</u> መንፈስ ቅዱስ በሰው ልጅ አድሮ እውነትን ያናግራል፥ ምሥጢር ያስተረጉማል፥ የእውነት መንፈስ ነውና እውነትን ያሠራል፥ ስለዚህም "ክርስቶስ እኔ የምልከው ከአብ የሠረፀ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ስለኔ ይመሰክራል፥ የእውነት መንፈስ ነውና" ሲል ይናገራል[6]። እውነት ተናጋሪው እውነትም ሠሪው ሰው እርሱ የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር ነው፥ በርሱ አድሮ መንፈስ ቅዱስ ይሠራልና። ሥጋዊ ደማዊ ሰው ግን ስለርሱ አያስብም አይናገርም፥ መንፈስን አያውቅምና ሊቀበለውም አይችልም፥ በርሱም አድሮበት አይኖርም፥ ስለዚህ በዚህ ዓይነቱ ሰው መንፈስ ቅዱስ አድሮ አይሠራም[7]። ክርስቶስን የማወቅ ኃይል የሚኖራቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር የሆኑ ብቻ ናቸው፥ በነዚህ ላይ ግን መንፈስ ቅዱስ ያድራል ይሠራል ያሠራል[8]። በመንፈስ የሚሠራው በክርስቶስ ያምናል፥ ስለ ክርስቶስም ይናገራል፥ ይመሰክራል፥ በእውነትም ይሠራል፥ እርሱም ይድናል። እኛ የዳነው በሥራችን በጥረታችን አይደለም፥ ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ እንደገና እንድንወለድ÷ እንድንታደስም ስላደረገን ነው እንጂ[9]:: መንፈስ ቅዱስ እንድንታደስ እንደገና እንድንወለድ ያደርጋል÷ ይኸም የመንፈስ ዋናው ሥራው ነው÷ አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቶ ያረጀው አካሉ በመንፈስ ቅዱስ ይታደሳል አዲስ ሰው ይሆናል አዲስ ሕይወትም ያገኛል[10]::

መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው÷ ይኸውም የሰው ዘር የሆነው ሁሉ ጌታችን ኢየሱስን ለመቀበል ይችል ዘንድ አስቀድሞ ለመዘጋጀት የተደረገ ነው:: ስለዚህም ቅዱስ መንፈስ የነቢያትን አእምሮ አበራላቸው ምሥጢሩን ገለጠላቸው÷የእውነት መንፈስ እንደመሆኑ ሁሉንም ወደ እውነተኛ መንገድ መራቸው[11]::

ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ትንቢት ሲናገሩ የሚነግራቸው የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃል የሆነው ወልድ ነው÷ የሚያበረታቸው የሚገልጥላቸው እንዲረዱም የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ ነው:: ስለዚህ ነቢያት ሲናገሩ "ቃለ እግዚአብሔር መጽአ ኀበ..." እያሉ ነው[12]:: እንዲሁም ጌታ እኔን እንዲህ አለኝ እያሉ የተናገሩ አሉ[13]::

መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ያቀርበናል÷ መድኃኒታችን ነውና ከርሱ አንድነት መለየት አይገባንምና:: መንፈስ ቅዱስ አእምሮአችን ያበራልናል÷ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን አምነን እንቀበል ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ መመራት አለብን÷ በእርሱ ካልተመራ በቀር እውነተኛውን እምነት የሰው ልጅ ሊያገኝ ሊያምንም አይችልምና::

መንፈስ ቅዱስ በእኛ ያድራል በእኛም ላይ ይሠራል፣ እኛንም ያሠራል÷ ለደኅንነታችን እንድንሠራ የሚያነሳሣን የሚገፋፋን ቅዱስ መንፈስ ነው÷ ምግባር ትሩፋት እንድንሠራ ያነሳሣናል÷ ከምግባራችን የተነሣ ጸጋውን ይሰጠናል÷ ይኸም ጸጋ ለድኅነታችን ለሕይወታችን ምክንያት ይሆናል::

፫ <u>የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ</u>÷

የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ብዙ ነው÷ ራሱ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን ሥጦታው በዓይነት÷ በመጠን የተለያየ ነው÷ ድውይ የመፈወስ÷ ትንቢት የመተንበይ÷ በቋንቋም የመናገር÷ ሌላም





ይኸን የመሰለ ብዙ ሀብትን ይሰጣል:: ስለመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ብዛት የተለያየም ዓይነት መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ በሰፊው ገልጦልን እናገኘዋለን[14]:: ነቢዩ ኢሳይያስ ግን የመንፈስ ሥጦታ ፯ ዓይነቶች እንደሆኑ ቆጥሮ ስማቸውን እንደሚከተለው ጠርቶ ነግሮናል "የጥበብ መንፈስ÷ የመረዳት መንፈስ÷ የምስክር መንፈስ÷ የመጽናናት መንፈስ÷ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ" ይላል[15]:: ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ የመንፈስ ፍሬ ናቸው ብሎ በሌላ መልክ እንደሚከተለው ያቀርብልናል "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ደስታም÷ ሰላምም÷ ትእግሥትም÷ ቸርነትም÷ በጎነትም÷ ሃይማኖትም÷ ገርነትም÷ መሻትንም መግዛትም ..."[16]:: እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ሥጦታዎች ናቸው÷ እነዚህም ሁሉ አንድ ሰው የግሉ ሊያደርጋቸው ሊፈጽማቸው አይችልም÷ ያለ መንፈስ ቅዱስ ርዳታና ሥጦታ::
የመንፈስ ሥጦታም የሚቆጠር ስሙም ተጠርቶ የሚያልቅ አይደለም÷ ቢሰጥም አያልቅም÷ ለያንዳንዱ ሰው እንደ ሃይማኖቱ ጽናት÷ እንደ ምግባሩ ብዛት ጸጋው ይሰጠዋል÷ ይጨመርለታልም:: መንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ሲያስተረጉም ቋንቋ ሲያናግር ይታወቃል እንጂ አይቆጠርም::

# <u>ክ ፍ ል ፯</u>

## <u>ክ ብ ረ ቅ ዱ ሳ ን</u>÷

### <u>ም ዕ ራ ፍ ፩ ቅ ዱ ሳ ን በ ጠ ቅ ላ ላ ው</u>÷

፩ የ<u>ቅድስና ትርጉም</u>÷ ቅዱስ ማለት "ቃዲሾ" መቀደስ ከሚለው ከዕብራይስጡ የወጣ ቃል ነው÷ ግዕዝም ከሴማውያን ቋንቋዎች አንዱ ስለሆነ÷ ያንኑ ድምፅ ያኑም ትርጉም ይዞ ይገኛል÷ ይሁን እንጅ ቅዱስ ማለት ብዙ ዓይነት ትርጉሞችን ይዞ ስለሚገኝ እያንዳንዱን እንደሚከተለው እንገልጣለን::

ሀ. ቅዱስ ማለት ምስጉን ስቡሕ ማለት ነው÷ ይህም ቃል ከፍተኛ የምስጋና ቃል ነው መላእክትም ደቂቅ አዳምም ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ የሚጠ



www.ethiopianorthodox.org

ቀሙብት ቃል ነው:: በዚህ ቃል መላእክት ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ በራእይ ለሰው ልጅ ተገልጠዋል፥ ለምሳሌ ሱራፌል ሥራቸው ምስጋና የሆነው ያለ ዕረፍት በዚሁ ቃል "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት..." እያሉ ሲያመሰግኑ ለኢሳይያስ በራዕይ ተገልጦለታል[1]:: ይህ ቃል በምስጋና ውሎ የተገለጠውም በዚህ ጊዜ ነው፥ በብሉይ ዘመን በዚህ መልክ ሲገለጥ በሐዲስ ኪዳን ጊዜ ደግሞ በመጀመሪያ ክርስቶስ ጸሎት ሲያስተምር "አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ" ብሎ አባቱን ቅዱስ በማለት ገልጦ ሲያስተምር እናገኘዋለን[2]:: በሌላ ቦታ ደግሞ አሁንም አባቱን "አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ በጽድቅከ" ብሎ ሲጸልይ ይገኛል[3]:: በዚሁ ምዕራፍ ለደቀ መዛሙርቱ ሲጸልይ አባቱን "ቀድሶሙ በጽድቅከ" ሲል እናገኘዋለን:: ስለራሱም ሲናገር "ዘቀደሶ አብ ወፈነዎ ውስተ ዓለም" ይላል[4]:: ይኸን በመሰለ አገላለጥ ስለ አባቱም ስለራሱም ቅዱስነት ተናግሯል:: ወንጌላዊው ዮሐንስ አሁንም "...ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ ዘትእኅዝ ኩሎ ..." እያሉ ፬ቱ እንስሳ ሲያመሰግኑ በራእይ ተገልጦለት ጽፏል[5]::

ሊቃውንትም ይኸን ተከትለው ቅዱስ የሚለውን ቃል የአምላክ ምስጋና መግለጫ አድርገው "ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው እያሉ፥ እንዲሁም ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር፥ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ አብ አኃዜ ኩሉ:: ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ወልድ ዋህድ ዘአንተ ቃለ አብ ሕያው፥ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ መንፈስ ቅዱስ ዘተአምር ኩሎ" እያሉና ሌላም በዚህ መልክ እያደረጉ ያመሰግኑታል[6]::

ይኸም ቃል መለወጫ የሌለው የፍጹምነት መታወቂያ፥ የምስጋናም ማቅረቢያ የአምላክንም ባሕርይ መግለጫ አድርገው ይጠቀሙበታል:: ሰውም መላእክትም የብሉይ ኪዳንም የሐዲስ ኪዳን አባቶች እንዲሁም የኋላ ዘመን ሊቃውንትም በዚሁ ተጠቅመው ለአምላክ የምስጋና ማቅረቢያ ቃል አድርገውታል::

ለ. ቅዱስ ማለት ቡሩክ ማለት ነው፥ ይኸም ማለት አምላክ በባሕርዩ ቡሩክ ቅዱስ ነው ማለት ነው እንጂ እንደሌላ





ፍጥረት ረክሶ ይቀደሳል ይባረካል ማለት አይደለም፥ ሁሉን የሚያከብር የሚባርክ የሚቀድስ አምላክ ሲሆን ቡሩክ ይባላል፥ ስለዚህ ቅዱስ ባልን ጊዜ ይኸንም ትርጉም ይሰጠናል:: ይኸን የመሰሉ ትርጉሞች የያዘው ቃል በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም እናገኛለን::

[illegible] ቅዱስ ማለት ክቡር ማለት ነው፥ ይኸም ማለት ተዋርዶ የሚከብር፥ ተሸሮ እንደገና የሚሾም፥ አጥቶም እንደገና የሚያገኝና የሚከብር ማለት አይደለም፥ ባለጸጋ የማይሰጠው ፍጹም ክቡር ባዕል ነው:: ክብር የባሕርዩ የሆነ አምላክ ነው፥ ሌላውን ፍጥረት የሚያከብር ለሌላው ሁሉ ክብርን የሚሰጥ በመብት በዕውቀት ...በሌላም ሁሉን የሚያከብር የባሕርይ አምላክ ነው:: በዚህም ቃል መመስገን ፈቃዱ ስለሆነ በብሉይ በሐዲስ ኪዳንም ይኸን ትርጉም የሚሰጡ ብዙዎች ዐረፍተ ነገሮች ይገኛሉ::

[illegible]. ቅዱስ ማለት ንጹሕ ማለት ነው፥ ይኸም ማለት እንደ ሌላው ፍጥረት ሁሉ ረክሶ ወይም አድፎ ይነጻል ማለት አይደለም፥ አምላክ በባሕርዩ ንጹሕ ነውና፥ እርሱ ሌላውን ያነጻል ይቀድሳል እንጂ ቅድስናን ከውጭ አይሻም፥ ንጽሕና ቅድስና የባሕርዩ ነውና፥ "እስመ ንጹሕት ጠባይዓቲሁ ለእግዚአብሔር እምነውር" ይለዋልና፥ ከላይ የገለጥናቸው የትርጉም ቃላት ሁሉ በሰው ልጅ የአነጋገር ልማድ የምስጋና መግለጫ እንደሆኑ ተናገርን እንጂ እንደ አምላክነቱ ምስጋናውን ለማናገር ጠባዮቹን ለመግለጥ እነዚህ ቃላት በቂዎች አይደሉም ደካማዎች ናቸው፥ ግን አምላክ ራሱ የተናገረው ነቢያትም የተከተሉት ሐዋርያትም ሊቃውንትም ያጸኑት ስለሆነ እኛም ይኸኑ እንከተላለን::

[illegible]. ቅዱስ ማለት ልዩ ማለት ነው፥ እስካሁን የቆጠርናቸውን የተለያዩ የአምላክን ጠባይዓት ሁሉ አጠቃሎ የሚገልጥልን ይኸ ልዩ የሚለው ቃል ነው ልዩ ምስጉን ልዩ ቡሩክ፥ ልዩ ክቡር፥ ልዩ ንጹሕ ልዩ ፍጹም ማለት ይሆናልና:: እንግዲህ የሁሉ መግለጫ የሆነውን ይኸን ቃል ተከትለን እንሔዳለን::

ይኸ ቅዱስ የሚለው ቃል በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጠው ለአምላክ በባሕርዩ ቅዱስ ለሆነው ሌላውንም ለመቀደስ ችሎታ



www.ethiopianorthodox.org

ላለው ብቻ ነው:: ቃሉም የተገለጠው አምላክ ብቻ ሊመሰገንበት ነው፥ ምክንያቱም እርሱ ብቻ የምስጋና ባለቤት የክብርም ጌታ ነውና:: ምስጉን፥ ስቡሕ፥ ቅዱስ ተብሎ ይመሰገናልና:: ሰውን ብናመሰግነው እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ፥ በዋለለትም ውለታ፥ ሰውም በሰጠው፥ በሾመው በሸለመው ነው፥ እንጂ የባሕርዩ የሆነ የሚያስመሰግነው ነገር ከቶ የለውም፥ አምላክ ግን ምስጋና የባሕርዩ ስለሆነ በዚህ ቃል ይመሰገናል:: ልዩ አምላክ ነውና፥ ልዩነቱም ከፍጥረቱ ሁሉ ነው፥ ማለት ለፍጥረቱ ሁሉ አምጭ አስገኝ ያሻዋል እንዲሁ በዕድሉ የተገኘ ነገር ከቶ የለምና:: አምላክ ብቻ ግን ነበር፥ አለ፥ ደግሞም ይኖራል፥ በዚህ ሁሉ ከፍጥረቱ ይለያል:: እንዲሁም ፍጥረቱ ሁሉ ያልፋል ይጠፋል፥ አምላክ ብቻ ነግሦ ለዘለዓለም ይኖራል:: እርሱ ብቻ በባሕርዩ ሞት፥ በመንግሥቱም ሽረት የለበትም፥ ኅልፈት ውላጤም የለበትም በዚህ ከፍጥረቱ ሁሉ ይለያልና ቅዱስ ይባላል::

እንዲሁም ፍጥረቱ ሁሉ ግዙፍ ነው ይዳሰሳል፥ ለአገልግሎት ይውላል እንጠቀምበታለን፥ አምላክ ብቻ ባሕርዩ ረቂቅ ምጡቅም ነው፥ ስለዚህ ማንም አስቦና መርምሮ የማይደርስበት ነው፥ ስለዚህም ልዩ አምላክ ነውና ቅዱስ ይባላል:: ፍጥረቱ ሁሉ ስሑት ነው ይበድላል፥ እግዚአብሔር ግን ከሐሰት የራቀ ንጹሕ የሆነ ነውና:: ማንኛውም ፍጥረት ከባሕርዩ ልዩ ቅዱስ ንጹሕም የሆነ የለም፥ አምላክ ግን በባሕርይ ንጹሕ ቅዱስ ሆኖ እኛም ንጹሓን ቅዱሳን እንድንሆን በንጽሕና በቅድስና እርሱን እንድንመስለው "እኔ ቅዱስ እንደሆንኩኝ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ይላል ለሰው ልጅ ሁሉ ምክርን ይሰጣል[7]::

ቅዱስ የሚለው ቃል የሚሰጠው ለአምላክ ብቻ ነው ብለን ነበር ግን እርሱ ለሚገለገልባቸው ቦታዎች ዕቃዎች እርሱንም ለሚያገለግሉ ሰዎች ለዕለቷ ሳይቀር ተሰጥቶ እናገኘዋለን፥ ለምሳሌ አምላክ መፍጠር ያቆመበትን ዕለት "ባረካት ቀደሳትም" ሲል እናገኛለ[8]:: ይኸችም ከዕለታት ተለይታ የተቀደሰች፥ የተከበረች የዕረፍት ዕለት ናት::

ከሰው ወገንም እንዲሁ የርሱ አገልጋዮች ካህናት ከሕዝብነት ተራ ወጥተው ከሰውም ተለይተው ጸሎት ተደርጎላቸው ተባርከው





ተቀድሰውም ወደ እግዚአብሔር አገልግሎት ስለሚቀርቡ ቅዱሳን ይባላሉ:: መሥዋዕት የሚሰዋበት የሚቀርብበት የእግዚአብሔር አምልኮት የሚፈጸምበት ቦታ ሁሉ መቅደስ፥ ቅድስተ ቅዱሳን ይባላል[9]:: ዋናው ዓላማው ግን አሁንም የእግዚአብሔርን ልዩ ቅዱስነት ለመግለጥ ነው፥ ይኸም ማለት ለሌላ አገልግሎት የማይውል በተባረከበት በተቀደሰበት ዓላማ ብቻ ለአገልግሎት የሚውል ቦታና ዕቃ ነውና::

ከዚህም በቀር ከሌላው የሰው ነገድ ተለይተው በመላው ነገደ እሥራኤል ቅዱስ ሕዝብ እየተባሉ ይጠራሉ፥ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር የተለዩ ሕዝቦች ይባላሉና ደግሞም ናቸውና[10]:: እግዚአብሔር አምላክ የራሱ ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ መርጧቸዋልና ባርኳቸዋልምና ይኸን የመሰለው ቅድስና በክርስትናም በኩል ይገኛል፥ ክርስቶስ ለሐዋርያት ሲጸልይላቸው "አባ ቀድሰሙ በጽድቅከ" ሲል እናገኘዋለን፥ ቅዱሳን ሐዋርያት ከሌላው ሕዝብ የተለዩ የተቀደሱ ሆነው ተገኝተዋልና[11]::

በዚህም መሠረት ማንኛውም በክርስቶስ ክርስቲያን የተባለው ሁሉ ከሌላው ከክርስትና ውጭ ከሚሆነው ሕዝብ የተለየና የተቀደሰ የተባረከም ሕዝብ ነው፥ አዲስ እሥራኤል ንጹሕ ሕዝብ ልዩ ነገድ ተብሎ ይጠራልና[12]::

ይኸንም ማዕረግ ለማግኘት የጾታ፥ የዕድሜ፥ የኅሣ፥ የማዕረግ ልዩነት አይከለክለውም፥ ማንኛውም ሰው ክርስቲያን ሲሆን በልዩ ጸሎትም ተባርኮ በማየ ገቦ ታጥቦ ተቀድሶም ነውና:: እንግዲህ በዚህ ሁሉ አስረጅነት ክርስቲያኑ ሕዝብ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ነው ለማት ይቻላል:: ቅዱስ ጳውሎስ በክርስትና መባረክ መቀደስ መከበር እንዳለ ሲያስረዳ በአመኑ ወንድና በአላመነች ሴት መካከል ስለሚደረገው ጋብቻና ከእነርሱም ስለሚወለዱት ልጆች ሲናገር እንዲህ ይላል "ማንኛዪቱም ሴት ሰው ቢኖራት የማያምን እርሱ ቢሻ ከርሷ ጋር ለመኖር አትለየው፥ የማያምን ወንድም በምታምን ሚስት ይቀደሳልና፥ የማታምን ሚስት በሚያምን ወንድ ትቀደሳለችና ያለዚያ ልጆቻቸው ርኩሳን ናቸው ዛሬ ግን የተቀደሱ ናቸው" ይላል[13]:: ክርስቲያኑ ዓለም በክርስቶስ ደም የታተመ ክርስቶስ በደሙ የዋጀው የተለየ ሕዝብ ስለሆነ ቅዱስ ይባላል፥ ቅዱስም ነው፥ ንጹሕም



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቅዱሳን ሆነዋል፥ ቅዱሳንም ይባላሉ፥ ክርስቶስ የቀደሳቸው የመረጣቸው መሆኑን ራሱ መስክሮላቸዋል[18]:: በዚህ መልክ እንግዲህ ቅድስና ለሰው ልጅ ሁሉ ተሰጠ ሰውም ሁሉ የተለየ የተቀደሰ ወገን ሆነ::

ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሕይወታቸውን ያሳለፉ ሁሉ ቅዱሳን ተብለዋል፥ የቅድስናም ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል:: ይህም የሆነው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሕይወታቸውን፥ አካላቸውን፥ አእምሮአቸውን የሰጡ ከሌላው ሰው የተለዩ የርሱ አገልጋዮች ናቸው በማለት ነው:: በምግባራቸው በሃይማኖታቸው ፍጹማን ሁነው የተገኙትን ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በይፋ ቅድስናቸውን ክብራቸውን ልትገልጥላቸው ይገባል፥ ምክንያቱም ውዳሴ ከንቱ ሳይሹ ወይም እንድሌሎች ሳያመነቱ ስለ እግዚአብሔር ክብር ራሳቸውን ለአገልግሎት የሰጡ እልፍም ብሎ ሕይወታቸውን ለሞት የለወጡ ስለሆነ የዝናቸው ነጋሪ፥ የቅድስናቸው መስካሪ ቤተ ክርስቲያን ናትና:: የዚህም ጥቅም ለሰዎች ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያኗ ነው፥ ማለት የቤተ ክርስቲያን ክብር የሚታወቀው ቤተ ክርስቲያኗ በዕውነት ፀንታ በጎ ተግባርን ሠርታ ቅዱሳንን ያፈራች ቅዱሳንንም ያስነሣች እንደሆነ ነው:: በየጊዜው ስለ እውነት ራሳቸውን የለወጡ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እውነትን በሚጠሉ ሰዎች ዘንድ ሕይወታቸው በአለፈች ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ወዲያው ቀድሳ ሞገስ የሰጠቻቸው ዝናቸውን በትክክል የነገረችላቸው እንደሆነ፥ ሌላው አማኝ ሁሉ ወደዚሁ ገድል በፈቀዱ ይሳባል፥ የቅድስናንም ጽዋ ይካፈላል፥ የቅድስና ማዕረግም ይሰጠዋል፥ ያለዚያ ግን የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ይለወጣል፥ ቀጥሎም የቤተ ክርስቲያን ሰው የሆነ ይጠፋል፥ ቤተ ክርስቲያንም እንደ አንድ የግል ድርጅት ትሆናለች እንጂ ቤተ ክርስቲያን የሚላት የለም::

ቤተ ክርስቲያን ከጊዜ ወደጊዜ ተሐድሶ የምታገኘው ካህኑ ቀርቶ የጨዋ ልጅ ሁሉ በእውነት የሚጸናው እውነትን የሚናገረው በእውነትም የሚሠራው ስለ እውነት ሕይወታቸውን በሞት የለወጡትን የቅዱሳንን ክብር ቤተ ክርስቲያን በገለጠችበት ጊዜ ለእውነትም ቦታ በሰጠችበት ጊዜ ነው::



www.ethiopianorthodox.org



፫. ቅዱሳን በብሉይ ኪዳን፥ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን የሚፈሩ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሕጉ የሚናገሩ ብዙዎች ቅዱሳን አባቶች ነቢያት ነበሩ፥ ነገር ግን ይኸን ሁሉ እየሠሩ የቅድስና ኑሮ እየኖሩ አምላክ ራሱ ድምፅ እያሰማ እየመሰከረላቸው የኖሩ እንደነ አብርሃም፥ ሔኖክ፥ ኢዮብ ሌሎችም ብዙዎች ሲኖሩ በሕይወታቸውም ሆነ፥ ከሞቱም በኋላ ቅዱሳን አልተባሉም ቅድስናም አልተሰጣቸውም፥ ልዩም የቅድስና ምልክት አልተደረገላቸውም፥ ለምሳሌ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ፩፻፳ ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረው ፍጹም የአምላክ ወዳጅ የነበረው ሰው፥ ሕጉንም የጻፈ ያስተማረ ሲሆን፥ ለእርሱ እንኳን ልዩ መታሰቢያ አልቆመለትም ቅዱሳም የሚያሰኝ ምልክት አልተሰጠውም::

በብሉይ ኪዳን ቅዱስ የሚለው ቃል ለአምላክ ብቻ የሚሰጥ እንጂ ለተለየ ሰው ሰጥቶ የማክበር ልማድ ለአይሁድ አልነበራቸውምና ነው:: ነገር ግን ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተናገርነው ቅዱስ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለሚውሉት ሁሉ ይሰጡ ነበር፥ እግዚአብሔር ቅድስና የባሕርዩ ስለሆነ ነቢያት በቀጥታ ለእርሱ ሲያውሉት እናገኛለን[19]:: አምላክን የሚያገለግሉ ከሰው ወገን እንዴት አድርገው ማምለክ እንዳለባቸው "በቅድስና ጌጥ ሰገዱ"[20]::

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ቅዱሳን መሆን መባልም እንዲገባቸው አምላክ ሲያመለክት "ቅዱሳን ሆይ ለእግዚአብሔር ዘምሩ ለቅዱስ ስሙም" ይላል[21]:: የእግዚአብሔር መገልገያም ሁሉ ንጹሕ መሆን እንደሚገባው ሲያጠይቅ "እግዚአብሔር በቅድስናው መቅደስ ይቀመጣል" ይላል[22]:: በጠቅላላውም የእግዚአብሔር ሕዝብ እየተባሉ የሚጠሩት እሥራኤል የተመረጡና የተለዩ ቅዱሳን ናቸው፥ ይኸንም አምላክ ሲመሰክርላቸው "የተቀደሰ ሕዝብ ትሆናለች" ይላል::[23]

አምላክ ለእርሱ መገልገያ በሚሆነው ዕቃ ቦታ ወይም ለእርሱ አገልግሎት ተሰጥተው የሚኖሩትን ያውቃል፥ ይመርጣል የመረጠውንም ሰው ወደርሱ ያቀርበዋል ይላል[24]::

በጠቅላላው አነጋገር አምላክ ዘለዓለማዊ ቅዱስ ስለሆነ፥ የርሱ የሆኑትን ሁሉ ይቀድሳል፥ ቅዱስም ያደርጋል:: እሥራኤላውያን

ቅዱሳን ስለሆኑ የሚመገቡት ሁሉ ንጹሕና ቅዱስ መሆን ስለነበረበት ቅድስናን ለምግቡ ሳይቀር ሰጥቶ ሲናገር እንዲህ ይላል "በቅዱስና ባልተቀደሰው በርኩሱና በንጹሑም መካከል መለየት እንድትችሉ" ሲል ተናግሯል[25]:: ለእግዚአብሔር አምልኮት ስግደት የሚቀርብበት ቦታ ሁሉ ተራራውም ቅዱስ ይባላል፥ ይኸንንም የሚያመለክት የተበተኑት ይመጣሉ ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ በቅዱስ ተራራ የኢየሩሳሌም"[26]:: ለአምላክ ቅድስና የባሕርዩ ስለሆነ ቅዱስ የሚባለው ቅዱስ ተብሎ የሚመሰገን፥ አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ለርሱው አገልግሎት የሚውለው ሁሉ ቅዱስ እንደሚባል ተናግረናል፥ ነገር ግን ከሰው ወገን በክርስትናው መንፈስ ቅዱስ ተብሎ መታሰቢያ የቆመለት ማንም አልነበረም፥ ወይም እኛ በክርስትና ሃይማኖት በአንዱ ቅዱስ ስም ቤተ ክርስቲያን እንደምናቆምለት ምኩራቡ መስጊዱ በስሙ የሚጠራለት ቅዱስ ከቶ አልነበረም::

ዛሬ በክርስቲያኑ እምነት ሰውን ቅዱስ ብሎ መታሰቢያ ማቆም ተገቢ እንደመሆኑ በብሉይ ዘመን ግን ሰውየው እንደተመለከ ስለሚቆጥሩት ማንንም በዚህ ስም ሳይጠሩ ይኖሩ ነበር::

፬. <u>ቅዱሳን በሐዲስ ኪዳን፥</u> በሐዲስ ኪዳን ቅዱስ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ቢሆንም ለርሱ አገልጋዮች ለርሱም መገልገያ የሆነው ሁሉ ቅዱስ ሲባል ኑሯል፥ ግን ሁሉን ቻይ ለሆነ አምለስክ ይቀርብለት ከነበረው የምስጋና ቃል አሁንም በብዛት የምንጠቀምበት ቅዱስ የሚለው ነው ለምሳሌ "...አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ይላል[27]:: ሌላም በዚህ መልክ ለአምላክ ምስጋና ማቅረቢያ ከፍተኛ ቃል ሁኖ ይገኛል፥ በዚህም መሠረት ይነገራል::

መድኃኒታችን ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ ጸሎት ሲያስተምራቸው አባቱን እንዴት አድርገው መቀደስ ማመስገን እንዳለባቸው ሲነግራቸው "አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ ..." ሲል ቅድስናውን በመግለጥ ነግሯቸዋል[28]:: በዚህ መልክ ፍጹም ቅዱስ አምላካችን እግዚአብሔር ይሁን እንጂ የርሱ አገልጋዮች ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸውን ቀድሷቸዋል፥ ቅዱሳንም አድርጓቸዋል፥ የራሱንም የደቀ መዛሙርቱን ቅድስና ሲናገር ስለርሳቸው ራሴን እቀድሳለሁ



www.ethiopianorthodox.org



ርሳቸው ደግሞ የተቀደሱ ይሆኑ ዘንድ ሲል ጸልዮላቸዋል:: ቤተ ክርስቲያንም ይኸነን አብነት ይዛ ሐዋርያትን ቅዱሳን ትላቸዋለች ለእነርሱም ቅድስናን ትሰጣለች::

ቅድስት ማርያም የቅዱስ እግዚአብሔር እናት በመሆኗ የእግዚአብሔርንም ጸጋ ስላገኘች ቅድስት ትባላለች፥ ቅድስናም ተሰጥቷታል:: ከዚህ አያይዛ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ብቻ አልተወሰነችም እንዲያውም ከዚህ አልፋ የብሉይ ኪዳን አባቶችንና ነቢያትን ቅዱሳን ብላለች ቅድስናንም ሰጥታለች::

የክርስትናውንም እምነት ሊያስፋፋው ያንንም ሊያጸናው የቻለው በክርስቶስ አምነው እውነትን ተናግረው ሕይወታቸውን ሳሳለፉ አባቶችና እናቶች ቤተ ክርስቲያን ቅድስናን እየሰጠች ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ስለ አስተማረች ነው፥ በዚህም መሠረት ትንሽ፥ ትልቅ፥ ወንድ፥ ሴት ሳይል ሁሉም በክርስቶስ ለማመን ስለ ክርስቶስም ስም ራሱን ለመከራ ለሞት መስጠት የተቀደሰ ተግባር አድርጎ ይፈጽመው ጀመር::

ጣዕመ ዓለምን ንቀው ንጽሕናን ጠብቀው ሕይወታቸውን በሞት የሚለውጡት እሳቱን ፍላቱን ታግሠው ስለ ክርስቶስ የመሰከሩና ሰማዕትነትን እየተቀበሉ ያረፉትን በቤተ ክርስቲያን መዝገብ እየመዘገቡ ገድላቸውን እየጻፉ ልዩ ልዩ መታሰቢያ እያቆሙ ከሕያዋኑ ይልቅ የነርሱ ክብር ጎልቶ ይታይ ጀመር፥ ወይም የተጋድሎውን ዓይነቱን ስሙን በመለየት ከ፩ኛው ቅዱስ ተጋድሎ የሌለው የበለጠ እንደሆነ ሲነገር፥ ሌላው ደግሞ ከዚያ የበለጠ በመሥራት ክርስትናን አስከበሩ አስወደዱ፥ ክርስቲያኑን ሁሉ እውነተኛ አሰኙ:: በዚህ መልክ ከቀን ወደቀን ተጋዳዩ እየበዛ ስለሔደ ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ደም አጌጠች አሸበረቀች፥ ደማቸው እንደ አበባ ጌጥ ሆነ ቅዱሳኑም በቁጥር በዙ::

ቅዱስ እግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ሥጋንም በመልበሱ የርሱ የሆነውን ቅድስና ለሰው ልጅ አካፈለው፥ የሰው ልጅም ቅዱስ መባል ጀመረ፥ በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ እንደተባልን በቅዱሱም ቅዱሳን ተብለናል፥ ቅድስናንም አግኝተናል::

ልዑል አምላክ ለሰው ልጅ የሰወረው ያልሰጠው፥ ያላሳየው ምስጢር ከቶ የለም ጸጋውን ገንዘብ አድርጎ ለሰው ልጅ ሁሉ አደለው፥ ግን ተቀብሎ አክብሮ መያዝ የእያንዳንዱ

በተከራከረ ጊዜ ስለሙሴ ሥጋ ሲናገር በፍርዱ ይሰድበው ዘንድ አልደፈረም፥ ነገር ግን አለው እግዚአብሔር ይቆጣህ"[39]::

ስለ መላእክት ሕልውና በቅዱስ መፅሐፍ የተገለጠ ስለሆነ እንቀበለዋለን እያንዳንዱም ከላይ እንደገለጥነው ስም ጠርቶ ሥራ ለይቶ የተነገረላቸው አሉ፥ ስለ ቅድስናቸውም ደግሞ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሚስማማበት ነው፥ እንዲያውም ለጥቂቶቹ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ታንጾላቸው የተለየም የመታሰቢያ ዕለት ተወስኖላቸው በዐል ይከበርላቸዋል፥ በስማቸው ምልጃ ይደረግላቸዋል::

ለ. ፓትርያርኮች፥ ፓትርያርክ ማለት የአባቶች አባት፥ የአባቶች ሁሉ ጀማሪ ማለት ነው:: እነዚህም የነገድ አባቶች የቤተ ሰብእ መሪዎች አስተዳዳሪዎች ናቸው፥ እነዚህ ጥንታውያን የሰው ዘር አባቶች ሁሉ ፓትርያርኮች ይባላሉ:: እንደ እብራውያን ሥርዓት ግን ፓትርያርኮች የሚሏቸው አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና ልጆቹ ፲፪ቱ ነገድ ናቸው[40]:: በቤተ ክርስቲያን በኩል ግን ዘመነ አበው ተብሎ የሚቆጠረው ከአዳም ጀምሮ ስለሆነ ርእስ አበውም የፍጥረቱም መጀመሪያ እርሱ በመሆኑ የፓትርያርክነት መነሻ እርሱው ይሆናል፥ እንዲያውም ንጉሡን ዳዊትን ሳይቀር ከፓትርያርክ ቁጥር ያስገባዋል[41]::

እነዚህም ፓትርያርኮች የእግዚአብሔር ወዳጆች እንደሆኑ እግዚአብሔር በቃሉ ያነጋገራቸው የመራቸው ስለሆኑ ክቡራን ቅዱሳን ናቸው:: በብሉይ ኪዳንም የተከበሩ ናቸው፥ ነገር ግን ከነርሱ ውስጥ ለአንደኛው እንኳን የተለየ መታሰቢያ የጽድቁ ወይም የጻድቅነቱ መልክት የሚሆን በአይሁድ ዘመን የቆመለት ነገር የለም:: በክርስቲያን እምነት ዘንድ ግን ከነዚህ ፓትርያርኮች ውስጥ ለጥቂቶቹ የጽድቃቸው ወይም የጻድቅነታቸው መታሰቢያ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን በስማቸው ቆሞላቸዋል፥ ጽላት ተቀርጾላቸዋል፥ ምልጃም ስለትና አስተበቁዖትም ይደረግላቸዋል፥ ከነዚህም ውስጥ የታወቁት አዳምና ሔዋን አብርሃም ይስሐቅ፥ ያዕቆብ... ናቸው፥ ሌሎችም እንዲሁ ይገኙባቸዋል:: እነዚህ ቅዱሳን የሆኑት ወይም የተባሉት በጸሎት ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን "ስእሉ ለነ ... አስተምሕሩ ለነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ" እየተባሉ ምልጃ ስእለት አስተበቁዖት ይደረግላቸዋል[42]::





ሐ. ነቢያት፥ ነቢያት ማለት ተነበየ ትንቢት ተናገረ ካለው ከግዕዙ ቃል የወጣ ነው፥ ይኸም ማለት ኃላፍያቱን መጻእያቱን የሚያውቁ ስለርሱም አስቀድመው የሚናገሩ የእግዚአብሔርን መንፈስ የተመሉ የተለዩ ሰዎች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ከሰው ተለይተው ለእግዚአብሔር ያደሩና በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚራመዱና የርሱን ፈቃድ ብቻ የሚጠብቁ ሲሆኑ የኑሮ ቅድስና አላቸው፥ ስለዚህም ቅዱሳን ይባላሉ፥ ቅድስናም ይሰጣቸዋል:: እንዲሁም በመጀመሪያ ሀብተ ትንቢት እንዲሰጣቸው ጸሎት ተጸልዮላቸው ዘይት ተቀብተው ተመርጠው ነውና::

በተለይም እነዚህ ነቢያት ስለክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ተገልጦላቸው ሱባኤ የቆጠሩ፥ ትንቢት የተናገሩ የእሥራኤልን ሕዝብ ትንሣኤ ያበሠሩ ናቸው:: ነቢያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕዝብ ገላጭዎች ሆነው የተናገሩ ለብዙ ዘመናት ኀቡዕ ሁኖ የኖረውን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ የወልድን ወደዚህ ዓለም መምጣት የተናገሩ ናቸው:: ከዚህም የተነሣ የተናገሩት የጻፉት ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ መጽሐፋቸው እስትንፋስ እግዚአብሔር ይባላል:: መጽሐፋቸውም ከቅዱስ መጽሐፍ አንደኛ ክፍል ሆኖ ተቆጥሯል፥ ሰዎችም ቅዱሳን ተብለው ተጠሩ::

ነቢያት በመባል የታወቁት ከዐበይት ነቢያት ውስጥ ፬ ናቸው፥ እነርሱም ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤል፥ ዳንኤል ናቸው:: ደቂቀ ነቢያት ተብለው የሚጠሩ ደግሞ ፲፪ ናቸው፥ እነርሱም ሆሴዕ፥ ኢዩኤል፥ አሞጽ፥ ዮናስ፥ ሚክያስ፥ ናሆም፥ ዕንባቆም፥ ሶፎንያስ፥ ሐጌ፥ ዘካርያስ፥ ሚልክያስ፥ አብድዩ ናቸው:: እነዚህ ነቢያት ብቻ ናቸው የትንቢት መጽሐፍ የጻፉ፥ ትንቢት አብዝተው የተናገሩ፥ እሥራኤልንም ያስተማሩ:: እንዲሁም በዚህ መጽሐፍ ያልተገለጡ ስማቸውና ሥራቸው ያልተገለጠ ሌሎች ነቢያት ይገኛሉ፥ ለምሳሌ እንደ ኤልያስ ያሉ ሳይሞቱ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ያረጉ፥ እንደርሱም ደቀ መዝሙር እንደ ኤልሳዕ እንደ አዛርያ አናንያ ሚሳኤል ያሉ ሌሎች ነቢያት ይባላሉ:: እነዚህ ሁሉ ስለ እግዚአብሔር አምልኮት ቀጥተኞች ሁነው በነገሥታት በሕዝብም ፊት ሳይፈሩና ሳያፍሩ



www.ethiopianorthodox.org

የመሰከሩ÷ እንዲሁም ዘመናቸውን ሙሉ ስለእውነት የሠሩ የተናገሩ÷ በዚህም ሁሉ ምክንያት÷ የተራቡ የተጠሙ÷ በልዩ ልዩ ጸዋትዎ መከራ የተፈተኑ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን ናቸው ቅድስናም ይሰጣቸዋል::

ከነዚህ ውስጥ ግማሹን አምላክ በቀጥታ የቀደሳቸው የጠራቸው የመረጣቸው ናቸው:: ሌሎችም ደግሞ በልዩ ልዩ አጋጣሚ የተጠሩ የተመረጡም ሀብተ ትንቢት የተሰጣቸው ናቸው÷ ስለዚህ የተቀደሱ ይባላሉ:: ቤተ ክርስቲያንም ቅድስናን ትሰጣቸዋለች÷ ኤርምያስ "በሆድ ሳለህ ሠራሁህ አወቅሁም ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀደስኩህ ለሕዝብ ነቢይ አደረግሁህ" ይለዋል[43]:: የሌሎች ምርጫ ግን በራእይና በሰው አማካይነት÷ በመንፈስም መራጭነት ነው::

ይኸም ሁሉ ሁኖ ዕብራውያን ነቢያትን ከሌላው የእሥራኤል ሕዝብ ለይተው አያይዋቸውም÷ መታሰቢያም አልሰጧቸውም÷ ግን ነቢይነታቸውን አምነው ትንቢታቸውን ሰምተው መጽሐፋቸውን ተቀብለው ለሌላው ዓለም አስተላልፈውት ይገኛል:: ክርስቲያኑ ዓለም ግን ይኸን ሁሉ በመመልከት የእግዚአብሔር ወገን ስለሆኑ ቅዱሳን ይላቸዋል::

ቤተ ክርስቲያንም ከነዚህ ውስጥ ለጥቂቶቹ ጽላት ቀርጻ ቤተ ክርስቲያን አንፃ ሰዎች ቅዱሳን ብላ መታሰቢያ ዕለት ወስና ታከብራለች÷ ለምሳሌም እንደነ ኤልያስ ያሉትን:: እንደ ሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን ስዕለት አስተብቁዖት ይደረግላቸዋል÷ ምንም ከክርስትናው ቅዱሳን ልዩነት እንደሌላቸው የታወቀ ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን እያንዳንዱን ነቢይ በስሙ የምትጠራበት ጊዜ አለ፤ እንዲሁም በጠቅላላው እገሌና እገሌ ሳትል "ስአሉ ለነ ነቢያት ስኩራነ መንፈስ ምሉዓነ ሞገስ ...." እያለች ሁሉንም በማውሳት ምልጃ ልመና ታደርጋለች[44]::

## ም ዕ ራ ፍ ፪

## ቅድስት ማርያም÷

ሀ. ቅድስናዋ÷ ቅድስት ማርያም የቅዱስ አምላክ እናት ስለሆነች ወላዲተ አምላክ እያልን እንጠራታለን ".... ወዘኒ





ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ..." ሲል ቅዱስ ሉቃስ ያስረዳናል[1]:: የቅዱስ አምላክ እናት ማርያም ክርስቶስን ያህል መለኮታዊ አካል ስለወሰነች ቅድስት ትባላለች:: የክርስትናው ቅዱስነት ሁሉ የተገኘው ቅዱስ አምላክ ከርሷ ከተወለደ ወዲህ ነውና::

ማርያም በነፍሷም በሥጋዋም ቅድስት ናት÷ ሰው የሆነ ሁሉ ኃጢአትን ከመሥራት እንጂ ከማየት÷ ከማሰብ÷ ከመናገር የሚነጻ የለም÷ ማርያም ግን ከማየት÷ ከመስማት÷ ከማሰብ÷ ከመናገር ሁሉ ንጽሕት ናትና:: አምላክ ከርሷ ለመወለድ ያበቃው ቅሉ ንጽሕናዋ ድንግልናዋ ቅድስናዋ ነው÷ ስለዚህም ድንግል በክልኤ ትባላለች::

የዓለም ቤተ ክርስቲያን በ፫ኛው ጉባዔ ላይ ወላዲተ አምላክ ተብላ ቅድስት ማርያም እንድትጠራ ወስኗል:: እርሷንም የወለዱ ኢያቄምና ሐና ቅዱሳን ተብለዋል:: ቅዱሱ መልአክ ገብርኤልም ከእግዚአብሔር ተልኮ መጥቶ "ቡሩክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ" ሲል ከሴቶች ሁሉ የተለየች መሆኗን በምስጋና ቃል ገልጦ ተናግሯል[2]::

የዚህን መልአክ ቃል በመደገፍ በማጽናትም ደግሞ ቅድስት ኤልሣቤጥ "አንች ከሴቶች የተባረክሽ ነሽ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው" ብላ ጮሃና አሰምታ ተናግራለች[3]:: ይኸም ቃል ቅድስት ማርያም በነፍስ በሥጋ ቅድስት መሆኗን መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን መሆኗን ያጠይቃል::

በጠቅላላም በቅድስት ማርያም አማላጅነትና ታዳጊነት ብዙዎች ቅዱሳን እንደሚነሡና ቅዱሳን እንደሚሆኑ ያመለክታል:: ከዚህም ጋር በልዩ ልዩ ቦታና ጊዜ የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቅድስናዋን በመግለጥ ድርሳን ጽፈውላታል፤ ተአምሯን አዘጋጅተውላታል:: ከነዚህም አባቶች ውስጥ ቅዱስ ኤፍሬም÷ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ÷ አባ ሕርያቆስና ሌሎችም ናቸው÷ እነርሱም በአማን ቅድስት÷ በአማን ውድስት÷ በአማን ክብርት ወልዕልት እያሉ አመስግነው ጽፈውላታል::

ቅድስት ማርያም እመቤትነትን ከገረድነት÷ እናትነትን ከድንግልና ጋር አስተባብራ የያዘች እመቤት ናት÷ ስለዚህ የክብር ስሟ ድንግል ወእም÷ እም ወዓመት የሚል ነው÷ ድንግልናዋም ዘለዓለማዊ ስለሆነ ድንግል ዘለዓለም እንላታለን::



www.ethiopianorthodox.org

የቅድስት ማርያምን ንጽሕና ቅድስና ቤተ ክርስቲያን በመረዳት "እሞሙ ለሰማዕታት ወእኅቶሙ ለመላእክት ትምክህቶሙ ለወራዙት ወለደናግል" እያለች ታመሰግናታለች። ቅድስት ማርያም አስቀድሞ በትንቢተ ነቢያት የከበረች ትንቢት የተነገረላት ምሳሌም የተመሰለላት ሱባዔም የተቆጠረላት እመቤት ናት።

ለ. <u>ክብረ ድንግል በነቢያት</u>፥

ቅድስት ማርያም አምላክን ከመጽነሷና ከመውለዷ በፊት ብዙ ትንቢት ተነግሮላታል፥ ሱባዔም ተቆጥሮላታል፥ ብዙዎች ምሳሌዎችም ተመስለውላታል፥ ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን ነቢያት ትንቢት ሲናገሩ ሱባዔም ሲቆጥሩ እንዲሁ ስለ እመቤታችን በሰፊው ተናግረዋል፥ ምሳሌም መስለዋል። ግን ከምሳሌውም በትንቢቱም ብዙው ለጊዜው ግልጥ ያልሆነ፥ ለማን እንደተነገረ፥ ምን ማለት እንደሆነ ለብዙ ሕዝብ ስውር ሁኖ ይኖር ነበር፥ ጌታችንና አምላካችን ከድንግል ማርያም ሲወለድ ግን ሁሉም ግልጽ ስለሆነ፥ የተነገረው ትንቢት፥ የተመሰለውም ምሳሌ ሁሉ ለቅድስት ማርያም አማናዊ ሆነ። ከዚህም በቀር ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በድርሳናቸው የረቀቀውን እያጎሉ፥ የጎደለውን እየሞሉ ስለ ቅድስት ማርያም አስፋፍተው ጻፉ። ቅድስት ማርያም የብሉይ ኪዳንም የሐዲስ ኪዳንም እመቤት ሁና በሁሉም የከበረች፥ በሁሉም ዘንድ ምስጋና የሚገባት እንደሆነች፥ በሰፊው ታውቀ ተረዳ፥ ግልጥ ሆነው ስለቅድስት ማርያም ከተነገሩላት ትንቢቶች በመጠኑ እንደሚከተለው እንገልጣለን። ነቢዩ ኢሳይያስ ጮኸ አሰምቶ "እነኋት ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ብሎ ንጹሑን ሐዲስ ተናገረ[4]። በዚህን ጊዜ ለዘለዓለም ድንግል ሆና የምትመሰገነውን የቅድስት ማርያምን የክብር ስም በእውነተኛ ትንቢት እንደመሰከረ ለሁሉም ግልጥ ነው። ነቢዩ ዳዊትም "እግዚአብሔር ጽዮንን መረጣት ማደሪያም ትሆነው ዘንድ ወደዳት ..." ሲል እግዚአብሔር ወልድ በማኅፀኗ ፱ ወር ከ፭ ቀን እንደሚያድር ገልጦ አስፋፍቶ ተናገረ[5]። ነቢዩ ኢሳይያስ እንደገና "ከጽዮን ሕግ ይወጣልና የእግዚአብሔር ቃል ከኢየሩሳሌም" ብሎ ትንቢት በተናገረ ሱባዔም በቆጠረ





ጊዜ ጽዮን ብሎ የጠራት ወይም በጽዮን የመሰላት አማናዊት ጽዮን ቅድስት ማርያምን ነውና[6]። ኢየሩሳሌም ያላትም ወይም በኢየሩሳሌም የመሰላትም፥ ድንግል ማርያምን ነው፥ ልዑል አምላክ ከርሷ ተወልዷልና። አሁንም እንደገና ይኸው ነቢይ "በትር ከዕሴይ ሥር ይወጣል ጫፍም ከሥሩ ትበቅላለች" ባለ ጊዜ በትር ያላት በበትርም የመሰላት ቅድስት ማርያምን ነው[7]። በዚህም ምሳሌ ብዙ ሊቃውንት መስለዋታል፥ ለአስረጅም ያህል ቅዱስ ኤፍሬም በትረ አሮን ብሏታል፥ እንደገናም ይኸው ቅዱስ በትረ ሃይማኖት ዘኢትጸንን ብሎ መስሏታል።

እንደገና ነቢዮ ኢሳይያስ "እነሆ እግዚአብሔር በቀሊል ዳመና ይወጣል፥ ወደምስርም ይገባል" ሲል ደመና ብሎ የምህረት ዝናምን ጌታን የጸነሰች ቅድስት ማርያም እንደሆነች በደመና መስሏታል[8]።

ይኸንም ይዞ ቅዱስ ኤፍሬም የምህረት ዝናም ውኃን የያዝሽ እውነተኛ ደመና አንች ነሽ ሲል አመሰግኗታል[9]። እንዲሁም ይኸው ነቢይ "ማነው እርሱ ከኤዶምያስ የመጣ ልብሱ ደም የሚመስል ..." ሲል የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣትና መከራ መቀበል ሲናገር ድንግል ማርያምን በኤዶምያስ መሰላት[10]። ነቢዩ ሕዝቅኤል ደግሞ "አምላክ አልፎበታልና የተቆለፈ ይሁን" ሲል በኖሕት በአንቀጽ መስሎ ስለ ቅድስት ማርያም ተናገረ[11]። በተለይ አይከፈት ሰውም አይለፍበት የተቆለፈ ይሁን ብሎ የቅድስት ማርያምን ዘለዓለማዊ ኀቱም የሆነውን ድንግልናዋን መስከረ፥ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋንም አመለከተ።

ይኸም ቃል በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ትወልዳለች ካለው ከኢሳይያስ ቃለ ትንቢት ጋር ይተባበራል። ይኸንም ምሳሌ ይዞ ቅዱስ ኤፍሬም "በታላቅ ቁልፍ የተቆለፈ ማንም ሊወጣበትና ሊገባበት ያልቻለች አንዲት አዳራሽ በምሥራቅ አየሁ ብሎ ነቢዩ ሕዝቅኤል የተናገረልሽ አማናዊት በኖሕት አንች ነሽ" እያለ አመሰግኗታል[12]። ነቢዮ እንባቆምም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ስለ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ሲናገር "... ቅዱስም ከፋራን ተራራ ይወጣል" ብሎ ተናግሯል[13]። የፋራን ተራራ የተባለች ቅዱስ ወልድ ዋሕድ ክርስቶስ የተወለደባት



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያወሳን የመጀመሪያዎቹ ቅዱሳን እነዚሁ ሐዋርያት ነበሩ፡ ክርስቶስ አስቀድሞ ለተቀደሰ ተግባር የመረጣቸው "እናንተ አልመረጣችሁኝም እኔ እናንተን መረጥኋችሁ እንጂ፡ አስነሣኋችሁም ትሔዱ ዘንድ ፍሬም ታፈሩ ዘንድ ..." እያለ በክርስቶስ መመረጣቸውን ይመሰክርላቸዋል[2]።

አባ ቅዱስ ቀድሶሙ በጽድቅከ እያለ ቅድስናን እንዲያገኙ ቅዱሳንም እንዲሆኑ ክርስቶስ ወደ ባሕርይ አባቱ ጸልዮላቸዋል፡ ከዚያም አያይዞ እነርሱም በእውነት የተቀደሱ እንደሆኑ እኔ ራሴን ስለነርሱ እቀድሳለሁ ሲል ተናግሯል[3]። ቅዱሳን ሐዋርያት ያሠሩት የታሠረ፡ እነርሱም የቀደሱት፡ የተቀደሰ ያነጹትና የፈቱት ደግሞ የተፈታ፡ የተቀደሰም እንደሚሆን ክርስቶስ በአምላካዊ ቃሉ መስክሮ ተናግሮላቸዋል[4]።

እነዚህ ቅዱሳን ሐዋርያት የዓለም ጨው የሆኑ፡ የዓለምን ምሬት ያጣፈጡ፡ በሥነ ምግባር ያልጣመውን ዓለም ጣዕመ ጸጋን ያሰጡ ናቸው፡ ሐዋርያት ጨለማ ለብሶ የነበረውን ዓለም ጨለማውን የገፈፉ፡ ብርሃኑን ያጎናጸፉ ናቸው፥ ስለዚህም ሁሉ የመጀመሪያውን ቅድስና የወሰዱ እነርሱ ሲሆኑ ከነርሱ በኋላ ቅድስና ለሁሉ ተላልፎ ሁሉም የቅድስናውን ጸጋ ተሣትፎ እንዲኖር ሆኗል።

ሐዋርያት በዚያን ጊዜ ከነበረው ማኅበራዊ ኑሮ ተለይተው የክርስቶስ ወገን ሆኖ መገኘት የተለየ ቅድስና ነው፡ በበለጠም ቅዱስ ያሰኛል፡ ስለዚህም ነው ክርስቶስ ወገናቸውን፡ ሀብታቸውን ሳይመለከት ቅድስናቸውን ብቻ በመመልከት የመረጣቸው። ሐዋርያት በመንፈስ ብቻ የከበሩ የበለጸጉም ነበሩ፡ ስለዚህ ክርስቶስ ስለ መሠረታት ቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸውን ለወጡ። ይኸው ተግባራቸው ቅድስናን፡ ብፅዕናን አሰጣቸው፡ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ቅዱሶች አድርጋ ሐዋርያትን ቅዱሳን ታደርጋቸዋለች፡ ቅዱሳን ትላቸዋለች። የቅዱሳን ሐዋርያት የዕረፍት ዕለት የቤተ ክርስቲያን የድል አድራጊነት ዕለት እንደሆነ አድርጋ በአዋጅ ታከብራለች። ከዚህ በኋላ የክርስትናው ቅድስና ተስፋፍ፡ ለሁሉም ተሰጠ፡ እንዲያውም ያመነው የተጠመቀው ሁሉ ከሌላው ሕዝብ ተለይቶ የክርስቶስ ተከታይ በመሆኑ እንደ ሐዋርያት ቅዱስ ይባላል ቅድስናም ይሰጠዋል።





# ም ዕ ራ ፍ ፬

## የቤተ ክርስቲያን አባቶች፥

### ፩. የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዓይነት፥

የቤተ ክርስቲያን አባቶች እየተባሉ የሚጠሩ አባቶች ኤጲስ ቆጶሳት ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርኮች ናቸው። እነዚህም አባቶች ሥልጣነ ክህነትን የማስተማር መብትን፡ ቤተ ክርስቲያንም የምትጠበቅበትን ሥልጣን ከሐዋርያት ተቀብለው ያስተማሩ፡ ቤተ ክርስቲያንን በእግሯ ያቆሙ፥ ቅዱሳን መጻሕፍትን ከልዩ ልዩ ቋንቋ እየተረጎሙ ያዳረሱ፡ እንዲሁም ቅዱስ መጽሐፍን አስመስለው ለቤተ ክርስቲያን መክፈቻ፥ ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍትን የጻፉ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ሥርዓትን የወሰኑ፡ ቤተ ክርስቲያን በቀና ዕምነት በጸና ሥርዓት እንድትመራ ያደረጉ፥ የመናፍቃንን ትምህርታቸውን የለዩ፥ ዕውነተኛውን ዕምነት ገልጠው ያስተማሩ ናቸው፥ እነርሱም እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ፥ ቅዱስ ቄርሎስ፥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፥ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ያሉና ሌሎችም ብዙዎች ናቸው።

እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በዕውቀት የጠለቁ እና የእግዚአብሔርን ሕግ የጠበቁ፥ መላ ዘመናቸውን በትምህርት በምናኔ ያሳለፉ፡ ዘመዶቻቸውን በምዕመናን የለወጡ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የሰጡ ናቸው፡ በዚህም መሠረት ከዓለም የተለዩ ናቸው። እነዚህ አባቶች በአንድ በክርስቶስ ክርስቲያን መሆናቸው ቅዱስ ሊያሰኛቸው ሲገባ፥ በ፪ኛው በኩል ደግሞ አኗኗራቸው ራሱ በቅድስና በንጽሕና የተዋበ ስለሆነ፥ ይኸ ስም ሊሰጣቸው ተገባ፡ ስለዚህም ቅዱሳን ተባሉ።

እነዚህን የመሳሰሉ ብዙዎች አባቶች በስንክሳር እናታውሳቸዋለን፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የደከመ የሠራ የመጀመሪያውን የመከራ ገፈታ የቀመሰ ሥራውን ሁሉ የጀመረ የፈጸመም ቅዱስ ፍሬምናጦስ ነው፡ ስለዚህ ታላቅ አባት ብለን እናከብረዋለን። ይኸን ዛሬ



www.ethiopianorthodox.org

ያረፈ የመጀመሪያው ሰማዕት እስጢፋኖስ የተባለው ነው፥ ስለዚህም ቀዳሚ ሰማዕት ሊቀ ዲያቆናት ይለዋል:: ከላይ እንደ ገለጥነው በሰማዕትነት የዐረፉት ቅዱሳን ብዙዎች ሲሆኑ ወደ ሀገራችን ስማቸውና ተጋድሏቸው የተላለፈልን በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ቅዱሳን ሰማዕታት ምስክርነታቸውን በመስጠት ያረፉበት ጊዜና ቦታ የተለየ ቢሆንም ቅዱስነታቸው የወል ሁኖ አብያተ ክርስቲያናት ቅድስናቸውን ትሰብካለች፤ ስማቸውን ትጠራለች፤ በአማላጅነታቸውም ትማጸናለች:: ሰማዕታት ብዙ ተጋድሎ አድርገው በመጨረሻው ድል ያደረጉ ስለሆነ፥ በድል አድራጊነት መልክ ቤተ ክርቲያን በስማቸው ይታነጽላቸዋል፤ ጽላት ይቀረጽላቸዋል፥ ሥዕል ይሣልላቸዋል፥ እነዚህ ሰማዕታት የእውነት ጠበቃ ሆነው ስለ እውነት የመሰከሩ ናቸው፥ ማንኛውም ሰው ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ሁሉም መሪው የወደደውን ዘመን የወለደውን እንከተላለን ራሳችን ከመከራና ከአደጋ እንጠብቃለን ብለው ከእውነት ሲርቁ ሰማዕታት ብቻ በተቃራኒው መንገድ ተራምደው ሐሰትን አጋለጡ እነርሱም ለሰው ይምሰል ሊሠሩና ሊኖሩ ይችሉ ነበር ነገር ግን ሕይወታቸው ለአንዲት ቀን እንኳን ብትሆን በዚያችው አጋጣሚ እውነትን ሠርተው፥ እውነትን ተናግረው ለማለፍ ወስነው እራሳቸውን አሳልፈው ለእውነት ሰጡ፥ ነገር ግን ለጊዜው በሥጋ ይሙቱ እንጂ በነፍስ ሕያዋን ሆነው ስማቸው ይጠራል፥ ክብር ይሰጣቸዋል፥ ቅዱሳን የሚል ማዕረግ ይሰጣቸዋል:: ሰማዕታት ለክርስቲያን ሕይወት ፍጹም ምሳሌዎች ስለሆኑ እውነተኛ ክርስቲያን ሁሉ እነርሱን ያከብራል፥ ቅድስናቸውን ይናገራል፥ እነርሱም በዚህ ሕይወት ጎዳና ለማለፍ ይጣጣራሉ::

፫. ጻድቃን፥ ጻድቃን ማለት ጸደቀ እውነተኛ ሆነ ካለው ከግዕዙ የወጣ ቃል ነው ስለዚህ ጻድቅ ስንል ቀጥተኛ ትርጉሙ ዕውነተኛ በዕውነት የኖረ በሚገባ የሠራ ማለት ነው::

በዚህ መልክ ጻድቅ ስንል የዕውነተኛነት ትርጉሙን ሳይለቅ አንድ ሰው ሕይዎቱን በተገቢው መንገድ ያሳለፈው፥ በእውነት የጸና፥ ስለ እውነት የሠራ ማለት ነው:: ይኸም ከክፉ ነገር ከኃጢአትም ርቆ ንጽሕናን ጠብቆ የኖረ፥ ከዕኩያት





ክፍትወታት ጋር ተጋድሎ አድርጎ ያቸነፈ፥ የድል አድራጊነት ክብር የተሰጠው፥ ለክርስቲያናዊ ሕይወት ሌላ ምስክርነትን የሰጠ ሰማዕት ነው::

በሰፊው አነጋገር ግን ጻድቅ ማለት ቅዱስ ማለት ነው እገሌ ጻድቅ ነው፥ ሲባል እንደሰማዕታት በእሳት በፍላት በሥለት አይፈተን እንጂ በልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ተፈትኖ ያቸነፈ፥ ራሱንም ብዙ ነገር ከማየት ከመስማት በበለጠም ከመሥራት ከልክሎና አቸንፎ የኖረ ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ በምድራዊ ሕይወቱ ቅድስናን ያሳየ፥ በቅድስናም የኖረ ጻድቅ ነው:: ይኸንንም ማዕረግ ለማግኘት አንድ ሰው ከቤቱ ወጥቶ ከዘመዱ ተለይቶ፥ ዝጉሐዊ ተሐራሚ ጸዋሚ ሆኖ ከሰው ተለይቶ፤ ቤት ዘግቶ የሚኖር፥ ለጸሎት ጽሙድ የሚሆን ሌላ ትሩፋት አብዝቶ የሚሠራ ነው::

እነዚህ በተለያየ መልክ ታሪካቸውን የገለጥነው ቅዱሳን ሁሉ ይኸን ዓለም አቸንፈው ወደሌላው ዓለም የተላለፉ የቤተ ክርስቲያን ዓባላት ናቸው:: ምንም በሥጋዊ ዓለም ባይታዩ በመንፈሳዊው ዓለም ሕያዋን ሆነው ስለሚገኙ ቤተ ክርስቲያን ታሞግሳቸዋለች፥ ዓባልነታቸውንም ትገልጥላቸዋለች::

## ም ዕ ራ ፍ ፳

## ከቅዱሳን ጋር ያለን ግንኙነት፥

እኛ በሕይወት የምንገኝ የቤተ ክርስቲያን ዓባላት ከላይ በተለያየ መልክ የዘረዘርናቸው ቅዱሳን እንደደመና የሚከቡን፥ ስለክርስቲያናዊ ሕይወት ምስክር የሚሆኑን በሰልፍና በውጊያ ሕይወታችን እንድናሳልፈው አብነት ሁነውናል:: እነዚህ ቅዱሳን ሁሉ የዘለዓለም ዕረፍትን አርፈው የሚገኙ ሲሆኑ ከኛ ጋር የማይለያይ የጠበቀም ግንኙነት አለን:: እኛ በጸሎት እናስባቸዋለን፥ ቤተ ክርስቲያን በጌታ አምነው ላረፉት ሁሉ ያለምንም ልዩነት ጸሎት ታደርጋለችና:: ይኸም ጸሎት የኃጢአት ሥርየት የመታሰቢያ ጸሎት ነው፥ እነርሱ ደግሞ ለኛ አምላክ በሰጣቸው የአማላጅነት ኪዳናቸው ልመና ያደርጉልናል::



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱሳን ሁሉ ምንም አምላክ የቅድስናን የብፅዕናን ማዕረግ ቢሰጣቸውም በምድር እንደመኖራቸው መበደላቸው አይቀርምና የኃጢአት ሥርየት የፍትሐት ጸሎት እናደርግላቸዋለን:: ኢዮብ ነቢይ "የሰው ሕይወቱ በምድር ላይ ለ፩ ቀን እንኳ ቢሆን ሰው መበደሉ አይቀርም" ይላል::[1] ወንጌላዊ ዮሐንስም "ኃጢአት የለብንም ብንል እኛ ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም የለችንም" ሲል ትክክለኛ አስረጅን ይሰጠናል::[2]

እንግዲህ እግዚአብሔር በጸጋው በቸርነቱ ያጸድቃቸዋል እንጂ ማንም ንጹሕ አይገኝም፥ ስለዚህ አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ትሸኘዋለች:: ስለ ሙታን ጸሎት እንዲደረግላቸው የጥንት ቤተ ክርስቲያን ያዘዘችው ስትፈጽመውም የቆየችው ቅዱስ ሥርዓት ነው:: ለቅዱሳን ክብርን በመግለጥ ተጋድሏቸውን በማውሳት፥ ስለኃጢአተኞች ደግሞ ስለ ኃጢአታቸው ሥርየት ጸሎት ፍትሐት ታደርጋለች::

ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ቅዱስ ሊሆን ይችላል፥ ይኸም ቅድስና ከእግዚአብሔር የሚሰጥ፥ በእርሱም የሚገለጥ እንጂ ሰው የሚሰጠው አይደለም፥ በሰውም ዘንድ አይታወቅም:: በሰማዕትነት የሞቱ አሉ፤ እንዲሁም ስለክርስቶስና ስለቤተ ክርስቲያኑ ሲሠሩ፥ ሲመሠክሩ የሞቱ አሉ፥ እንዲሁም በብሕትውና የኖሩ ዝጉሓዊ ተሐራሚ ሁነው ኑረው የሞቱ አሉ፥ እግዚአብሔር ተጋድሏቸውን ዓይቶ በቸርነቱ እንደ ድካማቸው ዋጋቸውን በሰጣቸው ጊዜ ተአምራት ሲሠሩ ምልክት ሲያሳዩ የቅድስናቸው የብቃታቸው ክብር ይገለጣል እንጂ እኛ ጻድቅ ኃጥእ ብለን ልንሰይም አንችልም፥ ቤተ ክርስቲያን ግን ማንም ይሁን ከዚህ ዓለም ሲለይ ለሁሉ የክብር አሸኛኘት ታደርጋለች፥ ጸሎተ ፍትሐት ታደርጋለች፥ የመታሰቢያም ጸሎት በየጊዜው ታደርጋለች::

እንደ ቅዱሳን ሐዋርያት ያሉ ጌታ ራሱ "ወዳጆቼ" ያላቸው ወዳጆቹም ያደርጋቸው::[3] በሰማያዊ መንግሥቱም የተለየ ቦታ ያዘጋጀላቸው የተስፋ ቃልም የተናገረላቸው ይገኛሉ::[4] እንደዚህም ያሉት ሁሉ ቢሆኑ በዕረፍታቸው ጊዜ የምልጃ ጸሎት ይደረግላቸዋል፥ በየዓመቱም የመታሰቢያ ጸሎት





ይደረግላቸዋል፥ እንዲያማልዱን ስእለት አስተበቁዓት እናደርጋለን:: ዮሐንስ ወንጌላዊ "በጌታ የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው አሁን ጀምረው" ሲል እንደተናገረው እንደነዚህ ያሉትን ቅዱሳን ሁሉ ብፁዓን እንላቸዋለን፥ ብፅዕና እንሰጣቸዋለን::[5] ጌታ ራሱ የእርሱን ክብር ለወዳጆቹ እንደሚሰጣቸው ራሱ ተናግሯል::[6] እኛም በርሱ አምነው ለሞቱት ሁሉ የክብር ክብርን እንሰጣቸዋለን፥ ከጌታ እንዲያማልዱን የምልጃ ጸሎት እናደርግላቸዋለን::

በዚህ ዓለም ያሉ ምእመናን ከቅዱሳን ጋር በዚህ መልክ የጠበቀ ግንኙነት አላቸው፥ ስለዚህ ግንኙነትም ጌታ ራሱ ሲናገር "ነቢዩን በነቢዩ ስም የተቀበለ የነቢዩን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቁንም በጻድቁ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል" ሲል በምድራዊ ሕይወት የምንገኝ በሰማያዊ ሕይወት በሚገኙ ቅዱሳን ስም ምጽዋት ስንሰጥ፥ ዝክር ስናደርግ ሰማያዊውን ዋጋ እንወስዳለን::[7] እንግዲህ ጻድቁን በጻድቁ ስም አሁንም እንቀበላለን ከጻድቁ ጋር አንድነት ይኖረናል፤ ጻድቃን የጌታ ወዳጆች ስለሆኑ የእኛም ወዳጆች ይሆናሉ::

ቅዱሳን የኛ መንፈሳዊያን አባቶች እናቶች ወንድሞች እኅቶች ናቸው፥ ፍቅራችንንም የምንገልጠው እነርሱንና እኛን በሚያገናኝ እውነተኛ ጸሎት ነው:: ስለዚህ ግንኙነታችን ሐዋርያው ዮሐንስ "ያየነውንም የሰማነውንም እርሱን ለእናንተ ደግሞ እናስታውቃችኋለን፥ ከእኛ ጋር አንድነት ይሆንላችሁ ዘንድ፥ የኛ አንድነት ግን ከአብ ጋር ናት፥ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር" ሲል ያስረዳናል::[8]

ከቅዱሳን ጋር በጸሎት መገናኘት በምድራዊቲቱና በሰማያዊቲቱ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ግንኙነት ያረጋግጣል፥ ይኸነንም እውነት ሐዋርያው ጳውሎስ "እላንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ ደረሳችሁ ወደ ሕያውም እግዚአብሔር አገር ወደ ሰማያዊቲቱ ኢየሩሳሌም ወደ አዕላፍም መላእክት:: በሰማይ ወደተጻፉም ወደበኩራት ማኅበር፥ ወደ እግዚአብሔርም ወደሁሉ ፈራጅ ወደ ተፈጸሙትም ወደ ቅዱሳን መናፍስት" ሲል ግልጥ በሆነ መንገድ ያስረዳናል::[9]



www.ethiopianorthodox.org

ጸጋ ለራሳቸው ብቻ አድርገው ባለማስቀረት ለተከታዮቻቸው አስተላልፈዋል፥ እነርሱም ደግሞ እንዲሁ ለተከታዮቻቸው።

በመጀመሪያ ሐዋርያትን ሲልክ እናንተን የሰማ እኔን ሰማ[7]። ብሎ የርሱ ወኪሎች አድርጎ ሙሉ መብትን ሙሉ ሥልጣንን ሰጥቶ ልኳቸዋል። እንዲሁም "እናንተ በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይኖናል"[8]። ሲል ሰማያዊ ሥልጣን በምድር እንዲሠራ፥ ምድራዊም ውሳኔ በሰማይ እንዲጸድቅ አድርጎ ልኳቸዋል። እንግዲህ የዚህ ሁሉ ሥልጣን መገኛ ቤተ ክርስቲያን ናት፥ ይኸንና ሌላዎችንም ምሥጢራት ሁሉ የምት ጠብቅ የምሥጢራት ሁሉ መዝገብ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ማኅደር ናት፥ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፥ ቤተ ክርስቲያን ካለችበት ከዚያ ክርስቶስ አለ የቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ግንኙነት መቼም ቢሆን፥ በምንም ምክንያት የማያቋርጥ ነውና።

የክርስቶስ የማዳን ሥራው በቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ስለሚቀጥል ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባው ሁሉ ወደ ድኅነት ገባ፥ ድኅነት የሚገኘው በቤተ ክርስቲያን ብቻ ነውና፥ ከቤተ ክርስቲያንም ውጭ ድኅነት የለምና ቤተ ክርስቲያን ዘለዓለ ማዊት ተቋም እንደመሆኗ ክርስቶስ እስከ ዘለዓለም አይለያ ትም፥ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የእውነትም፥ የጸጋ መዝገብ ሁና ከሐሰት ርቃ ለዘለዓለም እንድትኖር ያደርጋታል ይጠብቃ ታልም። ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ መንፈስ እንድትመራ ለዘለዓ ለሙም እንደሚጠብቃት ክርስቶስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፥ "እኔም አብን እለምነዋለሁ ሌላ የሚያጽናና ይሰጣችኋል፥ ከእናንተ ጋር ይኖር ዘንድ ለዘለዓለም"[9]። እንግዲህ ከቤተ ክርስቲያን ያልራቀ ሰው እግዚአብሔርን ቀረበ፥ ቤተ ክርስቲ ያንንም እናት ያደረገ እግዚአብሔርንም አባት ያደርጋል። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ስንል በእውነት በክርስቶስ አምኖ በዓባልነቱም ጸንቶ ምሥጢራቱን ተካፍሎ የሚኖረው ወገን ብቻ የሚድን መሆኑን ማመን አለብን። በስም ክርስቲያን በስም የክርስቶስ አካል፥ በስም ቤተ ክርስቲያን እየተባለ የሚጠራው ሁሉ ከድኅነት መዝገብ ውጭ መሆኑ መታወቅና መታመን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ወንዱም ሴቱም፥ ካህኑም የጨዋ





ልጁም በአባልነት የሚገኝበት አደባባይ ነው ብለናል፥ ይኸውም የሚያሳየው ክርስቶስ ሁሉንም ለድኅነት መጥራቱን፥ ለድኅነት ሁሉንም መመዝገቡን ነው። ነገር ግን በራሱ ምርጫ ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥ ከቤተ ክርስቲያንም ትእዛዝና አመራር ውጭ ሁኖ በስም አለሁ የሚለው ከተስፋው ውጭ መሆኑን በራሱ ፍርድ ወይም ምርጫ እንደወጣ ማወቅ አለበት።

ቤተ ክርስቲያን አንድ ማኅበር፥ አንድ ድርጅት፥ እንደመሆኗ አስተዳደር አላት ሥነ ሥርዓትም አላት፥ ስለዚህ ምዕመን ሁሉ ለዚህ ሥነ ሥርዓት ታዛዥና ተገዥ መሆን አለበት።

## ምዕራፍ ፲

## የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥

ቤተ ክርስቲያን ራሷን የቻለች አንዲት ማኅበር እንደመሆኗ የራሷ የሆነ የተለየ አስተዳደር አላት፥ ቤተ ክርስቲያን ልትፈጽማቸው የሚገባት ዓላማዋም የሆኑ ፲ቱ ታላላቅ ተግባራት አሏት፥ እነዚህም የእግዚአብሔር ቃልን መናገር፥ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም፥ ምዕመናንን መጠበቅና ማስተዳደር ናቸው። ይኸን የመሰለውን ይፈጽሙለት ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ በመጀመሪያ ፲፪ቱን ሐዋርያት ፸፪ቱን አርድእት መረጠ፥ ለነርሱም ሙሉ የማስተዳደርን የመምራትን፥ የማሠርንና የመፍታትን ሥልጣን ሰጣቸው። እንዲሁም ሥልጣኑን ሰጥቶ አልተዋቸውም አልተለያቸውም፥ ነገር ግን ምንም ጊዜ ከአደረ የማይለየው፥ ከተሰጠ የማይነሣው ቅዱስ መንፈሱ ተአምራትን በማድረግ ያጸናቸው ይረዳቸውም ነበር[1]።

እነዚህም የጌታ ደቀ መዛሙርት የተሰጣቸውን ሥልጣን ለግላቸው መጠቀሚያ ይሆናቸው ዘንድ እነርሱ ብቻ ይዘውት አልቀረም። ነገር ግን ለስብከት በየተበተኑበት አገር እነርሱም በበኩላቸው ለተከታዮቻቸው ሙሉ ሥልጣንን እየሰጡ ቅዱስ መንፈስን እያደሉ አስተላለፉ እንጂ። ስለዚህም ዲያቆናትን፥ ቀሳውስትን፥ ኤጲስ ቆጶሳትን በየሀገሩ እየሾሙ፥ መመሪያም እየሰጡ አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ አደረጉ። በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን የሚባለው አንቀጽ ከካህናትና



www.ethiopianorthodox.org

ነበር። አንድ ኤጲስ ቆጳስ ከሌላው ጋር እኩል የሆነ ሥልጣንም መብትም ያለው ሲሆን፣ የሁሉም ሰብሳቢ የሆነው የርእሰ ከተማው ኤጲስ ቆጳስ የተለየ የአስተዳደር ክብር ይሰጠው ነበር፣ እየዋለ እያደረ ግን ኤጲስ ቆጳሳት እየበዙ ሲሔዱ፣ ሰብሳቢያቸው ጳጳስ ሊቀ ጳጳሳት ተብሎ ይጠራ ጀመር። ግን አሁንም በሥልጣነ ክህነቱ ከሌሎች ምንም ልዩነት ሳይኖረው በአስተዳደር ሥልጣን ብቻ የሁሉ ርእስ ሁኖ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ይጠብቅ ነበር። ጳጳስ ኤጲስ ቆጳስ የሚለው የቃል ልዩነት እንጂ በሥልጣነ ክህነት በኩል ምንም ልጅነት የለውም፣ ጳጳሱ ኤጲስ ቆጳስ ይባላል፣ ኤጲስ ቆጳሱም ጳጳስ ይባላል፣ በዚህም መልክ በዚያን ጊዜ የታወቀውን ዓለም በትክክል ለመጠበቅ ሲባል ዓለሙን በ፬ ክፍል ከፍለው ፬ ሊቃነ ጳጳሳት ሾመው ነበር፣ እነርሱም፣

1. ሮም፣ ይኸም ምዕራቡን ዓለም የሚመለከት ነበር፣
2. እስክንድርያ፣ እርሱም በመላ አፍሪካን የሚመለከት መንበር ነበር፣
3. አንጾኪያ፣ እርሱም የመካከለኛውን ምሥራቅ የሚመለከት ነበር፣
4. ኢየሩሳሌም፣ እርሱም በመዲናነቱ ይከበር ነበር።

ቆይቶ ግን የሮማ መንግሥት ወደቁስጥንጥንያ ስለ ተዛቀወረ ቁስጥንጥንያ ፩ኛነትን አግኝታ ሁሉም እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ እየሆኑ በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ይሠሩ ነበር። ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልክ በትክክል ስትሠራ ኑፋቄን ጥርጥርን ስታጠፋ መናፍቃንን ስታወግዝ ኑራለች።

እየዋለ እያደረ ግን ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ መንፈስ ኃይል በመመራት ፈንታ በሥጋዊ ኃይል፣ በዓለማዊ ስሜት ለመምራት ሲሞክር ተቃዋሚው በዛ፣ መናፍቁ ከየቦታው ተነሣ ስለዚህም ልትከፈል የማትችለውን አንድም የማይገባትን አንዲቱን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክፍል ከፋፈሏት። ሁኖም የእግዚአብሔር መንፈስ በሁሉም አድሮ ስለአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አንድነት ይሠራ ዘንድ የሁሉም ጸሎት መሆን አለበት።





# ክ ፍ ል ፱

# የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት፣

## ም ዕ ራ ፍ ፩

## የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት፣

በተለያዩ አገልግሎቶች አማካይነት የሚፈጸሙ እውነተኛው የክርስቶስ ጸጋም ለምእመናን የሚተላለፍባቸው፣ ወይም የሚታደልባቸው በቤተ ክርስቲያንም መዝገብነት የሚጠብቁ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉ አሉ። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉትም አማንያን ሁሉ በትክክል በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋን የሚያገኙባቸው ናቸው፣ እነዚህም አገልግሎት የሚፈጸሙት የእግዚአብሔር እንደራሴ በሆነው በካህኑ ቡራኬና ጸሎት ነው፣ የአማንያኑም ተሣትፎ በግድ የሚያስፈልግበት ቅዱስ አገልግሎት ነው። እነዚህ የማዳን ኃይል ያላቸው ምሥጢራት ከክርስቶስ መስቀል የተነሣ የተገኙ ሲሆኑ አሁንም ክርስቶስ የማዳን ሥራውን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚቀጥልባቸው ኃይሎች ናቸው። እንግዲህ ምእመናን ጸጋንና በረከትን ያገኙ ዘንድ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተሣታፊ መሆን በግድ አለባቸው፣ ምክንያቱም ከምሥጢራት መጓደል የተነሣ የጸጋም መጓደል ድኅነትም የማጣት ችግር ይመጣልና። እንግዲያውስ ከሁሉ አስቀድሞ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ስንል ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ለሁሉ አስፈላጊ ነው፣ እንዲሁም ምሥጢራቱ ለምእመናን ሁሉ እንዲዳረሱ ማድረግ የግዴታ ተግባር ነው፣ ማለት እያንዳንዱ ምእመን ክርስቲያን እንደመሆኑ ተልእኮውን ይፈጽም ዘንድ ግዴታውንም ይወጣ ዘንድ ተገቢ መሆኑን ማወቅ አለበት። ሕፃናትን ምንም ሳያውቁ የምናጠምቃቸውና የምሥጢራት ሁሉ ተካፋይ የምናደርጋቸው የወላጆቻቸውንና የክርስትና አባቶቻቸውን፣ የክርስትና እናቶቻቸውን ኃላፊነት ተቀብለን ነው፣ ማለት በነርሱ ኃላፊነት በነርሱም ዋስትና ስናጠምቃቸው እነርሱ የተቻላቸውን ያህል ሕፃናቱን ያስተምሯቸዋል፣ ወደ ክርስቲያናዊ ሕይወት ይመሯ



www.ethiopianorthodox.org

፩ የምሥጢራት ቁጥራቸው:- ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉት ቤተ ክርስቲያናችን የምትቀበላቸው በቁጥር ሰባት ናቸው፤ እነርሱም ምሥጢረ ጥምቀት ምሥጢረ ሜሮን፥ ምሥጢረ ቁርባን፥ ምሥጢረ ንስሐ፥ ምሥጢረ ክህነት፥ ምሥጢረ ተክሊል፥ ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው:: እነዚህም ሰባቱ ምሥጢራት የሰው ልጅ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ሕይወቱ የሚደገፉበት ሰባት ዓምዶች ናቸው:: ምሥጢራተ ቤተ ክርስ ቲያን የሚባሉት ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን ውስጥ የወደቁትን የምታነሣበት፥ የደከሙትን የምታበረታበትና ኃይል የምትሰጥበት ያደፉትን የምታነጻበት ኃያል ነው::

፪ የምሥጢራት ተግባራቸው:- መንፈሳዊ ሕይወት በጥምቀት ይጀመራል፥ ይኸውም ጥምቀት ከሥላሴ መወለድ ነው:: አዲስ ሰው ለመሆን አዲስ ሕይወትም ለማግኘት ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ለሰው ወገን ሁሉ ጥምቀት በግድ ያስፈልጋል:: ጥምቀት ወደማንኛውም ምሥጢር ለመግባት የመጀመሪያ በር ነው በእርሱም በርነት ያላለፈ ሁሉ ማንኛውንም ምሥጢር ሊካፈል ከቶ አይችልም:: ይኸም በጥምቀት የሚገኝ ፪ኛው ወይም መንፈሳዊ ልደት በቅዱስ ሜሮን ይጸድቃል፥ ይታተማል፥ ይረጋገጣል፥ ማለትም ማንኛውም ሰው ከሥላሴ ለመወለዱ ቅዱስ መንፈስንም ለመቀበሉ በሜሮን ይታተማል::

አዲስ ልደት የተወለደው፥ መንፈሳዊውንም ልጅነት ያገኘው ሰው መንፈሳዊ ምግብ በግድ ያሻዋል:: መንፈሳዊ ሕይወት ወይም ዘለዓለማዊ ሕይወት ይኖር ዘንድ መንፈሳዊ ምግብ በግድ ያስፈልገዋል፥ ስለዚህ ቅዱስ ሥጋውን ይበላል ክቡር ደሙንም ይጠጣል፥ ማለት ቅዱስ ቁርባንን ይቀበላል፥ እግዚአብሔር ይቀርበዋል፥ እርሱም ወደ እግዚአብሔር ይቀርባል:: በዚህም መልክ አንዱ ምሥጢር ከሌላው ጋር እንደ ሠንሠለት የተያየዘ ስለሆነ ምሥጢራትን ሁሉ እርስ በርሳቸው የተያያዙና የተደጋገፉ ናቸው:: ምንም ምስጢራትን ለያይተን ብንፈጽማቸው መንፈሳቸው አንድ ስለሆነ ግንኙነት አላቸው፥ ጸጋንም በየመልኩ ያሰጣሉ መንጻት፥ መቀደስ፥ መታደስ፥ በግድ በየጊዜው ለሰው ሁሉ ስለሚያስፈልግ የሰው ልጅ ሁሉ አዲስ ይሆን ዘንድ በየጊዜው ንስሐ ይገባል፥ ከብለየትም ይታደሳል በአእምሮም





ይኀለምሳል፥ ሥጋውም ነፍሱም ጸድቶለት እግዚአብሔርን እስከ ማየት ሊደርስ ይችላል:: "ልቦናቸው የነፃ ብፁዓን ናቸው እነርሱም እግዚአብሔርን ያዩታልና" ሲል ቅዱስ ወንጌል ያስረዳናል[2]:: ሁሉንም የሚቀድስ፥ ሁሉንም የሚያከብር ምሥጢር ደግሞ ምሥጢረ ክህነት ስለሆነ የተለዩ ሰዎች ወደዚህ ማዕረግ ይገባሉ፥ ይኸንንም ማዕረግ ይቀበላሉ:: ካህናት የምድር መላእክት የሰማይ ሰዎች ይሆናሉ፥ ይባላሉም፥ ስለዚህ ምሥጢረ ክህነት ለሰው ልጅ ተሰጠ፥ "ዘኢተገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት" ሲል ዮሐንስ አፈወርቅ ተናግሯል[3]:: እንዲሁም ሁለቱ ጾታዎች አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ አንድ ሐሳብ አንድ መንፈስም ይኖራቸው ዘንድ በጸሎትና በተክሊል ወንድና ሴት ይጋባሉ፥ በዚህን ጊዜ መለያየት ይጠፋል፤ አንድነት ይፈጠራል፥ በዚህም መንፈሳዊም ምድራዊም ሕይወት ይመሠረታል:: የታመመ ይፈወስ፥ ኃጢ አትም የሠራ ይሠረይለት ዘንድ ጸሎተ ቀንዲል ይፈጸምለታል፥ በዚህን ጊዜ የሥጋም የመንፈስም በሽታ ያለው ይድናል፥ ሙሉ ጤነኛ ይሆናል[4]:: በጠቅላላው በነዚህ ሰባት ምሥጢራት መፈጸም የሰው መንፈሳዊ ሕይወቱ ተደግፎ ጸንቶም ይኖራል፥ የሰው ልጅም እነዚህን በየጊዜው ሊፈጽማቸው ግዴታ አለበት፥ ያለዚያ ለሰው ልጅ ሁሉ ተዋሕዶት የሚኖር ሕይወት የለውም::

፫ የሚደገሙና የማይደገሙ ምሥጢራት፥ ከነዚህ ምሥጢራት ውስጥ የሚደገሙ በየጊዜውም የሚፈጸሙ አሉ፥ እነዚህ የሚደገሙ በየጊዜው የሚፈጸሙ የተባሉት ምሥጢራት ምሥጢረ ቁርባን፥ ምሥጢረ ንስሐ፥ ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው:: ምሥጢረ ተክሊል ከሚደገሙትም ከማይደገሙት ምሥጢራት ውስጥ ነው፥ ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያናችን የሚታመነው በአንድ ጊዜ ጋብቻ ብቻ ነውና:: ነገር ግን በአንዳንድ በታወቁ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ጋብቻ ይደገማል፥ ማለት አንደኛው ወገን የሞተ እንደሆነ ሕያው የሆነው ወገን እንደገና ሊያገባ ይችላልና:: እንዲሁም አንዱ የጋብቻውን እምነት ያጎደለ እንደሆነ የሥነ ምግባር ሞት ስለሆነ ያላጠፋው ወገን እንደገና ማግባት ስለሚችል ምሥጢረ ተክሊል ከሚደገሙ ምሥጢራት ውስጥ ገብቶ ይቆጠራል:: የማይደገሙ ምሥጢራት ደግሞ



www.ethiopianorthodox.org

# ም ዕ ራ ፍ ፫

## ም ሥ ጢ ረ ጥ ም ቀ ት

፩. <u>የቃሉ ትርጉም</u>:- ጥምቀት ማለት ከቅዱሱ ውሀ መጥለቅ፥ መነከር፥ መጠመቅ ማለት ነው:: ይህንንም ስንል ጥምቀት በመረጨት ወይም በማፍሰስ የሚፈጸም ሳይሆን ሰውነትን በመላ እስኪያጠልም፥ እስኪያለብስም ድረስ መነከር፥ በሥላሴም ስም ፫ ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያሉ የሚፈጽሙት አገልግሎት ነው:: አዲስ አማኒውን በተባረከው ውሀ ሦስት ጊዜ እየነከሩ ያወጡታል፥ ብቅ ጥልቅም ያደርጉታል፤ ስለዚህ ጥምቀት ተባለ:: ይኸም ምሳሌ አለው በውሀው ውስጥ መጥለቅ ወደ መቃብር የመውረድ ምሳሌ ነው፥ ከውሀው መውጣት ደግሞ የትንሣኤው ምሳሌ ነው:: ይኸም ግብር እየተመላለሰ ፫ ጊዜ መፈጸሙ የሥላሴ አምሳል ነው፥ ግብሩ ደግሞ አንድ ዓይነት መሆኑ የሥላሴን አንድነት የሚገልጥ ምሳሌ ነው:: ጥምቀትም የመቃብር ምሳሌ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ "ወይስ አታውቁምን እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን በሞቱ እንደ ተጠመቅን እንግዲህ በጥምቀት ከርሱ ጋር ተቀበርን ለሞት፥ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ በአብ ክብር፤ እንዲሁ እኛም ደግሞ በአዲስ ሕይወት እንሔድ ዘንድ ከእርሱ ጋር የተተከልን ከሆነ በሞቱ ምሳሌ እንዲሁም ደግሞ እንሆናለን በትንሣኤ" ሲል አስፋፍቶ ተናግሯል[1]:: መቃብር በመላ ሰውነትን የሚውጥ የሚያለብስም እንደመሆኑ ጥምቀትም በመላ አካላችን የሚውጥ (የሚያለብስ) ውሀ መሆን አለበት:: በባሕረ ኃጢአት ሰጥሞ የነበረው ሰው ከተባረከው ውሃ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ በመግባትና በመውጣት አዲስ ልደትን ይወልዳል፥ ፍጹም የእግዚአብሔርም ልጅ የመንግሥተ ሰማያትም ወራሽ ይሆናል:: ሁላችን በሥላሴ ስም በውሀ በመጠመቃችን አዲስ ልደት እንደምንወለድና መንግሥተ ሰማያትንም እንደምንወርስ "ኢየሱስ መለሰ እውነት እውነት እልሃለሁ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይችልም" ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል[2]::



www.ethiopianorthodox.org



መጠመቅ ማለት በውሀ መነከር ሳይሆን በመንፈሳዊ አነጋገር መታጠብ፥ ከኃጢአትም መንጻት፤ ከኃጢአት ቁራኝነትም መላቀቅ ነው:: ይኸም ሁለተኛ ልደት ይሆናል፥ ያውም ከእግዚአብሔር የሚወለዱት ልደት ነው:: በዘር ቁራኝነትም የወረስነውን ጥንታዊ ኃጢአት ልናስተሠርየው የምንችለው በጥምቀት ነው፥ ማለት ከውሃና ከመንፈስ በመወለዳችን ነው:: ይኸንንም ሃይማኖታቸው የቀና አባቶች "በአንዲት ጥምቀት እናምናለን፥ ኃጢአትን ለማስተሠርይ" ሲሉ ተናግረዋል[3]:: ሰው ሁሉ በኃጢአት ተወልዷል ከዚህም ኃጢአት ለመላቀቅና ንጹሕ ለመሆን በግድ ጥምቀት አስፈለገ:: ሁሉ በኃጢአት መወለዱን ንጹሕም አለመሆኑን መጻሕፍት ተባብረው ገልጠውታል[4]:: ንጹሕም ያልሆነ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም[5]::

ጥምቀት ለክርስቲያናዊ ሕይወት የመጀመሪያው መግቢያ በር ነው፥ በዚህም በር ወደ ቤተ ክርስቲያን ማንም ካልገባ በቀር የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ተሣታፊ ሊሆን አይችልም:: እንግዲህ ጥምቀት ማለት በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋን ማግኘት ማለት ነው:: በጥምቀት መታጠብ ከኃጢአት ሁሉ መንጻት ስለሆነ የሰው ልጅ ሁሉ በግድ መጠመቅ አለበት:: በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ሕፃናትን ሳይቀር እናጠምቃለን፥ ምክንያቱም በዘር ቁራኝነት ከወላጆቻቸው ከመጣው ኃጢአት ሳይነጹ ከእግዚአብሔርም ሳይወለዱ እንዳይሞቱ በማለት ነው::

፪. <u>ጥምቀት አስቀድሞ በምሳሌ እንደተፈጸመ</u>:- የሰው ልጅ ተሐድሶ የሚያገኘው ከሥላሴም የሚወለደው በጥምቀት ስለሆነ ጥምቀት ከፍተኛ ምሥጢር ነው፥ ስለዚህ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን በምሳሌ ሲሠራ ሲፈጸም ቆይቷል:: ስለ እርሱም ትንቢት በሰፊው ተነግሯል፥ ሱባዔም ተቆጥሯል:: በብሉይ ዘመን ሲፈጸሙ ከቆዩት ምሳሌዎች በመጠኑ እንደሚከተለው እንገልጣለን፤

ሀ. እሥራኤል የኤርትራን ባሕር መሻገራቸው፥ ቀጥሎም በደመና ጥላ ሥር ምድረ በዳውን መጓዛቸው የጥምቀት ምሳሌ ሁኖ ተገኝቷል:: ይኸንም ምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ

መስክሮ ገልጦ ሲናገር "አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች እንደነበሩ ሁሉም በባሕር ተሻገሩ። ሁሉም ለሙሴ ተጠመቁ በደመናና በባሕር ...." ሲል ገልጦለታል[6]።

ለ. ኖሕ ከማየ አይኅ ይድን ዘንድ መርከብን ሠራ፥ ስለዚህ እርሱም ቤተሰቦቹም ወደመርከቡ ገብተው ዳኑ፥ የሰው ዘር እንስሳም ሁሉ ሲጠፉ በመርከቡ የነበሩ ፰ ሰዎች ብቻና መጠነኞች እንስሳት ዳኑ። ይኸም የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ገልጦልን እናገኘዋለን[7]፥ ማለት ኖሕና ቤተሰቦቹ የምእመናን፥ ባሕር የጥምቀት መርከብ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦቹ የምእመናን ምሳሌ ናቸው። በጥምቀት በርነት ያልገባ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ያልተገኘ አሁንም ድኅነት የለውም ሊኖረውም አይችልምና። ይኸንም ምሳሌ ማስተማሪያ አድርጎ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ያቀርብልናል "በኖሕ ዘመን እርሷም ጥምቀት ታድናለች ከሥጋ ዕድፍ ማጠብ አይደለም የበጎ ሕሊና ልመና ወደ እግዚአብሔር እንጂ"[8]።

ሐ. ንዕማን የተባለው የሶሪያ ንጉሥ ለብዙ ጊዜ በለምጽ በሽታ ሲሠቃይ ቆይቶ ነቢዩ ኤልሳዕ በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲታጠብ አዝዞት ታጥቦ ድኗል፥ ይኸም አድራጎት ቀጥታ የጥምቀት ምሳሌ ነው። ንዕማን የምእመናን፥ ለምጽ የፍዳና የመርገም፥ በዮርዳኖስ መታጠቡና መዳኑ የጥምቀት ምሳሌ ነው፥ ድኅነት የሚገኘው በጥምቀት ነውና[9]። ከላይ ከገለጥናቸው ምሳሌዎች ሌላ ስለ ጥምቀት አስቀድሞ ብዙ ትንቢት ተነግሯል። ከነዚህም ውስጥ "ለታውጽአ ባሕር ኵሎ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈስ ሕይወት" ብሎ ፈጣሬ ፍጥረታት አምላክ ተናግሯል[10]። ይህም በውሃ ተጠምቀው ሕያዋን ሆነው ስለሚኖሩት ምእመናን የተነገረ ትንቢት ነበርና።

እንዲሁም ይኸን የመሰለ "...ወተጠምቃ አገረሆሙ ለካህናት" ሲል ኢያሱ የተናገረው ትንቢት ይገኛል[11]። ሌላም "እነዝኃክሙ በማይ ከመትነጽሑ እምርኩስክሙ፥" ተብሎ አስቀድሞ ተነግሮ ነበርና ያ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ጥምቀት ተመሠረተ[12]።





ነቢዩ ዳዊትም አስቀድሞ "ባሕርኒ ርእየት ወጐየት፥ ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ" ሲል ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ ያሳየው ተአምር የጥምቀትን አመሠራረት መግለጡ ነውና[13]። ይኸ ሁሉ ምሳሌ ይኸ ሁሉ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ፴ ዓመት ሲሞላው በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠመቀ፥ ጥምቀትን ለኛ መሠረተ። ትንቢቱም ምሳሌውም ተፈጽሞ አሁን አማናዊ ጥምቀትን ተጠምቀን ከእግዚአብሔር ተወልደን ጸጋውን አግኝተን እንድንኖር አድሎናል።

፫. <u>የንስሐ ጥምቀት</u>:- መጥምቁ ዮሐንስ የክርስቶስን ጎዳና ለመጥረግ፣ ሕዝቡን ለክርስቶስ ለማዘጋጀት የንስሐ ጥምቀት ለማጥመቅ አስቀድሞ ተልኮ ነበር፥ ስለዚህም ወንጌላዊ ሲመሰክርለት በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለችው አገር ሁሉ መጣ፣ የንስሐ ጥምቀትን ሊሰብክ ለኃጢአት ሥርየትን ሊሰጥ[14]። ዮሐንስ ከዮርዳኖስ ምድረ በዳ ጀምሮ "ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና" እያለ እየሰበከ የንስሐ ጥምቀትም እያጠመቀ ሲመጣ የኢየሩሳሌም የይሁዳም ሕዝብ ሁሉ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ኃጢአቱን እየተናዘዘ ለመጠመቅ ወደርሱ ይሔድ ነበር[15]። የዮሐንስም ጥምቀት የሚባለው ጸጋንና ልጅነትን ለማግኘት የሚረዳ የሚያዘጋጅም፥ ከጥንተ አብሶ ኃጢአት ለመንጻት ሁለተኛ መወለድ የሚቻልበትን ጎዳና ጥርጊያ የሚያደርግ ነበር፥ በአጠቃላይም ለእውነተኛው ጥምቀት ብቻ የሚያዘጋጅ የንስሐ ወይም የመዘጋጃ ጥምቀት ነበር[16]። ዮሐንስ በዚህ መልክ እያጠመቀ ቆይቶ ነበር። ክርስቶስ ሲመጣ ግን ሥራውንም ደቀመዛሙርቱንም ለክርስቶስ አስረከበ[17]። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በዮሐንስ ጥምቀት ዓይነት ሕዝቡን ያዘጋጁ ነበር[18]። ይኸም የንስሐ ጥምቀት ወይም ጥምቀተ ዮሐንስ ይባላል እንጂ ደገኛው ወይም እውነተኛው ጥምቀት ገና አልነበረም።

፬. <u>እውነተኛው ጥምቀት መቼ በማን እንደተመሠረተ</u>:- ጥምቀት አስቀድሞ በምሳሌ ይኑር፥ እንዲሁም ጥምቀተ ዮሐንስን በመሰለው መንገድ ሲፈጸም ይቆይ እንጂ ጸጋ የሚያሰጠው



www.ethiopianorthodox.org

እውነተኛ ጥምቀት የተጀመረው ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ ነው፥ ይኸውም መሥራቹ ራሱ ክርስቶስ ሁኖ ነው:: ጌታም ደቀመዛሙርቱን "ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ስታጠምቋቸውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" ሲል በአወጀ ጊዜ እውነተኛውን ጥምቀት መሥርቷል[19]:: ጸጋ መስጠት መንፈስ ቅዱስ ማደር የጀመረው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የጰንጠቆስጤ ከወረደ ወዲህ ነው[20]:: ስለ እውነተኛው ጥምቀትና ስለ አመሠራረቱ ጌታ ራሱ ሲያስተምር ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ እንደማይችል ተናግሯል[21]:: ራሱም ጌታ ጥምቀትን ለመመሥረት በትምህርት የገለጠውን በሥራ ፈጽሞታል፥ ማለት በውሃ ራሱ ተጠምቋል[22]::

የምሥጢረ ጥምቀት መሥራች ጌታችን ሲሆን ወደ ክርስትና ለመግባት ደግሞ የመጀመሪያው በር ጥምቀት ነው፥ ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ በዚህ በር እንዲያልፍ ግዴታ ነው፥ ማለት ያላመነ ያልተጠመቀ እንደማይድን ጌታ አምላካዊ ቃሉን በግልጥ አስተላልፏል[23]::

፫. <u>ለጥምቀት የሚያስፈልጉ አንቀጾች</u>:- ምሥጢረ ጥምቀትን ለመፈጸም በግድ የተለዩ አንቀጾች መፈጸም አስፈላጊዎች ናቸው:: እነርሱም:-

ሀ. እምነት:- ይኸም በጌታችን በኢየሱስ አምላክነትና የዓለሙም አዳኝ እርሱ ብቻ እንደሆነ በፍጹም ልቦናው ማመንና መቀበል ነው:: እንዲሁም የክርስቲያን እምነት መለያ ወይም መታወቂያና ማኅተም የሆነውን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ማመን ነው:: ይኸን የመሰለው እምነት ለአንድ አማኒ በጣም አስፈላጊው ነው:: ተጠማቂው ሰው በዕድሜ ከፍ ያለ ከሆነ ሲያውቅ የሠራውንም ኃጢአት መናዘዝና የኃጢአት ሥርየትን ማግኘት፥ እንዲሁ ተፈላጊነት ያለው አንቀጽ ነው:: በዚህ መሠረት የሚፈጸመው ጥምቀት ከማንኛውም በደል ያነፃል፥ በቀጥታ ከሥላሴ ለመወለድ ያስችላል "ንስሐ ግቡ ከናንተም ሁሉ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጠመቅ ስለ ኃጢአት ሥርየት የመንፈስ ቅዱስንም ጸጋ ታገኛላችሁ" ሲል ጴጥሮስ ተናግሯልና[24]::





ለ. በሥላሴ ስም መጠመቅ፥ የአብን፥ የወልድን፥ የመንፈስ ቅዱሳን ስም በጠቅላላም የሥላሴን ስም እየጠሩ ማጥመቅ ግዴታ ነው፥ ጌታችን ኢየሱስ "እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ አጥምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም" ሲል ተናግሯል[25]:: የጥንት ክርስቲያኖች ግን በጌታችን በኢየሱስ ስም ብቻ ያጠምቁ ይጠመቁም ነበር፥ ግን ራሱ ጌታችን ያዘዘው በሥላሴ ስም እንድናጠምቅ ስለሆነ ይኸ አንቀጽ መጠበቅ አለበት::

ሐ. ጥምቀት በውሃ መሆን፥የምንጠመቀው ሁል ጊዜ በውሃ ብቻ መሆን አለበት፥ ውሃውም በተፈጥሮው ያለ፥ ምንም ያልተቀላቀለበት ንጹሕ ውሃ መሆን አለበት:: ይኸም ከአስፈላጊዎች አንቀጾች አንደኛው ነው፥ ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብነታችን በውሃ ብቻ ተጠምቋልና:: ሌላውም ሁሉ በውሃ እንዲጠመቅ አዞናል::[26]

እንዲሁ ራሱ ጌታ ሲያስተምር ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ እንደማይችል ገልጦ ተናግሯል[27]:: የኢትዮጵያ ጃንደረባም እነሆ ውሃ ከዚህ አለ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማነው ሲል ፊልጶስን የጠየቀው በውሃ ብቻ መጥመቁን የሚገልጥ ነው፥ ፊልጶስም ለሚያምን ሁሉ ይቻላል ሲለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን አምኖ በውሃ ተጠምቋል[28]:: ሐዋርያት ሁሉ እንዲሁ በውሃ ብቻ ያጠምቁ ነበር[29]:: እንዲሁም የጥንት ክርስቲያኖች በውሀ ብቻ ያጠምቁ ነበር፥ እኛም በውሀ ብቻ እንጠመቃለን እናጠምቃለንም::

መ. በካህን እጅ መጠመቅ፥ የካህኑ ዋና ተግባር ማስተማር ማጥመቅ ነውና:: ጌታችን ሐዋርያትን ዞረው እንዲያስተምሩ እንዲያጠምቁም አዟቸዋልና[30]::

፬. <u>ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ</u>:- የተጠመቀ ብቻ እንደሚድን ጌታ በተናገረው ቃል መሠረት ትልቁም ትንሹም ወንዱም ሴቱም በግድ መጠመቅ አለበት:: "ጌታችን ኢየሱስ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ሲል ባስተማረው



www.ethiopianorthodox.org

አንቀጽ መሠረት ማንኛውም ዕድሜ ያለውን ሁሉ እናጠምቃለን[31]:: የቤተ ክርስቲያናችንም ሕግ "ጥምቀትም የተሠራ ነው ለወንዶችም ለሴቶችም፥ ለትንሾችም ለትልልቆችም ......" ሲል ያስረዳል[32]:: ይኸም የሚያመለክተው የዕድሜ ገደብ፥ የጾታ ወይም የጎሣ ልዩነት ሊኖረው እንደማይገባ ሁሉም መጠመቅ እንዳለበት ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ሕዝብን ሁሉ አጥምቁ አለ እንጂ ትንሹን ብቻ ወይም ትልቁን ብቻ እየለያችሁ አጥምቁ አላለም[33]:: ቅዱሳን ሐዋርያትም የጌታን ትእዛዝ ይዘው ሁሉን ያጠምቁ ነበር፥ ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ የቀርኔሌዎስን ቤተሰብ ሁሉ አጠመቀ[34] ይኸም ማለት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ዕለት ከተወለደ ሕፃን እስከ ፸ ወይም ፹ ከዚያም በላይ ዕድሜ ያላቸው ሊገኙ ይችላሉና:: እንግዲህ ቤተሰብእን ሁሉ አጠመቀ አለ እንጂ ልጆችን ለይቶ ተወ፥ ወይም ሽማግሌዎችን ለይቶ ተወ አይልም ወይም በጾታ ወንዶችን ብቻ ወይም ሴቶችን ብቻ አጠመቀ አላለም::

ቅዱስ ጳውሎስ ለማስተማር እንጂ ለማጥመቅ አለመላኩን ገልጦ ካስረዳ በኋላ የእስጢፋኖስን ቤተሰብእ አጠመቅሁ ይላል[35]:: እንግዲህ ቤተሰብ ሲባል አሁንም ሕፃን፥ ሽማግሌ፥ ወንድ፥ ሴት፥ አገልጋይ፥ ጋሻ ጃግሬ የሚባለውን ሁሉ ይኸንም የመሰለውን ሁሉ ያጠቃልላል፥ ይኸም ከሆነ እኛም ሁሉን ልናጠምቅ ይገባናል፥ ማለት በዕድሜ፥ በማዕረግ፥ በጎሣ፥ ሌላም ይኸን የመሳሰለ ምክንያት በመፍጠር ሰውን ልንለይ ከቶ አይገባንምና ደግሞም አንችልም:: ያልተጠመቀ እንደማይድን በማመን ሕፃናትን በወላጆቻቸው እንዲሁም በክርስትና አባቶቻቸውና እናቶቻቸው አማካይነት እናጠምቃለን፥ እነርሱም ስለ እነርሱ ሆነው የእምነት ኑዛዜውን ይናገራሉ ይመሰክራሉም፥ የእምነት ጸሎትን ይጸልያሉ፥ እንዲሁም ወደፊት ሊያስተምሩ ሊከባከቡም ተያዥነታቸውንም በቤተ ክርስቲያን ፊት ያረጋግጣሉ::

የሕፃናት ጥምቀት በጣም አስፈላጊ ነው፥ ይኸውም በጥንተ አብሶ ከወረሱት ኃጢአት ይነጹ ዘንድ የእግዚአብሔርንም ጸጋ ሁሉ ተሳታፊ መሆን ስለ አለባቸው እንዲያውም ጌታ ሲያስተምር





"ኢየሱስም አለ ሕፃናትን ተው አትከልክሏቸው ወደኔ ይመጡ ዘንድ፥ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና" ይላል[36]:: ይኸም የሚያመለክተው ሕፃናት ናቸው ብለን ከምሥጢራት ሁሉ እንዳንከለክላቸው፥ ከጸጋው እንዳንለያቸው፥ በጠቅላላም ክርስቶስ ለድኅነት ከአዘጋጀው ምሥጢር እንዳናርቃቸው ነው:: እነርሱም የስሙ ቀዳሾች የመንግሥቱ ወራሾች ይሆኑ ዘንድ ክርስቶስ አድኗቸዋልና:: እንዲሁም ስለ ዕምነቱ ብቻ ወላጆች እንዲሁም የክርስትና አባቶችና እናቶች እንዲያስቡበት ሆኖ ስለ ጥምቀቱ ጊዜው ሳያልፍ፥ ምክንያትም ሳይኖር ሕፃናት መጠመቅ አለባቸው:: እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሕፃናት ከተወለዱ በኋላ ወንድ በ፵ ቀን፥ ሴት ደግሞ በ፹ ቀን ጥምቀተ ክርስትናን እንዲቀበሉ ተወስኗል፥ ይኸም ከብሉይ ኪዳን ተያይዞ የመጣውን ትውፊት በመጠበቅ ነው[37]:: ይሁን እንጂ አሁንም ሕፃናትን በሽታ የያዛቸው ሞትም የሚያስጋቸው መሆኑ ከተረዳ በማንኛውም ጊዜ ሊጠመቁ ይገባል፥ ግዴታም ነው:: እንዲያውም ሕፃኑ ሳይጠመቅ ቢሞት በካህኑ ጥፋት እንደሆነ በሥልጣነ ክህነቱ እንዲቀጣ፥ ጥፋቱ የወላጆች የሆነ እንደሆነ ለተወሰነ ጊዜ ከምእመናን አንድነት እንዲለዩ ቅጣት መኖሩን የቤተ ክርስቲያን ሕግ ይወስናል[38]::

፯. <u>የጥምቀት አንድ መሆን</u>:- ጥምቀት በ፵ ቀን በ፵ ዓመት ቢጠመቁትም አንድ ነው:: የጥምቀት ትንሽና ትልቅ የለውም፥ እንዲሁም ጥምቀት አይመለስም አይከለስም ጥምቀት አንዲት ናትና:: ኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን "ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየት ኃጢአት" ሲሉ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን የማይከለስም መሆኑን ያረጋግጣሉ:: ቅዱስ ጳውሎስም እውነተኛው ጥምቀት እውነተኛው እምነት አንድ ብቻ እንደሆነ ሲያስረዳ "አንድ ጌታ አንዲት ሃይማኖትም አንዲት ጥምቀት ......" ሲል ይገልጥልናል[39]::

ጥምቀት የክርስቶስ የሞቱና የመቃብሩ ምሳሌ እንደሆነ ቀደም አድርገን ተናግረናል[40]:: ይኸም ማለት ክርስቶስ እንደገና እንደማይሞት፥ እንደማይቀበር፥ አንድ ጊዜ ብቻ ስለ ሰው ልጅ



www.ethiopianorthodox.org

በሜሮን ይጸናል፥ ማለት አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ይሰጠዋል:: ከዚህ ዕለት ጀምሮ ይኸ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ይኖራል:: ይኸም ሜሮን የተባለ ቅብዓት ከቅብዓ ቅዱስ የተለየ ነው፥ ስለዚህ አንድ ጊዜ ብቻ እንደ ጥምቀት የሚፈጸም የማይደገም ምሥጢር ነው:: በዓይነቱም ፈጽሞ የተለየ ነው፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ልዩ ሽቱነት ካላቸው ዕፅዋት ተቀምሞ ማለት ነጥሮ የሚወጣ ቅባት ሲሆን በፓትርያርክና በሊቃነ ጳጳሳት ልዩ ጸሎት ይባረካል፥ ይከበራል፥ ከዚያ በኋላ ከጥምቀት ቀጥሎ ለአዲስ አማኝ መንፈስ ቅዱስን ለሚቀበል ማረጋገጫ ማኅተም ሆኖ የሚሰጥ ምሥጢር ይሆናል::

፪. <u>የምሥጢረ ሜሮን አመሠራረት</u>:- ምሥጢረ ሜሮንንም በቀጥታ አይሁን እንጂ በተዘዋዋሪ መንገድ የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ እንደሆነ ይታመናል:: ይኸው የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታን የሚያመለክት ስለሆነ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ተስፋውን ጌታ ከማረጉ በፊት እንዲህ ሲል ለደቀ መዛሙርቱ ተናግሯል፥ "እኔም እነሆ የአባቴን ተስፋ እልክላችኋለሁ እላንተ ግን በኢየሩሳሌም ከተማ ተቀመጡ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ ከላይ[1]"::

በዚህ ተስፋ መሠረት ሐዋርያት ሲጠብቁ ደጅም ሲጠኑ የጰንጤቆስጤ ዕለት ተፈጽሟል ማለት ቅዱስ መንፈስ ለሁሉ ተሰጥቷል፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጥምቀት አማካይነት የሚታይ ሆኗልና:: ሜሮን የሚታይ አገልግሎት ሲሆን የማይታይ ጸጋ ደግሞ አለው፥ ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ነው፥ የመንፈስ ማኅተም ሆኖ ሲሰጥ አይታይምና:: በዚህ በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ እንደሚሰጥ እርሱም ምን ዓይነት እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስረዳናል "እግዚአብሔር የሚያጽናናን ከእላንተ ጋር በክርስቶስ ሃይማኖት የቀባንም እርሱ ነው:: እርሱም ደግሞ አተመነ፥ የመንፍሱንም መያዣ በልባችን ሰጠን[2]:: እኛም ሜሮን ለአዲስ ተጠማቂው ስንቀባ መንፈስ ቅዱስን ተቀበል ብለን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን እንደ ተቀበለ ለማረጋገጥ ለማተም ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ ይኸንኑ ግልጥ አድርጎ መስክሮ ተናገረ፥ እንዳገና





በሌላ መልዕክቱ "የእግዚአብሔርንም አዲስ መንፈስን ለመድኃኒት ቀን የታተማችሁበትን አታሳዝኑ" ሲል አስረድቷል[3]:: እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ማኅተም መንፈስ ቅዱስን እንታተማለን ቅብዓ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን፥ በዚህ በሚታየው አገልግሎት የማይታየውን ጸጋ እናገኛለን:: ሐዋርያውና ወንጌላዊው ዮሐንስም በመልዕክቱ ስለዚህ ምሥጢር አመሠራረትና ስለ መንፈስ ቅዱስ ቅባት ይናገራል "እላንተም መቀባት አላችሁ ከቅዱሱ ሁሉንም አውቃችኋል" እንዲሁም በመቀጠል "ከርሱ የወሰዳችኋትም መቀባት በእናንተ ትጸናባችኋለች፥ ማንም ያስተምራችሁ ዘንድ አትሹም እንደዚሁ መቀባት ያስተምራችኋል እንጂ ስለሁሉ እርሱም እውነተኛ ነው፥ ሐሰትም የለበትም እንዳስተማራችሁም ትጸኑበታላችሁ" ሲል ተናግሯል[4]::

፫. <u>የምሥጢረ ሜሮን አገልግሎት መቼ በማን እንደ ተመሠረተ</u>፥ ምሥጢረ ሜሮን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ለማግኘት ለክርስትናው ማኅተም ስለሆነ መዋል ማደር የለበትም ዕለቱን መፈጸም አለበት:: ይኸንም የሚያስረዳ ቅዱሳን ሐዋርያት አዲስ አማንያንን አጥምቀው ወዲያው እጃቸውን ጭነው ሲጸልዩባቸው ቅዱስ መንፈስም ይሰጣቸው ነበር[5]:: ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን የሚገኙትን አማኞች መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ጠየቃቸው እነርሱ ግን እንኳን ልንቀበል መኖሩንም አልሰማን በአሉት ጊዜ አጠመቃቸውና ወዲያውኑ እጁን ጭኖ ጸለየላቸው መንፈስ ቅዱስም አደረባቸው[6]:: በዚህ መሠረት አማኝ ሁሉ እንደተጠመቀ ወዲያውኑ ሜሮን ይቀቡታል ቅዱስ መንፈስ ወርዶ ያድርበታል[7]:: ምሥጢረ ሜሮን በዚህ መልክ ከጥምቀት ቀጥሎ መስጠት ሲገባው በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን እስከ ፲፪ ዓመት እና ከዚያም በላይ ለሆኑ ዓመታት ሕፃናት እንዲቆዩ እንዲጠብቁም ደጅም እንዲጠኑ ይደረጋል፥ ዓላማውም ምሥጢረ ሜሮን ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነቱ፥ ለእግዚአብሔርም ልጅነቱ ማረጋገጫ ስለሆነ ሕፃኑ እስኪያውቅ፥ እስኪ ጠነቀቅም ለመጠበቅ ነው:: ይኸንም ለማስመልከት ምሥጢረ ሜሮን ኮንፈርሜሽን ብለውታል፥ ይኸም ለጥምቀቱ ማረጋገጫ ማኅተመ መንፈስ ቅዱስን



www.ethiopianorthodox.org

ለመቀበሉ አውቆና አምኖ ያድርገው ማለት ነው:: ይኸ አፈጻጸም ግን ለጥምቀት በቂ ያልሆነው ሰው ለሜሮንም በቂ አይደለም፥ ለሜሮንም በቂ ያልሆነው ለጥምቀትም በቂ አይሆንም ያሰኛል እንግዲያውስ በሕፃንነቱ ማጥመቁም በቂ አይደለም ማለት ነው:: ስለዚህ ጥምቀት በማንኛውም ጊዜ ለማንኛውም ሰው አስፈላጊ እንደመሆኑና እንደ መፈጸሙ ምሥጢረ ሜሮንም እንዲሁ ወዲያው ከጥምቀት ያለመለየት መፈጸም ያለበት ምሥጢር ነው::

እንዲሁም ምሥጢረ ሜሮን ከሌሎች ምሥጢራት በመለየት በጳጳሳት ብቻ እንዲፈጸም የሚያደርጉ አሉ፥ በኦርቶዶክሱ ዓለም ግን እንደማንኛውም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ቄስም ይፈጽመዋል:: እጅን ጭኖ በመጸለይና መንፈስ ቅዱስን በመስጠት ፈንታ ደግሞ ሜሮንን በመቀባት እንዲፈጸም ሆኗል:: ስለዚህ አሁን በኦርቶዶክሱ ዓለም ከጥምቀት በኋላ ሜሮንን በመቀባት ብቻ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አድርገው ይፈጽማሉ::

፬. <u>የምሥጢረ ሜሮን ጥቅም</u>:- ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማስገኘት፥ ከመንፈስ ለመወለድ ማረጋገጫ ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ለመሆን ሜሮን ጠቃሚ ይሆናል:: አንድ ሰው በሥጋ መወለዱ ብቻ ጠቃሚ አይሆነውም በግድ ማደግ መጽናት፥ ራስንም መቻል ያስፈልገዋል፤ እንግዲያውስ ጥምቀት ፪ኛ መወለድ ሲሆን ሜሮን መቀባትም ማደግ፥ መጽናት፥ ራስንም መቻል ጸጋ መንፈስ ቅዱስንም ማግኘት ይሆናልና ቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያን ሁሉ በግድ ያስፈልጋል::

ስለዚህ አዲስ አማኙ እንደ ተጠመቀ ወዲያው ምሥጢረ ሜሮን ይፈጸምለታል:: ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ፪ኛ ከመንፈስ ለመወለድ መጠመቅ እንዲሁም ለመጽናት ሜሮን መቀባትና ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ማግኘት አስፈላጊው ነው::





# <u>ም ዕ ራ ፍ ፫</u>

## <u>ምሥጢረ ቁርባን</u>፥

፩. <u>የቃሉ ትርጉም</u>:- ምሥጢረ ቁርባን ማለት የዘለዓለም ሕይወትን ለማግኘት፥ ክርስቶስን መስለን፥ ክርስቶስንም ተዋህደን ለዘለዓለም ሕያዋን ሆነን ለመኖር የሚያስችለን፥ ታላቁ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረተው፥ እርሱ ያስተማረው በመጨረሻም በዕለተ ዓርብ ራሱን መሥዋዕት በማድረግ የፈጸመው ታላቅ ምሥጢር ነው:: ቁርባን ማለት መቅረቢያ መቀራረቢያ መገናኛ ማለት ነው፥ አማንያኑ መሥዋዕት መብዓ ይዘው ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ፥ እግዚአብሔርም ስጦታውን በመቀበል ዋጋም በመክፈል ይቀርባል፥ ስለዚህ መቀራረቢያ መገናኛ ተባለ፥ በተለይ በክርስቲያናዊ አነጋገር ቁርባን ስንል የክርስቶስን ሥጋ በልተን ደሙን ጠጥተን ከእርሱ ጋር ተቀራርበን ለመኖር የሚያበቃ ምሥጢር መሆኑን የሚገልጥ ነው::

፪. ስለ ምሥጢረ ቁርባን በብሉይ ኪዳን የተደረገ ምሳሌ፥ ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን አምሳል መርግፍ እንደሆነ፥ ስለ እውነተኛው ቁርባንና መሥዋዕትም አስቀድሞ ምሳሌ ተመስሎ ትንቢትም ተነግሮ እንደቆየ እንደሚከተለው እንገልጣለን::

ሀ. እሥራኤል በግብጽ በባርነት አገዛዝ ሥር ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ እግዚአብሔር በምሕረቱ ጎበኛቸውና ከግብጽ ባርነት ነፃ የሚወጡበትን፥ ከግብፃውያን መቅሠፍት የሚድኑበትን በግዓ ፍሥሑን እንዲያርዱ፥ ደሙንም መቃኑንና መድረኩን እንዲቀቡ፥ ሥጋውን ደግሞ ጠብሰው እንዲበሉት ተነግሯቸው ነበር:: እሥራኤልም የተሰጠውን መመሪያ በትክክል ፈጽመው ከመቅሠፍት ድነዋል፥ ከግብጻዊያን ባርነትም ነፃ ወጥተዋል[1]:: እንግዲህ ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው በግዓ ፍሥሑ የጌታ ምሳሌ ነው፥ ደሙ ለመቅሠፍት መድኃኒት እንደሆነ ከባርነትም ነፃ ለመውጣት እንደረዳ በክርስቶስ ደም ምእመናን ከዲያብሎስ ሥቃይና አገዛዝ ነፃ ወጥተዋልና:: እሥራኤል ሥጋውን በልተው ከግብጽ እንደወጡ ዛሬም



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ቃል አምነን እንቀበለዋለን እንጂ በዚህ ሁናቴ በዚህም መልክ በዚህም ጊዜ ይለወጣል ብሎ አስረጅ ለመስጠት አይቻልም፥ ምሥጢር ነውና:: በእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ ግብር በካህኑም ጸሎት ይለወጣል መለኮታዊ ሥጋና መለኮታዊ ደም ይሆናል:: ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ንጹሑን ኅብስት በጻሕል፥ ንጹሑንም እውነተኛውን ወይን በጽዋዕ አድርገን እንባርካለን፥ እናከብራለን[17]:: በዚህን ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል፥ ይኸንም የክርስቶስ ቤተሰብእ የሆኑ ምእመናን ያለምንም ልዩነት አምነው ይቀበላሉ የዘለዓለም ሕይወትንም ያገኛሉ:: ይኸንም በየዕለቱ፥ በየሳምንቱ፥ በየወሩ እንደተመቸው ምእመኑ እየደጋገመ ሊቀበለው የሚገባ ነው::

፭. <u>ምሥጢረ ቁርባን መሥዋዕት መሆኑ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ቁርባንን ሲመሠርት መሥዋዕትም መሆኑን ከመግለጥ ጋር ነው፥ እርሱም እንዲህ ይላል፥ ይኸ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሉ በማለት፥ ጽዋዉንም አንሥቶ እንኩ ሁላችሁ ጠጡ፥ ይኸ ደሜ ነውና ለሐዲስ ኪዳን ስለ ብዙዎች ኃጢአትን ለማስተሠርይ የሚሰጥ በማለት አደላቸው:: ይኸም አገላለጥ ሥጋውና ደሙ ቁርባንም መሥዋዕትም መሆኑን በሰፊው የሚያስረዳ ነው:: ቁርባን ማለት ይኸን ሥጋ በልተን ደሙንም ጠጥተን ክርስቶስን ቀርበን እርሱም እኛን ቀርቦን የሚኖር ማለት ነው:: ቁርባን የሚለው የቃሉ ፍች መቅረብን መቀራረብን ያመለክታልና:: መሥዋዕት ማለት ግን ለብዙ ቤዛ ሆኖ መቅረብ ለሌላም ተላልፎ መሞትን ያሳያል:: እንግዲህ ዛሬም ጸሎተ ቅዳሴ ስናደርግ ቁርባንም መሥዋዕትም አድርገን እናቀርባለን ማለት ነው:: የተሠዋውን መሥዋዕት ስንቀበለው ቁርባን ይሆናል ቁርባንም ይባላል:: እንዲሁም ሥጋውን ስንሠዋ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ ለዓለሙ መድኃኒት መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን ይሆናል፤ ማለት ለዓለምም መድኃኒት ይሆናል::

ቅዱስ ጳውሎስም የጌታችንን ትምህርት ተከትሎ የምናቀርበው ምሥጢር ቁርባንም መሥዋዕትም እንደሆነ





በመግለጥ ነው እርሱም እንዲህ ሲል ጽፏል "በአመሰገነም ጊዜ ቆረሰው አለም እንኩ ብሉ ይኸ ነው ሥጋዬ ስለናንተ የሚቆረሰው ....."[18]::

ዛሬም እኛ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርገን አክብረን ለምእመናን በምንሰጥበት ጊዜ ቁርባንም መሥዋዕትም እንደሆን በማመን ነው:: ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሊቀካህናንነቱ እራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል መሥዋዕትም ሆኖ ራሱ በመቅረቡ ደግሞ ቁርባን ሆኗል::

፮. <u>መቼና መቼ መቁረብ እንደሚገባ</u>፥ የጥንት ክርስቲያኖች ዕለተ ዕሑድን የጌታ ዕለት አድርገው የምሥጋና የጸሎትም ዕለት አድርገው ወስነው በዚህች ዕለት ክርስቲያኖች ሁሉ በአንድነት ተገናኝተው የጸሎተ ቅዳሴው ተባባሪ ሆነው፥ የምሥጢረ ቁርባንም ተሣታፊ ይሆኑ ነበር:: በዚህም ዕለት መሥዋዕት ቀርቦ ጸሎተ ቅዳሴው ተፈጽሞ የማይቆርብ ከቶ ክርስቲያን አይባልም ነበር:: እየዋለ እያደረ ክርስትናው እየጸና ክርስቲያኑ እየበዛ ሲሄድ ደግሞ የልዩ ልዩ ቅዱሳንም የዕረፍት ዕለት መታሰቢያው ሲከበር ሌላ ልዩ ልዩ አጋጣሚ እየተፈለገ ጸሎተ ቅዳሴ ሲፈጸም ክርስቲያኑ ሁሉ ይቆርብ ነበር እንጂ ሳምንት ድረስ የሚጠብቅ አልነበረም::

ለዚህ ምሥጢረ ቁርባን መቀበልም ዕድሜ ጾታ አይለይለትም፥ ዕለትና ሰዓት አይወሰንለትም ነበር:: ንስሐውን ፈጽሞ ከጾምና ከጸሎት በኋላ ማንኛውም ክርስቲያን ከቅዱስ ቁርባኑ መቀበል ተገቢው ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ነበር:: አንድ ምዕመን ካመነበትና ከተጠመቀበት ዕለት ጀምሮ በየዕለቱ፥ በየሳምንቱ፥ በየወርኍ፥ ይኸም ባይቻል በየ፫ ወሩ ከቅዱስ ቁርባን መቀበል ነበረበት:: በዓመት አንድ ጊዜ እንኳን የማይቆርብ ግን ክርስትናውን ፈጽሞ የረሳ ከክርስቶስም አንድነት የተለየ ነው ለማለት ይቻላል:: በየጊዜው ከቅዱስ ቁርባን መቀበል እንደሚገባ ክርስቶስ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው" አለ እንጂ "ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ" ብሎ በአንድ ጊዜ ብቻ እንደሚፈጸም አድርጎ አልተናገረም:: ግን ልዩ ልዩ ምክንያት እያደረገን ከክርስቶስ



www.ethiopianorthodox.org

ክህነትን ለማደል በአንብሮተ እድ የሚተላለፍ ጸጋ ነው:: ካህናትን ከብዙ ጸሎት ስእለት በኋላ መምረጥ መሾምም እንዲገባ ራሱ ክርስቶስ ሐዋርያትን ለመምረጥ ሲል ሌሊቱን ሁሉ በጸሎት እንዳደረ ሲነጋም እንደመረጣቸውና እንደሾማቸው ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል[2]:: ከሕዝባዊነት ከተራም ሰውነት ለመለየት ፍጹም የእግዚአብሔር አገልጋይ ይሆን ዘንድ ልዩ ጸሎት ማድረግ በግድ ያስፈልጋል:: ካህናትን በአንብሮተ እድ መሾም እንዲገባ ወዲያው ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታ የተቀበሉትን ሥልጣን ለተተኪዎቻቸው ሲያስተላልፉ እጃቸውን ጭነው በመጸለይ ነው፥ እርሱንም እንዲህ ሲል እናገኛለን "በሐዋርያትም ፊት አቆሟቸው፥ በጸለዩም ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው"[3]:: ሌላም እንዲሁ በየቦታው ይገኛል "እርሳቸውም ለእግዚአብሔር ሲያገለግሉ ሲጾሙም መንፈስ ቅዱስ አለ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ ለጸራኋቸው ሥራ የዚያን ጊዜም ጾሙ ጸለዩም፥ እጃቸውንም በጫኑባቸው ጊዜ ሰደዷቸው"[4]::

ይኸን ሥልጣን ለመቀበል የሚቀርበው እግዚአብሔር የጠራው ለዚህም ትበቃለህ ያለው መሆን አለበት፥ ሰውየውም ራሱን መርምሮ ለዚህ ቅዱስ አገልግሎት ብቁ መሆኑን አመዛዝኖ መግባት አለበት:: ይኸም ሥልጣነ ክህነት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚፈጸም ምሥጢር እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጦታል "አሁንም ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ለመንጋውም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ጠባቆች አድርጎ የሾማችሁ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን"[5]:: ጌታ ራሱ የርሱ ዓይን እንዲሆኑ ሁሉንም በትክክል እንዲመለከቱ ለካህናት ሥልጣኑን ሰጣቸው፥ መዐርገ ክህነትን መሠረተላቸው፥ ስለዚህ ካህናት አእይንተ እግዚአብሔር ይባላሉ:: እንዲሁም ሥጋዊ ሹመት ሳይሆን የራሱን ሥልጣን ስለሰጣቸው ሥልጣነ ክህነት ሥልጣነ እግዚአብሔር ይባላል:: ካህናት የእግዚአብሔር ወኪሎች ወይም እንደራሴዎች ይባላሉ፥ ይኸም ለሕዝቡ በማሰባቸው ስለሕዝቡ በመሥራታቸው ፍጹም ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው ስለሚቀርቡ ነው::





እንግዲህ ክርስቶስ ሥልጣነ ክህነትን ለሐዋርያት ሰጠ። ሐዋርያቱም ደግሞ ለተከታዮቻቸው በአንብሮተ እድ አስተላለፉ። እነዚያም እንዲሁ ለተከታዮቻቸው በአንብሮተ እድ ሲያስተላልፉ የሐዋርያት ውርስ እየወረደ እስከኛ ደርሷል፤ ከዚያም እስከ ምጽአት ይደርሳል::

፫. የካህኑ ተግባር:- ጌታችን ኢየሱስ ሥልጣኑን ለሐዋርያት ሲሰጥ ፫ ኃይል ያለው አድርጎ ሰጥቷቸዋል፥ ይኸውም:-

ሀ. የማስተማር ኃይል ያለው አድርጎ፥ ይኸም የመጀመሪያውን ሥልጣን ለሐዋርያት ሲሰጥ የሰው ነገድ የሆነውን ሁሉ ማስተማርና ማጥመቅ እንደሆነ ከሙታን ከተነሣ በኋላ "እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፥ አጥምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" ሲል ከማንጻት ተግባር ጋር የማስተማር ኃይል ሰጥቷቸዋል:: አሁንም ከካህኑ የሚጠበቀው የመጀመሪያው ኃላፊነት ማስተማር ነው:: ይኸንም ተግባር በስብከት ትምህርት፥ በሞያም ትምህርት፥ ሌላም ይኸን የመሳሰለ ቢሆን ለዚህ ዓለም ብርሃን ሆኖ ዕውቀት የሚገኝበትን ትምህርት ማስተማር ለካህናት የተሰጠ ሀብትና የግዴታ ተግባር ነው:: ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን እስካሁን የትምህርት የዕውቀት መዝገብ ሆና ትገኛለች:: ካህን ሆኖ የማያስተምር አልጫ የሆነ የምድር ጨው ነው፥ በምንም መንገድ ለማጣፈጥ የማይቻል[6]::

ለ. የማንጻት ኃይል፥ ይኸም የማንጻት የመቀደስ ኃይልና ሥልጣን ለካህናት በብዙ መልክ እንዲፈጸም አድርጎ ሰጥቷቸዋል:: ይኸውም ሥጋውንና ደሙን በመስጠት ይፈጽማል "እንጀራም ወስዶ አመስግኖም ቆርሶም ሰጣቸው እንዲህ ሲል ይኸ ሥጋ ነው ስለናንተ የሚሰጠው ይኸንን አድርጉ ለመታሰቢያየ:: ደግሞም እንዲሁ ጽዋውን ከእራት በኋላ እንዲህ ሲል ይኸ ጽዋዕ አዲስ ኪዳን ነው በደሜ ስለናንተ የሚፈስ"[7]:: ስለኃጢአት ሥርየት ስለነፍስም ጽርየት ሁል ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

ሐ. <u>ዲያቆን</u>፥ ይኸ ማዕረግ ስሙ እንደሚያመለክተው የአገልጋይነት የረዳትነት ሥልጣን ያለው እንጂ የመቀደስ ሥልጣን የለውም:: ሐስበክ ማስተማር ጳጳሱን፥ ቄሱን የመላላክ የመርዳት ሥልጣን ስላለው ከነዚህ ከ፫ቱ ማዕርገ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ይቆጠራል:: ስለ ዲቁና ማዕረግ ስለ አገልግሎቱም ቅዱስ መጽሐፍ ሰፋ አድርጎ ጽፎ እናገኘዋለን:: "እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች ይሁኑ በ፪ ቃል የማይናገሩ ለብዙ የወይን ጠጅ የማይጎመጁ ነውረኛ ያልሆኑ ርኩስ ትርፍን የማይወዱ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል[14]"::

፭. <u>የምሥጢረ ክህነት የሚታይ አገልግሎትና የማይታይ ጸጋ</u>፥ እንደ ማንኛውም ምሥጢር ሁሉ ምሥጢረ ክህነትም የሚታይ አገልግሎት የማይታይም ጸጋ አለው:: ይኸውም ተሿሚው ሀብተ ክህነትን ሲሻ በተወሰነለት ቦታ ሆኖ ደጅ ሲጠና፥ ጳጳሱ ሀብተ ክህነትን (ሥልጣን ክህነትን) ለማስተላለፍ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ በተወሰነው ቦታ ላይ ሆኖ ሲጸልይ ይታያል:: በዚህ በሚታይ አገልግሎት ደግሞ የማይታይ ጸጋ ይታደላል፥ ማለት ሥልጣነ ክህነት ከጳጳሱ ወደ ተሿሚው ካህን ሲተላለፍ፤ ሀብተ ክህነትን (ሥልጣነ ክህነትን) ገንዘብ ሲያደርግ አይታይም:: በዚህ በሚታየው የምሥጢር አገልግሎት የማይታየውን ጸጋ የሰው ልጅ ገንዘብ ያደርጋል:: ለዚህ የክህነት ሥልጣን መተላለፍ ዘር፥ ወገን ጎሣ አያስፈልገውም፥ እንዲሁ ከእግዚአብሔር ጥሪ የተሰጠው ለዚህ ማዕረግ ብቁ ሆኖ የቀረበው ሁሉ በሚገባ ጸሎት ተፍጽሞለት፥ አንብሮተ እድ ሲደረግለት ሥልጣነ ክህነትን ያገኛል:: በዚህ መልክ ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ከጌታ አገኙ፥ እነርሱም ደግሞ ለተከታዮቻቸው እያስተላለፉ በመጠበቅ ላይ ይገኛል::

፮. <u>የምሥጢረ ክህነት ጥቅም</u>:- በዚህ በምሥጢረ ክህነት ተራው ሰው በአንብሮተ እድ ተሹሞ ምድራዊ መልአክ ሰማያዊ ሰው ይሆናል:: ካህኑ ምንም ሰው ቢሆን ከሕዝባዊነት ተራ ይወጣል፥ የእግዚአብሔርንም የእንደራሴነት ቦታ ይይዛል::





የማሠርን የመፍታትን ሥልጣን ያገኛል:: ማንኛውም ካህን ሥልጣነ ክህነትን እንደተቀበለ የማንጻትን፥ የማጽናትን፥ የማስተማርን፥ የመምራትን፥ የማስተዳደርን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኛል፥ ገንዘብም ያደርጋል:: እንግዲህ ካህኑ በልብሱ ብቻ ካህን ሳይሆን በመንፈሱም በሥራውም የተለወጠ እውነተኛ የእግዚአብሔር ካህን ሆኖ መገኘት አለበት::

## <u>ም ዕ ራ ፍ ፰</u>

### <u>ምሥጢረ ተክሊል</u>፥

፩. <u>ብሂል</u>:- ምሥጢረ ተክሊል ማለት አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴትም ከአንድ ወንድ ጋር ተስማምተው በነፃ ምርጫቸውና ፈቃዳቸው በሚያደርጉት ጋብቻ ላይ ካህኑ ስምምነታቸውን በማጽናት ስለ አንድነታቸው ከእግዚአብሔርም ዘንድ ጸጋን ያገኙ ዘንድ የሚፈጽመው አገልግሎት የሚያስተላልፈው ጸሎት ነው::

ሀ. ከለለ፥ ጋረደ ብሎ የመጋረድ፥ የማክበር ጸሎት ለማለት ጸሎተ ተክሊል ተብሏል:: ሙሽራውና ሙሽራይቱ አንድ መጎናጸፊያ ለብሰው የአረቦን ክብር ተሰጥቷቸው ጸሎት ይደርስላቸዋልና::

ለ. ተከለለ ተቀዳጀ ዘውድ፥ አክሊል ደፋ የአረቦን ክብር ተቀበለ ለማለት በሙሽራውና በሙሽራይቱ ራስ ላይ የሚደፋውን የአረቦን አክሊል በመመልከት የወጣም ስም ይመስላል:: የምሥጢረ ተክሊል አመሠራረት:- ይህን ቅዱስ ምሥጢር የመሠረተው የሁሉ ፈጣሪ ቅዱስ እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት ጊዜ ነው:: ይኸንም እውነት ሊቀ ነቢያት ሙሴ እንዲህ ሲል ያቀርብልናል "እግዚአብሔርም ሰውን ፈጠረ፥ እግዚአብሔርም ባረካቸው እግዚአብሔርም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፥ ግዟትም:: የባሕሩንም ዓሣ ግዙ የሰማይንም አፍ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውንም እንስሳ ሁሉ ..."[1]::



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር አምላክ ሁለቱን ጾታዎች ባረከ፥ ግንኙነታቸውንም ሕጋዊና የእርሱ ፈቃድ ሆኖ ከነርሱ ግንኙነት የተገኘ ምድርን የሰው ልጅ እንዲሞላ የመጀመሪያውን የተክሊል ቡራኬ እርሱው ፈጸመው። ዛሬም እኛ ለሁለቱ ጾታዎች ማለት ለሙሽራውና ለሙሽራይቱ ግንኙነታቸው ሕጋዊ መባዛታቸውም የአምላክ ፈቃድ እንደሆነ አምነን በዚያን ጊዜ አምላክ ያስተላለፈውን ቡራኬና ጸሎት በማስተላለፍ ተክሊል እናደርስላቸዋለን። እንዲሁም በጸሎት በቡራኬ ሁለትነት ጠፍቶ ባልና ሚስት አንድ እንዲሆኑ፥ እርሱ እርሷን ተከትሎ ወገኑን ትቶ መሄድ እንዳለበት እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ እንዲህ ሲል ተናግሯል "እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት አዳምም አለ አሁን ይኽች አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት ይችም ሴት ትባል ከወንድ ተገኝታለችና፥ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ"[2]። ይኽም ሁሉ ምሥጢረ ተክሊልን ቅዱስ እግዚአብሔር የጀመረው ያዘዘው የመሠረተው መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ጌታችን ኢየሱስም በሐዲስ ኪዳን አጽንቶ በትምህርት መልክ ንግግር በማድረግ በሠርግ ቤትም በመገኘት ጋብቻን ባረከ፤ ምሥጢርነቱንም አጸደቀ፥ ይኽም የ፴ ቀን ጾሙን በመፈጸም በ፫ኛው ቀን በገሊላ ቃና በሠርግ ቤት ተገኝቶ የመጀመሪያውን ተአምራት ገልጧል ጋብቻን ባርኳል[3]። እንዲሁም ለፈተና ፈሪሳውያን ስለ ባልና ሚስት ሕይወት በጠየቁት ጊዜ ማለት ባልና ሚስት መፋታት ወይም አለመፋታት እንደሚገባ በጠየቁት ጊዜ የሰጠው መልስ የመጀመሪያውን የሥነ ፍጥረቱን ዓላማና የጋብቻውን ቃል ኪዳን በመጥቀስ ነው[4]። ነገሩን በማጽናት ባልና ሚስት አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፥ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለይ አይችልም አይገባውም ሲል ተናግሯል[5]። ቅዱስ ጳውሎስም የጋብቻን ክብር፥ ትርጉሙንም ምሳሌውንም በመግለጥ ሙሽራውን በክርስቶስ፥ ሙሽራይቱን በቤተ ክርስቲያን እየመሰለ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ከቶ እንደማይለይ እንዲሁም ባል





ከሚስቱ ሊለይ እንደማይገባ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥቶ አስተምሯል ጽፏልም። በተለይ የምሥጢረ ተክሊልን እውነተኛ ምሥጢርነት ሲናገር "ይኽ ምሥጢር ዐቢይ ነው፥ እኔ ግን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ተናግሬያለሁ" ብሏል[6]። ምሥጢረ ተክሊል በዚህ መልክ የተመሠረተ ከፍተኛ ዓላማ ያለው ቅዱስ እግዚአብሔር ያዘዘው በመሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ የተደረገ የሰው ዘር የሆነ ሁሉ ሊደግፈው ሊፈጽመውም የሚገባ ነው፥ እውነተኛው ጋብቻ የሚሆነውም በዚሁ መልክ የሚፈጸመው አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ ብቻ ሆኖ በተክሊል በቤተ ክርስቲያን ጸሎት የተጋቡት ጋብቻ ነው።

፪. <u>የጋብቻ ዓላማ</u>፡- ጋብቻ በመሠረቱ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይሁን እንጂ የተለያዩ ዓላማዎች አሉት፥ እነርሱም፡-

ሀ. ዘር ለመተካት ምትክም ለማድረግ ነው፥ ቅዱስ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሏት ባለ ጊዜ እንደ ሌሎች እንስሳት በሥነ ፍጥረት ጊዜ ብዙ ወንድ ብዙም ሴት ስላልፈጠረ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ ጸንተው ሕጋዊ ጋብቻ ኑሯቸው በሕጋዊ ግንኙነታቸው ዘር ለመተው፥ ምትክ ለማድረግ እንዲችሉ ያደረገው የመጀመሪያ ዓላማ ነው።

ለ. ለመረዳዳት፥ ባል የውጭውን ሚስት ደግሞ የውስጡን የሚመለከታትንም ሁሉ እርሱም የሚመለከተውን ሁሉ በመፈጸም ተረዳድተው እንዲኖሩ ነው።

ሐ. ፈቃደ ሥጋቸውን ለመፈጸም፥ ማንኛውም ፍጥረት ሁሉ አንድ ጾታ ከሌላው ከአገኘው ጋር ግንኙነት ያደርጋል፥ ሰው ግን የተለየ ክቡር ፍጥረት ስለሆነ ወንዱም የራሱ የግሉ የሆነች ሴት እንድትኖረው፥ ሴቷም የግሏ የሆነ ወንድ ይኖራት ዘንድ ጋብቻ አስፈለገ። እንግዲህ ይኽ ግንኙነት ከሥጋዊ ስሜት የተነሣ ብቻ እንዳይሆን መንፈሳዊም ዓላማ ይኖረው ዘንድ በጸሎትና በቡራኬ በተክሊልም የሚፈጸም ምሥጢር ሆነ።



www.ethiopianorthodox.org

# ክ ፍ ል ፲

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን በጠቅላላው፡፡

## ም ዕ ራ ፍ ፩

## ጠቅላላ የሰው ትንሣኤ፤

ትንሣኤ ማለት ተንሥአ ካለው ከግዕዝ የወጣ ቃል ነው፥ ይኸም በተለይ ሰው ከፈረሰና ከበሰበሰ በኋላ አካል ገዝቶ ሕይወት አግኝቶ ለሚነሣው ትንሣኤ የሚነገር፥ ቃል ነው፡፡ ይኸም ነገር ረቂቅ በመሆኑ በአእምሮም ለመረዳትም ከባድ በመሆኑ ምሥጢር ተብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ማንም ሰው ሙቶ ፈርሶ በስብሶ እንደማይቀር በመጨረሻው ጊዜ እንደሚነሣ የታወቀ ነው ለዚህም አስረጅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሙታን በኩር ሁኖ አስቀድሞ ተነሥቷል፤ ሐዋርያው ጳውሎስም የክርስቶስን ትንሣኤ ለኛ አብነት እንደሆነ አስፋፍቶ ጽፎ እናገኘዋለን[1]፡፡

ከክርስቲያን እምነት ወይም ትምህርት ውስጥ ታላቁና ከፍ ያለው ምዕራፍ የሰው ልጅ ተስፋ የሚሆነው የሚጠባበቀውም የትንሣኤ ሙታን ነገር ነው፥ ምክንያቱም ሰው እንደ እንስሳትና እንደ አራዊት ሁሉ በዚህ ዓለም ብቻ ኑሮ ፈርሶ በስብሶ አመድና ትቢያ ሁኖ የሚቀር ወይም የሚጠፋ ቀላል ፍጥረት አይደለምና፡፡ ከሞተ በኋላ፥ እንደገና አካል ገዝቶ በክብር ወይም በሐሳር ይኖር ዘንድ ፍርድ የሚሰጠው ፍጥረት ነው፡፡ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ገንዘብ አድርጎ፥ የእግዚአብሔርንም ልጅነት አግኝቶ፥ መንግሥቱን ወርሶ የሚኖር፥ ወይም እሳቱ ወደማይጠፋ ትሉ ወደማያንቀላፋ ዘለዓለማዊ ፍዳ ተጥሎ ሲያለቅስ፥ የሚኖር ፍጥረት ነው እንጂ[2]፡፡

ሰውን ከሌላው ፍጥረት ለይቶ ክቡር ፍጥረት የሚያሰኘው መጀመሪያ እግዚአብሔር በአርአያውና በምሳሌው ስለ ፈጠረው፥ የሁሉም ገዥ የሁሉም አስተዳዳሪ ስለ አደረገው ነው[3]፡፡





፪ኛው ደግሞ ከሞተ በኋላ ተነሥቶ ሕይወትን አግኝቶ ልጅነትን ገንዘብ አድርጎ ለዘለዓለም እንዲኖር በቸርነቱ ያደለው ስለሆነ ነው፡፡ ሁላችን እንደምንረዳው ይኸ ዕድል ለማንኛውም ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ሁሉ ከቶ አልተሰጠውም፥ ነገር ግን አሁን ያለንበት ዓለም ወይም ይኸ አሁን ያለን ሕይወት እንደ ጥላ ወይም እንደምሳሌ ያለ ተለዋዋጭ ወይም ተሎ የሚያልፍ የሚጠፋ ያልተደላደለ ውጤቱም ያልታወቀለት ሕይወት ስለሆነ፥ ኑሯችን በዳበሳ ወይም በጥርጥር እንደሚገኝ ነው፥ ተስፋችንና ምኞታችን ሁሉ ወደፊት በምትመጣው ዘለዓለማዊ ሕይወት ብቻ የተደገፈ ነው፥ ስለዚህም ሃይማኖታቸው የቀና ሊቃውንት "ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለም ዓለም" ሲሉ ተስፋችን ምኞታችን የሙታን መነሣትንና የሚመጣውን ሕይወትም እንደሆነ አረጋግጠው መስክረዋል[4]፡፡

ነገር ግን የምትመጣዋ ዘለዓለማዊት ሕይወት ከዛሬው ሕይወታችን ጋር የተያያዘችና የተደገፈች ናት፥ ማለት ማንኛውም ሰው እንደ እውነተኛ ክርስቲያንነቱ በጎ አድራጎትን በመፈጸም ቅዱስ ስሙን በመጥራት ሕጉንም በመጠበቅ የኖረ እንደሆነ፥ ለምትመጣው ዘለዓለማዊ ሕይወት ተባባሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ልዑል እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለከንቱ አልፈጠረውም፥ ስሙን ቀድሶ ክብሩን እንዲወርስ አደለው እንጂ፥ ለዚህም ዓላማ ፈጠረው እንጂ፥ ስለዚህ ለሚወዱቸውና ቅዱስ ፈቃዱን ለሚፈጽሙ ሁሉ አስቀድሞ የሕይወትን የዕረፍትን ቦታ እንደ አዘጋጀ ለማጠየቁ "ኑ እናንተ የአባቴ ቡሩካን የሰማይ መንግሥትን ትወርሱ ዘንድ ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጀላችሁን" ሲል ክርስቶስ በኋላ ጊዜ እንደሚጠራቸው አስቀድሞ አስተምሯል[5]፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም ይኸን አምላካዊ ቃል በመመርኮዝ "ዓይን ያላየው ነው፥ ጆሮም ያልሰማው ነው በሰው ሕሊናም ያልታሰበ ነው እግዚአብሔር ለሚወዱቸው ያዘጋጀው"[6]፡፡ ሲል ልዑል እግዚአብሔር ለሰው ልጅ አስቀድሞ ያዘጋጀለትን በኋለኛው ዘመን የምትመጣውን ሕይወት መስል የሌላት



www.ethiopianorthodox.org

ሕፃናት ጎልምሰው አረጋውያን ታድሰው ወፍራም ቀጭን፥ ረጅም አጭር የሚባል ሳይኖር ሁሉም ትክክል ሆነው ይነሣሉ::

ልዑል እግዚአብሔር ኃያል ስለሆነ፥ ሁሉንም ለማድረግ ስለሚችል ለማስነሣት ከቶ አቅቶት የሚቀር ነገር የለም፥ ልዑል እግዚአብሔር ሲፈጥር ቾል ያላላቸውን ሰዎች በትንሣኤው ጊዜ ቾል አይላቸውም፥ ሲፈጥር ያልረሳቸውን ሰዎች በትንሣኤው ጊዜ አይረሳቸውም፥ ሲፈጥር ያልናቃቸውን ሰዎች በማስነሣትም ጊዜ አይንቃቸውም፥ ስለዚህ የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ አውሬ የበላው ውሀ የወሰደው በእሳት የተቃጠለው፥ በሥርዓት የተቀበረው እንዲሁም ወድቆ የቀረው ቀድሞ የተቀበረው፥ አሁንም የተቀበረው በትክክል ይነሣል::[4] እያንዳንዱ መጽሐፈ ዕዳውን ይዞ ወደ ፈጣሪው ይቀርባል፥ የትንሣኤውም ዋና ዓላማ ይኸ ነው፥ የሰው ልጅ ዋጋውን ያገኝ ዘንድ የክርስቶስም አቺናፊነት ዋጋም ከፋይነት ይገለጥ ዘንድ::[5] ይህ የትንሣኤ ሙታን ነገር ትልቅ ምሥጢር እውነተኛውም ትምህርት ነው፥ ቅዱስ ጳውሎስም "እነሆ በምሥጢር እነግራችኋለሁ እኛ ሁላችን እንድንተኛ ግን ሁላችን እንለወጣለን ሲል ገልጦልናል::[6] ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ አካሉን ክሶ ደሙን አፍስሶ አድኖን ነበር፥ ግን ቀድሞ ሲመጣ በሕፃን መልክ በዝቅተኛ ማዕረግ ነበር፥ ፪ኛ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ በእርሱ አምነው የሞቱትን ዋጋ ይከፍላል፥ የቅዱሳንን አንድነት ከርሱ ጋር ያደርጋል፤ ግን በግርማ በኃይል ይመጣል፥ ነፍስን ከሥጋ ሥጋን ደግሞ ከአጥንት የሚለይ ድምፅ ያሰማል፥ የሰው ዋጋ በዚያን ጊዜ ይከፈላል፥ ሰው የመሆን ዕድል በዚያን ጊዜ ይታወቃል፥ ሌላውን ፍጥረት እኛ ሰዎች የምንበልጠው በዚያን ጊዜ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል፥ እኛም ራሳችን የምናጽናናው ፍጹም ዋጋችንን በምናገኝበት በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ነው፥ በትንሣኤም ጊዜ ሳይሞቱ እንዳሉ ወደ ሕይወት የሚለወጡ እንዳሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ተስማምተዋል፥ ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ "ንሕነ ንትዌለጥ ለምእር ከመ ቅጽበተ ዓይን" ብሏል::[7]





እንዲሁም "ንሕነ ሕያዋን ኢንበጽሆሙ ለምውታን" ሲል ተናግሯል::[8] ሠለስቱ ምእት ሊቃውንትም "ይኮንን ሕያዋን ወሙታነ" ሲሉ መስክረዋል::[9] ይኸንንም ሊቃውንት ፪ ዓይነት አስተያየት ይሰጡታል፥ ፩ኛ የትንሣኤውን ዓይነት የሐሳር እና የክብር በማድረግ ሕያዋንና ሙታን አሉ እንጂ ሁሉም ይሞታሉ፥ ይለወጣሉ፥ በኋላም ይነሣሉ የሚል ነው:: ሌላውም ደግሞ ቀጥተኛውን ንባብ ቀጥተኛውንም ስሜት በመከተል ጌታ ሲመጣ ሳይሞቱ በቀጥታ ሕያዋን ሁነው ቆይተው የሚለወጡ ወደ ሕይወት ጎዳናም የሚሸጋገሩ አሉ ብለው ያምናሉ፥ ይኸንም ይከተላሉ::

## ም ዕ ራ ፍ ፲

## ም ሥ ጢ ረ ም ጽ አ ት፤

ክርስቶስ ካስተማራቸው ቀዋሚ ትምህርቶች አንደኛው የእርሱ ፪ኛ ጊዜ ወደዚህ ዓለም መምጣት ነው:: እኛም ሁሉ አልፎ ትንቢቱ ሁሉ ተፈጽሞ ገና የምንጠብቀው የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም ለ፪ኛ ጊዜ መምጣትን ነው:: ይኸ ትምህርት እርግጠኛና ቀዋሚ መሆኑን ጌታ ራሱ በተለያዩ ጊዜያቶችና አጋጣሚዎች እየመላለሰ ተናግሯል::[1]

ቅዱሳን መላእክትም ይኸ ምሥጢር ተገልጦላቸው ለቅዱሳን ሐዋርያት እንዲህ ሲሉ ገልጠው ተናግረዋል:: "የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደሰማይ እየተመለከታችሁ ለምን ቆማችኋል? ይኸ ከናንተ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል"[2]:: ከዚህም የተነሣ ቅዱሳን ሐዋርያት የጌታን ፪ኛ መምጣት በየግል መጽሐፋቸው ገልጠው ጽፈውት እናገኛለን:: ይሁዳ የጌታ ወንድም የሚባለው ስለክርስቶስ ፪ኛ መምጣት ገልጦ ጽፏል[3]:: ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእም የራሱን ምሥክርነት በመስጠት ጽፎ እናገኘዋለን[4]:: ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲሁ በሰፊው ገልጦ ጽፎ እናገኘዋለን[5]:: ቅዱስ ጳውሎስ በተለያዩ መልዕክቶቹ ሰፋ አድርጎ ጽፎ እናገኘዋለን::[6]



www.ethiopianorthodox.org

፮ኛ ፍርዱ የሚሰጠው በጠቅላላ የሰው ልጅ ለሆነው ሁሉ ነው፥ ለክፎችም ለደጎችም፥ ለሕያዋንም ለሙታንም:: ይኸንንም በመከተል ሃይማኖታቸው የቀና አባቶች "ይኮንን ሕያዋነ ወሙታነ" ሲሉ ተናግረዋል::[11] እንዲያውም ከሰው አልፎ በወደቁ መላእክት ላይም የመጨረሻ ፍርድ እንደሚፈረድባቸው ቅዱስ ጴጥሮስ "እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደገሀነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ከሰጣቸው..." ሲል ገልጦ ጽፎልናል::[12]

፯ኛ ፍርድ አሰጣጡ በግልጥ በትክክል መሆኑ፥ ጌታ በባሕርይ ክብሩ፥ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ለፍርድ ሲመጣ በግልጥ ለሁሉ ይፈርዳል፥ ዋጋንም ይከፍላል::

፰ኛ ቀጥተኛ እውነተኛ ፍርድ መስጠት፥ የመጨረሻ ፍድር የሚሰጥባት ያች ዕለት ዕለተ ፍዳ፥ ዕለተ ኩነኔ ትባላለች::[13] ምክንያቱም ሁሉም እንደሥራው ይፈረድ ለታልና::

፱ኛ ፍርዱ የመጨረሻና ዘለዓለማዊ መሆኑ፥ ሰው ሁሉ ይፈረድለታል፥ ይፈረድበትማል:: ጻድቃን የዘለዓለማዊ ሕይወትን ሽልማትን ቡራኬን ያገኛሉ፥ እንዲሁም ኃጥአን የዘለዓለም ሥቃይን ፍዳን ያገኛሉ:: "ንዑ ኀቤዬ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት ዘድልው ለክሙ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም" ብሎ ለጻድቃን በክቡር መንግሥቱን ያወርሳቸዋል:: በዚህም አንፃር ኃጥአንን "ሑሩ እምኔዬ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም ዘድልው ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ" ሲል ያሰናብታቸዋል::[14] ይኸ ኃጥአን ለመጨረሻ ጊዜ የሚገቡበት የሥቃይ ቦታ ገሃነም፥ ወይም ገሃነም እሳት ተብሎ ይጠራል:: ገሃነም የተባለበትም በዚህ በምድራዊው ዓለም ከኢየሩሳሌም ውጭ በሄኖን ሸለቆ ውስጥ ያለ ሁል ጊዜ እሳት ሲነድበት የሚኖረውን ቦታ ምሳሌ በማድረግ ነው:: ይኸ ቦታ ቀድሞ ሰው እንዲሞት ሲፈረድበት በሚገደልበት፥ ቆሻሻው ሁሉ የሚጣልበት በሽታም እንዳያመጣ በእሳት





የሚቃጠልበት ቦታ ነበር፥ ስለዚህ እሳቱ ከዓመት እስከ ዓመት የማይጠፋበት ቦታ ነበር ይኸም ገኸነም ከእርሱ ምሳሌ ተወስዶ የተነገረለት እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋ ብዙ ሥቃይ የሚታይበት ቦታ መሆኑን ያመለክታል::

ይኸ ገሃነም የተባለው ቦታ የሥቃይ የመከራ ቦታ መሆኑን ጌታ ሲያስተምር ገልጦ ተናግሯል "እጅህ ብታሰናክልህ ቁረጣት፥ ሁለት እጅ ኑሮህ ትላቸው ወደማይሞትባት፥ እሳቱ ወደማይጠፋበት ወደገሃነም ከመሔድ ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል" ሲል ገልጦ ተናግሯል::[15] ይኸን በመሰለ መልክ በተለያየ ቦታ ጌታ ገልጦ ተናግሮት እናገኘዋለን::[16] ዮሐንስ ወንጌላዊም በራእዩ ኃጥአን የሚገቡበትን ቦታ የእሳት ሓይቅ ብሎ ጠርቶት እናገኛለን::[17] የሥቃዩን ጽናት ለማጠየቅ ጌታ ትሉ ወደማይሞትበት እሳቱ ወደማይጠፋበት ሲል ተናገረ እንጂ በቀጥታ ትሉ የማይሞት፥ እሳቱ የማይጠፋ ሁኖ አይደለም፥ እሳቱም ይኸ የእኛ መጠቀሚያ እሳት አይደለም እግዚአብሔር ባወቀ የተናገረው ነው::

ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው ሊቅ በብዙ ቦታ ስለ ገሃነም የተነገሩትን ከተመለከተ በኋላ የግል አስተያየቱን እንዲህ ሲል ይሰጣል፥ እግዚአብሔር መሐሪ አምላክ ነው፥ ሰውን ለዘለዓለም በማይጠፋ እሳት ሲቀጣው አይኖርም:: ነገር ግን ክፉዎች ከእግዚአብሔር የክብር መንግሥት ይለያሉ፥ ይኸ መለየት ከእሳት የበለጠ ያቃጥላቸዋል፥ ያንገበግባቸዋል ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል::[18] ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ፊት መራቅ መቸም ቢሆን የማይፈጸም ጸጸት ኀዘን ነው::፥ እርሱ ራሱ ከገሃነም የበለጠ ያቃጥላል::

ይኸን የፍርድ ሁኔታ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት በሌላ መልኩ እንዲህ ሲል ይገልጠዋል፥ "ትንሣኤ ሙታን በጠቅላላው መሆኑ ትክክል ነው ጠቅላላ ፍርድም ለሰው ልጅ ሁሉ መስጠት ትክክል ነው፥ ግን እንደሽልማት እንደመልካም ሥጦታ ሁኖ ለጻድቃን የሚቀርብላቸው ብርሃን ነው፥ ብርሃንን ይለብሳሉ፥ በብርሃን ይጎናጸፋሉ፥ ሁሉም ብሩህ ሁኖላቸው ሁሉንም



www.ethiopianorthodox.org

የሚመለከት የማወቅ ኃይል ይኖራቸዋል፥ ስለዚህ አምላክንም እንደ አምላክነቱ የማየትም የማወቅ ኃይል ይኖራቸዋል:: ለኃጥአን ደግሞ ጨለማ ዕድል ፈንታቸው ይሆናል፥ አለማየት አለማወቅ ነው፥ ስለዚህ ለእግዚአብሔር መንግሥት መለየት እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ አለማወቅ የዘለዓለም ጸጸት የዘለዓለም ሞት ነው" ብሏል::[19]

ለእግዚአብሔር ምሕረት ወሰንና ደንበር ልናደርግለት አንችልም፥ ሥጦታውን ልንቀንስ፥ ወይም ልንጨምር አንችልም:: ምናልባት ቅዱስ ጳውሎስ ለሚወደው ልጁ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልዕክቱ እንደገለጠው ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ እርሱን የማወቅ ኃይል ይሰጣቸዋል ከዚህም የተነሣ ይድናሉ:: እርሱም እንዲህ ሲል ይገልጥልናል "ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር፥ በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይኸ ነው"::[20] ሁኖም ሰው የተባለው ሁሉን ለማድረግ የሚችል ፍጥረት ነው፥ ስለዚህ በራሱ ነፃ ምርጫ በእምቢተኝነቱ የእግዚአብሔርን ምሕረት ንቆ ቢወጣ ምርጫው የራሱ ነው፥ ስለዚህ ኩነኔ ቢፈረድበት ራሱ እንጂ እግዚአብሔር አልፈረደበትም ማለት ነው:: ይኸንንም እውነት የሚያረጋግጥ ቃል ጌታ ለጻድቃን መንግሥተ ሰማያትን ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ ያዘጋጀ ሲሆን ለኃጥአን የሚሆን ቦታ እንዳላዘጋጀ የታወቀ ነው፥ ግን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ሂዱ እንደሚላቸው ተናገረ እንጂ:: ለኃጢአተኞች ወደተዘጋጀው ቦታ ሂዱ የሚል ጽሑፍ የለም፥ ይኸም የሚያመለክተው ሰዎች በክፉ ተግባራቸው ሰይጣን የሆኑ፥ ወይም ሰይጣንን የመሰሉ በመሆናቸው ሰይጣናዊ ግብርንም ሲፈጽሙ በመቆየታቸው በራሳቸው ነፃ ምርጫ ከሰይጣን ጋር በመተባበራቸ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ቦታ እንዲገቡ ይፈረድባቸዋል::[21]

እግዚአብሔር አምላክ ለኃጢአተኛ መቅጫ ቦታ ሳያዘጋጅ ሰው ወዶ በሠራው ሰይጣን ሁኖ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል፤ ያስቆጣዋል፥ ስለዚህም ወደ ሰይጣን መቅጫ ቦታ እንዲገባ ያደርገዋል:: ስለዚህም አገላለጥ ነቢዩ ዳዊት "ኃጢአተኛ





ስለምን እግዚአብሔርን አስቆጣው? በልቡ አይመራመረኝም ይላልና" ሲል ያስረዳል::[22]

ለኛ ለሰዎች በግል የተዘጋጀልን ቦታ የዘለዓለም ደስታ ያለበት የዕረፍት ቦታ መንግሥተ ሰማያት ነው፥ ሁሉም ወደዚህ ለመግባት መጣጣር የግሉ ምርጫ ነው፥ ግን በራሱ ምርጫ ገሃነመ እሳት ቢገባ የእግዚአብሔርን ጨካኝነት አያሳይም::

## ም ዕ ራ ፍ ፳

## ዘለዓለማዊ መንግሥት፤

በመጨረሻ ጊዜ በጠቅላላው ዓለሙ ይለወጣል፥ አሁን ያለው ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ይጠፋሉ፥ የተሻለ ሌላ ሕይወት ይመጣል፥ በአለፉት ሰማይና ምድር እግር አዲስ ሰማይ አዲስ ምድር ይተካል::[1] ይኸም የእግዚአብሔር መንግሥት የክብር መንግሥት ወይም መንግሥተ ሰማያት ይባላል::

ይኸ ጊዜያዊ ወይም ምድራዊ መንግሥት ያልፋል፥ ይጠፋል፥ ምድራዊቲቱ ወይም ሰልፈኛዋ ቤተ ክርስቲያን ታልፋለች፥ በእርሷ እግር ሰማያዊቲቱ ቤተ ክርስቲያን ትተካለች:: ምድራዊው ነገር ሁሉ አልፎ ሌላ አዲስ እንደሚተካ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ እንዲህ ይላል" ... በኋላ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንንም ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናልና:: ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና:: የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፥ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና:: ነገር ግን ሁሉ ተገዝቷል ሲል ሁሉን ከአስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው:: ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ለአስገዛለት ይገዛል"::[2] ከዚህ ላይ ወልድ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል፥ ማለት ወልድን ለማሳነስ፥ ወይም የፍጡርነት ጠባይን ለማሳየት፥ አይደለም፥ ነገር ግን ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ተልዕኮ እንዲፈጽም ለመጠ



www.ethiopianorthodox.org

# የጥቅሶች ዝርዝር

## መቅድም

1. በብሉይ ኪዳን ዳንኤል 2፡ 13÷ 6፡ 8-9÷ በሐዲስ ኪዳንም ሉቃ፡ 2፡1÷ የሐ. ሥራ 17፡7፤ ኤፌ 2፡15፡፡

## መግቢያ

1. ፩ ቆሮ. 2፡12፡፡

## ክፍል ፩ ስለእግዚአብሔር መኖር በጠቅላላው÷

### ምዕራፍ ፩ የእግዚአብሔር ህልውና፣

1. ዮሐ. 1፡3፡፡
2. ዮሐ. 1፡18÷ ፩ኛ ዮሐ. 4፡12፡፡
3. ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቅዳሴ ቁጥር 5፡፡
4. የጼፋንዮስ ቅዳሴ ቁጥር 6፡፡
5. ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቅዳሴ ቁጥር 8፡፡
6. ሮሜ 1፡ 19-20፡፡
7. መዝ. 49፡20፡፡
8. ርቱዐ ሃይማኖት ድርሳን ዘስብከት፡፡
9. ሮሜ 1፡ 19-20፡፡
10. ዘፍጥ.12፡ 1-8፡፡
11. ፩ኛ ቆሮ. 2፡ 10፡፡
12. ቅዳሴ ዘ፫ቱ ፻ ቁጥ.21፡፡
13. ዮሐ. 4፡24፡፡
14. ፩ኛ ቆሮ. 1፡ 18፡፡





### ምዕራፍ ፪ ስለ እግዚአብሔር መኖር ÷

1. መዝ. 14፡ 1፡፡
2. " 18፡ 1፡፡
3. ሮሜ. 1፡ 20፡፡
4. ዮሐ. 1፡ 1-3÷ የሐ. ሥራ 17፡ 23÷ ፀሎተ ሃይማኖት፡፡
5. ዘፍ. 1፡ 31÷ ሮሜ. 14፡14÷ ፩ኛ ጢሞ. 4፡ 4፡፡
6. መዝ. 104፡ 24፡፡
7. ዮሐ. 1፡ 1-3፡፡
8. ማቴ. 7፡ 17፡፡
9. ዮሐ. 11፡ 25፡፡
10. ማቴ. 15፡ 14

### ምዕራፍ ፫ የእግዚአብሔር አንድነት÷

1. ዘዳግ. 4፡ 35፡፡
2. ዘጸአ. 20፡ 2-3፡፡
3. ዘዳግ. 6፡ 4፡፡
4. ኢሳይ. 44፡ 6÷ 43፡ 10-11÷ 45፡ 5፡፡
5. ኢሳይ. 44፡ 6፡፡
6. ፩ኛ ቆሮ. 8፡ 4-6፡፡
7. ፩ኛ ጢሞ. 2፡ 5፡፡
8. ማር. 10፡ 18፡፡
9. ጸሎተ ሃይማኖት፡፡
10. አመንክዮ ዘሐዋርያት፡፡
11. ዘፍጥ. 2፡ 24፡፡
12. " 11፡ 6፡፡



www.ethiopianorthodox.org

13. ማቴ. 6፡ 9።
14. ኢሳ. 6፡ 8።
15. ዘካርያስ 2፡ 10-11።
16. ዮሐ. 1፡ 1።
17. ማቴ. 3፡ 16-17፥ ምዕ. 26፡ 63-64፥ 2ኛ ቆሮ. 13፡13።
18. ዮሐ. 14፡ 16።
19. ማር. 1፡ 10-11፥ ማቴ. 3፡ 16።
20. ማቴ. 28፡ 19።
21. ዘፍጥ. 1፡ 26።
22. መዝ. 34፡ 16-17።
23. ዮሐ. 1፡ 18።
24. ዘፍጥ. 33፡ 19-20።
25. ዮሐ. 4፡ 24፥ ሉቃ. 24፡ 38-39።
26. ቅዳሴ ማርያም።
27. ርቱዐ ሃይማኖት ዘኛወ፬ቱ።
28. ማቴ. 3፡ 17።
29. ዘጸአ. 33፡ 19-20።
30. ኢሳይ. 6፡ 1።
31. ዳንኤል 10፡ 5።
32. ራእይ 4፡ 2-3፥ ኢሳ. 6፡ 1።

## ምዕራፍ ፬ የእግዚአብሔር ባሕርይ መግለጫዎች፥

1. ፩ኛ ቆሮ. 13፡ 12።
2. ፩ኛ ዮሐንስ 4፡ 24።
3. ኢሳ. 40፡ 18።
4. ኤርም. 23፡ 23-24።





5. መዝ. 24፡ 1።
6. የሐዋ. ሥራ 17፡ 24-28።
7. መዝ. 139፡ 7-10።
8. የሐ. ሥራ 17፡ 24-28።
9. ማቴ. 6፡ 9፥ ፩ኛ ጢሞ. 6፡ 16።
10. መዝ. 115፡ 3።
11. " 148፡ 5።
12. ዘፍጥ. 18፡ 14።
13. ኢዮብ 42፡ 2።
14. ሉቃ. 1፡ 37።
15. ማቴ. 19፡ 26።
16. ኤርም. 32፡ 17።
17. ኢሳ. 59፡ 1-9።
18. ወልደ ነጎድጓድ ቅዳሴ።
19. መዝ. 90፡ 2-30።
20. ኢዮብ. 36፡ 26-28።
21. መዝ. 102፡ 12።
22. ኢሳይ. 40፡ 28።
23. ራእይ 22፡ 13-17።
24. መዝ. 90፡ 2።
25. መዝ. 102፡ 25-27፥ ዕብራ. 1፡ 10-12።
26. መዝ. 145፡ 13።
27. ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ።
28. ኢሳይ. 40፡ 28።
29. ያዕቆብ 1፡ 17።



www.ethiopianorthodox.org

30. ዘፍጥ. 21፡ 33፡፡
31. ፪ኛ ጴጥ. 3፡ 8፡፡
32. ዕብራ. 4፡ 13፡፡
33. ፩ኛ ዮሐ. 3፡ 20፡፡
34. መዝ. 139፡ 3-4፡፡
35. መጽሐፈ ምሳሌ 15፡ 3
36. መዝ. 147፡ 5፡፡
37. ምሳሌ 16፡ 3፡፡
38. መዝ. 147፡ 4፡፡
39. መዝ. 147፡ 4፡፡
40. መዝ. 139፡ 1-3፡፡
41. ሮሜ. 11፡ 33፡፡
42. መዝ. 104፡ 24፡፡
43. ቅዳሴ ማርያም፡፡
44. ኢሳ. 6፡ 3፡፡
45. ራእይ 4፡ 8፡፡
46. ኢያሱ 24፡ 19፡፡
47. መዝ. 99፡ 5፡፡
48. " 145፡ 17፡፡
49. ዘሌዋ. 19፡ 2÷ ፩ኛ ጴጥ. 1፡ 16፡፡
50. ማር. ይስሐቅ፡፡
51. ዮሐ. 8፡ 46፡፡
52. ዮሐ. 4፡ 24፡፡
53. ሉቃ. 24፡ 39፡፡
54. ቆላስ. 3፡ 10፡፡





55. ኤፌ. 4፡ 23-24፡፡
56. ዮሐ. 1፡ 32÷ ዮሐ. ሥራ 2፡ 4፡፡
57. " 1፡ 18፡፡
58. ዘጸአ. 33፡ 19-20፡፡
59. ዘፍ. 16፡ 7-10, 13÷ ም. 21፡ 17-18
60. ኢሳ. 6፡ 1÷ መሳፍ. 2፡ 1-2፡፡
61. ዘፍ. 18፡ 17-20፡፡
62. መዝ. 145፡ 17÷ 116፡ 5፡፡
63. ዮሐ. 17፡ 25፡፡
64. ዮሐ. 8፡ 31፡፡
65. ራእይ 16፡ 5-6፡፡
66. ፪ኛ ጢሞ. 4፡ 10፡፡
67. መዝ. 103፡ 1፡፡
68. ዘዳግ. 4፡ 31፡፡
69. መዝ. 62፡ 12÷ መዝ. 145፡ 8÷ 86፡15፡፡
70. ሮሜ. 9፡ 15፡፡
71. ሉቃስ 1፡ 4፡፡
72. ዘዳግ. 7፡ 9፡፡
73. መዝ. 106
74. " 27፡ 15፡፡
75. ዘዳግ. 32፡ 4፡፡
76. ዘኁል. 23፡ 19፡፡
77. ፩ኛ ቆሮ. 10፡ 13፡፡
78. ፩ኛ ተሰሎ. 5፡ 24፡፡
79. ማቴ. 24፡ 35፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፪ ቅዱስ ትውፊት፤

1. ዮሐ. 16፡ 17።
2. ሉቃስ 1፡ 1።
3. ፪ኛ ጢሞ. 13፡ 14።
4. ፩ኛ ቆሮ. 11፡ 2።
5. ዮሐ. 20፡ 30-31።
6. ዮሐ. 21፡ 25።
7. ፪ኛ ዮሐ. ቁጥር 12።
8. ፩ኛ ተሰሎ. 2፡ 15።
9. ፪ኛ ተሰሎ. 3፡ 6።
10. ማቴ. 15፡ 3።
11. ማቴ. 15፡ 6።

## ክፍል ፫ ምሥጢረ ሥላሴ በጠቅላላው፤

## ምዕራፍ ፩ እግዚአብሔር በሥላሴነቱ፥

1. ማቴ. 3፡ 17።
2. ዘፍጥ. 1፡ 26
3. ዘፍጥ. 3፡ 22።
4. ዘፍጥ. 11፡ 7።
5. ፪ኛ ቆሮን. 3፡ 15።
6. ማቴ. 22፡ 32፥ ዘጸ. 3፡ 15-16።
7. ዘኁል. 6፡ 25-26።
8. መዝ. 147፡ 5።
9. መዝ. 33፡ 5-6።





10. ኢሳ. 6፡ 3-4።
11. ዘፍ. 18፡ 2-22።
12. ማቴ. 11፡ 27።
13. ማቴ. 3፡ 16-17።
14. ማቴ. 17፡ 5።
15. ፩ኛ ጴጥ. 1፡ 2።
16. ማቴ. 28፡ 12።
17. ፩ኛ ዮሐ. 5፡ 7።
18. ፪ኛ ቆሮ. 13፡ 13።
19. መጽሐፈ ባሕርይ አንቀጽ 1።
20. ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ (ሃይማኖት አበው)።
21. መጽሐፈ ባሕርይ ድርሳን ቀዳማዊ በእንተ ፍካሬ ፫ቱ ሕላዊያት።
22. ባስልዮስ ዘቂሳርያ (ሃይማኖት አበው)።
23. ሲንዮትስ ክፍል 1።
24. ቆዝሞስ ኀበ ባስልዮስ
25. ዘፍጥ. 1፡ 1።
26. መጽሐፈ ምሳሌ 8፡ 30፥ ዮሐ. 1፡ 1-3፥ ዕብራ. 1፡ 3፥
    ቆላስ. 1፡ 16፥ መዝ. 33፡ 6።
27. ኢዮ. 33፡ 4፥ መዝ. 33፡ 6።
28. ዘፍጥ. 1፡ 1።
29. አግናጥዮስ ክፍል 1 (ሃይማኖተ አበው)።
30. ቄርሎስ።
31. ማቴ. 28፡ 19።
32. ሃይማኖተ አበው ሕንፃ መነኮሳት።



www.ethiopianorthodox.org

33. አትናቴዎስ ክፍል 4 (ሃይማኖት አበው)::
34. ዮሐ. 1፡ 10::
35. ጎርጎርዮስ ክፍል 1::
36. ድርሳን ዘዲዮናስዮስ::
37. ሃይማኖተ አበው::
38. " "
39. ዮሐ. 1፡ 1÷ ሔሬኔዎስ ክፍል 1::
40. አትናቴዎስ ክፍል 1::
41. ዘዳግ. 6፡ 4::
42. ቴዎዶጦስ ዘዕንቆ ክፍል 1::
43. ጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምራት ክፍል 1::
44. ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪ ኀበ ሚናስ ክፍል 1::
45. ፊላታዎስ ዘእስክንድርያ ክፍል 2::
46. አቡሊዲስ ዘሮሜ ኀበ በርደንበ ክፍል 2::
47. ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ኀበ ማርቆስ ዘእስክንድርያ::
48. አባ ሕርያቆስ ቅዳሴ ማርያም::
49. ዮሐ. 14፡ 9::
50. ሃይማኖተ አበው (ኪራኮስ ዘአንጾኪያ)::
51. ሃይማኖተ አበው ሕንፃ መነኮሳት::
52. መዝ. 147፡ 5::
53. አባ ሕርያቆስ ቅዳሴ ማርያም::
54. ሳዊሮስ ኀበ አንስጣስዮስ ክፍል 1::





## ክፍል ፩ ፍጥረተ ዓለም በጠቅላላው÷ ምዕራፍ ፩ እግዚአብሔር በፍጥረቱ፤

1. ዘፍጥ. 1፡ 1::
2. ሮሜ 11፡ 36::
3. መዝ. 134፡ 3::
4. ኢሳ. 42፡ 5-7::
5. መዝ. 136፡ 5-10::
6. መዝ. 146፡ 5::
7. የሐ. ሥራ 4፡ 24::
8. ራእይ 4፡ 11::
9. ዕብራ. 11፡ 3::
10. ዘፍጥ. 1፡ 26-30::
11. ኢዮብ 38፡ 4::
12. ዕብራ. 11፡ 3÷ ዘፍጥ. 1፡ 3-25::
13. ሮሜ 4፡ 17::
14. ዘፍጥ. 1፡ 1::
15. መዝ. 90፡ 2÷ ምሳሌ 8፡ 25-30÷ መዝ. 102፡ 25-27::
16. ዮሐን. 5፡ 17::
17. ዘፍጥ. 1፡ 1::
18. መዝ. 104፡ 24::
19. ኢዮብ 42፡ 2÷ ኤርም. 32፡ 17÷ ሉቃ. 1፡ 37::
20. መዝ. 136፡ 25::
21. መዝ. 19፡ 1::
22. ዳን. 3፡ 57::



www.ethiopianorthodox.org

23. ሉቃ. 2፡ 14።
24. ሮሜ. 11፡ 36።
25. ዘፍጥ. 1፡ 28።
26. ሮሜ. 1፡ 19።
27. መዝ. 135፡ 6።
28. ዘፍጥ. 2፡ 7።
29. ዘፍጥ. 1፡ 1-27።
30. ዘፍጥ. 2፡ 1።

## ምዕራፍ ፪ ዓለም በጠቅላላው፤

1. ዘፍጥ. 1፡ 1።
2. ዕብራ. 3፡4፥ ጥበብ 11፡ 17፥ የሐ. ሥራ 17፡ 24፥ ፩ኛ ቆሮ. 8፡ 6።
3. ጸሎተ ሃይማኖት 1።
4. ዘፍጥ. 1፡ 1-31።
5. ጸሎተ ሃይማኖት።
6. ማቴ. 5፡ 34።
7. መዝ. 19፡ 1።
8. " 114፡ 24።
9. " 148፡ 3።
10. ማቴ. 6፡ 9።
11. ማቴ. 7፡ 21።
12. ማቴ. 3፡ 2፥ ምሳ. 14፡ 7።
13. ጸሎተ ሃይማኖት።
14. ኪዳነ ውልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት።
15. ያልታተሙ ምዕላዶች፥ አክሲማሮስ።





16. ፪ኛ ቆሮ. 12፡ 1 - 4።
17. የሐ. 14፡ 2።
18. ማቴ. 25፡ 34።
19. ዘፍ. 1፡ 16-18።
20. ዘፍ. 1፡ 14-16።
21. ሄኖክ።
22. ማቴ. 4፡ 25።
23. ዘፍ. 1:16፥ 15፡ 5።
24. " 1፡ 16።
25. ዘፍ. 15:5።
26. መዝ. 114፡ 6።
27. ዘፍ. 1፡ 14።
28. ድጓ. መዝ. ዘጽጌ።
29. መዝ. 145፡ 2-5።
30. መዝ. 19፡ 1።
31. ሮሜ. 1፡ 20።
32. መዝ. 147፡ 7።
33. ዘፍ. 1፡ 11-13።
34. ዳንኤል 3፡ 57።
35. ማር ይስሐቅ።

## ምዕራፍ ፫ የእግዚአብሔር መግቦት፤

1. ጥበብ 11፡ 24-27።
2. መዝ. 104፡ 28-29።
3. የሐ. ሥራ 17፡ 18፥ ዕብራ 1፡ 3።
4. መዝ. 3፡ 18-19፥ 34፡ 15-19፥ ምሳሌ 16፡ 9፥ 20፡ 24፥



www.ethiopianorthodox.org

ማቴ. 6፡ 26÷ የሐ. ሥራ 14፡ 17÷ ፩ኛ ጴጥ. 5፡ 6-7፡፡

5. መዝ. 78፡ 43-53፡፡

## ምዕራፍ ፬ የመላእክት ሀልውና፣

1. ዘፍ. 3፡ 24፡፡
2. " 33፡ 2፡፡
3. " 3፡ 24፡፡
4. ሉቃ. 2፡ 9-15፡፡
5. ማቴ. 4፡ 11፡፡
6. ሉቃ. 22፡ 43፡፡
7. ማቴ. 25፡ 51፡፡
8. ሉቃ. 11፡ 11-19÷ 26-38፡፡
9. ድርሳነ ሚካኤል፡፡
10. መዝ. 104፡ 4፡፡
11. ቆላስ. 1፡ 16÷ ዮሐ. 1፡ 3፡፡
12. ፪ኛ ተሰሎ. 1፡ 7÷ መዝ. 103፡ 20፡፡
13. ፪ኛ ጴጥ. 2፡ 16፡፡
14. ማቴ. 22፡ 10-30፡፡
15. ሉቃ. 24፡ 39፡፡
16. " 24፡ 4÷ ማቴ. 28፡ 3፡፡
17. ፪ኛ ነገ. 6፡ 16÷ ዘፍ. 32፡ 25፡፡
18. ራእይ 14፡ 6÷ ኢሳ. 6፡ 2፡፡
19. ማቴ. 32፡ 30÷ ማር. 12፡ 25÷ ሉቃ. 20፡ 36፡፡
20. ማቴ. 4፡ 11-12፡፡
21. ዘፍ. 16፡ 7-11÷ መሳፍ. 6፡ 11÷ ሉቃ. 1፡ 11÷ 20፡ 26÷ የሐ. ሥራ 19፡ 3-7÷ ማቴ. 4፡ 11÷ መዝ. 94፡ 4፡፡





22. መዝ. 91፡ 11-12÷ ማቴ. 18፡ 10፡፡
23. ማቴ. 18፡ 10፡፡
24. ዘፍ. 19፡ 10-11÷ ምሳ. 29፡ 12÷ ዳን. 10፡ 13÷ ነገ. 6፡ 18÷ መዝ. 34፡ 7፡፡
25. የሐ. ሥራ 12፡ 7-11÷ ዳን. 6፡ 22፡፡
26. የሐ. ሥራ 12፡ 23÷ ኢሳ. 37፡ 36÷ ፪ኛ ነገ. 19፡ 35፡፡
27. ማቴ. 13፡ 24-30፡፡
28. ዕብራ. 12፡ 22÷ መዝ. 68፡ 17÷ ዳን. 7፡ 10÷ ራእ. 7፡ 10፡፡
29. ማቴ. 26፡ 53፡፡
30. ሉቃ. 2፡ 13፡፡
31. ዕብራ. 12፡ 22፡፡
32. ቆላስ. 1፡ 16÷ ኤፌ. 1፡ 2-15፡፡
33. ዳን. 10፡ 13÷ 12፡ 1÷ ም. ይሁዳ 9÷ ራእይ 12፡ 7፡፡
34. ዳን. 8፡ 16÷ ሉቃ. 11፡ 1÷ 20-26፡፡
35. ጦቢት 8፡፡
36. ኢሳ. 6፡ 2፡፡
37. መዝ. 18፡ 10÷ 8፡ 1፡፡
38. ሄኖክ 10፡ 14፡፡
39. ሄኖክ 5፡ 13፡፡
40. ሄኖክ 4፡ 57፡፡
41. ሄኖክ ፯፡ 33፡ 8፡፡
42. ሄኖክ 6፡ 42፡፡
43. ሄኖክ 6፡ 11፡፡
44. ሄኖክ 3፡ 1፡፡
45. " 20፡ 38፡፡



www.ethiopianorthodox.org

46. " 10: 15::

47. "

48. " 8: 20::

49. " 6: 6::

50. " 28: 13::

51. ሉቃ. 1: 19÷ ማቴ. 18: 10::

52. መዝ. 34. 7::

## ምዕራፍ ፲፰ አጋንንት በጠቅላላው፤

1. ማር. 3: 11-12÷ 1: 23-26::
2. ማቴ. 4: 24÷ ሉቃ. 6: 17::
3. ማቴ. 4: 3-11÷ ሉቃ. 4: 3-13::
4. ኤፌ. 6: 12::
5. አፌ. 6:12
6. ራእይ 12: 7-10::
7. ፩ኛ ቆሮ. 5: 5::
8. ፪ኛ ተሰሎ. 2: 9-10::
9. ማቴ. 4: 1-12::
10. ትምህርተ ኅቡዓት::
11. መቅድመ ወንጌል::
12. ማቴ. 25: 46::

## ምዕራፍ ፲፱ ስለ ሰው በጠቅላላው፤

1. ዘፍ. 1: 26::
2. ዘፍ. 2: 7::
3. " " "





4. ዘፍ. 1: 26-30
5. ፩ኛ ቆሮ. 15: 53-55::
6. ዘፍ. 2: 21-22::
7. ማቴ. 19: 4::
8. ዘፍ. 2: 1::
9. መዝገበ ሃይማኖት አንቀጽ ሐምሳዊ ቁ. 10::
10. " " " " ገጽ 103 ቁጥር 33::
11. ዘፍ. 5: 3::
12. " 2: 7::
13. ፩ኛ ተሰሎ. 5: 23÷ ዕብራ 4: 12::
14. ቅዳሴ ማርያም::
15. መዝሙር 73: 26÷ 84: 2÷ ማቴ. 6: 25÷ 10: 28::
16. ዘፍጥ. 3: 20÷ 2: 7::
17. " 2: 21::
18. የሐ. ሥራ 17: 26::
19. ሮሜ. 5: 12-17::
20. ዘፍጥ. 1: 28::
21. " 1: 26::
22. መዝ. 49: 20::
23. ፩ኛ ጴጥ. 2: 15::
24. ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ ሕያው ሁኖ ይኖራልና::

## ምዕራፍ ፳ ጥንተ አብሶ (ጥንታዊ በደል)፤

1. ሮሜ. 6: 23::
2. ዘፍጥ. 3: 3-24::



www.ethiopianorthodox.org

3. ዘፍጥ. 6: 5-7÷ ፩ኛ ነገሥ. 8: 46÷ መዝ. 12: 1÷ 104: 2÷ ኢሳ. 59: 3፤ ምሳሌ 20: 9÷ ጥበብ. 7: 21÷ ገላት. 3: 22÷ ሮሜ. 3: 11-17::
4. ኢዮብ 14: 4::
5. መዝ. 50: 5::
6. ዮሐ. 3: 3-8::
7. ዮሐ. 3: 5-6::
8. ኤፌ. 2: 3::
9. ሮሜ. 5: 12::
10. ድጓ ዘፍልሰታ ኪዳነ ምሕረት::
11. ሮሜ. 5: 12::
12. ሮሜ. 5: 18::
13. ሮሜ. 5: 18::
14. ሮሜ. 5: 14::
15. ዘፍጥ. 3: 19::
16. ዘፍጥ. 3: 22::
17. ሮሜ. 6: 23::
18. ሮሜ. 5: 15-21::
19. ፩ኛ ቆሮን. 15: 55::

## ክፍል ፫ ድኅነተ ዓለም፤

### ምዕራፍ ፩ ምሥጢረ ሥጋዌ በጠቅላላው፥

1. ኢሳ. 3: 1::
2. ዮሐ. 8: 56::
3. መዝ. 43: 3::





4. ማር. 1: 1÷ ሉቃ. 3: 38÷ 22: 70÷ ዕብራ 1: 2::
5. ዮሐ. 1: 1-14::
6. ማቴ. 1: 21÷ ሉቃ. 1: 31÷ 2: 21::
7. ዮሐ. 1: 22÷ መዝ. 2: 2÷ ዳን. 9: 25-27::
8. ኢሳ. 7: 14÷ ማቴ. 1: 23::
9. ቅዳሴ ማርያም::
10. ጸሎተ ሃይማኖት::
11. ጸሎተ ሃይማኖት::
12. ፩ኛ ጢሞ. 1: 17::
13. ራእይ 1: 8÷ 17-18÷ 22: 13÷ ኢሳ. 41: 44÷ 48:12::
14. ፪ኛ ቆሮ. 5: 21÷ ገላት. 3: 13::
15. ሉቃ. 2: 52::
16. ዮሐ. 1: 1::
17. ፩ኛ ዮሐ. 1: 1::
18. ራእ. 1: 17-18::
19. " 1: 17-18::
20. ኢሳ. 41: 4::
21. ዮሐ. 1: 3::
22. ኢሳ. 44: 6::
23. ኢሳ. 48: 12-31::
24. ዮሐ. 8: 25::
25. ሉቃ. 22: 70::
26. " 1: 35::
27. ማር. 3: 17÷ 17: 5÷ ማር. 1: 11÷ ሉቃ. 3: 22::
28. ዮሐ. 5: 18::



www.ethiopianorthodox.org

29. ዮሐ. 1፡ 17።
30. " 3፡ 26።
31. ሉቃ. 1፡ 26።
32. ማቴ. 1፡ 18።
33. ሉቃ. 1፡ 28።
34. " 1፡ 42።
35. ኤፍሬም ክፍል 5።
36. አግናጥዎስ ክፍል 1።
37. ፊልጽስዮስ 2፡ 5።
38. ማቴ. 1፡ 18-20፥ ሉቃ. 1፡ 35።
39. ማቴ. 20፡ 28።
40. " 8፡ 20
41. ሉቃ. 21፡ 37።
42. ዮሐ. 4፡ 6-10።
43. ሉቃ. 24፡ 41።
44. ማቴ. 5፡
45. ሉቃ. 2፡ 42።
46. ዮሐ. 6፡ 15-25።
47. " 2፡ 12።
48. ማቴ. 26፡ 6፥ ሉቃ. 7፡ 38-43፥ 10፡ 38።
49. ማቴ. 8፡ 1-17።
50. ዮሐ. 5፡ 1-8፥ ማቴ. 8፡ 1-34፥ 9፡ 1-38።
51. ዮሐ. 11፡ 1-44
52. ሉቃ. 19፡ 41-43።
53. ማቴ. 19፡ 13-15፥ ሉቃ. 18፡ 18-30።





54. ማቴ. 18፡ 2-7።
55. ማር. 15፡ 40፥ ሉቃ. 23፡ 49።
56. ዮሐ. 19፡ 25።
57. ማቴ. 28፡ 1፥ ማር. 16፡ 1፥ ዮሐ. 20፡ 1።
58. ማቴ. 22፡ 15-22፥ ማር. 12፡ 31፥ ሉቃ. 20፡ 20-40።
59. ማቴ. 17፡ 24-27።
60. ማቴ. 20፡ 28፥ ፩ኛ ጢሞ. 2፡ 7።
61. ማቴ. 5፡ 13።
62. ማቴ. 5፡ 14።
63. ዮሐ. 7፡ 3።
64. " 12፡ 48።

## ምዕራፍ ፪ ስለ ክርስቶስ አምላካዊ ባሕርይ፥

1. ሉቃ. 1፡ 35።
2. ሆሴዕ 11፡ 9።
3. መዝ. 2፡ 2።
4. የሐ. ሥራ 4፡ 20።
5. መዝ. 110፡ 1።
6. ማቴ. 22፡ 43-44።
7. ዘጸ. 10፡ 17፥ ራእይ 17፡ 14።
8. ፩ኛ ቆሮ. 2፡ 8-9።
9. ሉቃ. 23፡ 42።
10. ፩ኛ ቆሮ. 8፡ 6።
11. ሉቃ. 2፡ 11።
12. ዮሐ. 20፡ 28።
13. ሉቃ. 1፡ 43።



www.ethiopianorthodox.org

14. ማቴ. 7፡ 22፥ ሉቃ. 6፡ 46፥ ማቴ. 25፡ 31፥
ሉቃ. 13፡ 25።
15. የሐ. ሥራ 7፡ 59።
16. " " 16፡ 31።
17. ዮሐ. 1፡ 1።
18. " 20፡ 28።
19. ሮሜ. 9፡ 5፥ ቲቶ. 2፡ 13።
20. ኢሳ. 7፡ 14፥ ማቴ. 1፡ 23።
21. ማቴ. 1፡ 23።
22. ኢሳ. 9፡ 6።
23. " 45፡ 5።
24. ፩ኛ ጢሞ. 3፡ 16።
25. የሐ. ሥራ 20፡ 28
26. ማቴ. 28፡ 19።
27. ዕብራ. 1፡ 5-8።
28. ፩ኛ ዮሐ. 5፡ 20።
29. ዮሐ. 3፡ 36፥ ቁ. 17-18።
30. " 14፡ 6።
31. ዮሐ. 2፡ 25።
32. 2ኛ ዜና መዋዕል 6፡ 30፥ ኤርም. 17፡ 9-10፥
ዮሐ. 2፡ 25።
33. ዮሐ. 1፡ 38።
34. ዮሐ. 21፡ 15-17።
35. ማቴ. 18፡ 20።
36. ዮሐ. 3፡ 13።





37. " 14፡ 20።
38. ኢሳ. 9፡ 6።
39. ዮሐ. 17፡ 5።
40. " 8፡ 58።
41. ዕብራ 13፡ 8።
42. " 1፡ 22።
43. ፊልጵ 2፡ 6-7።
44. ቆላስ. 2፡ 9።
45. ዕብራ. 1፡ 10፥ መዝ. 102፡ 25-27።
46. ዮሐ. 1፡ 3።
47. ቆላስ. 1፡ 16-17።
48. ዕብራ. 1፡ 3።
49. ማቴ. 9፡ 3-8፥ ሉቃ. 7፡ 48፥ 7፡ 40-47።
50. መዝ. 100፡ 24-27።
51. ዕብራ. 1፡ 10-12።
52. ኢሳ. 40፡ 3-5።
53. ማቴ. 3፡ 3፥ ሉቃ. 1፡ 68-69።
54. ኤርም. 11፡ 20፥ ም. 17፡ 10።
55. ራእይ 2፡ 23።
56. 2ኛ ቆሮ. 13፡ 14።
57. ማቴ. 28፡ 19።
58. ፩ኛ ተሰሎ. 3፡ 11።
59. ፩ኛ ቆሮ. 2፡ 4-7።
60. ያዕቆ. 1፡ 1።
61. ዮሐ. 14፡ 23።



www.ethiopianorthodox.org

62. " 1: 1::
63. ፪ኛ ጴጥ. 1: 1::
64. ፩ኛ ጴጥ. 1: 2::
65. ቆላስ. 2: 2::
66. ዮሐ. 17: 3::
67. " 14: 1::
68. ራእይ. 7: 10::
69. ዮሐ. 5: 23::
70. ራእይ. 5: 13::
71. ማቴ. 28: 9::
72. ሉቃ. 24: 52::
73. ማቴ. 14: 33::
74. ዘዳግ. 7: 13÷ ማቴ. 4::
75. ዕብራ 1: 6::
76. ፊልጵ. 2: 10::
77. ኢሳ. 45: 21-23::

## ምዕራፍ ፫ ምሥጢረ ተዋሕዶ÷

1. ቄርሎስ::
2. ሉቃ. 3: 23::
3. አርካቦስ ክፍል 1÷ ሃይማኖተ አበው::
4. ኢራክሊስ ክፍል 3÷ " "
5. ቄርሎስ
6. ፩ኛ ጴጥ. 3: 18::
7. ሮሜ. 5: 10::
8. ፊላታዎስ ክፍል 1::





9. ጸሎተ ሃይማኖት::

## ምዕራፍ ፬ የክርስቶስ ፫ቱ ማዕርጎች÷

1. ዘዳግ. 18: 15-18÷ የሐ. ሥራ 3: 22::
2. መዝ. 110: 4::
3. ሚክ. 5: 2÷ መዝ. 2: 7÷ ማቴ. 2: 5-6::
4. ሉቃ. 13: 33÷ ማቴ. 13::
5. ዮሐ. 17: 19÷ ማቴ. 20: 28÷ ዕብራ 1: 14÷ 5: 1-11::
6. ማቴ. 25: 14-47÷ 27: 11÷ ሉቃ. 19: 12÷
   ዮሐ. 18: 33-36::
7.
8. መጽ. ሰዓታት ዘአባ ጊዮርጊስ::
9. ዕብራ 4: 14::
10. ዕብራ 5: 5::
11. መዝ. 110: 4÷ ዕብራ 6: 20-21::
12. ዕብራ 5: 1-8::
13. ፊልጵ. 2: 3÷ ሮሜ. 5: 19::
14. ገላት. 1: 4÷ 2: 20÷ ፩ኛ ቆሮ. 15: 3÷ 57::
15. " 3: 13÷ ሮሜ. 3: 25÷ ፪ኛ ቆሮ. 5: 21÷
    ዮሐ. 2: 2::
16. ዮሐ. 1: 29::
17. " 14: 6-8÷ 12::
18. " 10: 38::
19. " 1: 18::
20. ዘዳግ. 18: 15÷ 18::



www.ethiopianorthodox.org

12. ኢሳ. 11፡ 2።
13. ሮሜ. 8፡ 9።
14. ገላት. 4፡ 6።
15. ሉቃ. 24፡ 49፥ የሐ. ሥራ 1፡ 4።
16. የሐ. ሥራ 1፡ 1።
17. ፩ኛ ዮሐ. 5፡ 6።
18. ዕብራ. 9፡ 14።
19. ኢዮብ 33፡ 4።
20. መዝ. 104፡ 30።
21. ፩ኛ ቆሮ. 12፡ 4።
22. ፪ኛ ቆሮ. 13፡ 14።
23. የሐ. ሥራ 5፡ 3-4።
24. ሉቃስ 3፡ 21-22።
25. ጸሎተ ፫ቱ ደቂቅ።
26. ሉቃስ 3፡ 21-22።
27. ዮሐ. 14፡ 16።

## ምዕራፍ ፪ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥

1. መዝ. 33፡ 6።
2. ኢዮብ 33፡ 4።
3. ቅዳሴ ማርያም።
4. ዘፍጥ. 2፡ 7።
5. ዘፍጥ. 2፡ 7።
6. ዮሐ. 14፡ 17።
7. ዮሐ. 14፡ 6።
8. ፩ኛ ቆሮ. 12፡ 13።





9. ቲቶ. 3፡ 5።
10. ኤፌ. 2፡ 1።
11. የሐ. ሥራ 16፡ 13።
12. ኤርም. 1፡ 11።
13. ኢሳ. 11፡ 2።
14. ፩ኛ ቆሮ. 12፡ 4-13።
15. ኢሳ. 11፡ 2።
16. ገላት. 5፡ 22፥ ኤፌ. 5፡ 9።

## ክፍል ፯ ክብረ ቅዱሳን፥

## ምዕራፍ ፩ ክብረ ቅዱሳን በጠቅላላው፥

1. ኢሳ. 6፡ 3።
2. ማቴ. 6፡ 9።
3. ዮሐ. 17፡ 11።
4. ዮሐ. 10፡ 36።
5. ራእይ 4፡ 8።
6. ሥርዓተ ቅዳሴ።
7. ዘሌዋ. 19፡ 2።
8. ዘፍጥ. 2፡ 3።
9. ጸዘአ. 25፡ 33፥ 29፡ 30።
10. ዘጸአ. 19፡ 6።
11. ዮሐ. 17፡ 12።
12. ፩ኛ ጴጥ. 2፡ 9።
13. ፩ኛ ቆሮ. 7፡ 13-16።
14. ፩ኛ ጴጥ. 1፡ 15።



www.ethiopianorthodox.org

15. ሮሜ. 8፡ 33-34።
16. ኤርም. 1፡ 5።
17. ዮሐ. 17፡ 11።
18. ዮሐ. 15፡ 17።
19. ዘጸአ. 28፡ 36÷ 39-36።
20. ፩ኛ ዜና መዋዕል 16፡ 29÷ መዝ. 29፡ 2÷ 96፡ 9።
21. መዝ. 30፡ 4።
22. መዝ. 47፡ 8÷ 60፡ 6።
23. ዘጸአ. 19፡ 6።
24. ዘኁል. 16፡ 5÷ ፪ኛ ነገሥት 4፡ 9።
25. ዘሌዋ. 10፡ 10።
26. ኢሳ. 27፡ 13።
27. ሥርዓተ ቅዳሴ።
28. ማቴ. 6፡ 9።
29. ዮሐ. 17፡ 19።
30. የሐ. ሥራ 10፡ 3-7።
31. ዘፍ. 3፡ 24።
32. ዘፍጥ. 16፡ 7÷ 21፡ 17።
33. ዘፍጥ. 22፡ 11።
34. ዘፍጥ. 31፡ 13።
35. ዘጸአ. 3፡ 2።
36. መሳፍንት 6፡ 11፡ ፪ኛ ሳሙ. 24፡ 16÷ ዘካር. 1፡ 12።
37. የሐ. ሥራ 12፡ 7-11÷ ምሳ. 5፡ 19÷ 8፡ 26።
38. ሉቃ. 1፡ 19።
39. ይሁዳ 9።





40. ዘፍጥ. ከምዕራፍ 12 እሽከ 50 ተመልከት።
41. የሐ. ሥራ 2፡ 29።
42. ጸሎተ ሰዓታት።
43. ኤርም. 1፡ 5።
44. ጸሎተ ሰዓታት።

## ምዕራፍ ፪ ቅድስት ማርያም÷

1. ሉቃስ 1፡ 35።
2. ሉቃስ 1፡ 28።
3. ሉቃስ 1፡ 42።
4. ኢሳ. 7፡ 14።
5. መዝ. 132፡ 53።
6. ኢሳ. 2፡ 3።
7. ኢሳ. 11፡ .1።
8. ኢሳ. 19፡ 1።
9. ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ።
10. ኢሳ. 63፡ 1።
11. ሕዝቅ. 44፡ 2።
12. ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ።
13. ዕባቆም 3፡ 3።
14. ቅዳሴ ማርያም።
15. መዝ. 72፡ 6።
16. መዝ. 66፡ 1።
17. ዘፍጥ. 8፡ 8።
18. ውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ÷ ዘሰንበተ ክርስቲያን።
19. ውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ።



www.ethiopianorthodox.org

20. ዘፍጥ. 3: 2::
21. ዘጸአ. 25: 10፥ 36፥ ም. 26: 1፥ 34: 1::
22. ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስቲያን::
23. ሉቃስ 1: 28-37::
24. ሉቃስ 1: 43-45::
25. ሉቃስ 1: 48::
26. ሉቃስ 1: 27::
27. ኢሳ. 7: 14::
28. ሉቃስ 1: 27::
29. ማቴ. 1: 25::
30. ሉቃስ 1: 41-45::
31. ሉቃስ 1: 46::
32. ሉቃስ 11: 27::
33. ሮሜ. 8: 29::
34. ማቴ. 11: 12::

## ምዕራፍ ፫ ቅዱሳን ሐዋርያት፥

1. ማቴ. 10: 1-2::
2. ዮሐ. 15: 16::
3. ዮሐ. 17: 19::
4. ማቴ. 16: 19፥ ም. 18: 18፥ ዮሐ. 20: 23::

## ምዕራፍ ፬ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፥

1. ዮሐ. ሥራ 1: 8::

## ምዕራፍ ፭ ከቅዱሳን ጋር ያለን ግንኙነት፥

1. ኢዮብ 9: 2::





2. ፩ኛ ዮሐ. 1: 8::
3. ዮሐ. 15: 14-15::
4. ዮሐ. 14: 13::
5. ራእይ 14: 13::
6. ዮሐ. 17: 22::
7. ማቴ. 10: 41::
8. ፩ኛ ዮሐ. 1: 3::
9. ዕብራ. 12: 22-23::
10. ሮሜ. 8: 29-30::

## ምዕራፍ ፮ ጸሎት፥

1. ኤፌ. 4: 16::
2. ፩ኛ ተሰሎ. 6: 17::
3. ኤፌ. 6: 18::
4. ሉቃ. 18: 1-12::
5. ማቴ. 6: 9::
6. ማቴ. 7: 7::
7. ማቴ. 6: 9-13::
8. ሉቃስ 22: 32::
9. 
10. ፪ኛ ተሰሎ. 3: 1::
11. ሮሜ. 15: 30፥ ያዕቆ. 5: 16::
12. ራእይ 5: 8::

## ምዕራፍ ፯ ጸሎተ ፍትሐት፥

1. ሮሜ. 8: 38-39::
2. ፩ኛ ዮሐ. 5: 14-16::



www.ethiopianorthodox.org

4. ያዕቆ. 5፡ 14-15፡፡
5. ኤፌ. 4፡ 5-6፡፡
6. ጸሎተ ሃይማኖት፡፡
7. ማቴ. 19፡ 11-12፡፡

## ምዕራፍ ፫ ምሥጢረ ጥምቀት፥

1. ሮሜ. 6፡ 3-5፡፡
2. ዮሐ. 3፡ 3-5፡፡
3. ጸሎተ ሃይማኖት፡፡
4. መዝ. 51፡ 5፥ ኢዮ. 14፡ 4፡፡
5. ፩ኛ ቆሮ. 15፡ 50፡፡
6. 1ኛ ቆሮ. 10፡ 1-2፡፡
7. ዘፍጥ. 7፡ 6-7፡፡
8. ፩ኛ ጴጥ. 3፡ 20-21፥ ዘፍጥ. 7፡ 17፡፡
9. ፪ኛ ነገሥት 5፡ 1-16፡፡
10. ዘፍጥ. 1፡ 20፡፡
11. ኢያሱ 7፡ 3-13፡፡
12. ሕዝቅ. 36፡ 25፡፡
13. መዝ. 114፡ 3፡፡
14. ሉቃ. 3፡ 3፡፡
15. ማቴ. 3፡ 1-4፡፡
16. የሐ. ሥራ 13፡ 24፥ 19፡ 3፡፡
17. ዮሐ. 3፡ 19-31፡፡
18. ዮሐ. 4፡ 2፡፡
19. ማቴ. 28፡ 19፡፡
20. የሐ. ሥራ 2፡ 1-5፥ 19፡6፡፡





21. ዮሐ. 3፡ 3፡፡
22. ማቴ. 3፡ 3-16፥ ማር. 1፡ 9-11፥ ሉቃ. 3፡ 21-22፡፡
23. ማር. 16፡ 16፡፡
24. የሐ. ሥራ 2፡ 38፥ 3፡ 17፡፡
25. ማቴ. 28፡ 19፡፡
26. ማቴ. 3፡ 17፥ ማር. 1፡ 9-10፡፡
27. ዮሐ. 3፡፡ 5፡፡
28. የሐ. ሥራ 8፡ 38፡፡
29. ዮሐ. 3፡ 46-47፡፡
30. ማቴ. 28፡ 19፡፡
31. ማር. 16፡ 16፡፡
32. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3፡፡
33. ማቴ. 28፡ 19፡፡
34. የሐ. ሥራ 10፡ 34-48፡፡
35. ፩ኛ ቆሮ. 1፡ 16፡፡
36. ማቴ. 19፡ 14፡፡
37. ዘሌዋ. 12፡ 2-7፡፡
38. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሣልስ፡፡
39. ኤፌ. 4፡ 5፡፡
40. ሮሜ. 6፡ 3-10፡፡
41. ቲቶ. 3፡ 5፡፡
42. ማቴ. 10፡ 39፡፡
43. ማቴ. 10፡ 33-39፥ ሉቃ. 17፡ 33፥ ዮሐ. 12፡ 25፡፡
44. ማቴ. 10፡ 32፥



www.ethiopianorthodox.org

45. የሐ. ሥራ 2: 38-39÷ 22: 16÷ ቆላስ. 2: 12-13÷ ፩ኛ ጴጥ. 3: 21::
46. ገላት. 3: 27÷
47. ማር. 16: 16÷ ዮሐ. 3: 5÷ ቲቶ. 3: 5::

## ምዕራፍ ፬ ምሥጢረ ሜሮን÷

1. ሉቃ. 24: 49÷ የሐ. ሥራ 1: 4::
2. ፪ኛ ቆሮ. 1: 21-22::
3. ኤፌ. 4: 30::
4. ፩ኛ ዮሐ. 2: 20-27::
5. የሐ. ሥራ 8: 15-17::
6. የሐ. ሥራ 19: 2-6::
7. ኤፌ. 1: 13÷ 4: 3÷ ፪ኛ ቆሮ. 1: 21-23÷ ፩ኛ ዮሐ. 2: 20-27::

## ምዕራፍ ፭ ምሥጢረ ቁርባን÷

1. ዘጸአ. 12: 14::
2. ዘጸአ. 16: 16-23::
3. ዮሐ. 6: 49::
4. ዮሐ. 6: 50-51::
5. ዘፍጥ. 14: 18-20÷ ዕብራ 7: 1-3::
6. ዘጸአ. 16: 32-34::
7. ምሳ. 9: 1-5::
8. ኢሳ. 55: 1-3::
9. ማቴ. 26: 26-30÷ ማር. 14: 17-18÷ ሉቃ. 22: 14-20÷ ፩ኛ ቆሮ. 11: 23-25::
10. ማቴ. 26: 26::





11. ማቴ. 26: 27::
12. ሉቃስ 22: 19÷ ፩ኛ ቆሮ. 11: 25::
13. ቅዳሴ ሐዋርያት::
14. ዮሐ. 6: 53-54::
15. ዮሐ. 6: 51::
16. ዮሐ. 6: 53-54::
17. ፩ኛ ቆሮ. 11: 34::
18. ቅዳሴ ሐዋርያት::

## ምዕራፍ ፮ ምሥጢረ ንስሓ÷

1. ማቴ. 3: 2::
2. ማቴ. 9: 6::
3. ማቴ. 16: 19::
4. ማቴ. 18: 18::
5. ዮሐ. 20: 22-23::
6. ማቴ. 16: 18-19::
7. ማቴ. 8: 1-4::
8. ማቴ. 6: 14-15::
9. ፩ኛ ቆሮ. 5: 2-4::
10. ማቴ. 5: 4::

## ምዕራፍ ፯ ምሥጢረ ክህነት÷

1. ዮሐ. 20: 21-23::
2. ሉቃ. 6: 12-13::
3. የሐ. ሥራ 6: 6::
4. የሐ. ሥራ 13: 2-3÷ 14: 23÷ ፩ኛ ጢሞ. 5: 22::



www.ethiopianorthodox.org

14. መዝ. 17: 20::
15. ሆሴዕ 13: 14::
16. ኢሳይ. 26: 19::

## ምዕራፍ ፱ የትንሣኤው ዓይነት÷

1. ፩ኛ ቆሮ. 15: 43::
2. " " 15: 42-44::
3. " " 15: 42-44::
4. ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ::
5. ማቴ. 25: 36-40::
6. ፩ኛ ቆሮ. 15: 51-58::
7. ፩ኛ ተሰሎ. 4: 17::
8. ፩ኛ ተሰሎ. 4: 15::
9. ጸሎተ ሃይማኖት::

## ምዕራፍ ፲ ምሥጢረ ምጽአት÷

1. ማቴ. 16: 27÷ ማር. 8: 38÷ ሉቃ. 12: 40÷ 17: 2÷ ዮሐ. 14: 3::
2. የሐ. ሥራ 1: 11::
3. ይሁዳ 14: 15::
4. ፩ኛ ዮሐ. 2: 28::
5. ፩ኛ ጴጥ. 4: 13::
6. ፩ኛ ቆሮ. 4: 5÷ ፩ኛ ተሰሎ. 5: 2-6÷ ፩ኛ ቆሮ. 15: 51-58::
7. ዮሐ. 3: 17::
8. ፪ኛ ጢሞ. 4: 8::
9. ጸሎተ ሃይማኖት::





10. ማቴ. 24: 36::
11. የሐ. ሥራ 1: 11::
12. ማቴ. 24: 43::
13. " 24: 7::
14. " " 7::
15. " " 5::
16. " " 14::
17. ማቴ. 24: 12::
18. ማቴ. 24: 32÷
19. ማቴ. 24: 30::
20. ፪ኛ ጢሞ. 3: 1-4::

## ምዕራፍ ፬ የመጨረሻ ፍርድ÷

1. ማቴ. 22: 32÷ ሉቃ. 20: 38::
2. ፪ኛ ጴጥ. 1: 15::
3. ፪ኛ ቆሮ. 5: 4::
4. ፪ኛ ጴጥ. 1: 14::
5. ፊልጵ. 1: 23::
6. የሐ. ሥራ 13: 36::
7. ሉቃ. 16: 19-31::
8. ሉቃ. 23: 43::
9. ዮሐ. 5: 22-29÷ ማቴ. 16: 27÷ 7: 21-23÷ 11: 22-24÷ 12: 36-42÷ 13: 37-43÷ 19: 28-30÷ 24: 30÷ 25: 31-46÷ የሐ. ሥራ 17: 31÷ ይሁዳ 14-15÷ ፪ኛ ቆሮ. 5: 10÷ ሮሜ. 2: 5-7÷ 14: 10÷ ፩ኛ ቆሮ. 4: 5÷ ኤፌሶ. 6: 8÷ ቆላስ. 3: 24-25÷ ፪ኛ ተሰሎ. 1: 6-10÷ ፪ኛ ጢሞ. 4: 1÷ ራእይ 20: 11-15::
10. ማቴ. 25: 31-46::



www.ethiopianorthodox.org

11. ጸሎተ ሃይማኖት።
12. ፪ኛ ጴጥ. 2፡ 4፥ ይሁዳ 6።
13. ሮሜ. 2፡ 5።
14. ማቴ. 25፡ 41-46።
15. ማር. 9፡ 43-48።
16. ማቴ. 8፡ 12።
17. ራእይ 19፡ 20።
18. ዮሐንስ አፈወርቅ 23 ንግግር።
19. " " 40ኛው ንግግር ስለ ምሥጢረ ጥምቀት።
20. ፩ኛ ጢሞ. 2፡ 4።
21. ማቴ. 25፡ 34-40።
22. መዝ. 9፡ 33።

## ምዕራፍ ፲፰ ዘለዓለማዊ መንግሥት፥

1. ራእይ 21፡ 1።
2. ፩ኛ ቆሮ. 15፡ 24-28።
3. ሉቃ. 1፡ 33።
4. ጸሎተ ሃይማኖት።
5. ፩ኛ ቆሮ. 15፡ 26።
6. " " 15፡ 54።
7. ፪ኛ ጴጥሮ. 1፡ 4።
8. ራእይ 3፡ 2፥ ሮሜ. 8፡ 12፥ ፪ኛ ጢሞ. 2።
9. ማቴ. 25፡ 46።
10. ዮሐ. 14፡ 2።
11. ማቴ. 16፡ 27።
12. ፩ኛ ቆሮ. 3፡ 8።
13. " " 15፡ 41፥



www.ethiopianorthodox.org